**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የሂዩማኒቲ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሙዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል**


**የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር**

# የሴቶችና የወንዶች አለባበስና አጊያጊያጥ በመርሐቤቴ ወረዳ

በ

ፍስሃ ጌታቸው

መስከረም 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የሴቶችና የወንዶች አለባበስና አጊያጊያጥ በመርሐቤቴ ወረዳ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሙዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

ለአርት ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ፍስሃ ጌታቸው

አማካሪ

የኔዓለም አረዶ (ዶ/ር)

መስከረም 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሙዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# የሴቶችና የወንዶች አለባበስና አጊያጊያጥ በመርሐቤቴ ወረዳ

በ

ፍስሃ ጌታቸው

የፈተና ቦርድ አባላት

የአማካሪ ስም ___________________________ ፊርማ _______________

የውስጥ ፈታኝ ስም ___________________________ ፊርማ _______________

የውጭ ፈታኝ ስም ___________________________ ፊርማ _______________

# ምስጋና

ከሁሉም በፊት ጤና ሰጥቶኝ ይህን ጥናት እንድሰራ ያደረገኝ ፈጣሪ ልዑል እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን፡፡ በመቀጠል ይህ ጥናት ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ያለመሰልቸት በማረምና በትጋት እንድሰራ በማበረታታት፣ ለፍፃሜ እንዲበቃ ያገዙኝ አማካሪዬን ዶክተር የኔዓለም አረዶ እጅግ በጣም አመሰግናለሁ፡፡ እንዲሁም ይህን የትምህርት ስርዓት ዘርግቶ እንድማር ያስቻለኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን አመሰግናለሁ፡፡

በመስክ ቆይታዬ መረጃ በመስጠት ጥናቱ እንዲሳካ ቀና ትብብር ያደረጋችሁልኝ በአባሪው ክፍል ስማችሁ የተዘረዘረው መረጃ አቀባዮቼ እንዲሁም አርቴፊሻል መቼት እንድጠቀም ላገዛችሁኝ የሰንደቅ ባህል ቡድን አባላት ይህ ጥናት ከግብ እንዲደርስ የበኩላችሁን ድርሻ ስለተወጣችሁ አመሰግናለሁ፡፡

በተጨማሪም የመርሐቤቴ ወረዳ አስተዳደር የተሽከርካሪ ድጋፍ በማድረግ፣ የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ባለሙያዎችና ኃላፊዎች በመስክ ጉዞዎች አብሮ በመሆንና መረጃውን ለመሰብሰብ ቀድሞ በማመቻቸት፣ የኮሙዩኒኬሽን ጽ/ቤት የፎቶና ቪዲዮ ባለሙያን፣ የሚሊሻ ጽ/ቤት የፀጥታ አስከባሪዎችን በመመደብ እንዲሁም ከየተቋማቱ የተመድባችሁ ባለሙያዎችና ኃላፊዎች በተጓዝሁባቸው ቦታዎች አብራችሁኝ ተጉዛችሁ፣ የመስክ ዕቃዎችን ሸክም በማገዝ፣ የድምፅና የምስል መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ ፀጥታን በማስከበር፣ ተሽከርካሪ በማይገባባቸው ቦታዎች ተስፋ እንዳልቆርጥ በመምከርና በማበረታታት ላደረጋችሁልኝ ቀና ትብብር ከልብ የመነጨ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

በመጨረሻም ጥናቱን በማደርግበት ወቅት ከጎኔ ሆናችሁ ስታበረታቱኝ የነበራችሁ ውድ ቤተሰቦቼ፣ ጓደኞቼ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

# አጠቃሎ

*ይህ ጥናት በመርሐቤቴ ወረዳ የሴቶችና የወንዶች አለባበስና አጊያጊያጥ ላይ የሚያተኩር ነው። አልባሳትና ጌጣጌጦች በማጥናት የተጠኘውን ማህበረሰብ ፈጠራ ውጤት፣ እምነት፣ መለያና የአኗኗር ዘይቤን መመርመር የመጀመሪያው አነሳሽ ምክንያት ሲሆን በቁሶቹ ላይ የሚስተዋለውን የለውጥ ምክንያት መፈተሽና ቁሶቹን ለቀጣይ ትውልድ በመረጃነት ሰንዶ ማቆየት ደግሞ ሁለተኛው የጥናቱ መነሻ ምክንያት ነው። የዚህ ጥናት ዓብይ ዓላማ ለጥናት በተመረጠው አካባቢ የሚከወኑ የሴቶችና ወንዶች አለባበስና አጊያጊያጥ ፋይዳን መመርመር ነው። እንዲሁም የቁሶቹን አካላዊ ገፅታ ማሳየት፣ ትዕምርታዊ ትርጉም መግለፅ፣ ለውጥ የተስተዋለባቸውንም ሆነ ያልተስተዋለባቸውን ቁሶቹ መመርመር እና ቁሶቹን ለመጪው ትውልድ እንዲሸጋገሩ ሰንዶ ማቆየት የሚሉ ንዑሳን ዓላማዎች አሉት። ጥናቱ ከዓይነታዊ  የምርምር ዘዴ አንዱ የሆነው ገላጭ የምርምር ስልትን የተከተለ ሲሆን ቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮችን በመጠቀምና ለጥናቱ አስፈላጊ መረጃዎችን በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በተተኳሪ የቡድን ውይይት መረጃዎቹ ተሰብስበዋል። እንዲሁም ዘጠኙ (9) የSchlereth መተንተኛ ሞዴሎች ለመረጃ መተንተኛነት፣መዋቅራዊ ተግባራዊነት እና ለውጥና ቀጣይነት ንድፈ ሃሳቦች ደግሞ ለጥናቱ መቀንበቢያነት ውለዋል። በታላሚ ናሙና (Purposive sampling) አመራረጥ ዘዴ መሰረት በወረዳው ከሚገኙ 23 ቀበሌዎች ቁሶቹ እስካሁን ድረስ ሳይበረዙ ያቆዩና ባላቸው የአየር ንብረት ልዩነት መሰረት አምስት ቀበሌዎች፣ እንዲሁም ከወጣት እስከ አዛውንት ያሉና ባህሉን በደንብ የሚያውቁ 23 ወንዶችና 13 ሴቶች በድምሩ 36 መረጃ አቀባዮች በሀገር ሽማግሌዎችና በባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት መረጃ ሰጭነት ተመርጠዋል። በተመረጡ 22 አልባሳት እና 24 ጌጣጌጦች እንዲሁም 9 የፀጉር አሰራር ዓይነቶች ላይ ትንተና ተደርጓል። ጥናቱ በማህበረሰቡ የሚታወቁ አልባሳትና ጌጣጌጥ የትኞቹ ናቸው? የአለባበስ ሥርዓታቸው ምን ይመስላል? የመልበሻ አጋጣሚዎች የትኞቹ ናቸው? ቁሶቹ በማን መቼ እንዴትና ለምን ይሰራሉ? በየዕድሜ ደረጃቸው ያሉ አልባሳትና ጌጣጌጦች መለያቸው ምንድነው? በአልባሳቱና ጌጣጌጡ ላይ ለሚታዩ ለውጦች ምክንያታቸው ምንድነው? የሚሉ ጥያቄዎችን መልሷል። ከዚህ አንፃር የሚከተሉትን ነጥቦች በጥናቱ ግኝት የተመላከቱ ናቸው። እነሱም የማህበረሰቡ አልባሳትና ጌጣጌጦች በአካባቢው ከሚገኙ ጥሬ ዕቃዎችና የፋብሪካ ምርት ከሆኑ ግብዓቶች በአካባቢው ሽማኔ፣ ልብስ ሰፊዎች፣ በእደ ጥበብ ሙያተኞች የሚዘጋጁና ገበያው በሚያቀርባቸው መሰረት የሚገኙ ናቸው። ከአገልግሎት አኳያ የለባሹን ደህንነት የማስጠበቅ፣ ውበትን የማጉላት፣ ያታን፣ ማንነትን፣ ዕድሜን፣ ጀግንነትን ኃይማኖትን፣ ማህበራዊ ግንኙነትን፣ ማህበራዊ ደረጃዎችን የሚገልፁ ሲሆን ከመዋቅር አኳያ ደግሞ ቁሶቹ ሰርዓተ ማህበሩ እንዲቀጥል የሚያደርጉ ናቸው። የቁሶቹ ተምሳሌታዊ ትርጉም የማህበረሰቡን አመለካከት፣ ፍልስፍና፣ እውቀት፣ እምነት፣ ማንነት፣ ማህበራዊ ደረጃ፣ ውበት፣ ያታ ወዘተ ጉዳዮችን የሚገልፁ ሲሆኑ አሰራራቸው ደግሞ ጥበባዊ፣ ታሪካዊ፣ አካባቢያዊ፣ መዋቅራዊ፣ ማህበረሰባዊ ወዘተ መለያ ያላቸው ናቸው። እንዲሁም ከለውጥና ቀጣይነት አኳያ ምንም ያልተለወጡ፣ በከፊል የተለወጡ፣ ሙሉ ለሙሉ የተለወጡ ቁሶች መኖራቸው የጥናቱ ግኝት ያመላክታል። በዚህም መነሻነት የማህበረሰቡ ማንነት መገለጫ የሆኑትን ቁሶች የማልማትና ጠቃሚነታቸውን የማጉላት ስራ በድግግሞሽ ቢሰራ ማህበረሰቡን ለማስተዋወቅ፣ ማንነቱን በዘላቂነት ይዞ ለማስቀጠልና ከባህሉ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚ የሚያደርገው ይሆናል የሚል የይሁንታ ሃሳብ በማቅረብ ጥናቱ ተጠናቋል።*

## ማውጫ ገፅ

ምስጋና ........................................ i
አጠቃሎ ........................................ ii
የፎቶ ማውጫ ........................................ vii
የሰንጠረዥ ማውጫ ........................................ ix
ሙዳየ ቃላት ........................................ x
ምዕራፍ አንድ ........................................ 1
መግቢያ ........................................ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ........................................ 1
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........................................ 4
1.3. የምርምር ጥያቄዎች ........................................ 5
1.4. የጥናቱ ዓላማዎች ........................................ 5
1.5. የጥናቱ ወሰን ........................................ 5
1.6. የጥናቱ ጠቀሜታ ........................................ 6
1.7. የጥናቱ ዘዴዎች ........................................ 6
1.7.1 የጥናቱ አከዋወን ሂደትና ቅደም ተከተል ........................................ 6
1.7.2. የናሙና አመራረጥ ........................................ 7
1.7.3. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ........................................ 7
1.7.3.1 ምልከታ ........................................ 8
1.7.3.2. ቃለ-መጠይቅ ዘዴ ........................................ 8
1.7.3.3. የተተኳሪ ቡድን ውይይት ........................................ 9
1.7.4. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ........................................ 9
1.7.5 ቁሳዊ ባህልን የመተንተኛ ሞዴሎች ........................................ 10
1.8. በመስክ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች ........................................ 11
1.9. የመስክ ቆይታ ዘገባ ........................................ 11
1.10. የጥናቱ አደረጃጀት ........................................ 12

ምዕራፍ ሁለት ........................................................................................................ 13
ክለሳ ድርሳናት......................................................................................................... 13
2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ..................................................................................... 13
2.2. ጽንሰ ሀሳዊ ቅኝት ............................................................................................ 20
2.2.1. ቁሳዊ ባህል ...................................................................................................... 20
2.2.2. የቁሳዊ ባህል ጥናትና አስፈላጊነቱ......................................................................... 22
2.2.3. የቁሳዊ ባህል ምደባ............................................................................................ 24
2.2.3.1. ማህበራዊ ደረጃን ማሳየት ................................................................................ 25
2.2.3.2 ሃይማኖታዊ ተግባር.......................................................................................... 25
2.2.3.3 ሥርዓት ያታን የማመልከት ተግባር ...................................................................... 26
2.2.3.4. የተግባቦት (Communication) ተግባር ............................................................... 26
2.2.3.5. አልባሳትና ማንነት (Dress and Identity) ........................................................... 26
2.2.3.6. የመከላከል ተግባር............................................................................................. 27
2.2.4. የቁሳዊ ባህል መለያ ባህሪያት ............................................................................... 27
2.2.5. የአለባበስ ስያሜዎችና ትርጓሜዎች ......................................................................... 27
2.2.5.1. አልባሳት (Clothing) ........................................................................................ 27
2.2.5.2 ሀገረሰባዊ አልባሳት (Folk costume)................................................................... 28
2.2.5.3. አልባሳት (DRESS)........................................................................................... 28
2.2.6 አልባሳትና ትዕምርቶች........................................................................................ 28
2.2.7 ሀገረሰባዊ ጌጣጌጥ............................................................................................... 29
2.2.8 ሀገረሰባዊ መዋቢያ .............................................................................................. 29
2.2.9. ሀገረሰባዊ ዕጅ ስራ............................................................................................. 30
2.3 ንድፈ-ሃሳባዊ ማዕቀፍ ........................................................................................... 31
2.3.1 የመዋቅራዊ ተግባራዊነት ንድፈ-ሃሳብ...................................................................... 31
2.3.2 የለውጥና ቀጣይነት ንድፈ-ሃሳብ ........................................................................... 31

ምዕራፍ ሦስት ........ 34
ጥናቱ የተደረገበት አካባቢ ገፅታና የማህበረሰቡ ዳራዊ መግለጫ ........ 34
3.1. የመርሐቤቴ ወረዳና አካባቢያዊ ገፅታዋ ........ 34
3.2. የመርሐቤቴ ስያሜ ........ 35
3.3. ዋና ዋና ኃይማኖታዊና ብሄራዊ በዓላት ........ 36
3.3.1. እንቁጣጣሽ ........ 38
3.3.2. በመስቀል (ደመራ) ........ 38
3.3.3. ገና በዓል (የእየሱስ ክርስቶስ ልደት) ........ 39
3.3.4. የጥምቀት በዓል ........ 39
3.3.5. የፋሲካ በዓል ........ 40
3.3.6. ቡሄ (ነሐሴ 13) ........ 40
3.4. የመርሐቤቴ ወረዳ ባህላዊ የወሊድ ስነ-ስርዓት ........ 41
3.5.የመርሐቤቴ ወረዳ የሰርግ ስነ-ስርዓት ........ 41
3.6. የመርሐቤቴ ወረዳ የለቅሶ ስነ-ስርአት ........ 43
3.7. ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ........ 43
ምዕራፍ አራት ........ 45
የመርሐቤቴ ማህበረሰብ አለባበስና አጊያጊያጥ ........ 45
4.1 ሀገረሰባዊ አለባበስ ........ 45
4.1.1. የሴቶች ሀገረሰባዊ ልብሶች ........ 45
4.1.1.1. ጉያ ቀሚስ ........ 46
4.1.1.2. እጀ ጠባብ ቀሚስ ........ 49
4.1.1.3. አርባሽንሽን ቀሚስ ........ 51
4.1.1.4. መቀነት ........ 52
4.1.1.5. አንገት ልብስ ........ 54
4.1.1.6. ሻሽ ........ 56
4.1.1.7 የውስጥ ልብስ ........ 58
4..1.2. የወንዶች ሀገረሰባዊ ልብሶች ........ 49
4.1.2.1 ቁምጣ ........ 59

4.1.2.2. ሱሪ ........ 61
4.1.2.3. ኮት (jacket) ........ 62
4.1.2.4. ሹራብ እና ካኒቴራ ........ 63
4.1.2.5. ባርኔጣ እና ኮፍያ ........ 65
4.1.2.6 ፎጣ ........ 66
4.1.2.7. ኩታ ........ 67
4.1.2.8. ጋቢ እና ነጠላ ........ 68
4.1.2.9. ቡልኮ ........ 70
4.1.2.10. የመነኩሴ ልብስ ........ 71
4.1.2.11 ጥምጣም ........ 71
4.1.3. ሀገረሰባዊ መጫሚያ (ጫማ) ........ 72
4.2. ሀገረሰባዊ ጌጣጌጦች በወንዶችና በሴቶች ........ 74
4.2.1 የራስ ጌጦች ........ 74
4.2.2. የአንገት ጌጦች ........ 75
4.2.3. የጆሮ ጌጦች ........ 82
4.2.4.የወገብ ጌጥ ........ 83
4.2.5. የእጅ ጌጦች ........ 84
4.2 የፀጉር አሰራር ........ 90
4.4 የአልባሳቱና ጌጣጌጦች የለውጥ ሂደትና ማህበረሰባዊ አተያይ ........ 93
4.4.1. የአልባሳትና ጌጣጌጦች ለውጥ ንፅፅር ........ 96
4.4.2. የህፃናት ወንዶችና ሴቶች አለባበስና አጊያጊያጥ ንፅፅር ........ 96
ምዕራፍ አምስት ........ 102
5.1.ማጠቃለያና የይሁንታ ሃሳቦች ........ 102
5.2. የይሁንታ ሃሳቦች ........ 106
የአማርኛ ዋቢ ጽሑፎች ........ 107
የእንግሊዝኛ ዋቢ ጽሑፎች ........ 109
አባሪዎች

## የፎቶ ማውጫ


ፎቶ 1. የጉያ/ጉንፍ ቀሚስ አለባበስ ....... 48
ፎቶ 2. የወጣቶችና አዋቂዎች እጀ ጠባብ ቀሚስ አለባበስ ....... 50
ፎቶ 3. በተለያዩ የዕድሜ ክልል የአርባ ሽንሽን ቀሚስ አለባበስ ....... 52
ፎቶ 4. መቀነትና አንገት ልብስ ባላገቡና ባላገቡ ሴቶች ....... 54
ፎቶ 5. ሻሽ አስተሳሰር ....... 57
ፎቶ 6. በተለያዩ ዕድሜ ክልል ውስጥ ልብስ ሲለበስ ....... 58
ፎቶ 7. በተለያየ ዕድሜ ቁምጣ ሲለበስ ....... 60
ፎቶ 8. ሱሪ ....... 61
ፎቶ 9. ኮትና ሱሪ (ሙሉ ልብስ) ....... 63
ፎቶ 10. የጥለት ሹራብ ....... 64
ፎቶ 11. ባለሰረዝ ካኒቴራ ....... 64
ፎቶ 12. ባርኔጣ ....... 65
ፎቶ 13 ኮፍያ ....... 65
ፎቶ 14. ፎጣ ....... 66
ፎቶ 15. የኩታ አለባበስ ....... 67
ፎቶ 16. የአዋቂዎች ወንዶች ጋቢ አለባበስ ....... 68
ፎቶ 17. የአዋቂዎች ሴቶች ነጠላ አለባበስ ....... 68
ፎቶ 18. በለቅሶ የጊዜ የአዋቂ ሴቶች ነጠላና ጋቢ አለባበስ ....... 69
ፎቶ. 19. በለቅሶ የጊዜ የአዋቂ ወንዶች ነጠላና ጋቢ አለባበስ ....... 70
ፎቶ 20. ሀገረሰባዊ ጫማዎች ....... 73
ፎቶ 21. ዛጎልና አዝራር ....... 74
ፎቶ 22. ሚዶ የራስ ጌጦች ....... 75
ፎቶ 23. ድንብል ....... 76
ፎቶ 24. ዶቃ ....... 77
ፎቶ 25. ብርቅጥል ....... 78
ፎቶ 26. አርጌሽ ልሙት ....... 78

ፎቶ 27 የሴቶች ማህተብ (ጎፍታ)....................79
ፎቶ 28. የወንዶች ማህተብ (ጎፍታ)....................79
ፎቶ 29.አሸንክታብ በህፃትና ወጣቶች....................80
ፎቶ 30. ሙሽራ አገልግል....................80
ፎቶ 31. የአንገት ነጭ ክር (ማህተብ)....................81
ፎቶ 32. የጆሮ ጌጥ....................83
ፎቶ 33. የወገብ ጌጥ....................84
ፎቶ 34. የወጣቶች ብራምባር....................85
ፎቶ 35. የእናቶች ብራምባር....................85
ፎቶ 36. የእጅ ጎፍታ....................86
ፎቶ 37. ዱላ....................87
ፎቶ 38. የፀጉር አሰራር ዓይነቶች....................92
ፎቶ 39. የህፃናት አለባበስና አጊያጊያጥ....................96
ፎቶ 40. የወጣት ወንዶች አለባበስና አጊያጊያጥ....................98
ፎቶ 41. የወጣት ሴቶች አለባበስና አጊያጊያጥ....................99

**የሰንጠረዥ ማውጫ** **ገፅ**

ሠንጠረዥ 1. የህፃናት ወንድና ሴት የአዘቦት ቀናት አለባበስና አጊያጊያጥ ንፅፅር….97
ሠንጠረዥ 2. የወጣት ወንዶች የአዘቦት ቀናት አለባበስና አጊያጊያጥ ንፅፅር..........98
ሠንጠረዥ 3. የወጣት ወንዶች የአዘቦት ቀናት አለባበስና አጊያጊያጥ ንፅፅር........100

## ሙዳየ ቃላት

በጥናት የሚገኙ ቃላት በሚከተለው ፍች እንደሚከተለው ቀርበዋል፤

| | |
|---|---|
| – ሎቲ | የጆሮ ጌጥ |
| – መሂነኛ | ልብስ ሰፊ |
| – መንግስት ይሙት | በሰርግ ወቅት የሚከናወን መሀላ |
| – ማረባየት | መርገጥ/መረምረም |
| – ሠርክ/አዘቦት | በየቀኑ ወይም በየዕለቱ |
| – ሲሶ | 1/3ኛ ድርሻ |
| – ሸማኔ | ከድና ማግ ሸማ የሚሰራ የእጅ ሙያተኛ |
| – ነገር ቁርጫ | ሰርግ የሚሰረግበትን ቀንና የስጦታ ዕቃዎችን መወሰን |
| – አልባብ | ጥሩ ሽቶ |
| – አርባሸንሸን ቀሚስ፣ | ከወገቡ ተሸብሽቦ የሚዘጋጅ ቀሚስ |
| – አርቲ | የተፈጥሮ ጥሩ ሽታ ያለው የተክል ዓይነት |
| – አርጌሽ ልሙት፣ | ከብር፣ መዳብና ነሃስ የሚሰራ የአንገት ጌጥ |
| – አሸክርት | ሁለንተናው ሻካራ የሆነ ቅጠል ለመዋቢያ የሚያገለግል |
| – እናትያ | የአግቢዋ ሙሽራ አጫዋቾች የሰፈር ወጣቶች |
| – እንሶስላ/ግሽልጥ | የሴቶች እጅና እግር መዋቢያ ተክል |
| – እንግጫ | ጥሩ ሽታ ያለው የሳር ዓይነት |
| – እጀ ጠባብ ቀሚስ፣ | ከጥጥ ፈትል የሚሰራ የወጣቶች ቀሚስ |
| – ወለባ | ከብር የተሰራ ፀጉር ላይ የሚሰካ ጌጥ |
| – ወንፈል | አንዱ ለአንዱ እየተጋገዙ በጋራ መስራት |
| – ዐርበ ወጥ | ያልተሰፋ ብትን ጨርቅ |
| – ደቦ | ብዙ ሰው በጋራ የሚከውኑት የኅብረት ሥራ |
| – ዶቃ | ድቡልቡል ሆኖ የክር ማሳለፊያ ያለው የአንገት ጌጥ |
| – ጉያ ቀሚስ፣ | ከጥጥ ፈትል የሚሰራ የእናቶች ቀሚስ |
| – ጎፍታ | ከተለያዩ የጥለት ዓይነቶች የሚሰራ የአንገት ጌጥ/ማህተብ |
| – ዳስ | ከቅጠል ለማረፍያ የሚዘጋጅ ድንኳን |
| – ዛጎልና | ከተሳቢ እንስሳት የሚሰራ ጌጥ |

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

ይህ ጥናት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሰሜን ሸዋ ዞን መስተዳድር በመርሐቤቴ ወረዳ በሚገኙ በሴቶችና በወንዶች አልባሳትና ጌጣጌጦች ላይ የተደረገ  ነው፡፡ ማህበረሰቡ በሁሉም ዕድሜና ፆታ በበዓላት፣ በልዩ ፕሮግራምና የአዘቦት ቀናት የሚለበሱ/የሚደረጉ የአለባበስና አጊያጊያጥ ሥርዓት አሉት፡፡ ይህ ምዕራፍ መግቢያ፣ የጥናቱ ዳራ፣ አነሳሽ ምክንያት፣ የምርምር ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ ዘዴ እና የናሙና አመራረጥ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ ወሰን፣ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች እንዲሁም የመስክ ዘገባን ጨምሮ የቀረበበት ክፍል ነው፡፡

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

በርካታ የፎክሎር ባለሙያዎች የተለያዩ የፎክሎር ብያኔዎችን ሰጥተዋል፡፡ ለብያኔዎቹ መለያየት ደግሞ Leach Maria (1949) ፎክሎር አንድ ወጥ የሆነና ሁሉንም የሚያስማማ ተግባራዊ (operational) ብያኔ የሌለው ነው ሲሉ ያስረዳሉ፡፡ ይሁንና የተለያዩ ምሁራን የሰጧቸውን ብያኔዎች ከብዙ በጥቂቱ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ፎክሎር የሚለው መጠሪያ እ.ኤ.አ በ1846 በእንግሊዛዊው William Thoms ከተፈጠረበት ጊዜ አንስቶ ለሙያው መጠሪያና ለጥናት መስኩም በጋራ የሚያገለግል ስያሜ ሆኖ ቆይቷል፡፡ Thoms አቴናየም “Athenaeum” ለተሰኘ መጽሔት “Ambrose Merton” በሚል የብዕር ስም በላከው ጽሁፍ ላይም ለመጀመሪያ ጊዜ ፎክሎር የሚለውን ቃል የያዘ ጽሁፍ በመጽሔቱ ላይ ታትሞ እንደወጣና ለንባብ እንደበቃ እንዲሁም ፎክሎር “የሕዝቦች የጋራ ጥበብ (Folklore- The Lore of the People)” የሚል ብያኔን እንደሰጠው ሰለሞን ተሾመ (2007) ጽፈዋል፡፡

Dorson (1972) ፎክሎር የሰው ልጅ ስለአካባቢውና ስለዓለም ያለው ዕይታና ዕይታውን የሚገልፅባቸው ቃላዊ፣ መንፈሳዊና ቁሳዊ ሀብቶች፣ የማንነቱ ማሳያ አሻራ የሆኑትንና ከትውልድ ወደ ትውልድ እያስተላለፈ ያቆያቸውን የሕይወት ዘመን ተመክሮዎች የሚገልጽበት ጽንሰ ሃሳብ እንደሆነ ጠቅሰዋል ፎክሎርን በአራት መድበዋቸዋል፡፡ እነሱም ስነ-ቃል (oral literature) ከትውልድ ትውልድ በቃል የሚተላለፉ ቃላዊ ስነፅሁፎች (አፈ-ታሪኮችን፣ ሥነ ግጥሞችምን፣ መዝሙሮችን) ወዘተ ያካተተ፣ ሃገረሰባዊ ትውን ጥበባት (performing folk arts) ደግሞ ባህላዊ ዘፈኖችን፣ ጭፈራዎችንና ድራማዎችን የያዘ ሲሆን ሃገረሰባዊ ልማድ (social folk custom) ከአካባቢዎች (መንደሮች)፣ ከቤተሰብ፣

ከማህበረሰብ፣ ከአብያተ-ክርስቲያናት፣ ከበዓላት ጋር የሚዛመዱ ልማዶችን የሚዳስስ እንደሆነና ቁሳዊ ባህል (material culture) ደግሞ የሚጨበጥ የሚዳሰስ ነው በማለት አብራርተዋል፡፡ የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሣይንስና ባህል ድርጅት UNESCO (2010) የDorsonን ምደባ ይቀበልና ሀገረሰባዊ ልማድ “Intangible Cultural Heritage” የሚለውን “የተፈጥሮ እውቀትና ትግበራ” በማለት ለሁለት ከፍሎ በአምስት መድቧቸዋል። እንዲሁም ፈቃደ አዘዘ (1991) በበኩላቸው “ፎክሎር የሚለው ቃል አራቱን የጥናት መስኮች የሚያጠቃልል አድርገን እንውሰደው፡፡” ሲሉ በDorson ምደባ ይስማማሉ፡፡

ሌላኛው የዘርፉ ተመራማሪ Prown (1982) የDorsonን ምደባ መሰረት አድርገው ቁሳዊ ባህል አንድ ማህበረሰብ ለመገልገያነት የሚሰራቸው፣ በዓይን የሚታዩና የሚዳሰሱ ተጨባጭ ቁሶች ናቸው ሲሉ ያብራራሉ፡፡ ሰለሞን ተሾመ (2011) በበኩላቸው ቁሳዊ ባህል አንዱ የፎክሎር ዘውግ መሆኑን ጠቅሰው የሚታዩ፣ የሚዳሰሱና የሚቀመሱ ናቸው ሲሉ Glassie Henery (1968) ባህላዊ ቁሶች የማህበረሰቡን ፍልስፍና፣ ታሪክ፣ ባህል እምነትና ሃይማኖት የሚያሳዩ ጥበባዊ ውጤቶች መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡

የዘርፉ ምሁራን ከላይ በሰጡር ትርጓሜና ምደባ መሰረት የሰው ልጅ ዘወትር መገልገያ የሆኑት አልባሳትና ጌጣጌጦች በቁሳዊ ባህል ስር የሚመደቡ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ Danesi (2004) የሰው ልጅ አልባሳትን በትክክል መቼ መጠቀም እንደጀመረ ለማወቅ አዳጋች መሆኑን ገልፀው እንደ አርኪኦሎጂ ማስረጃዎች ከ100,000 ዓመታት በላይ ሊሆን እንደሚችል ግምታቸውን ተናግረዋል፡፡ Tortora & Eubank (1989) የተባሉ ተመራማሪዎች ደግሞ “The use of clothing was first discovered through “prehistoric cave paintings, from the Old stone Age, or Early Paleolithic Period, some 30,000 years ago” በማለት የአልባሳት አጠቃቀም ታሪክ በቀደምት የፓሎሊቲክ ዘመን የተገኘ እንደሆነ ይመሰክራሉ፡፡

በተጨማሪም Aishwariya (2018) የጥንታዊ ዘመን ሰዎች አልባሳትን ከእንስሳት ቆዳ እያዘጋጁ ይጠቀሙ እንደነበር “In early prehistoric times, the range of materials for clothing was small. Until about 10,000 years ago, people used animal skins for clothing.” በማለት የአልባሳት ታሪክን ይናገራሉ፡፡ እንዲሁም የኔዓለም አረዶ በበኩላቸው ኔያንደርታል (Neanderthal) የተባለው የሰው ዘር ከ 200,000 እስከ 30,000 ከክርስቶስ ልደት በፊት እንደ ቢላዋ ያሉ ጦር መሣሪያዎችን በመስራትና እንስሳት በማደን

በሂደትም ሰውነታቸውን መሸፈን እንደጀመሩ እ.ኤ.አ (2016) ለሦስተኛ ድግሪ ባቀረቡት የጥናት ስራቸው ላይ ገልፀዋል፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ኦሪት ዘፍጥረት (3፥7) “የሁለቱም ዐይኖች ተከፈቱ እነርሱም ራቁታቸውን እንደሆኑ አወቁ የበለስንም ቅጠሎች ሰፍተው ለእነርሱ ለራሳቸው ግልድም አደረጉ፡፡” እንዲሁም በዘፍጥረት (3፥ 21) ደግሞ በኋላም “እግዚአብሔር ለአዳምና ሚስቱ ከእንስሳ ቆዳ የተሠራ ልብስ (ቁርበት) አደረገላቸው አለበሳቸው” በማለት ያስረዳል፡፡

እንዲሁም በቅዱስ ቁርዓን (ምዕ.7 አል-አዕራፍ ክፍል 26) ላይ “የአደም ልጆች ሆይ ኀፍረተ-ገላችሁን የሚሸሽግን ልብስ ጌጥንም በእርግጥ በእናንተ ላይ አወረድን፤ አላህን የመፍራትም ልብስ ይህ የተሻለ ነው:: ይህ ከአላህ ታምራት ነው ይገሠፁ ዘንድ (አወረደላቸው)” በማለት ይገልፃል፡፡ ከሁለቱም የእምነት አስተምህሮ መረዳት እንደሚቻለው ልብስ (clothing) የሚባለው ቁስ ከሰው ልጅ ፍጥረት ጀምሮ የነበረ፣ ከተለያዩ ቁሶች መሰራት የሚችል እንዲሁም አካልን ለመሸፈንና ለማስዋብ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን ነው፡፡ Dorson (1972) “አልባሳት የአንድን ማህበረሰብ ሁለንተናዊ ኃይማኖታዊ ሥርዓት፣ ክብረ በዓላት፣ ሥርዓተ ንግስና፣ ዳኝነት፣ ህክምና፣ ወዘተ ጉዳዮችን ለመግለፅ ያገለግላል ሲሉ” L. Sebesta (1994) “the study of costume illustrates how interwoven the humanities are, not only with each other, but with other areas of study as well” በማለት የአልባሳት ጥናት ያላቸውን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያስረዳሉ፡፡

ሌላኛው የዚህ ጥናት አንዱ አካል የሆነውና በቁሳዊ ባህል ስር የሚመደበው ሀገረሰባዊ ጌጣጌጥ ሲሆን Clark (1986) ጌጣጌጦች ከመዋቢያነት ባለፈ የተጠቃሚውን ማህበረሰብ ወይም ግለሰብ ማንነት፣ የኑሮ ደረጃ፣ ዕድሜ እና ፆታ ለማመልከት ትዕምርታዊ ፋይዳ እንዳላቸው አብራርተዋል::

በጥቅሉ ከዚህ ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው አለባበስና አጊያጊያጥ የአንድን ማህበረሰብ ማንነት መለየት ወይም መግለፅ የሚያስችል መሆኑን ነው፡፡ ይሁንና የማህበረሰቡ ማንነት መገለጫ የሆኑት አልባሳትና ጌጣጌጦች በሌሎች ሀገራት ምርቶች ሲተኩ ይስተዋላል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ Tardif and Farchy (2006) የተባሉ የዘርፉ ተመራማሪዎች በአሁኑ ዘመን ለአኗኗር ዘይቤዎች መቀየር፣ ለቁሳዊ ባህሎች መጥፋትና ማንነቶች መሸርሸር የዘመነ ሉላዊነት ተፅዕኖ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ በተጨማሪም Sheikh (2014) ነባር ልማዶችን በአዳዲስ ሁኔታዎች የማሻሻል ማህበረሰባዊ ፍላጎት መኖሩን ይጠቅሳሉ፡፡

የጥናቱ መከናወን በቀጣይ በርከት ያሉ የጥናት ስራዎች እንዲቀርቡና በጥናቱ ለተለዩ ችግሮች ጉዳዩ በቀጥታ ለሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ አካላት ችግሩ

እንዲያውቁትና መፍትሄ እንዲያበጁለት ያግዛል፡፡ ይህም በዘርፉ ለሚደረግ የምርምር ስራ አንዱ አጋዥ በመሆን የራሱን አስተዋፅኦ እንዲያበረክት ያስችለዋል ተብሎ ይታመናል፡፡

በዚህ መነሻነት የመርሐቤቴ ማህበረሰብ አልባሳትና ጌጣጌጦችን ማጥናት የማህበረሰቡን የሕይወት ፍልስፍና፣ ማህበራዊ መስተጋብር፣ ታሪክ፣ እምነትና ሃይማኖት እንዴት እንደሚገልፁ? ለቁሶቹ መስሪያ የሚያገለግሉ ግብዓቶችን እንዴት እንደሚለዩ፣ በማን እንደሚሰሩ፣ ለምን እንደተመረጡ የአሰራር ሂደቱ ከዘመናዊ ቁሶች ጋር ያላቸውን መስተጋብርና የሚከወኑበትን ሥርዓት ምን ምን እንደሆኑ፣ ለቁሶቹ የመለወጥ ምክንያት የዘመነ ሉላዊነት ጣጣ ያስከተለው ተፅዕኖ ወይስ በማህበረሰቡ የለውጥ ፍላጎት በመኖሩ ይሆን? የሚሉ ጉዳዮችን መመርመር ነው፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህን ጥናት ለማከናወን ያነሳሱኝ ሁለት ምክንያቶች ናቸው፡፡ የመጀመሪያውና ዋናው ጉዳይ መርሐቤቴ የትውልድ ቦታዬ በመሆኑ በአካባቢው ያለውን የሴቶችና የወንዶች አለባበስና አጊያጊያጥ ሥርዓትን አየውና አውቀው ስለነበር ከፎክሎር ትምህርት ባገኘሁት እውቀት መሠረት ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ መጠናት ቢችሉ የማህበረሰቡ ፈጠራ ውጤት፣ እምነት፣ መለያና የአኗኗር ዘይቤን መመርመር ተገቢ መሆኑን በማመኔ ነው፡፡

ሁለተኛው ምክንያቴ ዕድሜን፣ ፆታን፣ ማንነትና ሃይማኖትን መሰረት ተደርገው የሚለበሱ እነዚህ ቁሳዊ ሀብቶች በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ምክንያቶች ሲለወጡና አንዳንዶቹም ሲጠፉ በመስተዋሉ ነው፡፡ በመሆኑም የማህበረሰቡ ማንነት መገለጫ በሆኑት አልባሳትና ጌጣጌጦች ላይ ለሚስተዋለው ለውጥ ምክንያት የሆነው የዘመነ ሉላዊነት (globalization) ተፅዕኖ ከፍተኛ መሆን? ወይስ የማህበረሰቡ የለውጥ ፍላጎት መኖር ይሆን? በሚል ጥያቄ ከራሴ ጋር ስሟገት ከቆየሁ በኋላ የማህበረሰቡን አልባሳትና አጊያጊያጥ ማጥናት ለቀጣይ ትውልድ በመረጃነት ሰንዶ ማቆየት የሚስችል እንደሆነ በማመን ማህበረሰቡ የሚታወቅባቸውን ባህላዊ አልባሳትና ጌጣጌጥ ለማጥናት ወሰንኩ፡፡ በዚህም ምክንያት በአካባቢው ላይ በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ የተሰሩ ጥናቶችን በምዳስስበት ወቅትም በዳራው ላይ የጠቀስኳቸውን ክፍተቶች በማግኘቴ ርዕሱን አሁን ባለው መልኩ ለመቀንበብ አስችሎኛል፡፡

በተለይም ሀገሪቱ ካላት የባህል ብዝሃነት አኳያ በሴቶችና በወንዶች አለባበስና አጊያጊያጥ ወይም ከእኔ ጥናት ርዕስ ጋር ቀጥተኛ ተዛምዷዊ ግንኙነት ያላቸውን የመጀመሪያ፣ የሁለተኛና የሦስተኛ ዲግሪ የጥናት ሥራዎችን በቤተ-መፃህፍት ቅኝት ባደርግኩበት ጊዜ በቁጥር ከአስር ልቀው አላገኘኋቸውም፡፡ ይህም ለጉዳዩ በቂ ትኩረት የተሰጠው አለመሆኑን

እንድረዳ አድርጎኛል፡፡ በመሆኑም እንደ አንድ የሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር ባለሙያ ተገቢውን ዕውቀት በመቅሰምና ልምድን በማካበት የፎክሎር ዘርፍ ላይ ጥልቅ ምርምር ለማድረግ ያለኝ ፍላጎት ለዚህ ጥናት እንድነሳሳ አድርገውኛል፡፡

## 1.3. የምርምር ጥያቄዎች

ጥናቱ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚከተሉትን የምርምር ጥያቄዎች ይመልሳል፡፡

1. በማህበረሰቡ የሚታወቁ አልባሳትና ጌጣጌጥ የትኞቹ ናቸው?
2. የአለባበስ ሥርዓታቸው ምን ይመስላል? የመልበሻ አጋጣሚዎች የትኞቹ ናቸው?
3. አልባሳትና ጌጣጌጦች በማን መቼ እንዴትና ለምን ይሰራሉ?
4. በሁለቱም ፆታና በተለያየ ዕድሜ ያሉ አልባሳትና ጌጣጌጦች መለያቸው ምንድነው?
5. በአልባሳቱና ጌጣጌጡ ላይ ለሚታዩ ለውጦች ምክንያታቸው ምንድነው?

## 1.4. የጥናቱ ዓላማዎች

የዚህ ጥናት ዓብይ ዓላማ ለጥናት በተመረጠው አካባቢ የሚከወኑ የሴቶችና ወንዶች አለባበስና አጊያጊያጥ ፋይዳ መመርመር ነው፡፡ ይህንን ተግባር ለማሳካት ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡ እነሱም፡-

1. አልባሳትና ጌጣጌጦችን አካላዊ ገፅታ ማሳየት፣
2. የአልባሳትና ጌጣጌጦች ትዕምርታዊ ትርጉም መግለፅ፣
3. ለውጥ የተስተዋለባቸውንና ያልተስተዋለባቸውን ቁሶቹ መመርመር፣
4. አልባሳቱና ጌጣጌጦች ለመጪው ትውልድ እንዲሸጋገሩ ሰንዶ ማቆየት፣

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

ሀገረሰባዊ አልባሳትና ጌጣጌጥ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ይገኛሉ፡፡ ሁሉንም አካባቢ ማዳረስ ደግሞ ጊዜ፣ ገንዘብ እና አቅም የሚጠይቅ ነው፡፡ በመሆኑም ጥናቱ በርዕሰ ጉዳይ፣ በጊዜና በቦታ የተገደበ ነው፡፡ ከቦታ አንፃር በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በሰሜን ሸዋ ዞን በመርሐቤቴ ወረዳ ላይ እንዲሁም ከጊዜ አንፃር ከነሐሴ 2013 ዓ.ም እስከ ሐምሌ 2016 ዓ.ም ባሉ 3 ዓመታት የተገደበ ነው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ቁሶቹ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ፈጣን ለውጥ እያሳዩ በመሆኑ የለውጥ ሂደቱን ለመፈተሽ በማለም ነው፡፡ ከርዕሰ ጉዳይ አንፃር ደግሞ በቁሳዊ ባህል ዘርፍ ከሚካተቱት ውስጥ በሀገረሰባዊ አልባሳትና ጌጣጌጦች ላይ ያተኮረ ነው፡፡ Wilson (1986) ሃገረሰባዊ አልባሳት (Folk Costume) የተለያዩ ጌጣጌጦችን

(Jewelry) የፀጉር አሰራርን (Hair styles) ንቅሳትን (Tattoos) እና የገላ ላይ ጌጦችን (Body decorations) የሚያጠቃልል የጥናት ዘርፍ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ በመሆኑም ተጠኚው ማህበረሰብ ንቅሳትን እየተወ በመምጣቱ ይህ ጥናት በሀገረሰባዊ አልባሳትና ጌጣጌጥ እንዲሁም ፀጉር አሰራር ላይ የተገደበ ነው::

## 1.6. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል፡፡

- ❖ አልባሳቱና ጌጣጌጦቹ የማህበረሰቡን መንፈሳዊ አስተሳሰብን፣ የአሰራር ስነ-ዘዴን፣ ክህሎትን፣ ሥርዓትን፣ እንዲሁም ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍበትን ቀመር (formula) ምን እንደሚመስል ለሌሎች ለመግለፅ ያሳያል፡፡
- ❖ በሀገራችን ያሉ የብሄረሰብ አልባሳትና ጌጣጌጥ በስፋት ባለመጠናቱ በፎክሎር መስክ ላይ ያለውን ክፍተት በመሙላት ረገድ የራሱን አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡
- ❖ የማህበረሰቡ የፈጠራ ውጤቶች የሆኑት ሀገራዊ አልባሳቱና ጌጣጌጡ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተለወጡ በመሆናቸው ለመጭው ትውልድ ማስተላለፍ ያስችል ዘንድ በሰነድ መያዙ የራሱ አስተዋፅዖ ይኖረዋል፡፡
- ❖ የወረዳውን አለባበስና አጊያጊያጥ ቁሳዊ ባህሎች ማወቅ ለሚፈልጉ አካላት እና ጥናት ለሚያካሂዱ፣ የዘርፉ ታሪክ አጥኚዎች፣ ለፀኃፊያን፣ ፊልም አዘጋጆች፣ ለባለድርሻና አጋር አካላት የመረጃ ምንጭነት ያገለግላል፡፡

## 1.7. የጥናቱ ዘዴዎች

ጥናቱ የተከናወነው ከዓይነታዊ የምርምር ዘዴ አንዱ የሆነው ገላጭ የምርምር ስልትን በመከተል ነው:: ይህን የጥናት ቅርጽ (design) መከተል ያስፈለገበትም ዋና ምክንያት ልዩ ልዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን፣ የመረጃ ምንጮችን ለመጠቀም በማስቻሉና መረጃዎችን ለመተንተን አመቺ ነው:: ገላጭ የምርምር ስልት ደግሞ አንድን ጉዳይ እያነሳ ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንፃር የችግሩን አሳሳቢነት በትረካዊ መንገድ ለማቅረብ የሚያስችል ነው፡፡

### 1.7.1 የጥናቱ አከዋወን ሂደትና ቅደም ተከተል

ርዕሱን በሚመለከት የተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝት፣ ለመረጃ መሰብሰቢያነት የሚያገለግሉ (ካሜራ፣ድምፅ መረፅ የሚችል የእጅ ስልክ፣ የእጅ ባትሪ፣ ብዕር፣ ማስታወሻ ደብተር፣ እርሳስ፣ ባትሪ ድንጋይ ወዘተ) የመሳሰሉትን የመስክ መሣሪያዎችን በበቂ ሁኔታ ቀድሞ ማሰናዳት የመጀመሪያ ክንውኖች ናቸው፡፡ በመቀጠልም የድርጊት መርሐ ግብር

በማዘጋጀት፣ ለጥናቱ ግብዓት አስፈላጊ የሚሆኑ መረጃዎችን ማግኘት እንዲያስቸለኝ በአካባቢው የሚኖሩ የእምነት አባቶችን፣ የሀገር ሽማግሌዎችን፣ ወጣቶችን እና የመንግስት አካላትን ቀድሞ የማነጋገር ስራ ሰርቻለሁ፡፡ በመጨረሻም በወጣው መርኃ ግብር መሠረት በመስክ ተገኝቼ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በመሰብሰብና በየፈርጃቸው በመመደብ ትንተና አድርጌያለሁ፡፡

## 1.7.2. የናሙና አመራረጥ

ጥናቱ ታላሚ ናሙና (Purposive sampling) አመራረጥ ዘዴን መሰረት ያደረገ ሲሆን በመርሐቤቴ ወረዳ ከሚገኙ 23 ቀበሌዎች ውስጥ አምስት ቀበሌዎች ለጥናቱ ተመርጠዋል፡፡ ቀበሌዎቹ ካላቸው የቆዳ ስፋት እና የህዝብ ብዛት አኳያ የተለያዩ ቁጥር ያላቸው መረጃ ሰጪዎች ተመርጠዋል፡፡ እሱም 9 (ዘጠኝ) ከጎራንዳ ማሪያም ሰርቃ፣ 9 (ዘጠኝ) ከግሬት ዋሪኝ፣ 5 (አምስት) ከገረን፣ 5 (አምስት) ከዘይታ ማጋስ፣ 5 (አምስት) ከኮሩ ወንጪት፣ ቀበሌዎች፣ እንዲሁም 3 (ሦስት) ኑሯቸውን ከገጠር ወደ ወደ ዓለም ከተማ ያደረጉና ባህሉን በደንብ የሚያውቁ የባህልና ቱሪዝም አመራርና ሰራተኞችን ጨምሮ 23 ወንዶችና 13 ሴቶች በድምሩ 36 መረጃ አቀባዮች በጥናቱ ተሳትፈዋል፡፡ ቀበሌዎቹ የተመረጡበት ምክንያት የወረዳውን አልባሳትና ጌጣጌጥ ሳይበረዙ እስካሁን ድረስ የቆዩባቸው በመሆናቸው ሲሆን ሌላኛው ምክንያት ደግሞ ቀበሌዎቹ ደጋ፣ ወይና ደጋና ቆላ የሚባሉ የአየር ንብረት ዓይነት ያሏቸው በመሆኑ በተወሰነ መልኩ የአለባበስና አጊያጊያጥ ልዩነት የሚስተዋል በመሆኑ ነው፡፡ እንዲሁም ስለ ባህሉ ያውቃሉ የተባሉትን መረጃ አቀባዮችን ደግሞ ከቀበሌዎቹ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የእምነት አባቶች፣ የቀበሌ አመራሮችና የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት በሰጡኝ ጥቆማ መሰረት የተመረጡ ናቸው፡፡ በዚህ ሂደት ላይ ሁለት ከ20 ዓመት በታች፣ ስምንት ከ21 እስከ 30፣ ሰባት ከ31 እስከ 40፣ ሰባት ከ41 እስከ 50፣ አምስት ከ51 እስከ 60 እንዲሁም ሰባት ከ61 በላይ ዕድሜ ያላቸው ሰዎች በመረጃ አቀባይት ተሳትፈዋል፡፡

## 1.7.3. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ለጥናቱም ማስኬጃነት ቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮች ተግባር ላይ ውለዋል፡፡ Goldstein (1964) የተሟላ መረጃ ለመሰብሰብ ጥልቀት ያለው መረጃ አሰባሰብ ዘዴ ተመራጭ እንደሆነ ይመክራሉ፡፡ በዚህም መሰረት ለጥናቱ ግብዓት የሚሆኑ ቀዳማይ መረጃዎቹ ተጠኚው ማህበረሰብ ወደ አለበት አካባቢ በመሄድ ከዋኝና ታዳሚዎችን፣ በመመልከት፣ በመጠየቅ፣ በተፈጥሯዊ መቼት የተሰበሰቡ ናቸው፡፡ ክዋኔውን ማግኘት ያልተቻለውን መረጃ ደግሞ በአርቲፊሻል መቼት በቃለ መጠይቅና በምልከታ ሰብስቤያለሁ፡፡

ጥናቱ ግቡን ይመታ ዘንድ ሦስቱንም የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ማለትም ምልከታ (ተሳትፏዊና ዕሞናዊ ዘዴዎች)፣ ቃለ መጠይቅና ተተኳሪ ቡድን ወይይት ስልትን በተግባር ላይ ውለዋል። እንዲሁም ርዕስ ጉዳዩን የተመለከቱ ንድፈ ሀሳቦችና ፅንሰ ሀሳቦችን ከተለያዩ መፃህፍት፣ መጣጥፎች፣ ከቤተ መፃህፍትና ኢንተርኔት በአጠቃላይ ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጥናቶች በካልዓይ የመረጃ ምንጭነት ተጠቅሜያለሁ።

### 1.7.3.1 ምልከታ

ለፎክሎር ጥናት መረጃ ከሚሰበሰብባቸው ዘዴዎች ውስጥ አንዱ ምልከታ ሲሆን አንድን ጉዳይ በንቃት የመከታተል፣ ትዕይንቱን በአግባቡ ቀርፆ የማስቀመጥና የተጠኚዎችን ባህሪ የመፈከር እውቀት የሚጠይቅ መሆኑን የዘርፉ ምሁራን ያስረዳሉ። Kothari (2004) ምልከታ ተሳትፏዊና ኢ-ተሳትፏዊ በሚባሉ መንገዶች ሊከናወን እንደሚችል ይገልፃሉ። ተሳትፏዊ የሚባለው አጥኚው የተጠኚው ማህበረሰብ አባል ሆኖ ሲገኝ ወይም ተጠኚውን ማህበረሰብ መስሎ የሚሳተፍበት ሂደት ነው። ኢ-ተሳትፏዊ ምልከታ የሚባለው ደግሞ ተመራማሪው ስለሚያጠናው ማህበረሰብ ባህል የማያውቅ በመሆኑ ምክንያት ዳር ቆሞ የሚያየውን በሙሉ የሚመዘገብበት ሂደትን የሚመለከት እንደሆነ አብራርተዋል።

በዚህ መሰረት ሦስት ጊዜ ምልከታ የተደረገ ሲሆን የመጀመሪያው ከነሐሴ 10 ቀን 2013 ዓ.ም እስከ መስከረም 30 ቀን 2014 ዓ.ም፣ ሁለተኛው ከታህሳስ 27 ቀን 2014 ዓ.ም እስከ ጥር 14 ቀን 2014 ዓ.ም፣ የመጨረሻው ደግሞ ከሚያዚያ 02 ቀን 2015 ዓ.ም እስከ ግንቦት 05 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ ሦስት ጊዜ ተከናውኗል። ይህ ወቅት የተመረጠበት አንደኛው ምክንያት በተጠኚው ማህበረሰብ የሚከበሩ ልዩ ልዩ ህዝባዊ እና ሃይማኖታዊ በዓላት በመኖራቸው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በሦስት ዓመታት ልዩነት ውስጥ በየትኞቹ አልባሳትና ጌጣጌጦቹ ፈጣን ለውጥ በመስተዋሉ ነው። በመሆኑም በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ያለውን የለውጥ ሂደት ማነፃፀር ለጥናቱ የተሻለ ውጤት ያመጣል በሚል እምነት ነው። ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በተፈጥሯዊ መቼት አማካኝነት በህዝባዊ እና ሃይማታዊ በዓላት፣ በመኖሪያና የገበያ ቦታዎች፣ በወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት እንዲሁም አርቴፊሻል መቼት "ስንደቅ የባህል ቡድን" በመጠቀም መረጃዎቹን ሰብስቤያለሁ።

### 1.7.3.2. ቃለ-መጠይቅ ዘዴ

ቃለመጠይቅ መረጃ ሰብሳቢው ለመረጃ አቀባዩ ጥያቄ በማቅረብ መረጃ የሚሰበሰብበት ዘዴ መሆኑን Gray (2004) በማለት ገልፀውታል። ይህ ዘዴ ከጊዜ አንፃር በምልከታ ሊገኙ የማይችሉ ጉዳዮችን ወደኋላ በመመለስ አጥኚው ያላያቸውን መረጃዎችን ለማግኘት

የሚያስችል ነው፡፡ የጥናቱ ጉዳይ የሆኑትን የአልባሳትና ጌጣጌጦች ጥያቄዎችን በሁለቱም ፆታ ከወጣት እስከ አዛውንት ካሉ የለባሹ ማህበረሰብ አባላት ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ዘዴ ሆኖ አገልግሏል፡፡

### 1.7.3.3. የተተኳሪ ቡድን ውይይት

የተተኳሪ ቡድን ውይይት በቃለ-መጠይቅም ሆነ በምልከታ ያልተሟሉና ግልፅ ያልሆኑ ወይም ማብራሪያ የሚፈልጉ መረጃዎችን ስለ ርዕሰ ጉዳዩ በሚገባ ያውቃሉ ከሚባሉ ሰዎች እርግጠኛና ሁሉን አቀፍ መረጃ ለማግኘት የሚያገለግል ስነ ዘዴ ነው፡፡ Schensul (1999) የተተኳሪ ቡድን ውይይት በርካታና አስተማማኝ መረጃ በአጭር ጊዜ ውስጥ ማግኘት ያስችላል ይላሉ፡፡ መሆኑም ይህን የመረጃ መሰበሰቢያ ዘዴ በመጠቀም ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ስለ ቁሶች በደንብ ከሚያውቁ የእምነት አባቶችን፣ ሀገር ሽማግሌዎችን፣ ወጣቶች፣ በግልና በመንግስት ተቋማት ከሚሰሩ ሰዎች ጋር ውይይት በማድረግ ግልጽ ያልሆኑና በቃለ መጠይቅ ያልተካተቱ መረጃዎችን እንድሰበስብ ረድቶኛል፡፡

በዚህም መሰረት ስለ አልባሳትና ጌጣጌጦቹ እንዲሁም ማህበራዊ ሁኔታ መልስ የሚሰጡ ሦስት የተለያዩ ቡድኖች እንዲደራጁ ተደርጓል፡፡ የመጀመሪያው ቡድን ሦስት የሀገር ሽማግሌዎች፣ ሁለት የእምነት አባቶች በድምሩ አምስት ሰዎችን ያካተተ ሲሆን በወንዶች አልባሳትና ጌጣጌጦች ላይ መስከረም 15 ቀን 2014 ዓ.ም በጎራንዳ ቀበሌ ውይይት አካሂደዋል፡፡ ተወያይተዋል፡፡ ሁለተኛው ቡድን ሦስት አዋቂ እናቶችን እና ሁለት ወጣት ሴቶች በድምሩ አምስት ሰዎች ያሉት ሲሆን በሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጥ ላይ ግንቦት 01 ቀን 2015 ዓ.ም በገረን ቀበሌ ውይይት አካሂደዋል፡፡ የመጨረሻውና ሦስተኛው ቡድን ሦስት የሀገር ሽማግሌዎችና ሁለት ወጣቶች በድምሩ አምስት ሰዎች የያዘ ሲሆን ስለማህበረሰቡ ማህበራዊ ሁኔታ መስከረም 21 ቀን 2014 ዓ.ም በኮራ ቀበሌ ውይይት በማካሄድ ለጥናቱ በቂ መረጃ ሰጥተዋል፡፡ በጥቅሉ ይህ ዘዴ ለጥናቱ እንዲውል መደረጉ ቡድኑ የእኔ ሲል የተስማማባቸውንና ዋጋ የሰጣቸውን ትክክለኛ መረጃዎች ለማግኘት እና ከሌሎች በቃለ መጠይቅ የተገኘውን መረጃ እውነተኝነት ለመመርመር አስችሎኛል፡፡

### 1.7.4. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

የመረጃ ትንተና ሲባል ለትናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ መረጃዎችን የመመደብ፣ የማደራጀት ወይም በየፈርጃቸው መልክ የምናስይዝበትና ትርጉም የምንሰጥበት የጥናት ሂደት ነው፡፡ Schwandt (2007) “it is the activity of making sense of, interpreting and theorizing data that signifies a search for general statements

among categories of data” በማለት ከመስክ የተሰበሰበውን ጥሬ መረጃ በንድፈ ሃሳቦችና ቀድሞ በተገኙ ውጤቶች እየተገናዘበ ትርጉም እንዲያገኝ የማድረግ ተግባር እንደሆነ አስረድተዋል፡፡ በዚህ መነሻነት በቀዳማይና ካልዓይ መረጃ ምንጮች ያገኘኋቸው መረጃዎች ከንድፈ ሃሳቦችና ፅንሰ-ሃሳቦች ጋር እያገናዘብሁ እንዲሁም ከዚህ በፊት የSchlereth የመተንተኛ ሞዴሎች እና የPrown መተንተኛ ስልቶች የተገለገሉ አጥኚዎችን መነሻ በማድረግ ጥናቱን ተንትኛለሁ፡፡

## 1.7.5 ቁሳዊ ባህልን የመተንተኛ ሞዴሎች

በዚህ ክፍል የቁሳዊ ባህል ጥናት ትኩረት ሊያደርግባቸው የሚገቡ ጉዳዮችንና የአጠናን ሂደቶችን Fleming (1974) በዘርፉ ላይ የተሰማራ አንድ አጥኚ የቁሱን ታሪክ፣ ቁሱ የተሰራበትን ንጥረ ነገር አካባቢያዊ ሁኔታውን ጨምሮ፣ የቁሱን አወቃቀር ከነባለሙያው፣ ምስሉንና ተግባሩን ማጥናት አለበት፡፡ ሲሉ 5 የትኩረት ነጥቦች ያስገነዝባሉ፡፡ በዚህም መሰረት Fleming በ5 ያስቀመጧቸውን የትኩረት አቅጣጫዎች Schlereth (1980) ሰፋባለ መልኩ ቁሳዊ ባህልን ለመተንተን ከታች የቀረቡትን 9 (ዘጠኝ) ሞዴሎችን ልንከተል ይገባል ሲሉ መክረዋል፡፡ እነሱም፡-

የባህላዊ ቁስን ጥበብ ታሪካዊነት (Art Historical-evaluation)፣ ተምሳሌታዊነት (Symbolic)፣ ባህላዊነት (Cultural)፣ አካባቢያዊነት (Environmenta)፣ አገልግሎት (Functionalist)፣ መዋቅራዊነት (Structuralist)፣ ባህርይ አመላካችነት (Behavioristy)፣ ማህበረሰባዊነት (Community) እና ማህበረሰባዊ ታሪካዊነትን (Social Historical) የትኩረት አቅጣጫ ያደረጉ ናቸው፡፡ በተጨማሪም የትኩረት አቅጣጫዎች (ሞዴሎችን) መሠረት አድርገን የተገነዘብናቸውን ጉዳዮች ልናሳይባቸው የሚገቡ የመተንተኛ ሂደቶች መኖራቸውን ማወቅ እንዳለብን ምሁራኑ ይናገራሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል Prown (1982) አንድ ጥናት በገለፃ (Description)፣ በትርጓሜ (Deduction) እና በመላምት (Speculation) ሂደቶች ማለፍ እንዳለበት ሲመክሩ Fleming ደግሞ በሦስቱ ሂደቶች ላይ “ግምገማ” (Evaluation) የሚል አንድ የትንተና ሂደትን በማካተት አራት አድርሰዋቸዋል፡፡ በመሆኑም ጥናቱ በተደረገበት የመርሐቤቴ ወረዳ ውስጥ ከሚገኙ 5 ቀበሌዎች የተሰበሰቡ መረጃዎችን በ prown የመተንተኛ ስልት በገለፃ (Description)፣ በትርጓሜ (Deduction) እና በመላምት (Speculation) ምርምር ስልት መሠረት ትንተና አከናውኛለሁ፡፡

## 1.8. በመስክ ያጋጥሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች

በመስክ ቆይታዬ ፈታኝ የሚባሉ ችግሮች አጋጥመውኛል፡፡ ከእነዚህ መካከል መጀመሪያ የተጓዝኩባቸው ጊዜያት በነሐሴ እና በመስከረም ወራት ስለነበር ወደ ገጠር ቀበሌ የሚወስዱ መንገዶች በጎርፍ መሸርሸራቸው፣ አንዳንዶቹ የገጠር ቀበሌዎች ተሽከርካሪ የሚይገባባቸው መሆኑ፣ የፀጥታ ችግር መኖሩ እንዲሁም በመረጃ አቀባይነት ሰዎችን በቀላሉ ማግኘት አለመቻሌና መረጃ ለመስጠት ቃል ገብተውልኝ የነበሩ ሰዎች የፎቶና የቪዲዮ ካሜራ ሲያዩ "በቴሌቭዥን ልንታይ ነው" በሚል የተሳሳተ ግምት መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው መረጃውን በቀላሉ እንዳልሰበሰብ ያጋጠሙኝ ችግሮች/ፈተናዎች ነበሩ፡፡

ይሁንና የጥናቱ ግብ እውን ይሆን ዘንድ በወቅቱ ያጋጠሙኝ ችግሮችን መቋቋም ግዴታ ስለነበር ለመኪና አመቺ በሆኑ የገጠር ቀበሌዎች የወረዳውን አስተዳደር፣ ባህልና ቱሪዝም፣ ኮሙዩኒኬሽን፣ የሚሊሻ ጽ/ቤቶችን የመኪና፣ የባህል ልማት፣ የፀጥታ አስከባሪና የፎቶና ቪዲዮ ባለሙያ ድጋፍ እንዲያደርጉልኝ በመጠየቅና ለሁሉም ጥያቄዎቼ ቀና ምላሽ በማግኘት፣ መኪና የማይደርስባቸውን ቀበሌዎች ደግሞ ሞተርሳይክል በመከራየት እንዲሁም ምንም ዓይነት ተሽከርካሪ በማይደርስባቸው አካባቢዎች ከአራት ሰዓት በላይ የእግር ጉዞ በማድረግ መረጃ የመሰብሰብ ዓላማዬን አሳክቻለሁ፡፡

በተጨማሪም ቀድሜ ባዘጋጀኋቸው የመረጃ አቀባዮቼ ምትክ ሌሎች የመረጃ አቀባዮችን እንዲሁም "በቴሌቭዥን ልንታይ ነው" የሚል የተሳሳተ ግምት ያላቸውን ሰዎች ከወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽቤት ባለሙያዎች፣ ከቀበሌ አስተዳደር አመራሮች ጋር በመመካከር የማሳመን እንዲሁም ተተኪ መረጃ አቀባዮችን በማዘጋጀት መረጃ ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡

## 1.9. የመስክ ቆይታ ዘገባ

በጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ላይ እንደገለፅኩት የመርሐቤቴ ወረዳ የትውልድ አካባቢዬ ቢሆንም በወቅቱ የነበረው የፀጥታ ችግር፣ መረጃ የተሰበሰበባቸው ቀበሌዎች ለተሽከርካሪ ምቹ ባለመሆኑ ረጅም ርቀት ያለው የእግር ጉዞ ማድረግን መገጠየቁ፣ እንዲሁም አንዳንድ የመረጃ አቀባዮች ፈቃደኛ አለመሆን ለጥናቱ ስራ ፈታኝ ያደረጉ ጉዳዮች ነበሩ፡፡ ይሁንና ከሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማትና፣ የቀበሌ አመራሮች እንዲሁም የሀገር ሽማግሌዎች ጋር ውይይት በማድረግ ያጋጠሙኝን ችግሮች መፍትሄ እንዲያገኙ አድርጌያለሁ፡፡ በመሆኑም ጥናቱ ሙሉ ይሆን ዘንድ በተለያዩ ወቅቶች ማለትም በክረምትና በፀደይ ወቅት ከቀን 10/12/2013 ዓ/ም እስከ 30/01/2014 ዓ.ም ባሉ ቀናት ውስጥ ከሦስት ጊዜ በላይ፣ እንዲሁም በበጋ እና በመፀው ወቅት ደግሞ ከቀን 27/04/2014 ዓ.ም እስከ 27/05/2014

ዓ.ም ድረስ አንድ ጊዜ፣ ከሚያዚያ 02 ቀን 2015 ዓ.ም እስከ ግንቦት 05 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ ሁለት ጊዜ በድምሩ ስድስት ጊዜ ወደ መርሐቤቴ ወረዳ ጉዞ አድርጌያሁ፡፡

ይህም በተለያዩ ወቅቶች የሚገለገሉባቸውን አልባሳትና ጌጣጌጦችን የተመለከቱ መረጃዎች ለመሰበስብ ነው፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ጊዜያት ባህላዊና ሃይማኖታዊ በዓላት ማለትም፡- የቡሄ፣ የፍልሰታ፣ የእንቁጣጣሽ (እንግጫ ነቀላ)፣ የመስቀል ደመራ፣ መስከረም 21 (ብዙኃን ማሪያም)፣ የገና፣ የጥምቀት፣ የፋሲካ በዓላት በማህበረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጣቸው ናቸው፡፡ እነዚህ አጋጣሚዎች ደግሞ የተጠኚው ማህበረሰብ አልባሳትና ጌጣጌጦችን እንዴት? መቼ? ለምን? እንደሚጠቀምባቸው ለማወቅ የሚያስችሉ በመሆኑ እኔም በቦታውም ተገኝቼ መረጃዎችን በቃለ መጠይቅ፣ በምልታና በተተኳሪ የቡድን ውይይት ለመሰብሰብ አስችለውኛል፡፡ ለዚህ ሂደት ደግሞ የውስጥ አወቅ (Intrinsic) አጥኚ መሆኔ አግዞኛል፡፡ ምክንያቱም ከመረጃ አቀባዮቼ ጋር በነበረኝ ቆይታ በጥያቄ ከተዘጋጁት በተጨማሪ በሚያነሷቸው ምላሾችና እኔም በማውቃቸው ጉዳዮች ላይ በጥልቀት ለመወያየት ዕድል ሰጥቶኛል፡፡

በጥቅሉ የመስክ ምልከታ ባደረግኩባቸው የተለያዩ ጊዜያት ላጋጠሙኝ ችግሮች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር እዚያው መፍትሄ በመስጠት ለጥናቱ አስፈላጊ ያልኳቸውን መረጃዎች ትክክለኛውን መረጃ መስጠት ከሚችሉ የማህበሰረቡ አባላት በድምፅ፣ በፎቶ፣ በቪዲዮና በጽሁፍ መሰብሰብ ችያለሁ፡፡ በመጨረሻም በመስክ የሰበሰብኳቸውን መረጃዎቼን በየፈርጁ የማደራጀትና የማረጋገጥ ስራዎችን አከናውኜ ወደ አዲስ አበባ ተመልሻለሁ፡፡

## 1.10. የጥናቱ አደረጃጀት

ጥናቱ አምስት ምዕራፎች አሉት፡፡ ምዕራፍ አንድ የጥናቱ መግቢያ፣ የጥናቱ ዳራ፣ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዓላማ፣ የምርምር ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ዘዴ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ ወሰን፣ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች እንዲሁም የመስክ ዘገባን የያዘ ነው፡፡ በምዕራፍ ሁለት የተዛማጅ ፅሁፎች፣ ጽንሰ ሀሳባዊና ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት የቀረበ ሲሆን በምዕራፍ ሦስት ደግሞ ጥናቱ የተካሄደበት ቦታ አጠቃላይ ገፅታ፣ የማህበረሰቡ ማህበራዊም ሆነ ባህላዊ ክዋኔዎችና መስተጋብሮች ተካተዋል፡፡ በምዕራፍ አራት በወረዳው ያሉ ሴቶችና ወንዶች የሚጠቀሙባቸውን ሀገረሰባዊ አልባሳትና ጌጣጌጦች ምን ምን እንደሆኑ፣ ምን ዓይነት ማህበራዊ ፋይዳና ትርጓሜ እንዳላቸው ትንተና የተካሄደበት ሲሆን በመጨረሻም ምዕራፍ አምስት የጥናቱ ማጠቃለያና የይሁንታ ሃሳቦችን የያዘ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ክፍል ሦስት መሰረታዊ ጉዳዮች ይነሳሉ። አንደኛው ከጥናቱ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ዝምድና ያላቸው ሥራዎች ቅኝት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በቁሳዊ ባህል ስር ከሚመደቡት አልባሳትና ጌጣጌጦችን አስመልክቶ የዘርፉ ተመራማሪዎች ያስተዋወቋቸውን ጽንሰ ሃሳቦች፣ ሦስተኛው ጉዳይ ደግሞ ለጥናቱ መቀንበቢያ የዋሉ ንድፈ ሃሳባዊ ጉዳዮች የቀረቡበት ነው።

## 2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ንዑስ ክፍል ከዚህ ጥናት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ጥናታዊ ጽሁፎችን ቅኝት አድርጊያለሁ። በቤተ መፃህፍት ቅኝት ከተደረገባቸው የጥናት ስራዎች መካካል በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሙዩኒኬሽን ኮሌጅ ለአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል እና በGraduate School of Emory University የቀረቡ ናቸው። በዚህም መሰረት ለአርትስ ባችለር ድግሪ ማሟያ የቀረቡ 2 (ሁለት) ስራዎች፣ ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ 6 (ስድስት) እንዲሁም ለዶክትሬት ድግሪ ማሟያ የቀረቡ 2 (ሁለት) በድምሩ 10 የጥናት ሥራዎች ሲሆኑ አንደኛው የዶክትሬት ድግሪ በGraduate School of Emory University በምስራቅ ሀረርጌ አፍረንቀሎ የኦሮሞ ማህበረሰብን አስመልክቶ የተጠና ነው።

በዚህም መነሻነት ለአርትስ ባችለር ድግሪ ከቀረቡ የጥናት ስራዎች ውስጥ መጀመሪያ የተመለከትኩት ውብሸት አሰፋ (1978) "የወይዛዝርት አልባሳትና ጌጣጌጥ ስሞች በአማራው ባህል" በሚል ርዕስ የቀረበ ነው። የጥናቱ ዓላማ በተሰራበት ዘመን መለበሳቸውና መደረጋቸው እየቀረ የመጣውን የአማራ ወይዛዝርት አልባሳትንና የጌጣጌጦችን ስም በመሰብሰብ ለተተኪ ትውልድ በማስተላለፍ ቅርሶቹን በሚገባ እንዲያውቃቸው ማድረግ የሚል ነው።

በዚህም መሠረት 34 የአልባሳት፣ 2 የጫማ እና 60 የጌጣጌጥ ስሞችን በመሰብሰብ የቁሶቹን መጠሪያ ስሞች ግለሰቦችን በማነጋገር፣ ከተለያዩ መጻህፍት በመሰብሰብ፣ የቃላቱ ፍቺ (ትርጉም) ምን እንደሆነ ትንተና ተካሂዶበታል። ወይዛዝርቱ የሚጠቀሙባቸውን አልባሳትና ጌጣጌጥ ዓይነቶችን፣ ለምን? መቼ? የሚሉ ጉዳዮችን መዘርዘሩ፣ የአለባበስን ታሪካዊ ዳራ መግለፁ እንዲሁም የቁሶቹ ባህላዊነት እንዲጠበቅ መምከሩ፣ አልባሳቱና ጌጣጌጡ

ከማህበረሰብ እምነት፣ ልማድ፣ አስተሳሰብ ጋር ያላቸውን የጠበቀ ግንኙነት ማሳየት መቻሉ ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ነው። የውብሸት ጥናት በወይዛዝርት አለባበስ ላይ ብቻ ያተኮረ ሲሆን የእኔ ጥናት ደግሞ በፆታና በዕድሜ ያልተገደበ መሆኑ፣ ጥናቱ መስክ ምልከታ ተገኝቶ ሳይሆን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ውስጥ ያሉት መረጃዎች ብቻ መሰረት ያደረገ የመረጃ አሰባሰብ ስልትን መጠቀሙ፣ የስያሜዎቹን ፍቺ ከመዝገበ ቃላትና ሰዎችን በመጠየቅ ላይ ብቻ ያተኮረ መሆኑ፣ በመረጃ አሰባሰብ ስነ-ዘዴው እንዲሁም ጥናቱ በተደረገበት ቦታና ጊዜ ከእኔ ጥናት ጋር ይለያል።

በመጀመሪያ ድግሪ ከተሰሩ ጥናቶች ውስጥ በሁለተኛነት የተመለከትኩት የአያል አድማሱ (1992) "የጎጃም አካባቢ አልባሳት ስያሜ" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ክፍለ ትምህርት ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበውን ጥናት ነው። የጥናቱ ዋና ዓላማ የአልባሳቱ መጠሪያ ቃላት ስነ-ቃላዊ ሆነው የተፈጠሩ መሆን አለመሆናቸውን መመርመርና ስለህብረተሰቡ ሁኔታ የሚገልፁትን ስያሜዎች ምንን መሰረት እንዳደረጉ መተንተን ነው።

በጥናቱ የፋብሪካ ምርት የሆኑትን ከዘመናዊ አልባሳት (ፋሽን) ጋር የተያያዙ አልባሳት ዋጋቸውን፣ ቀለማቸውን፣ ተፈላጊነታቸውን መሠረት ያደረጉ ስያሜዎች መጀመሪያ እንደሚሰጣቸውና በኋላም እየቆዩና እየተለመዱ ሲሄዱ የለባሻቸውን ዕድሜ ፆታ ሙያ እንዲሁም የመሰልቸታቸውን ሁኔታ በሚያመላክቱ ቃላት መጠራታቸውን፣ እንዲሁም በለባሹም ሆነ በተመልካቹ ላይ አልባሳቱ የሚያሳድሩት ስሜት ለአብዛኛዎቹ ልብሶች ስያሜ ምንጭ ሆኖ እንዲሚያገለግል በጥናቱ ላይ ተመልክቷል። በአጠቃላይ የአያል ጥናት በአልባሳት ላይ ትኩረት ማድረጉ፣ በፆታና በዕድሜ ያልተገደበ መሆኑ ከእኔ የጥናት ሥራ ጋር የሚያመሳስለው ቢሆንም የአልባሳቱን የመልበሻ አጋጣሚዎችና ባህላዊ እንድምታዎችን ባለመመልከቱ እንዲሁም ጥናቱ በተደረገበት ቦታና ጊዜ ከእኔ ጥናት ጋር የሚለይ ነው።

ሌላው ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ከተሰሩት የጥናት ስራዎች እንደጠኑበት ዘመን ቀድሜ የተመለከትኩት ጥናት የየኔዓለም አረዶ (2000) "የአርሲ ሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጥ ጥናት (በኮኮሳና ገደብ ሀሳሳ ወረዳዎች)" የሚለውን ነው። የጥናቱ ዓላማ በሁለቱ ወረዳዎች የሴቶችን የባህል አልባሳትና ጌጣጌጥ የቀድሞና የአሁን ይዘታ መመርመርና ያለበትን ሁኔታ ማሳየት ነው። ጥናቱ በተካሔደባቸው ወረዳዎች የሚገኙት ሴቶች በቀደሙት ጊዜያት የሚለብሷቸው ልብሶች በአብዛኛው ከቆዳ የተሰሩ እንደነበሩ፣ እነዚህም የተለያየ የአለባበስ ስርዓትና የመለበሻ አጋጣሚዎች እንዳላቸው እንዲሁም ጌጣጌጦቹ ከሚውሉበት የሰውነት ክፍል አንጻር በተናጠል ትንተና ሰጥታባቸዋለች። ለጥናቱ መተንተኛነት ዓይነታዊ የምርምር

ዘዴን የተጠቀመች ሲሆን ከዚህም የምርምር ዓይነት ገላጭ የምርምር ዘዴን በመጠቀም በ12 አልባሳትና በ28 ጌጣጌጦች ላይ ትንታኔ ሰጥታለች፡፡

የእኔና የየኔዓለም ጥናት በጥናቱ ርዕስ ከመመሳሰሉ በተጨማሪ በልብሶቹ ላይ ለውጥ መከሰት አለመከሰቱን መፈተሽ ከዓላማችን አንዱ መሆኑና ቁሳዊ ባህሉን ከማህበረሰቡ አተያይ አንጻር መመልከታችን ያመሳስለናል፡፡ ሆኖም ግን ከቦታ አንጻር የየኔዓለም ጥናት በሁለት ወረዳዎች ላይ የተደረገ ንፅፅራዊ ጥናት ሲሆን የእኔ ጥናት ደግሞ በአንድ ወረዳ ላይ ብቻ ማተኮሩ እንዲሁም የየኔዓለም ጥናት በሴቶች ላይ ብቻ መወሰኑና የእኔ ጥናት ደግሞ ወንዶችንም የሚመለከት በመሆኑ እንዲሁም ቦታና ጊዜ መለያየቱ ጥናቱ እንዳይመሳሰል አድርጎታል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የተመለከትኩት ሰይድ ይማም (2002) “በከሚሴ ከተማ ዙሪያ በሚገኙ ገጠር አካባቢዎች የወጣት ወንዶችና ሴቶች አለባበስና አጊያጊያጥ” የሚለው ሌላኛው በተዛማጅነት የተመረጠ ጥናት ነው፡፡ ይህም ከእኔ የጥናት ርዕስ ጋር የሚያመሳስለው ይሆናል፡፡ የዚህ ዓላማ በከሚሴ ከተማ ዙሪያ በሚገኙ አምስት የገጠር አካባቢዎች ያሉ ወጣት ወንዶችና ሴቶች ምን ምን አልባሳትን እና ጌጣጌጦችን እንደሚጠቀሙ፣ አልባሳቱና ጌጣጌጦቹም ያሏቸው አገልግሎቶች፣ ባህላዊና ማህበራዊ ፋይዳዎች ምን ምን አንደሆኑ መርምሮ ለማሳየት ነው፡፡

ቃለመጠይቅ፣ ምልከታ እና የቡድን ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ ስነዘዴዎችን በመጠቀም ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች የተሰበሰቡ ሲሆን ለተሰበሰቡ መረጃዎች መተንተኛነት ደግሞ ከዓይነታዊ የምርምር ዘዴ ገላጭ የምርምር ዓይነትን በመጠቀም ሴቶች ከመታጨታቸው በፊት፣ በሚታጩበት ወቅትና ካገቡ በኋላ በሚጠቀሙባቸው 6 አልባሳትና 15 ጌጣጌጦች ላይ ትንተና ሰጥቷል፡፡

የሰይድን ጥናት የአልባሳትና ጌጣጌጦችን ምንነት መግለፅ፣ ሀገረሰባዊ አልባሳትና ጌጣጌጦች በሌላ ሳይተኩ ተጠብቀው እንዲቆዩና ለቀጣዩ ትውልድም እንዲተላለፉ በማድረግ በኩል መንግስታዊ ሆኑ መንግስታዊ ባልሆኑ አካላት ትኩረት እንዲያደርጉ ያመላከተበት መንገድ ከኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡ ነገር ግን ሰይድ ከጌጣጌጦቹ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የተወሰኑ ቃላዊ ግጥሞችን የተመለከታቸው በመሆኑና የእኔ ጥናት ደግሞ ቃላዊ ግጥሞችን የተመለከታቸው ባለመሆኑ፣ እንዲሁም በወጣት ሴቶችና ወንዶች ላይ ብቻ ትኩረት ያደረገ ሲሆን የእኔ ጥናት ደግሞ በዕድሜ ያልተገደበ በመሆኑ፣ የጥናቱ ቦታና ጊዜ መለያየትም ለልዩነቱ ምክንያት ሆኗል፡፡

ቀጥሎ ያሬድ ተፈራ (2002) “በሰቆጣና በአበርገሌ ገጠራማ ወረዳዎች የሴቶችና የወንዶች የአለባበስና የአጊያጊያጥ ማህበራዊ እሴቶች” በሚለው ጥናቱ በሁለቱ ወረዳዎች ያለውን የአለባበስና አጊያጊያጥ ልምድ የመረመረ ሲሆን ቁሶቹን፣ የቁሶቹን አሰራር፣ ተግባር፣ ባለሙያዎቹን፣ የተደረገባቸውን ለውጥና ከቁሶቹ ጋር ተያይዘው የሚባሉ ሥነ-ቃሎችን የዳሰሰ ነው፡፡ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ እንዲያስችለው ቃለመጠይቅ፣ ምልከታና ተተኳሪ የቡድን ውይይት ስነዘዴዎችን ተጠቅሟል፡፡ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ከንድፈ ሃሳቦቹ ጋር በማገናዘብ በFleming 5 የትኩረት አቅጣጫዎች መሰረት 4 አልባሳትና 7 ማጌጫዎችን ተንትኗል፡፡ በተጨማሪም በአልባሳቱና ጌጣጌጦቹ ላይ የሚታየውን ለውጥና ምክንያት እንዲሁም ማህበረሰቡ ለለውጡ ያለውን አተያይ አመላክቷል፡፡

ይህ ጥናት በተመረጠው ቦታ የሴቶችንና የወንዶችን አለባበስና አጊያጊያጥ የሚመለከት በመሆኑ፣ የአልባሳቱን የመሰሪያ ቁስ መግለጹ፣ በአልባሳቱና ጌጣጌጦቹ ላይ ያለውን ለውጥና የለውጡን ምክንያት መዳሰሱ፣ ከእኔ ጥናት ጋር ይመሳሰላል፡፡ እንዲሁም በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴውም ተመሳሳይነት ይታይበታል፡፡ ሆኖም ግን የያሬድ ጥናት በአልባሳቱና ጌጣጌጦቹ ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ሥነ-ቃሎችን መካተቱ ለትንታኔው ማስኬጃነት የFlemingን 5 የትኩረት አቅጣጫዎች የተጠቀመ መሆኑ እንዲሁም ጥናቱ የተደረገበት ቦታና ጊዜ ከእኔ ጥናት ይለያል፡፡

በአራተኛ ደረጃ የተመለከትኩት በአፀደ ያረጋል (2003) የተካሄደው “የኮንሶ ሃገረሰባዊ አልባሳት እና ጌጣጌጦች፡- ገላጭ- ተንታኝ ጥናት” የሚለው ነው፡፡ የዚህ ጥናት ዓላማ የኮንሶን ሃገረሰባዊ አልባሳትና ጌጣጌጦች ዓበይት ቁሳዊ ገጽታዎችን ማህበራዊና ጥበባዊ ፋይዳዎችን መመርመር ነው፡፡ አፀደ በጥናቷ የባህላዊ አልባሳቱን፣ ጌጣጌጦችንና የማህበረሰቡን የፀጉር አሰራር ገጽታ በመግለጽ የአለባበስ ስርዓቱን፣አጋጣሚዎችንና ማህበራዊ ፋይዳዎቹን አሳይታለች፡፡ በተጨማሪም አልባሳቱ የማህበረሰቡን አባላት ማንነት እና እሴቶች እንደሚገልጹ፣ በቁሶቹ ዙሪያ እየተደረጉ ያሉ ለውጦችን ከነምክንያታቸው አሳይታለች፡፡ በዚህም ማሳያነት የተመረጡ ሦስት የፀጉር አሰራር፣ ሰባት አልባሳትን እና 12 የጌጣጌጥ ዓይነቶችን ተንትናለች፡፡

የአፀደ ጥናት በአልባሳትና ጌጣጌጥ እንዲሁም የፀጉር አሰራር ላይ ትኩረት ማድረጉ፣ አልባሳቱ የማህበረሰቡን አባላት ማንነትና እሴቶች እንዴት እንደሚገልፁ ማሳየቱና የቁሶቹን ለውጦች ከነምክንያታቸው መግለፁ ከኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ምልከታንና ቃለመጠይቅ ዘዴን የተጠቀመች ሲሆን የእኔ ጥናት ደግሞ በተጨማሪ ተተኳሪ የቡድን ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ተጠቅሟል፡፡

በመሆኑም የእኔ ጥናት በዕድሜ ያልተገደበ ሲሆን የአፀደ ጥናት ልጆች አልባሳትን አያካትትም፣ እንዲሁም የእኔ ጥናት ዘጠኙን የSchelereth መተንተኛ ሲጠቀም የአፀደ ጥናት ደግሞ የFleming መተንተኛ ሞዴል መጠቀሟ በተጨማሪም ጥናቱ በተደረገበት ቦታና ጊዜ ከእኔ የጥናት ርዕስ ጋር የሚለይ ነው፡፡

በአምስተኛ ደረጃ የተመለከትኩት የአመልማል ተሻለ (2004 ዓ.ም) "በባንጃ ወረዳና አካባቢዋ የአዊ ብሄረሰብ አለባበስና ጌጣጌጦች ገላጭ-ጥናት" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሙዩኒኬሽን ኮሌጅ ለኢትዮጵያ ሥነጽሁፍና ፎክሎር ለኤምኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበውን ነው፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ በአዊ ብሔረሰብ ባንጃ ወረዳና አካባቢዋ ያሉትን አለባበስና አጊያጊያጥ ውክልናቸውን መመርመር፣ መሰነድ፣ መግለፅና ማሳየት የሚል ነው፡፡

ለጥናቱ ማስኬጃነት በምልከታ፣ ቃለ-መጠይቅና ተተኳሪ የቡድን ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ ካልዓይ የመረጃ ምንጭ እንዲሁም ገላጭ (Description) የምርምር ዘዴን ተጠቅማለች፡፡ አመልማል 10 አልባሳት፣ 6 ጌጣጌጦችን በFleming (1974:156) መተንተኛ ሞዴል ትንተና ሰጥታባቸዋለች፡፡ እንዲሁም በ3 የፀጉር አሰራሮች እና ንቅሳቶች፣ ከቁሱ ጋር የሚነገሩ ስነ ቃሎችን ትንተና አድርጋበታለች፡፡

አመልማል በልብሶችና ጌጣጌጦች ላይ እየተስተዋሉ ያሉ የለውጥ ሁኔታዎች፣ በፀጉር መላጨትና ንቅሳት ከመስሪያ ቁሶች ጀምሮ ላለው መለወጥ የዘመናዊ ትምህርት መስፋፋት እንደሆነ ገልፃለች፡፡ በመሆኑም በቁሶቹ ላይ እየተስተዋሉ ያሉ የለውጥ ሂደቶች፣ ጌጣጌጦቹ ከማጌጫነት በተጨማሪ ለሽታዎች መፈወሻነት የሚያገለግሉ መሆኑን በትንታኔ ማካተቷ ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡ ሆኖም ግን በልብሶችና ጌጣጌጦች ላይ ለሚስተዋሉ ለውጦች የዘመናዊ ትምህርት መስፋፋት እንደሆነ የደረሰችበት ድምዳሜና የተጠቀመችው መተንተኛ ሞዴል እንዲሁም ጥናቱ የተካሄደበት ቦታና ጊዜ ከእኔ ጥነናት ጋር ይለያል፡፡

በስድስተኛ ደረጃ አዜብ ወርቅነህ (2006 ዓ.ም) "የካፍቾ ብሔረሰብ የሴቶችና የወንዶች አለባበስና አጊያጊያጥ ገላጭ ጥናት" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሙዩኒኬሽን ኮሌጅ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር ለድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር ማሟያ የቀረበውን ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ በካፍቾ ብሔረሰብ የሴቶችና የወንዶች የአለባበስና አጊያጊያጥ ባህሎችን በመመርመር ልብሶችና ጌጣጌጦች፣ የፀጉር አሰራር ዓይነቶቹ በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸውን ማህበረሰባዊ ፋይዳ ማሳየት እንዲሁም ሰንዶ ማኖር የሚል ነው፡፡

ለጥናቱ ምልከታ፣ ቃለ-መጠይቅና ተተኳሪ የቡድን ውይይትና ካልዓይ የመረጃ መሰብሰቢያ ስልቶችን እንዲሁም ገላጭ (Description) የምርምር ዘዴን ተጠቅማለች፡፡ እንዲሁም በሁለቱም ፆታዎች 12 አልባሳት፣ 19 ጌጣጌጦች፣ 4 የፀጉር አሰራሮችንና ከቁሶቹ ጋር የሚነገሩ ግጥሞችን በመሰብሰብ የይዘት ትንተና አድርጋለች፡፡ ለትንታኔው ማስኬጃነት ዘጠኙ የSchlereth ሞዴሎችን ተጠቅማለች፡፡ አዜብ ለጥናቱ መተንተኛነት የተጠቀመችው ስነዘዴ ለውጥን በጥልቀት መመልከቷ ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ሲሆን ከአለባበስና አጊያጊያጥ ጋር የሚነገሩ ስነ-ቃሎችን በጥናቷ ማካተቷ እንዲሁም ጥናቱ በተካሄደበት ቦታና ጊዜ ከእኔ ይለየዋል፡፡

ሌላው ከእኔ ጥናት ጋር ተዛማጅ የሆኑ የሦስተኛ ድግሪ ማሟያ ጥናት ስራዎችን በዳሰስኩበት ወቅት ያገኘኋቸውን ሁለት ጥናቾች የመረጥኩበት ምክንያት ቁሳዊ ባህሎች በውስጥ አወቅ (Intrinsic) በውጭ አወቅ (Extrinsic) አጥኚዎች ሲጠኑ ያላቸውን እንድምታ ለመረዳት ነው፡፡ በዚህም መሰረት ቅድሚያ የተመለከትኩት የKlemm, Peri (2002) “Shaping the Future, Wearing the Past: Dress and Decorated Female Body among the Afran Qallo Oromo in Eastern Hararghe Ethiopia” በሚል ርዕስ ለFaculty of the Graduate School of Emory University የቀረበውን ነው፡፡ የጥናቱ ዓላማ በማህበረሰብ ጥናት የጥበብ ታሪክ እና የቁሳዊ ባህላቸው በተለይም የአለባበስን ግንኙነት ለመመርመር ያለመ ሲሆን በተለይም በሀረርጌ ኦሮሞ የሴት አለባበስ የጥበብ ታሪክ ላይ ልዩ ትኩረት አድርጓል፡፡ ከአለባበስ ዓይነቶች ጋር የሚዛመዱ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁነቶችን በጥናቱ ተመላክተዋል፡፡ ጥናቱ አልባሳትና ጌጣጌጥን በመመልከቱ ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ሲሆን በሴቶች አልባሳት ላይ መወሰኑ፣ ጥናቱ የተካሄደበት ቦታ፣ ጊዜ፣ የተጠቀመው የምርመራ (examining) ስነዘዴ ከእኔ ጥናት ጋር እንዲለያይ ያደርገዋል፡፡

ሌላው የተመለከትኩት Yenealem Aredo (2016) “Description and Documentation of Traditinal Dress: the Case of Arsi Oromo” በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሙዩኒኬሽን ኮሌጅ ሥነልሳንና ፊሎሎጂ ትምህርት ክፍል ለሦስተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበውን ጥናት ነው፡፡

የጥናቱ ዋና ዓላማ በአርሲ ኦሮሞ ያለውን ሀገር በቀል የልብስ አሰራርና እና የአለባበስ ባህል ክህሎት እና ዕውቀት ለመግለፅ እና ጠብቆ ለማቆየት ሲሆን ይህን በማድረግ በዘመነ ሉላዊነት (globalization) ለአደጋ የተጋለጠውን የባህላዊ አለባበስ ከመጥፋት መታደግ እንደሚያስችል ትኩረት ያደረገ እንደሆነ በዓላማው ተጠቅሷል፡፡ ጥናቱ ዓይነታዊ የምርምር

ዘዴን የተከተለ ሲሆን ከተጠቀማቸው ዘዴዎች ዓላማን መሰረት ያደረገ (purposive sampling) እና "ጥቆማን መሠረት ያደረገ" (snowball sampling) ናሙና ዘዴዎች የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ለቡድን ውይይት 21 ለቃለ መጠይቅ ደግሞ 24 መረጃ ሰጪዎችን በመምረጥ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ እና ተተኳሪ ቡድን ውይይት አማካኝነት ለጥናቱ አስፈላጊ የሆነውን መረጃ ሰብስባለች፡፡ እንዲሁም ለጥናቱ ትንተና ማስኬጃነት ቅይጥ የምርምር ዘዴን በመጠቀም ትንተና አካሂዳለች፡፡

ጥናቱ በህዝቡ መካከል የባህላዊ አለባበስ አጠቃቀም እና ተግባር ላይ ቀጣይነት ያለው ለውጥ እንዳለ፣ ባህላዊ አለባበስ በህፃናትና በወጣቶች ላይ እየተዘወተረ አለመሆኑና ዕድሜያቸው 35 እና ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች ብቻ የሚለበስ መሆኑን፣ የዕደ ጥበብ ሙያተኞች እየጠፉ ስለመሆኑ የጥናቱ ግኝት ያመላክታል፡፡ እንዲሁም እየተስተዋሉ ያሉ የለውጥ አደጋዎችን ለመካከል ወይም ለመቀነስ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ሰፋ ባለና በተጠናከረ መልኩ የአርሲ ኦሮሞ ባህልና አለባበስ ለመጠበቅ ከፍተኛ ተሳትፎ ማድረግ እንዳለባቸው አመላክተዋል፡፡ ይህም ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ሲሆን የጥናቱ ርዕስ ባህላዊ አልባሳት (Traditinal Dress) ላይ ብቻ የተገደበ መሆኑ እንዲሁም ለጥናቱ ማስኬጃነት የተመረጠው ስነዘዴ ከእኔ ጥናት የሚለይ ነው፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ ጥናት ጋር ቀጥታ ተዛማጅ ናቸው ተብለው ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ጥናቶች ዋና ትኩረታቸው ለጥናት የመረጧቸውን ቁሶች የአሰራር ሂደት ምን እንደሚመስል፣ ቁሶቹ ከምን ከምን እንደተሰሩ መግለጽ፣ ለማህበረሰቡ የሚሰጡት አገልግሎት ምን እንደሆነ፣ ማህበረሰቡ ለቁሶቹ የሚሰጠው ትርጓሜ ምን እንደሆነ እንዲሁም ከቁሶቹ ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ቃላዊ ግጥሞችን መሰብሰብና የባለሙያዎቹ ማህበራዊ ህይወት ምን እንደሚመስል ማሳየት ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡

በመሆኑም አጥኚዎቹ ለጥናት በመረጧቸው ቁሶች፣ እንዲሁም ቁሶቹ ለማህበረሰቡ የሚሰጡት አገልግሎትና ማህበረሰቡ ለቁሶቹ የሚሰጠው ተምሳሌትነት በዚህ ጥናትም የሚታዩ መሆናቸው ከላይ ከተገለፁት ጥናቶች ጋር የሚያመሳስለው ነው፡፡ ነገር ግን ከላይ በቀረበው ምልከታ መሰረት በስነ-ዘዴ አመራረጥ፣ በዓላማ፣ በጾታ፣ በዕድሜ፣ በዘመን፣ በቦታ ላይ የተስተዋሉ ልዩነቶች ከእኔ ጥናት ጋር እንዳይመሰሳሰሉ ያደርጋቸዋል፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት ከቀደሙት የጥናት ስራዎች በርዕሰ ጉዳይ ሁሉንም የዕድሜ ደረጃና ፆታ በማካተቱ፣ ከጥናት ስነዘዴ፣ ከዓላማ፣ ከዘመን፣ ከቦታ ወዘተ ጉዳዮች አንፃር ይዞት በሚመጣው ግኝት በዘርፉ ለሚደረግ ምርምር የራሱን አስተዋፅኦ የሚያበረክት ይሆናል፡፡

## 2.2. ጽንሰ ሀሳዊ ቅኝት

አንድን የፎክሎር ዘርፍ ለማጥናት ተስማሚ የሆኑትን የጽንሰ-ሃሳብ አቅጣጫዎች ለይቶ ማወቅና ተግባራዊ ማድረግ ተገቢ ነው። ስለሆነም በቁሳዊ ባህል ዙሪያ በተለይም ስለ አልባሳትና ጌጣጌጥ ምንነት፣ ፋይዳ፣ አስፈላጊነት፣ አመዳደብና አተናተን ዘዴዎች በተለያዩ ምሁራን የተበየኑት ጽንሰ ሀሳቦች እንደሚከተለው ተካተው ቀርበዋል።

### 2.2.1. ቁሳዊ ባህል

የቁሳዊ ባህል ምንነትን አስመልክቶ በርካታ የዘርፉ ተመራማሪዎች የየራሳቸውን ትርጓሜ ሰጥተዋል። በ19ኛው ክፍለ ዘመን የሥነ-ሰብ ተመራማሪዎች ቁሳዊ ባህልን ለመግለጽ የመጀመሪያዎቹ ናቸው። Pitt-Rivers በ1875 “On the Evolution of Culture” በሚል የጥናት ሥራ ላይ ቁሳዊ ባህል በአዕምሮ ውስጥ ያሉ ልዩ እሳቤዎች ውጫዊ ማሳያ ምልክቶች/አርማዎች መሆናቸውን material culture as “the outward signs or symbols of particular ideas in the mind” (1906) ሲሉ ያመላከቱ መሆኑን ጠቅሷል።

ይህም አስተሳሰብ ከአንድ ምዕተ ዓመት በኋላ በሥነ-ሰብ ተመራማሪዎች ከፍተኛ ድጋፍን ያገኘ ሲሆን በተለይም Schlereth ቁሳዊ ባህል የምናስባቸውን ጉዳዮች ለማሳካት፣ በሰዎች ፍላጎት የሚቀረፁ/የሚሰሩ መሆናቸውን *"Material culture is that segment of human kind’s biosocial environment that has been purposely shaped by people according to culturally dictated plans.” (1985)* በማለት ከPitt-Rivers ትርጓሜ በስፋትም ሆነ በአስተሳሰባዊ ረቂቅነት ተጨባጭ ሀሳብ አንስተዋል።

ይህም ቁሳዊ ባህል በ19ኛው መገባደጃ በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ በማኅበራዊ ሳይንስ ውስጥ እያደገ የመጣ ሲሆን በቅርሶች እና በማህበራዊ ግንኙነቶች መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያመለክት ነው። ይህን ሃሳብ Deetz (1997) የቁሳዊ ባህል እሳቤ በ20ኛው ክፍለ ዘመን በአሜሪካ የትምህርት ተቋማት በሰው ዘር ጥናት ባለሙያዎች (ethnologists) እና በቁሳዊ ባህል ታሪክ ምሁራን አማካኝነት እንደተጀመረ ያስረዳሉ። Campbell (1987) ቁሳዊ ባህል ወደ ምናባዊ ዓለም መግባት የሚያስችል ዕይታ ያለውና የምንገለገልባቸው ቁሶችም የፍላጎታችን ማሳያ ውጤቶች ናቸው ይላሉ። Woodward (2007) አንድ ማህበረሰብ ጉልበቱን፣ ጊዜውን፣ ሃብቱንና እውቀቱን አፍስሶ በሚሰራቸው ቁሶች የዕለት ተዕለት ህይወቱ መገልገያዎቹና እምነቱን፣ አስተሳሰቡን፣ አመለካከቱን የሚያንፀባርቅበት ዋነኛ ዘዴዎቹ ናቸው ሲሉ Prown (1982) ቁሳዊ ባህል የአንድን

ማህበረሰብ መንፈሳዊ ሃብቱን ለማስተላለፍ፣ ለማስቀመጥና ለመጠበቅ የሚጠቀምበት ዓይነተኛ መንገድ መሆኑን ያስረዳሉ።

Miller (1987) "ቁሳዊ ባህል ራሱን የቻለ የትምህርት መስክ መሆኑንና የቁሳዊ ባህል ጥናቶችም በቁሳዊ እና በማኅበራዊ መካከል ያሉትን ሁሉንም የግንኙነት ሁኔዎች የሚመለከት የትምህርት መስክ ነው ይላሉ። ሌላው ቁሳዊ ባህልን በርካታ ጸሃፍት የተለያየ ትርጓሜ ሲሰጡት የሚስተዋል ነው። በተለይም ቁሳዊ የሚለውን ቃል በተለያዩ ቃላትና ከሌሎች መጠሪያዎች ጋር የተያያዘ በመሆኑም ቁሳዊ ባህልን ለመግለፅ የትኛው ቃል የተሻለ እንደሆነ Woodward Ian እንደሚከተለው መልስ ሰጥተውበታል።

> *The term 'material culture' is often used in conjunction with 'things', 'objects', 'artefacts', 'goods', 'commodities' and, more recently, 'actants'. These terms (with the exception of the last) are, for most purposes, used interchangeably. There are, however, some important nuances in the meaning of each term, which help to demarcate the context in which it should be used (2007).*

ከዚህ ሀሳብ እንደምንረዳው "ቁሳዊ ባህል" ሲባል ብዙውን ጊዜ የሚዳሰሱ ወይም ተጨባጭ ከሆኑ ነገሮች ጋር ብቻ የሚያያዝ መሆኑን ነው። ነገር ግን ቁሳዊ ባህል ሲባል ቋሚና ተንቀሳቃሽ የሚዳሰሱ ግዑዛን ነገሮች (things) ልዩ ልዩ ቁሶች (objects)፤ የሰዎች ልዩ የፈጠራ ችሎታ ያረፈባቸው የእጅ ስራ ውጤቶች ወይም የእደ ጥበብ ስራዎች (artefacts)፤ በገበያ ግንኙነት የሚመረቱ ምርቶች (goods)፤ ሸቀጣ ሸቀጦች (commodities)፤ እንዲሁም ለምርቶቹ መመረት የድርጊቱ ፈፃሚዎች ወይም ተዋንያን (actants) የሚባሉት ሁሉ እንደየ አውዳቸው ከቁሳዊ ባህል ጋር የሚገናኙ መሆኑን ነው።

Aronin and Singleton ቁሳዊ ባህል በአካባቢያዊና ዓለም አቀፋዊ አስተሳሰብ፣ ባህል፣ ወግና ማህበራዊ ህይወት ጋር የተሳሰሩ መሆናቸውን ሲገልፁ፡-

> *Matrial culture is the realm of physcal items embarcing everyday object, such as goods and products, food and utensils, furniture, pieces of art, medications and medical devices, books, pens and carpentry tools; also roads, monuments and clay tablets of the past, technology appliances of the present, all produced by humans and interconected by and with local and global mindset, culture, tradition and social life (2012).*

ከዚህ ሀሳብ መረዳ እንደሚቻለው ቁሳዊ ባህል ከትንሽ እስከ ትልቅ ያሉ የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ባህላዊና ዘመናዊ ምርቶችን በሙሉ አካቶ የያዘ ነው። Selby & Garretson (1981) Schlerethን ጠቅሰው ቁሳዊ ባህል የሰውን ልጅ ማህበራዊና ባህላዊ ክዋኔ የሚገልፅና ከቦታ ቦታ ሊንቀሳቀስ፣ ሊዳሰስ፣ ሊታይ የሚችል አካላዊ ቁስ መሆኑን ሲገልፁ ሰለሞን ተሾመ (2011) በበኩላቸው ቁሳዊ ባህል አንዱ የፎክሎር ዘውግ እንደሆነና

የሚታዩ፣ የሚዳሰሱና የሚቀመሱ መሆናቸውንና ማህበረሰቡ በአካባቢው ግብዓቶችና እውቀት እንዲሁም ማምረቻ መሳሪያዎች የሚሰራቸው ቁሶች ናቸው ይላሉ። እንዲሁም Ferguson (1977) አካላዊ ቁሶች በሙሉ የሚመለከት እንደሆነ *“all of the things people leave behind ….All of the things people make from the physical world - farm tools, ceramics, houses, furniture, toys, buttons, roads and cities”* በማለት አሰረድተዋል።

MIller (1994) በበኩላቸው የጥንታዊ የእጅ ስራ መሳሪያዎች ስለራሳችን፣ ስለ ሌሎች ወይም እንደ ህዝብ ያሉ ረቂቅ ነገሮችን ቅፅ የምንሰጥባቸው እና የምንረዳባቸው መንገዶች ናቸው። Schlerlth (1985) በበኩላቸው የዕደ ጥበብ ውጤቶች (articacts)፣ ልዩ ልዩ ቁሶች (objects)፤ ወይም ግዑዝ የሆኑ ነገሮች (things) የሚባሉ ሙያዊ ቃላት ለቁሳዊ ባህል ተመሳሳይ ወይም ተተኪ መጠሪያ መሆናቸውንና የተስተላልፎ ሂደቱ በቀዳሚዎቹም ሆነ በዛሬዎቹ ምሁራን ጽሁፍ ውስጥ የሚታይ መሆኑን ጠቁመዋል። ቁሳዊ ባህል እንደ ቅርስ ስብስብና ባህላዊ ምልክዓ-ምድር እንደሚታዩ Marshall እንደሚከተለው ያስረዳሉ።

> *Material culture is seen as the “array of artefacts and cultural landscapes: that people create according to traditional, patterned, and often tacit concepts of value and utility that has been developed over time through use and experimentation. (1981).*

በአጠቃላይ ቁሳዊ ባህሎች ለዕለት ተዕለት ሆነ ለወቅታዊ ፍላጎት መጠቀሚያነት የሰው ልጅ ጉልበቱን፣ ጊዜውን፣ ሃብቱንና እውቀቱን አፍስሶ የሰራቸውና የሕይወት ዘመን ተሞክሮዎች የሚገልፅበት የእጅ ስራ ውጤት መሆናቸውን ከላይ ከቀረቡት ብያኔዎች መረዳት ያስችላል።

## 2.2.2. የቁሳዊ ባህል ጥናትና አስፈላጊነቱ

ፎክሎር የባህል ጥናት መስክ እንደመሆኑ ሁሉም የፎክሎር ዘውጎች በልዩ ባህርያቸው እና በይነዲሲፕሊናዊ ነገሮቻቸው ራሳቸውን ችለው ሊጠኑ ይችላሉ። ይህ ማለት እያንዳንዱ የፎክሎር ዋና ዘውግ ትኩረታቸው ባህላዊ በሆኑ የተለያዩ የጥናት መስኮች ሊጠና ይችላል። ይህን ሃሳብ Sims and Stephens’s የፎክሎር ጥናት እያንዳንዱን የሰው ልጅ ልምድንና የኪነ-ጥበብን አገላለጽ የሚዳስስ መሆኑን “The study of folklore touches on every dimension of human experience and artistic expression.” (2005) ነው ይላሉ።

የቁሳዊ ባህል ጥናት በቁሶችና በማህበራዊ ግንኙነቶች መካከል ያለውን መስተጋብር የሚመለከት ራሱን የቻለ አንድ የጥናት መስክ (discipline) መሆኑን *"Material culture studies is a discipline concerned with all aspects of the relationship between the material and the social. It strives to overcome the logistic constraints of any discipline*" Miller (1998) ሲሉ Oesigaard (2004) የቁሳዊ ባህል ጥናት ዋና ትኩረቱ በቁሶችና በማህበረሰቡ ባለው ግንኙነት ላይ ነው ሲሉ የMiller ሃሳብን ያጠናክራሉ፡፡

ሰለሞን ተሾመ (2011) ቁሳዊ ባህሎችን በምናጠናበት ወይም በምንሰበስብበት ወቅት ቁሶች ያላቸውን ቅርጽ፣ ቀለም፣ መጠን ወይም ያላቸውን ጠቀሜታ ብቻ ሳይሆን ለቁሶቹ መስሪያ የሚያገለግሉ ግብዓቶችን፣ አሰራር ሂደት፣ በማን? መቼ? እንደሚሰሩ ወዘተ ጭምር መመልከት እንዳለብን ይመክራሉ፡፡ በተጨማሪም Schlereth (1985) የቁሳዊ ባህል ጥናቶች በመጀመሪያ እንደ አንድ የትምህርት መስክ (discipline) ሲታዩ የእውቀትና ምርምር ስራዎችን ለማሳያነት፣ በሁለተኛነት ደግሞ የሰው ልጅ ስለራሱና ስለማህበረሰቡ እውቀት ንድፈ ሃሳባዊ ዘዴዎችን፣ የፈጠራ ስራን ለማስረዳት ወሳኝ ናቸው ሲሉ ገልፀዋል፡፡

የቁሳዊ ባህል ጥናት መሰረታዊ ዓላማ የአንድን ማህበረሰብ ባህላዊ የእምነት ስርዓቶችን እና ተዛምዶ እንደሆነ Prown (1982) "The fundamental purpose of the study of material culture is the quest for cultural belief systems, the patterns of belief of a particular group of people in a certain time and place" ሲሉ ይገልፃሉ፡፡

በእርግጥ በዚህ ጉዳይ ላይ የዘርፉ ተመራማሪዎች በሁለት ጎራ ተከፍለው ቁሳዊ ባህል የጥናት ዘርፍ ነው አይደለም በማለት ይሞግታሉ፡፡ Woodward ቁሳዊ ባህል የጥናት ዘርፍ እንደሆነ ከሚሞግቱ ምሁራን መካከል አንዱ ሲሆኑ የቁሳዊ ባህል ጥናት ከአራቱ የፎክሎር ዘውጎች መካከል አንዱ የጥናት ዘርፍ እንደሆነና በቁሳዊ ባህል ላይ የተደረጉ ዘመናዊ ጥናቶች የሁለንተናዊ ተሳትፎ (interdisciplinary) ባህሪን በደንብ ያዳበሩ መሆናቸውን እንደሚከተለው አብራርተዋል፡፡

> *"…Contemporary studies of material culture have developed a strongly interdisciplinary nature. Various disciplines have aspects of material culture as their concern: art history, design and fashion studies, architecture and landscape design, consumer research and marketing studies." (2007)*

በተጨማሪም Henry Glassie የሰው ልጅ ባህልን መነሻ በማድረግ ለዕለት ከዕለት ኑሮው ማከናወኛ የሚሰራቸውን ተጨባጭ ቁሶች መነሻ በማድረግ የቁሱ ባለቤት የሆነውን የሰውን ልጅ አስተሳሰብና ፍልስፍና በቁሶቹ አማካኝነት መመርመር ወይም ማጥናት የሚያስችል

መሆኑን *“The study of material culture uses objects to approach human thought and action* (1999) በማለት ይገልፃሉ፡፡

ፈቃደ አዘዘ Dorsonንን ጠቅሰው ቁሳዊ ባህል በዓይን የሚታየውን በእጅ የሚዳሰሰውን ከዘመናዊ ኢንደስትሪ በፊት ጀምሮ የሰው ልጅ ፈጥሮ የተገለገለባቸውን ቁሳቁሶች እንደሆኑና እነዚህ ቁሳቁሶች የተሰሩበትን ዘዴ ወይም ቴክኒክ የልዩ ልዩ ምግቦች አሰራር፣ የቅመም አቀማመም ብልሃትን፣ የልብስ፣ የቤት የአጥር ወዘተ አሰራርን የሰዎች ልዩ ልዩ ስራዎችን የሚያጠና የጥናት ዘርፍ ነው፡፡ (1991)፡፡

Cleary ቁሳዊ ባህል የቁሶች ስበስብ እንጂ የጥናት መስክ አይደለም ከሚሉት የዘርፉ ተመራማሪዎቸ ውስጥ አንዱ ናቸው፡፡ “ቁሳዊ ባህል የጥናት ዘርፍ ነው” የሚለውን የGlassieን እና የWoodwardን ብያኔ በመቃወም Cleary (2004) “ቁሳዊ ባህል በባህላዊ መንገድ የተሰሩና ለዕለት ተዕለት (የዘወትር) ተግባራት የምንገለገልባቸውን ቁሶች ስብስብ እንጂ የጥናት ዘርፍ አይደለም” በማለት ሞግተዋል፡፡

ከላይ የቀረቡ ሁለቱን ተቃራኒ ሃሳቦች ለማስታረቅ ከሞከሩት ተመራማሪዎች ውስጥ Schlereth (1985) ቁሳዊ ባህል በይነ-ዲሲፕሊናዊነትን የሚገልፅ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ቁሳዊ ባህልን በተለያዩ ዘርፎች የሚገኙ ምሁራን እየተጠቀሙበት ይገኛሉ፡፡ እነዚህም ምሁራን ራሳቸው የሚገኙበትን የትምህርት መስክ አመለካከት በሚያንፀባርቅ መልኩ በተለያየ መንገድ እንደሚበይኑትና እንደሚጠቀሙበት በመግለፅ ቁሳዊ ባህል በቁስነት ወይም ደግሞ በጥናት ዘርፍ የሚታይበት አጋጣሚ ሊኖር እንደሚችል በመጠቆም ሁለቱን ተቃራኒ ሃሳቦች ለማስታረቅ ሞክዋል፡፡ Prown (1982) በበኩላቸው የቁሳዊ ባህል ጥናት አንድ ማህበረሰብ በኖረበት ዘመን በፈጠራቸው ቁሶች (artifacts) አማካኝነትን የግለሰቡን የቡድኑን እምነቶች፣ እሴቶች፣ አስተሳሰቦች ወዘተ ለመመርመር የሚረዳ ሳይንሳዊ መስክ ነው ይላሉ፡፡

### 2.2.3. የቁሳዊ ባህል ምደባ

የዘርፉ ምሁራን ቁሳዊ ባህሎች አንዱ ከሌላው የሚወራረስ በመሆኑ ግልፅ መመዘኛዎችን ማዘጋጀትና መመደብ አስቸጋሪ መሆኑን ጠቅሰው ጎላ ባሉ ጉዳዮች ምደባ መስጠት እንደሚቻል ያቀረቡትን ሃሳብ እንደሚከተለው ተመድበዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል Dorson (1972) በአምስት ንዑሳን ምድቦች ማለትም ሀገረሰባዊ ስዕል (folk art)፣ሀገረሰባዊ ምህንድስና (folk architecture)፣ሀገረሰባዊ ዕጅ ሥራ (folk crafts)፣ ሀገረሰባዊ ልብስ (folk costume)፣ ሀገረሰባዊ ምግብ አሰራር (folk cookery) ሲሉ መድበዋቸዋል፡፡

Adams W.Y. እና Adams E.W. (1991) ዓይነታቸውና ተግባራቸው ዓላማ አድርገው ቅርሶችን "purely morphological typologies, functional classifications, "emic" classifications, and distributional typologies" ሲሉ በአራት መድበዋቸዋል፡፡ Prown (1982) በበኩላቸው ቁሳዊ ባህልን እንደ ተግባራቸው ዓይነት "ስነ ስዕል (Art)፣ መዝናኛዎች (Diversions)፣ ስነመዋቢያ (Adornment)፣ ተስማሚነት (Modifications of the landscape)፣ እደ ጥበብ (Applied arts) እና መሳሪያዎች (Devices)" በማለት በስድስት ንዑሳን ዘርፎች መድበዋቸዋል፡፡ እኔም ከላይ ከቀረቡት የተለያዩ የመመደቢያ መስፈርቶችን መካከል በPrownን መመደቢያ መስፈርት አማካኝነት ጥናቴን ተግባራዊ አድርጌያለሁ፡፡ ለዚህም ምክንያቴ የቁሶቹን አካላዊ ገፅታ ቅርጽና ዘመን መነሻ አድርጎ መመደብ ከቁሶቹ አገልግሎት ወይም ተግባር አንፃር ሲታይ በቂ ምርምር ማከናወን የሚያስችል በመሆኑ ነው፡፡ በዚህ ጥናት ተግባራዊ ለተደረገው ምሁራኑ ከጠቀሷቸው አከፋፈል ውስጥ የሚከተሉት በጥቂቱ ቀርበዋል፡፡

### 2.2.3.1. ማህበራዊ ደረጃን ማሳየት

አልባሳት ካላቸው በርካታ ተግባራት መካከል Kaisser (1990) አልባሳት ማህበራዊ ደረጃና ማንነትን በማሳየት በኩል ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው ሲገልፁ Yoder (1972) በበኩላቸው የሀገረሰባዊ አልባሳት ተግባር በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ያለን ክፍፍል ማሳየት ነው ሲሉ ይገልፃሉ፡፡ እንዲሁም Chavarria (2002) በበኩላቸው *"In traditional societies, clothing functions almost as reson's age, gender, and marital status, place of origin, religion,' social status, or occupation"* በማለት አልባሳት ዕድሜ፣ ፆታ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የትውልድ ቦታ፣ ሃይማኖት፣ ማህበራዊ ደረጃን የሚያመላክት እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ በጥቅሉ ከዚህ ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ አልባሳትና ጌጣጌጦች ማህበራዊ ደረጃን መሰረት ተደርገው የሚለበሱ/የሚገለገሉ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በቁሶቹ አማካኝነት የአባላቱን ማህበራዊ ደረጃ ማወቅ የሚያስችል ነው፡፡

### 2.2.3.2 ሃይማኖታዊ ተግባር

አንድን የእምነት አባት (ቄስ ወይም ሼህ) ለመለየት በራስ የሰውነት ክፍላቸው (head) ላይ የሚለብሷቸው የአልባሳት ዓይነት ሃይማኖትን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ Bradly and Homberger (2015) አልባሳት ሃይማኖትን ለመግለፅ እንደ ቋንቋ የሚያገለግሉ መሆናቸውን ሲገልጹ Gracia (2008) አልባሳት የሰውን ልጅ ውጫዊ አካል ከመሸፈን ባለፈ በአንዳንድ ማህበረሰቦች ዘንድ ከተለያዩ ክፉ መናፍስት መከላከል/መጠበቅ የሚያስችል እምነት እንዳላቸው ያስረዳሉ፡፡ ይህም አልባሳት ኃይማኖታዊ ተግባር ያላቸው መሆኑ ነው፡፡

### 2.2.3.3 ሥርዓተ ፆታን የማመልከት ተግባር

ወንዶችና ሴቶች የየራሳቸው አለባበስ ዘይቤ ያላቸው በመሆኑ ከሚለብሱት ልብስ በመነሳት ፆታን በቀላሉ መለየት እንደሚቻል Barton (1969) አልባሳት ሥርዓተ ፆታን ለማመላከት የሚያገለግል መሆኑን ሲጠቅሱ Yenealem (2016) በበኩላቸው በርካታ ባህሎች የወንድና ሴት ወይም የፆታ ልዩነትን መሠረት ያደረገ የአለባበስ ስርዓት ይከተላሉ ሲሉ ለዶክትሬት ማሟያ ባቀረቡት የጥናት ስራ ላይ ገልፀዋል፡፡

### 2.2.3.4. የተግባቦት (Communication) ተግባር

ልብሶች በሰውነት ልክ ተስተካክሎ የተገጣጠመ ወይም ለሰውነት አጋዥ የሆኑና የህብረተሰቡን ባህልን የሚያንፀባርቁ መልዕክቶችን የሚያስተላልፍ የግንኙነት መንገድ መሆኑን Eicher & Roach-Higgins (1992) ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም Wilson (1986) አልባሳት የተለያዩ መልዕክቶችን በማስተላለፍ በኩል ከፍተኛ የሆነ ብቃት ያላቸው መሆኑን ሲገልፁ Gracia (2008) በበኩላቸው አልባሳት ልክ እንደ ቋንቋ ሁሉ አንድን ማህበረሰብ ለመግለፅ በዋናነት የሚያገለግሉ መሆናቸውን

### 2.2.3.5. አልባሳትና ማንነት (Dress and Identity)

ማንነት በቀላሉ ሲገለፅ "እኔ ማን ነኝ" ለሚለው ጥያቄ ወይም ማህበረሰቡ "ማን ነህ፣ ከየት ነው የመጣኸው?" ለሚለው ጥያቄ መልስ የሚሰጥ ነው፡፡ Yoder (1972) ባህላዊ አልባሳትና ጌጣጌጦች የአንድን ግለሰብ ወይም ቡድን ማንነት እንደሚገልፅ ሲናገሩ Twigg (2007፣10) አልባሳት ማንነትን በማሳየትም ሆነ በመቀየር ወይም በማጥፋት ረገድ የራሳቸው ድርሻ እንዳላቸው ያስረዳሉ፡፡ በተጨማሪም የኔዓለም አረዶ (2000 ዓ.ም) ልብሶች የሰዎችን ፆታ፣ ዕድሜ፣ አካባቢ፣ ማንነትን ወዘተ ጉዳዮችን ሊነግሩን ይችላሉ በማለት በጥናት ስራቸው ላይ ይጠቅሳሉ፡፡ Lurie (1981) በበኩላቸው ልብስን የምንለብሰው የሥራም ሆነ የኑሮ ሁኔታችንን ጤናማ ለማድረግና ማንነታችንን ለማሳየት እንዲሁም ውበትን ለማጉላት እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ እንዲሁም ሰሎሞን ተሾመ (2007) በተለያዩ ባህሎች ውስጥ የሚገኙት አልባሳት የለባሹን ማህበረሰብ ኃይማኖት፣ ዘር፣ ጎሳ ወዘተ ጉዳዮችን ከመግለፃቸው ባለፈ እንደ ትዕምርታዊ ቋንቋ (as symbolic language) እና የፎክ ቡድኑ ማንነት መለያ (badge of folk-group identity) ሆነው ያገለግላሉ ይላሉ፡፡

በአጠቃላይ ከሁሉም ምሁራኑ ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው አልባሳት የአንድን ግለሰብ ሙያ፣ ገቢ፣ ማህበራዊ መደብ፣ ጎሳ፣ ሃይማኖት፣ ዝምድና፣ አመለካከት፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ፣ ዕድሜ ወዘተ... የሚያመላክት መሆኑን ነው፡፡

### 2.2.3.6. የመከላከል ተግባር

አልባሳት ከላይ ከተዘረዘሩት አገልግሎት በተጨማሪ ሰውነትን ከሙቀት፣ ከቅዝቃዜና ከጎጂ ነገር የሚከላከሉ ናቸው። ይህን ሃሳብ Pheto-Moeti (2005) አልባሳት ማንነትን ከመግለፅ በተጨማሪ የአካል ክፍሎችን ከተለያዩ ጎጂ ነገሮች የመከላከል፣ ሀፍረትን የመሸፈን፣ አትኩሮትን የመሳብ እና የማስዋብ አራት ተግባራት እንዳላቸው ይጠቅሳሉ።

## 2.2.4. የቁሳዊ ባህል መለያ ባህሪያት

ከቁሳዊ ባህሎች በርካታ መለያ ባህሪያት ውስጥ ዘመን ተሻጋሪነታቸው የሚጠቀስ ነው። Dorson (1972) ቁሶችና የቁሶቹን ባለሙያዎች ወይም ሠራተኞች የአሰራር ሂደት፣ የፈጠራ ስልት ከትውልድ ትውልድ የሚሻገሩ መሆኑን ሲያስረዱ Lincolin and Guba (1985) ቁሳዊ ባህሎች ከዘርፈ ብዝሃነነት መለያ አንፃር የቀደሙ የድንጋይ ላይ ጽሁፎች፣ መዛግብት፣ የጉዞ ማስታወሻዎች፣ ግለታሪኮች፣ ደብዳቤዎች፣ የትምህርት ማስረጃዎች፣ ውሎች፣ የሚመለከት መሆኑ ይገልፃሉ። በተጨማሪም prown (1982) ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ጥቂቶች በነበሩበት ጥንታዊ ዘመን የሰዎችን ፈጠራ፣ ፍልስፍና እንደ ጽሁፍ ማስረጃነት መሆናቸውን ሲጠቅሱ Renfrew and score (1998) ቁሳዊ ባህል የመረጃ ቋት መገለጫ መሆናቸውን ከብዙ በጥቂቱ የሚለዩባቸው ባህሪያት እንደሆነ ገልጸዋል። እንዲሁም ቁሳዊ ባህሎች በሁሉም ማህበረሰብ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ መሆናቸው ከሌሎቹ የሚለያቸው ባህሪያቸው ነው።

## 2.2.5. የአለባበስ ስያሜዎችና ትርጓሜዎች

አልባሳት የሰው ልጅ ውጫዊ አካሉን ከተለያዩ ነገሮች ለመጠበቅ፣ ማህበራዊ ደረጃውን ለማሳየት፣ ውበቱን ለማጉላትና ሀሳቡን ለመግለፅ ያገለግላሉ። እነዚህ የአልባሳት ዓይነትን የዘርፉ ምሁራን አልባሳት (costume)፣ ልብስ (dress)፣ አለባበስ (clothing) በማለት ሲጠሯቸው ይደመጣሉ። እነዚህ በሦስት ስያሜዎች የሚጠሩትን አልባሳት ከሰው ውጫዊ ክፍሎች ጋር ያላቸውን ጠቀሜታና ምሁራኑ የሰጧቸውን ትርጓሜ ቀጥሎ እንመለከታለን።

### 2.2.5.1. አልባሳት (Clothing)

የሰው ልጅ ሙሉ ወይም ከፊል አካሉን የሚሸፍን የአለባበስ ስርዓት አለው። አለባበስ ሲባል በተለያዩ የሰውነት ክፍሎች ላይ የሚለበሱ ወይም የሚደረጉ የጨርቃጨርቅ፣ የእንስሳት ቆዳዎች፣ የፕላቲክ ወዘተ ውጤቶች የሆኑ ልብሶችንና ጌጣጌጦችን ጭምር የሚያካትት ነው።

Ozougwu (2004) Horn and Gurelን (1981) ጠቅሰው "*clothing" described by embodies wearing of apparel and accessories such as garments, jewelleries, shoes, scarves"* ሲሉ Pheto-Moeti እና ሎሌች (2018) ልብስ ማለት አካልን ሚሸፍን የሚጨበጥ/የሚዳሰስ ቁስ በሙሉ ልብስ ነው ይላሉ፡፡

### 2.2.5.2 *ሀገረሰባዊ* አልባሳት (Folk costume)

*ሀገረሰባዊ አልባሳት የአንድን ማህበረሰብ ልማድ፣ ማንነት፣ ኃይማኖት፣ የሥራ ሁኔታዎችን ጉዳዮች ለመግለፅ የሚያገለግል መሆኑን* Dorson (1972) *በማለት ይናገራሉ፡፡* Yoder (1972) *ሀገራዊ አልባሳት አንድን ማህበረሰብ ወይም ቡድን ማንነትን፣ ማህበራዊ ደረጃን፣ ጾታን፣ ሙያን፣ ጎሳን፣ ብሔርን፣ ተግባርን ወይም ዘመንን የሚያንፀባርቅ የአለባበስ ዘይቤ ለመግለፅ የሚገለግል ውጫዊ ማሳያ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ ሰለሞን ተሾመ* (2011) በበኩላቸው *ሀገረሰባዊ* የክት ልብስ (Folk costume) *ማህበረሰቡ ልዩ በሆኑ ኃይማኖታዊና ማህበራዊ ቀናት የሚለብሳቸው እንደሆኑ ይጠቅሳሉ፡፡ እንዲሁም* Eicher *እና ሌሎች* (1992) *ሀገረሰባዊ አልባሳት የአንድን ማህበረሰብ ማንነት በተለይም አካባቢን፣ ዘመንን፣ ታሪክን ኃይማኖትንና ማህበራዊ ስርዓትን የሚያመላክቱ ናቸው ይላሉ፡፡*

### 2.2.5.3. አልባሳት (DRESS)

ልብስ (dress) ሲባል አካል *የሚያሻሽሉ ወይም ሊያሚሉ የሚችሉ የፀጉር አሰራር* ዘይቤዎች፣ የቆዳ ቀለም፣ የተበሳ ጆሮ፣ የሰውነት *መሸፈኛ* ጨርቆችና የጌጣጌጥ *መለዋወጫዎች ሁሉ የሚያካትት መሆኑን* Eicher እና ሌሎች (1992) *ገልፀዋል፡፡* በተጨማሪም በሁሉም የስሜት ህዋሳቶቻችን ማለትም በእጅ የሚዳሰሱ፣ በዐይን የሚታዩ፣ በጆሮ የሚሰሙ ጌጣጌጦች፣ በአፍንጫ የሚሸተቱ መዓዛዎችና በምላስ የሚቀመሱ ሰውነት *ማሻሻያዎች* (body modifying) እና አካልን *ማሟያዎች* (body supplementing) *ሁሉ የሚያካትት መሆኑን* አስረድተዋል፡፡ ይህን ሃሳብ Damhorst (2008) በበኩላቸው በሚታዩ ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች ላይ አካልን ለማሻሻል ወይም ለማሟላት የተጨመሩ ቁሶች በሙሉ ልብስ (dress) ተብለው የሚጠሩ *መሆኑን* ይገልፃሉ፡፡

## 2.2.6 አልባሳትና ትዕምርቶች

*ትዕምርት አንድና ከዚያ በላይ ትርጉም ወይም ውክልና ያለው ነገር ነው፡፡ ለምሳሌ የአልባሳት ትዕምርቶች የሰዎችን ስሜት በተሻለ መልኩ ሲገለፁ እንደሚታዩ* Kaiser (1985) *ገልፀውታል፡፡ ምንም እንኳን ከሀገር ሀገር ወይም ከአካባቢ አካባቢ የሚለያይ ቢሆንም በአንዳንድ ሀገራት ጥቁር መልበስ የሀዘን ምልክት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ይህም ሀዘን*

ያጋጠመውን ሰው ስሜት አይቶ ከመረዳት ይልቅ በለበሰው ነገር ተመስርቶ በሞት የተለየ ሰው እንዳለ የሚያመላክት ነው፡፡ ትዕምርት ሲባል ቁሶችን ወይም ምግባራቸውን የሚያመላክትና የራሱን ትርጉም የሚሰጥ እንደሆነ Charon (1998) ገልፀዋል፡፡

## 2.2.7 ሀገረሰባዊ ጌጣጌጥ

ሌላኛውና የዚህ ጥናት አንዱ አካል የሆነው እና በቁሳዊ ባህል ሥር የሚመደበው ሀገረሰባዊ ጌጣጌጥ ነው፡፡ Clark (986) ሀገረሰባዊ ጌጣጌጥ እንደ ማህበረሰቡ ባህልና ወግ እንዲሁም መኖሪያ አካባቢው መለያየት ሁሉ የሚበጁበት/የሚሰሩበት ቁስና ቅርጽም ልዩነት መኖሩንና ከመዋቢያነት ባለፈ ተምሳሌታዊ ፋይዳ እንዳላቸው እና አንድን ማህበረሰብ ከማህበረሰብ፣ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥም እድሜን ፆታን እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታን የማሳየት አቅም እንዳላቸው ገልፀዋል፡፡ የጌጣጌጥ ጥበብ ከጥንታዊ አለባበስ ዓይነቶች አንዱ ነው፡፡ ቀደም ባሉት ጊዜያትም ጌጣጌጦች በቀላሉ ከሚገኙ የተፈጥሮ ቁሳቁሶች ማለትም ከእንስሳት ጥርስ፣ አጥንት፣ ከተቀረጹ ድንጋዮች፣ እንጨቶች ወዘተ ነበር፡፡ አሁን ላይ ግን ከተለያዩ ማዕድናት ይሰራሉ፡፡ ሰለሞን ተሾመ (2011) አንድ ማህበረሰብ ከአካባቢው በሚያገኛቸው ግበዓቶች ተጠቅሞ ራሱን፣ የሚያረባቸውን እንስሳት ለማስዋብ የሚጠቀማቸው ቁሳዊ ባህሎች ሀገረሰባዊ ጌጣጌጥ የሚባሉ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ከዚህ አንፃር የጌጣጌጦች ቀዳሚ ተግባር የተጠቃሚውን ውበትን ማጉላት ወይም ማሳመር እንደሆነ Brett (2005) “a primary role of ornamentation is to beautify objects or processes, to contribute to their aesthetics” ይገልፃሉ፡፡ እዚህ ላይ ጌጣጌጦች (jewelrys) ውበት መጠበቂያ ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች ማህበራዊና ሃይማኖታዊ ጠቀሜታዎች አሏቸው፡፡ እነሱም በጭንቅላት፣ በጆሮ፣ በአንገት፣ በእጅና በእጅ ጣት ላይ ወዘተ የሚደረጉ ጌጣጌጦች ውበትን፣ ማህበራዊ ደረጃን፣ አብሮነት ቃል ኪዳን፣ ከህመም ለመፈወስ/ለመዳንየሚያገለግሉ ናቸው፡፡

## 2.2.8 ሀገረሰባዊ መዋቢያ

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረቱ በቁሳዊ ባህል ዘርፍ ውስጥ በሚመደቡት ሀገረሰባዊ አለባበስና አጊያጊያጥ ሥርዓት ላይ ቢሆንም የአካባቢው ማህበረሰብ ለመዋቢያ (ለማጌጫነት) ከሚጠቀምባቸው ድርጊቶች መካከል የተለያዩ የፀጉር አሰራር ዓይነቶች፣ እጅን ወይም እግርን በተለያዩ የእፅዋት ምርቶች የማስዋብ ወዘተ... ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ ከሚያከናውነው የአጊያጊያጥ ስርዓት ጋር ከጉዳዩ ጋር ተያይዞ ቢጠና የአካባቢውን የአጊያጊያጥ ስርዓት ጥናቱ በተሻለ መንገድ ይገልፀዋል በሚል እምነት የፀጉር አሰራሮችን በዚህ ጥናት ተካተዋል፡፡

*ሀገረሰባዊ መዋቢያ* (Folk Decoration) *ሀገር በቀል የማስዋቢያ ስልት መሆኑን ሰለሞን ተሾመ እንደሚከተለው ያብራራሉ።*

> በተለያዩ ማህበረሰቦች ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ የፀጉር አሰራር ስልቶች፣ በተለያየ የሠውነት አካል ላይ ለውበት ሲባል የሚደረግ ንቅሳት፣ በተለያዩ የቀለም ዓይነቶች ሰውነት ላይ የተለያዩ ቅርፆች መሳል (body painting)፣ እጅን ወይም እግርን በተለያዩ የእፅዋት ቅጠሎች፣ ስሮች፣ ቅርፊቶች ወይም በእንስሳት ተረፈ ምርቶች ማሳመር (body adornment) በወይባ ጢስ መታጠን፣ ግንባርን፣ ፊትን፣ እጅን ወይም ሌሎች የተለያዩ የሰውነት አካላትን ስለት ባለው ነገር መተልተል (scarification)፣ በከንፈር ውስጥ ገል ማስገባት (lip plugs) የመሳሰሉት ዘርፍ ይመደባሉ። (2007)

ከዚህ ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው ሰዎች ውበታቸው ጎልቶ እንዲታይ በአካባቢያቸው ካሉ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ነገሮች በመጠቀም ለዓይን ሳቢ/ ማራኪ እንዲሆኑ የሚያከናውኑ መሆኑን ነው።

## 2.2.9. *ሀገረሰባዊ ዕጅ ስራ*

የተጠኚው ማህበረሰቡ አልባሳትና ጌጣጌጦች በአካባቢው ካሉ የእጅ ሙያተኞቹ አማካኝነት የሚዘጋጁ ናቸው። እነዚህ የእጅ ሙያተኞቹ ደግሞ በዚህ ጥናት ውስጥ ቀጥተኛ ግንኙነት አላቸው። ሰለሞን ተሾመ (2011) የእጅ ሙያተኞች ሀገረሰባዊ የእጅ ስራውን በአካባቢው ከሚያገኟቸው ጥሬ ዕቃዎች አማካኝነት በሀገር በቀል አሰራር እንዲሁም ቴክኖሎጂዎች ታግዘው የሚያመርታቸው መሆኑን ያስረዳሉ።

Dorson, (1972) በበኩላቸው ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ (folk Carafts) በቁሳዊ ባህል ጥናት የሚመደብ መሆኑን ጠቅሰው ሀገረሰባዊ እጅ ስራ የሚባለው ልዩ ልዩ የሸክላ ስራዎችን፣ በአንጥረኛ የሚሰሩ ለልዩ ልዩ ተግባር የሚውሉ ዕቃዎችን፣ ስፌቶችንና በወንዶች የእጅ ስራነት የሚታወቁትን እንዲሁም ከልዩ ልዩ እንስሳት ቆዳዎች የሚሰሩትን ቁሶች እንደሚያካትት አብራርተዋል። እንዲሁም ሰለሞን ተሾመ (2011) ሀረሰባዊ እጅ ስራዎች ሲባል በተለያዩ አካባቢዎች ከሚታወቁ ሀገረሰባዊ እጅ ስራዎች መካካል የሽመና፣ የሸክላ ስራ፣ የስፌት ስራ፣ የብረት ስራ፣ የቀርቀሃ ስራ፣ የእንጨት ስራ፣ የቆዳ ስራ እና የቀንድ ስራ የመሳሰሉትን አመላክተዋል።

በጥቅሉ ማህበረሰቡ የሚገለገልባቸው ቁሶች በአካባቢው በሚገኙ እጅ ጥበብ ባለሙያዎች አማካኝት የሚዘጋጁ በመሆናቸው የእጅ ጥበብ ሙያተኞች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ጥናቱ ዳሰሳ አድርጎባቸዋል።

## 2.3 ንድፈ-ሃሳባዊ ማዕቀፍ

### 2.3.1 የመዋቅራዊ ተግባራዊነት ንድፈ-ሃሳብ

የመዋቅራዊ ተግባራዊነት አንዳንድ ጊዜም ተግባራዊነት (functionalism) ተብሎ የሚጠራው ይህ ንድፈ ሃሳብ በሥነ ሰብዕ (anthropology) እና በህብረተሰብ ጥናት (sociology) ዋና ዋና ከሚባሉ ንድፈ ሃሳቦች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ የዚህ ንድፈ ሃሳብ ዋና ዓላማ ጠንካራ መሰረት ያላቸው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ ተቋማት ባሉበት ሁኔታ እንዲቀጥሉ የሚያስችሏቸዉን ሁኔታዎች ማጥናትና መተንተን ነዉ፡፡

ይህ ንድፈ ሃሳብ የህብረተሰቡን ፍላጎቶች ለማሟላት ሥርዓተ ማህበሩን እንደ አንድ የፍላጎት ማሟያ ስልት የሚመለከት ነው፡፡ ይህም ማለት ስርዓተ ማህበሩ እንዲቀጥል ወይም እንዲጠናከር በርካታ ተቋማት ማከናውን የሚገባቸው ጉዳዮች መኖራቸውን ይጠቁማል፡፡ በዚህ የጥናት ፈለግ ውስጥ በማህበረሰቡ ደንብና ስርዓት መሰረት ግለሰቦች መልካም ነገር የማምረት/ የማዘጋጀት ተቋማት ደግሞ ተገቢ አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለባቸው፡፡ እንደ ንድፈ ሃሳቡ አተያይ ማህበረሰቡ በጋራ እየተደራጀ ወይም ተቋም እየመሰረተ በእሴቱ መሰረት ለማህበረሰቡ መልሶ በጋራ አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው፡፡

የመዋቅራዊ ተግባራዊን ንድፈ ሃሳብ በዋናነት በሦስት ሀገራት ማለትም በፈረንሳይ፣ በእንግሊዝና በአሜሪካ የምርምር ማዕከላት ሰፊ ጥናት ተካሂዶበታል፡፡ የመዋቅራዊ ተግባራዊነት የጥናት ፈለግ በ19ኛው መ/ክ ዘመን በአዲስ መልክ የተቀነቀነ ቢሆንም ፈረንሳዊው Saint-Simon (1823) በቀደሙ የህብረተሰብ ጥናቶች (sociology) ውስጥ የተዳሰሰ እንደነበር በሰነድ ማረጋገጥ እንደተቻለ ይገልፃሉ፡፡ Simon ድርጅት (organization) የሚለውን ቃል ሥነ ሕይወታዊ መዋቅር (organic structure) የሚል ትርጓሜ በመስጠት ህይወት እንዳለው ዘአካል (organism) የሚወለድና የሚያድግ መሆኑን አስተዋውቀዋል፡ ሌላኛው ፈረንሳዊው Comte (1855) ማህበራዊ መዋቅሩን ህይወት እንዳለው ዘአካል (organism) በንፅፅር ገልፀውታል፡፡ ይህም ማለት ህይወት ያለው አንድ ዘአካል (organism) በሂደት እያደገና እየዳበረ እንደሚሄድ ሁሉ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለው ስርዓተ መዋቅር ከቤተሰብ ጀምሮ እያደገና እየሰፋ የሚሄድ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ሌላኛው የዚህ ንድፈ ሃሳብ አቀንቃኝ እንግሊዛዊው Spencer የነ Comteን ሃሳብ ሰፋ በማድረግ ለንድፈ ሃሳቡ አዲስ ዕይታን ይዘው መጥተዋል፡፡ ይህም Principles of Sociology (1898) በተባለው መፅሃፍ ውስጥ ህይወት ስላለው ዘአካል (organism) እና ማህበረሰብ (society) የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ማህበራዊ ስርዓቱን ለማስጠበቅ በጋራ

ሆነው የተለያዩ ተግባራን ያከናውናሉ በማለት ለመዋቅራዊ ተግባራዊነት መመስረት ዕድል ፈጥረዋል፡፡ እንዲሁም ፈረንሳዊው Durkheim (1893) በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ እንደ ቤተሰብ፣ ሃይማኖት፣ መንግስት፣ የንግድ ተቋማት የማህበረሰቡን መዋቅራዊ አንድነት ስርዓት ለማስጠበቅ ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ ሲሉ የእነ Spencerን ሃሳብ አዳብረዋል፡፡

እንዲሁም አሜሪካዊው Parsons (1951) “The Social System” በተባለው መፅሃፋቸው “ማህበራዊ መዋቅር በስርዓት የተቀናጁ ተቋማት፣ ድርጅቶች እና ማህበራዊ መስተጋብሮች እንዲሁም ግለሰቦች በሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች የሚተገበር መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ሌላኛው አሜሪካዊ Merton (1968) ማህበራዊ መዋቅር በርካታ ተግባራት እንዳላቸውና አንዳንዶቹ በግልፅ የሚታወቁ (manifest) አንዳንዶቹ ደግሞ በግልፅ የማይታወቁ ወይም ስውር (latent) ተግባራት እንደሆኑ አመላክተዋል፡፡

በሌላ በኩል እንግሊዛዊው Malinowski (1944) የሰው ልጅ የተለያዩ ፍላጎቶች ያሉት መሆኑን ጠቅሶ የግለሰቦችን ወይም የህብረተሰቡን ፍላጎት ለማሟሏት እርስ በርስ የተያያዙና የተዛመዱ የማህበራዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ወዘተ ተቋማትን የሚያቋቁም መሆኑን አስረድተዋል፡፡ በዚህ ሂደት ላይ ሌላኛው እንግሊዛዊ Brown (1952) በበኩላቸው የስርዓተ መዋቅሩ አካላት ሰዎች ናቸው፡፡ መዋቅሩ የሚመሰረተውም በሰዎች ለሰዎች እንደሆነ ያብራራሉ፡፡

ይህ ንድፈ ሃሳብ የአንድን ማህበረሰብ ስርዓተ- መዋቅርና ባህላዊ ተቋማቱ የሚሰጡትን አገልግሎት ወይም ተግባራዊ ፋይዳ (function) በመመርመር እና በመፈከር ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ ስርዓተ መዋቅሩ ሚዛኑን ጠብቆ ለመቀጠል ደግሞ Parsons (1951) የማህበረሰቡን ቀጣይነት ለማረጋገጥ መላመድ (Adaptation) ዓላማን መቅረፅ (Goal Attainment)፤ ቅንጅት/ውህደት (Integration)፤ ማቆየት/መጠገን (Latency) የሚባሉ 4 ተግባራዊ ግዳጆችን እንደሚያስፈልግ ያናገራሉ፡፡ በጥቅሉ የመዋቅራዊ ተግባራዊነት (**structural functionalism**) ንድፈ ሃሳብ ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ ሥርዓተ ማህበሩን የሚያስጠብቁ (maintenance of social stability) የጋራ ተግባራትን (collective functioning) እና ማህበራዊ ዝግመተ ለውጥን (social evolution) የሚያስገነዝቡ ሦስት መሰረታዊ መርሆች አሉት፡፡

## 2.3.2 የለውጥና ቀጣይነት ንድፈ ሃሳብ

እንደ ለውጥና ቀጣይነት ንድፈ ሃሳብ አተያይ ግለሰብም ሆነ ቡድን በውስጣዊ ወይም ውጫዊ ጉዳዮች ማለትም በሰው ሰራሽም ይሁን በተፈጥሯዊ ምክንያት እየተለወጠ መሄዱ አይቀሬ መሆኑን ነው፡፡ Haferkamp (1992) ለውጥ በግለሰቦች፣ በታዋቂ ሰዎች፣ በቡድኖች፣ በማህበራዊ ሁኔታዎች፣ በቁሶች አማካኝነት ሊጀመር እንደሚችል ይጠቅሳሉ፡፡ በተጨማሪም Rosenberg (1987) የባህል ለውጥን ከሚያፋጥኑ ነገሮች አንዱና ዋነኛው ቴክኖሎጂ መሆኑን ጠቅሰው፤ ቴክኖሎጂ መረጃን ለማሰራጨትና ግንኙነትን ለማስፋፋት ከፍተኛ ጥቅም የሚሰጥ መሆኑን ሲገልፁ Chalfart (1988) የለውጥ አይቀሬነት "ለውጥ የተፈጥሮ ሕግ ነው" በማለት ያስረዳሉ፡፡ እንዲሁም Haferkamp (1992) "*modern societies concern with a secure and better life, which first means survival, then living the good life"* በማለት ዘመናዊው ማህበረሰብ አስተማማኝ እና የተሻለ ህይወት ለመኖር የሚያደርገውን ሂደት ይገልፃሉ፡፡ ለለውጥ አንዱ ምክንያት ያደጉ ሀገራት መስፋፋት በሌሎች ሀገራት ባህል ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደሩ ነው፡፡ ይህንም ሃሳብ Yenealem (2016) Adeyemiን (2008) በመጥቀስ *"the phenomenon of change and its impact on material culture as a visual means to translate societal cultural values and social organization is profound in the developing society of Africa"* በማለት የለውጥ ክስተቱ ባላደጉ ሀገራት ቁሳዊ ባህሎች ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ከፍተኛ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡

ሌላው ቀጣይነት (Continuity) ሲሆን Sims and Stephens (2005) በየትኛውም የጊዜ ርዝመት የሚደረግ ድግግሞሽ ልምድን የሚፈጥር እንደሆነ ስለቀጣይነት አስረድተዋል፡፡ እንዲሁም Shove and Pantzar (2012) አንድን ነገር በተደጋጋሚ ከተከወነ ልምድ እየሆነ እንደሚመጣ ገልፀዋል፡፡ በአጠቃላይ አንድ ነገር በውስጣዊ ወይም በውጫዊ ጉዳዮች ማለትም በሰው ሰራሽም ይሁን በተፈጥሯዊ ምክንያት እየተለወጠ መሄዱ የማይቀር እንደሆነ ከንድፈ ሃሳቡ መረዳት ያስችላል፡፡

በዚህም ጥናት ውስጥ የአልባሳትና ጌጣጌጦች መረጃዎቹ በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን አገልግሎት በመዋቅራዊ ተግባራዊነት እንዲሁም በአልባሳትና ጌጣጌጦች ላይ የሚታየውን የመፅናት ወይም የመቆየት፣ እንዲሁም የመለወጥ ወይም የመቀየር ሂደትን በለውጥና ቀጣይነትን ንድፈ ሃሳቦች ትንተና ተሰጥቶባቸዋል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## ጥናቱ የተደረገበት አካባቢ ገፅታና የማህበረሰቡ ዳራዊ መግለጫ

በዚህ ምዕራፍ ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የተጠኚውን ማህበረሰብ አካባቢያዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ማለትም መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ፣ የወረዳው ስያሜ፣ ባህላዊ መገለጫዎችና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ከወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤትና መሬ መጽሄት በተገኘው መረጃ መሰረት እንደሚከተለው ቀርቧል።

### 3.1 መርሐቤቴ ወረዳ አካባቢያዊ ገፅታዋ

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሰሜን ሸዋ ዞን መስተዳደር ከሚገኙ 5 የከተማ አስተዳደሮች እና 22 የገጠር ወረዳዎች ውስጥ የመርሐቤቴ ወረዳ አንዱ ሲሆን ከመዲናችን አዲስ አበባ በስተሰሜን 182 ኪ.ሜ ከክልሉ ዋና ከተማ ባህርዳር በስተምስራቅ 742 ኪ.ሜ እና ከዞኑ ዋና ከተማ ደብረ ብርሀን በስተደቡብ ምዕራብ 142 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል። ወረዳውን በስተሰሜን ሚዳ ወረሞ ወረዳ በስተደቡብ ሞረትና ጁሩ በስተምስራቅ ወንዝ ጌራ ቀያ በስተደቡብ ምዕራብ የእንሳሮ ወረዳ በስተሰሜን ምዕራብ ደግሞ በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን የደራ ወረዳ ያዋስኑታል (መሬ መጽሄት (1996) ።

የመርሐቤቴ ወረዳ በ$90^0 54^0$ $10^0$ $13^0$ ሰሜን ኬክሮስ እና $38^0$ $39^0$ $14^0$ ምስራቅ ኬንትሮስ መካከል ላይ የሚገኝ ሲሆን 42,324 ካሬ ሜትር ቆዳ ስፋትና 23 የገጠር አንድ የከተማ ቀበሌ እንዲሁም ራሱን የቻለ 1 (አንድ) የከተማ አስተዳደር አለው። ወረዳው በ1993 ዓ.ም የተሰራ ፕላን ያለው ሲሆን 5% ደጋ 65% ወይና ደጋ 30% ደግሞ ቆላ የሚባሉ የአየር ንብረቶች ያሉት መሆኑን ከመርሐቤቴ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት 2013 ዓ.ም የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

የወረዳው ማህበረሰብ የመግባቢያ ቋንቋው አማርኛ ሲሆን 99.9% የሚሆነው ህዝብ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ፣ ቀሪው 0.1% ደግሞ የሌሎች እምነት ተከታዮች አሉት። የመርሐቤቴ ወረዳ ከዓመት እስከ ዓመት የሚፈስ በስተደቡብ የጀማ ወንዝ፣ በስተሰሜን የወንጭት ወንዝ እንዲሁም ኮላሽና ዞማ የሚባሉ ተራራዎች ባለቤት ነው። (ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት 2013 ዓ.ም)።

### 3.2. የመርሐቤቴ ስያሜ

መርሐቤቴ የሚለው ቃል ሰርዎ ቃሉ/ ምንጩ/ የግዕዝ ቋንቋ ሲሆን ትርጓሜውም መርሐ ማለት በግዕዝ "መምራት" ሲሆን "ቤተ" ማለት ደግሞ "ቤት" ማለት ነው። ስለሆነም መርሐቤቴ ማለት "ወደ ቤት ምራኝ" የሚል ትርጓሜ አለው። ይህን ሃሳብ የሚያጠናክርልን የአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት "መርሐ" ማለት መራ፣ መርህ፣ የሚመራ፣ መራሒ፣ መሪ፣ ቤት ማለት በቁሙ ቤት፣ ቤትየ፣ ቤቴ መጠለያየ፣ መኖሪያ ማደሪያ ወ.ዘ.ተ.....እያለ ይተረጉመዋል። በዚህም መሰረት "መርሐቤቴ" የሀገር ስም እንደሆነና ትርጉሙም "ወደ ቤቴ መርቶ አደረሰኝ" እንደ ማለት ነው ሲሉ ተርጉመውታል (1948)።

ይሁንና መርሐቤቴ የሚለው ስያሜ በማን ከማንና መቼ እንደተሰጠ በፅሁፍ የተደገፈ ማስረጃ ማግኘት አልተቻለም። ሆኖም "አባትህን ጠይቅ ይነግርሃል፣ ሊቃውንቶችንም ጠይቅ ያስረዱሃል" እንደሚሉት አበው መርሐቤቴ የሚለውን አጠራር ከአባቶቻችን ሲያያዝ የመጣው ትውፊት እንደሚያስረዳን በ4ኛው ክፍለ ዘመን በነገስታቱ አብርሀ ወአፅብሐ እንደተሰየመ ከመርሐቤቴ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት የተገኘው መረጃ ያስረዳል። ይኸውም ነገስታቱ በ328 ዓ.ም ክርስትናን ከተቀበሉ በኂላ ከመጀመሪያው የኢትዮጵያ ጳጳስ ከሳቴ ብርሃን አባ ሰላማ ጋር እየተዘዋወሩ ክርስትናን ሲያስፋፉ ከተከተሏቸው አብያተ ክርስቲያናት አንዱ በመርሐቤቴ ወረዳ ዓለም ከተማ የሚገኘው የኦፍና አማኑኤል እንደነበረና በአካባቢው ባደረጉት ቆይታ የአካባቢውን መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ ሲመለከቱት ከመናገሻቸው አክሱምና አካባቢው ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ስላገኙት ከሀገራቸው አንስቶ እስከዚህ ያደረሳቸው ጎዳና የሚደነቅ "ኦ" "ፍና" ታላቅ መንገድ እንዳሉትና ይህም ታላቅ መንገድ መርቶ እቤት አደረሰኝ በማለት አካባቢውን "መርሐቤቴ" የሚል ስያሜ እንደሰጡት የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ ሲል ከመርሐቤቴ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት 2013 ዓ.ም የተገኘው መረጃ ያመላክታል።

መርሐቤቴ የሚለው አጠራር በቅርብ ጊዜ የተሰጠ ስያሜ ሳይሆን ከጥንት ጀምሮ የነበረ የሀገር ስም መሆኑን ለማስረጃነት የሚያገለግለው አባህርያቆስ (በ4ኛ እና 5ኛ ክፍለ ዘመን) አካባቢ እንደጻፉት በሚነገረው ድርሳነ ዑራኤል (2011) በታህሳስ ወር ድርሳን በምዕራፍ 2 እና በ13ኛው ክፍለ ዘመን በተፃፈው በገድለ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ምዕራፍ 62 ላይ ይህ መጠሪያ በመገለፁ ነው።

መርሐቤቴ ለሚለው ስያሜው ጥንታዊነት ሌላኛው ማስረጃ ዋቢ የሚሆነው በኢትዮጵያ ታሪክ እውቅ ተመራማሪና ፀሐፊ የነበሩት ተክለ ፃዲቅ መኩሪያ የኢትዮጵያ ታሪክ፡- ኑብያ አክሱም ዛጉዌ (1951 ዓ.ም) በሚለው መጽሃፋቸው ስለዮዲት ጉዲትና ህፃኑ ንጉስ አንበሳ ውድም ሲገልፁ፡-

> ንጉስ አንበሳ ወንድም የአባቱን ዙፋን ከአክሱም ትቶ ወደ ሸዋ ሸሽቶ በመጣ ጊዜ የሸዋ ህዝብ በደስታ ተቀበለው፡፡ ዮዲት ይህን በሰማች ጊዜ በነገሰች በ23ኛው ዓመት ብዙ ሠራዊት ሰብስባ ወደ ሸዋ ላከች አንበሳ ውድምም የመንዝን ባላገር ይዞ የዮዲትን ጦር ተዋግቶ መለሰው፡፡ ከዚህ በኋላ ራሷ ዮዲት የቀረውን ጦሯን ሰብስባ ራሷ እየመራች ወደ ሸዋ መጣች፡፡ አንበሳ ውድምም መምጣቷን ሲሰማ ከመንዝ ወደ መርሐቤቴ ወረደ፡፡ እርሷም እስከ መርሐቤቴ ለመከታተል ሞክራ ሳለ በመካካል የአህያ ፈጅና የዶባ መንገድ ገደላ ገደሉ ስላስቸገራት በዚህም ላይ አንበሳ ውድምን የሚረዳው የሸዋ ህዝብ በሚያውቀው አገር ላይ እያደፈጠም ፊት ለፊትም እየወጋ አደጋ እየጣለ ስላወካት ከሸዋ ወደ አክሱም ተመልሳ 17 ዓመት ያህል ኖራ በሙሉ 40 ዓመት ነግሳ ሞተች" በማለት ያስረዳሉ፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ተክለ ፃዲቅ መኩሪያ ከአጼ ልብነ ድንግል እስከ አፄ ቴዎድሮስ በሚለው መፅሀፋቸው የአፄ ልብነ ድንግል ልጅ የአቤቶ ያእቆብ የልጅ ልጅ የሆነው አቤቶ ስብከቴ ከወንድሞቹ ተጣልቶ መርሐቤቴ መጥቶ የአካባቢው ገዥ በነበረው ለመዘመር አገልጋይ ሆኖ እንደተቀመጠ (1953) ሲሉ ጽፈዋል፡፡

### 3.3. ዋና ዋና ኃይማኖታዊና ብሄራዊ በዓላት

የመርሐቤቴ ማህበረሰቡ የሚታወቅባቸው የተለያዩ ባህሎች ወጎችና ልማዶች አሉት፡፡ እነዚህ ልምዶች፣ ወጎች፣ ባህሎችና ስርዓቶች ከትውልድ ትውልድ እየተላለፉ ዛሬ ላይ ደርሰዋል፡፡ የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ማሰልጠኛ ተቋም በ2005 ዓ.ም ከአጋር አካላት ጋር ስለጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ባደረገው ጥናት ኢትዮጵያ ውስጥ ጠቃሚ የሚባሉ ልማዳዊ ድርጊቶች እንደ ጡት ማጥባት፣ ዕቁብ፣ ዕድር፣ ማህበር፣ አረጋዊያና አካል ጉዳተኞችን የመንከባከብ ወዘተ… እንዲሁም ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት የሚባሉ እንደ ሴት ልጅ ግርዛት፣ ያለ ዕድሜ ጋብቻ፣ ጠለፋ፣ የነፍሰ ጡር ሴትን በቅቤ ማሸት፣ ኮሶ ማጠጣት ወዘተ.. ልማዳዊ ድርጊቶች መኖራቸውን ይገልፃል፡፡

ከዚህም አንፃር በወረዳው ማህበረሰብ የሚከናወኑ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ከሞላ ጎደል የማስወገድና ሌሎች ጠቃሚ የሚባሉትን ወግ፣ ልማድ፣ ባህልና ስርዓትን በማልማት ለህብረተሰቡ ከፍተኛ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ በወረዳው የሚከበሩ ዋና ዋና ሃይማኖታዊና ብሄራዊ በዓላት እንዲሁም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁነቶችን ምን ምን እንደሆኑ ከወረዳው ባ/ቱ/ ጽ/ቤት (2013 ዓ.ም) የተገኘው መረጃ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በተጨማሪም የፅሁፍ ድግግሞሽ ለመቀነስ በሁለቱም ፆታ ያሉ የማህበረሰቡ አባላት እንደ ዕድሜ ደረጃቸው በሃይማኖታዊና ብሄራዊ በዓላት አከባባር ላይ የሚለብሷቸውን አልባሳትና ጌጣጌጦች ምን ምን እንደሆኑ በመስክ ምልከታና በቃለ መጠይቅ ከተጠኚው ማህበረሰብ አባላት ያገኙሁትን መረጃ ጠቅለል ባለ መልኩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ ይኸውም ህፃናት ሴቶች ከፋብሪካ ምርት ብትን ጨርቆች በልዩ ጌጥ የተዘጋጁ አርባሸንሸን ቀሚስ በመልበስና የአንገት መስቀል፣ ጨሌ፣ ዶቃ/ድምርጥ፣ ብር ቅጥል፣ እንቆ፣ አሸንክታብ/ቁርበተ ሀሊም፣ አንገት ክር/ማህተብ ጌጦችን በማድረግ፣ ጉድሮ፣ ቅምቅሞ የፀጉር አሰራሮችን ይሰራሉ፡፡ እንዲሁም ህፃናት ወንዶች ደግሞ ቁምጣ ከነአላባሹ፣ ቲሸርቶችን በመልበስ፣ የአንገት መስቀል፣ እንቆ፣ አርጌሽ ልሙት ጌጣጌጥ በማድረግና ቁንጮ፣ ጋሜ፣ ልጩ፣ ጉድሮ የሚባሉ የፀጉር አሰራር ዓይቶች ይጠቀማሉ፡፡

ወጣት ሴቶቹ ደግሞ ከአልባሳት እጅ ጠባብ ቀሚስ፣ አርባ ሸንሸን፣ መቀነት፣ አንገት ልብስ፣ ነጠላ በመልበስና የተለያዩ የፕላስቲክ/የጠፍር ጫማዎችን በማድረግ፣ ከጌጣጌጥ ብር መስቀል፣ ድንብል፣ ዶቃ/ድምርጥ፣ ብር ቅጥል፣ እንቆ፣ ማህተብ/ጎፍታ፣አሸንክታብ፣ ጃንጥላ፣ ብራባር፣ ወዘተ በተለያዩ የሰውነት ክፍል ላይ በማድረግ እንዲሁም እንደ ዕድሜ ደረጃቸው ቅምቅሞ፣ ቁንዲድ፣ ሹርባ የፀጉር አሰራሮችን በመሰራት ይዋባሉ፡፡

በተመሳሳይ ወጣት ወንዶች ከአልባሳት ቁምጣ፣ ባለአግድም ሰረዝና ቲሸርቶች፣ ካኒቴራዎች፣ የጥለት ሹራብ፣ ሱሪ፣ ፎጣ፣ ኩታ፣ ዱላ፣ ቆብ ወይም ኮፍያ በመልበስና የጎማ፣ የፕላስቲክ፣ የጠፍር ጫማዎችን በማድረግ፣ ከጌጣጌጥ ደግሞ የአንገት መስቀል፣ ድንብል፣ ድምርጥ፣ እንቆ፣ አርጌሽ ልሙት፣ ማህተብ/ጎፍታ፣ በማድረግ እንዲሁም በየዕድሜ ደረጃቸው ቁንጮ፣ ጋሜ፣ ጎፈሬ፣ ፍሪዝ/ቁጥጥር የፀጉር አሰራር ዓይነቶችን ተሰርተው ይዋባሉ፡፡

እንዲሁም አዋቂ ሴቶች ከጥጥና ከፋብሪካ ምርት ብትን ጨርቆች የሚዘጋጁ እንደ ጉያና እጅ ጠባብ ቀሚስ፣ መቀነት፣ ነጠላ፣ ጋቢ፣ ሻሽ በመልበስና የአንገት መስቀል፣ አንዳንዶቹ ብራምባር፣ ማተብ/የአንገት ክር፣ ድንብል አዋቂ ወንዶች ደግሞ ቦላሌና ተነፋነፍ ሱሪ ከነአላባሹ፣ ነጠላ፣ ጋቢ፣ ቡልኮ፣ ኮፍያ በመልበስ ከጌጣጌጥ ደግሞ የአንገት መስቀል፣ እንቆ፣ የእጅ ጭራ፣ ዱላ በመያዝ በዓላትን ያከብራሉ፡፡ በሁለቱም ፆታ ያሉ አዋቂዎች ብዙ ጊዜ ቅምቅሞ የተባለውን የፀጉር አሰራር ይጠቀማሉ፡፡

### 3.3.1. እንቁጣጣሽ

የእንቁጣጣሽ በዓል በሁሉም የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚያከብሩት ዓመታዊ ክብረ በዓል ነው፡፡ በተለይ በገጠር ቀበሌዎች የሚኖሩ ወጣቶች በዓሉን ለየት ባለ መልኩ በዓሉን ያከብራሉ፡፡ ይኸውም በክብረ በዓሉ ላይ ወንዶችና ሴቶች የሚሳተፉ ቢሆንም በአብዛኛው ግን የሴቶች ተሳትፎ ላቅ ያለ ነው፡፡ ቀደም ሲል በተገለፀው የአለባበስና አጊያጊያጥ ስርዓት መሰረት ወጣት ሴቶች ከበዓሉ ዋዜማ በአካበቢው አጠራር አሳስራ፣ ልምጭ ሳዱላ፣ ቡቅር ዛሌዋ ወዘተ..ፀጉር አሰራሮችን ወንዶቹ ደግሞ ፍሪዝ ጎፈሬና ቁንጮ የተባሉትን የፀጉር አሰራሮችን በመሰራት ይዋባሉ፡፡

በተጨማሪም ወጣቶች ከየመንደራቸው አቅራቢ ከሚገኙ ማሳዎች፣ ተራራዎች፣ ቦታዎች ተሰባስበው አደይ አበባ ወይም ሳር ይዘው ወደ ቤታቸው ይሄዳሉ፡፡ ይዘውት የመጡትን አደይ አበባ ወይም (እንግጫ ሳር) ከበዓሉ ቀን በፊት በገመድ መልክ ይገምዱታል፡፡ የተገመደውን ቁጠማ (እንግጫ ሳር) በአሮጌው በአዲስ በመቀየር በተለያዩ የቤት ዕቃዎች ላይ (ሞሰብ፣ ገበታ፣ ውሃ መቅጃ እንስራ፣ ጠላ መጥመቂያ ጋንና ማዲጋ) ወዘተ… ላይ ዓመቱን ሙሉ አስረው ያከርሙታል፡፡ በበዓሉ ዋዜማ የነቀሉትን አደይ አበባ ሁሉም የሰፈሩ ልጆች የእንቁጣጣሽ ዕለት ወደ ቤተክርስቲያን ቅጽር ግቢ ይዘውት ይሄዳሉ፡፡ ከዚያም የተለያዩ የአካበቢውን ባህላዊ ዘፈኖችና ጭፈራዎችን በቅብብል ይዘፍናሉ፣ ይጨፍራሉ፡፡

### 3.3.2. በመስቀል (ደመራ)

በመርሐቤቴ ወረዳ የመስቀል በዓል አከባበርን ስንመለከት የደመራ በዓል ከመስከረም 16-17 ለሁለት ቀን ያህል ይከበራል፡፡ መስከረም 16 በሚከበረው የአካባበር ሂደት የማህበረሰቡ አባላት የሆኑት ወንዶች ለድምር የሚሆን የተለያዩ ቁመት ያላቸውን እርጥብ እንጨት ይዘው ደመራው ወደሚደመርበት አጥቢያ ቤተክርስቲያን ወይም ወደተዘጋጀው ቦታ ይዘው ይሄዳሉ፤ ይደምራሉ፡፡

እንዲሁም ሴቶቹ ቀደም ሲል በተገለፀው መሰረት የክት ልብሶቻቸውን ለብሰው እንዲሁም የተለያዩ የፀጉር አሰራሮችን ተሰርተው፣ ወደ ደመራ ቦታ በመሄድ የክብረ በዓሉ ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡ ነገር ግን ለመደመሪያ የሚሆን እንጨት ይዞ በመሄድና በድምሩ ላይ የማስቀመጥ ወይም የመደመር ተግባርን አያከናውኑም፡፡ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያኑም በዕለቱ ዋዜማ ቆመው በዓሉን ለማክበር መስቀል ይዘው ይወጣሉ፡፡ የተለያዩ ያሬዳዊ ዝማሬዎችን በመዘመር ያከብራሉ፡፡ የደመራው ስነ-ስርዓት ወደ መጠናቀቅ ደረጃ ሲደርስ አባቶች ካህናት የደመራውን እንጨት ባርከው ችቦ መለኮስ እንዲነድ ያደርጉታል፡፡ ከዚያም ሦስት ጊዜ ዞረው ድምሩ ነዶ ከወደቀ በኋላ ወደቤታቸው ይመለሳሉ፡፡

መስከረም 17 ቀን ጧት ላይ ድመሩ ወዳለበት ቦታ በመሄድ ከበሽታ ለመከላከል እንዲያስችል የድምሩ እሳት ላይ አንደ አሽክርትና ሌሎች ቅጠሎችን በማድረግ እግርን የማሞቅ ስራ ይከናወናል፡፡ ከነደደው እንጨት በሚወጣው እሳት ላይ በቅጠል ዳቦ በማብሰል እንዲሁም ከአዲሱ ዓመት ቀድሞ ከደረሰው አዝዕርት እህል ገንፎ በማገንፋት ይመገባሉ፡፡ ይህም አዲስ ዓመት የሰላም የጥጋብ፣ የጤናና የደስታ እንዲሆነ በማሰብ ነው፡፡ በተጨማሪም አባቶች የታመሙ እንስሳትን ወደ ድምሩ ቦታ በመውሰድና ሲነድ ካደረው የእሳቱ ፍም ላይ ብረት በማጋል የታመሙትን ከብቶች ህመም የተሰማቸው ቦታ ላይ በግለት ይተኩሷቸዋል ወይም ያክሟቸዋል፡፡ በመጨረሻም አዋቂዎች ከጎረቤቶቻቸው ጋር ወጣቶቹም ከአቻዎቻቸው ጋር በመሆን የተለያዩ ጨዋታዎችን እየተጫወቱ ይውላሉ፡፡

### 3.3.3. ገና በዓል

የገና በዓል በሰፊውና በደመቀ ሁኔታ በመርሐቤቴ ወረዳ የሚከበር በዓል ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ከታህሳስ 27 እስከ 29 ለተከታታይ 3 ቀናቶች በዓለም ከተማ አፍና አማኑኤል ቤተክርስቲያን የወረዳ የገጠር ቀበሌ ነዋሪዎችና ከተለያዩ አካባቢዎች በመምጣት የተለያዩ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ስርዓቶች በተዋበ መልኩ የሚከወንበት በዓል ነው፡፡

በመርሐቤቴ ወረዳ ገና ሲከበር ሴቶችም ወንዶችም የተለያዩ ሀገረሰባዊ አልባሳትና ጌጣጌጦች ተጠቅመው ይዋባሉ፡፡ ከእነዚህ ሀገረሰባዊ የመዋቢያ ስርዓት አንዱ ሴቶቹ የእጅ መዳፋቸውና የውስጥ እግራቸው ቀይ ወይም ቡናማ መልክ እንዲኖረው የሚያደርጉበት የእንሶስላ ወይም ግሽልጥ የሚባለው ነው፡፡ ይህ ተክል የሴቶቹን እጅና እግር ከማስዋቡ በተጨማሪ አልባብ አልባብ (ከተጠቀሙት ተፈጥሯዊ ተክል የሚገኝ ሽታ) እየሸተቱ፣ ወንዶቹ ደግሞ እግራቸውን በሽቶ ሳሙና ተወልውለው (ተሞንድለው) ፎጣና ዱላ ይዘው ወደ ክበረ በዓሉ ሄደው የተለያዩ ባህላዊ ጨዋታዎችን ይጫወታሉ፡፡

### 3.3.4. ጥምቀት

የጥምቀት ክብረ በዓል በመርሐቤቴ ወረዳ ከገጠር እስከ ከተማ በሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ሃይማኖታዊ ይዘቱን ጠብቆ በድምቀት የሚከበር በዓል ነው፡፡ ከኃይማኖታዊ ይዘቱ በተጨማሪ ማህበረሰብ የራሱ የሆኑ ባህላዊ የአከባበር ስርዓትን ተከትሎ ያከብሩታል፡፡ በተለይ ወጣቶች ለስርዓተ ጋብቻ የሚተዋወቁበት አንዱ አጋጣሚ በመሆኑ የተለያዩ ቀለም ያላቸውን የክት ልብሶችና ጫማዎችን በመልበስ እንዲሁም የተለያዩ የራስ፣ የአንገት፣ የእጅ፣ የወገብ ወዘተ ጌጦችን በማድረግ እንዲሁም የተለያዩ ፀጉር አሰራሮችን በመሰራትና እንሶስላ፣ ግሽልጥ፣ ኩል ወዘተ የሚባሉ መዋቢያዎችን በመጠቀም ይዋባሉ፡፡ ወጣት ሴቶች በዚህ መዋቢያ መጠቀም እንዲስችላቸው በዓሉ አንድ ሳምንት ሲቀረው ተክሉ ወደሚገኝበት

ቦታ ለመሄድ ቀድመው ቀጠሮ ይይዛሉ። ይዘው የመጡትን የእንሶስላ ወይም ግሽልጥ ተክል ከ3-7 ባሉ ቀናት መሬት ውስጥ ይቀብሩታል። በከተራ (በጥምቀት ዋዜማ) ሴቶች በሰፈር በሰፈር በመሆን በጋራ አንድ ቤት ስለሚያሳልፉ የተለያዩ ስራዎችን ለመስራት ቀድመው ይከፋፈላሉ። የተወሰኑት ልጃገረዶች ለሊቱን ሙሉ ሲጫወቱና ሲዘፍኑ ስለሚያድሩ ንፍሮ ያዘጋጃሉ፤ ሌሎቹ ደግሞ የተቀበረውን ግሽልጥ ለመዋቢያ እንዲሆን ያዘጋጁና ሁሉም ይዋቡበታል። በጥቅሉ ለጥምቀት በዓል ሁሉም ያለውን ልብስ ለብሶ አምሮና አጊጦ የሚውልበት በዓል በመሆኑ ውበታቸውን ለመጠበቅ የክት ልብስን ከመልበስ ጀምሮ ልዩ ልዩ ፀጉር አሰራሮችን በመሰራት፣ የራስ፣ የእጅና የአንገት ጌጦችን በማድረግ በዓሉን ያከብራሉ።

### 3.3.5. የፋሲካ በዓል

የፋሲካ ክብረ-በዓል በማህበረሰቡ በደማቅ ሁኔታ በተለያዩ ባህላዊ ክዋኔዎች የሚከበር ነው። ሆኖም ግን የፋሲካ በዓል አከባበር የራሱ የሆነ ስርዓት አለው። ይኸውም የፋሲካ በዓል አንድ ሳምንት ሲቀረው ወጣቶች በሰሞነ ህማማት ቤተሰቦቻቸው የሚጠቀሙበት ማገዶ እንጨት፣ የከብት መኖ ሰብስበው ያስቀምጣሉ። እንዲሁም አዲስ ልብስ በማሰፋትና በማሰራት የአንገት ልብስ፣ መቀነት፣ ከከብት ቆዳ የተሰራ የቆዳ ጥልፍልፍ ጫማቸውን 2 ወር ያሙ እስከሚያበቃ ጭስ ላይ በመስቀል ያስቀምጡታል። ከዚያም ከጭሱ ላይ ከበዓሉ አንድ ቀን ቀድም ብሎ ከጭሱ ላይ በማውረድ በሎሚና በቅቤ ያሹታል።

የትንሳዔ ዕለት ያገቡ ሴቶች አንገታቸው ላይ ከጥለት የተሰራ ማተብ (ጎፍታ)፣ አርጌሽ ልሙት፣ ድንብል፣ ድንብሌ፣አሽን ክታብ፣ ቁርበተ ሀሊም እና በእጃቸው ላይ አምባር በማድረግ ያላገቡ ሴቶች ደግሞ ድንብሌ፣ አሽን ክታብ፣ በማድረግ ያገቡም ያላገቡም ፀጉራቸውን አሳ ስራ፣ ልምጭ ከዱላ እና ዛሌዋ የሚባሉ የፀጉር አሰራሮችና ጌጣጌጦች ደምቀው ወደ መጫዎቻ ቦታዎች ይሄዳሉ።

### 3.3.6. ቡሄ (ነሐሴ 13)

ቡሄ በወረዳው ማህበረሰብ ከሚከበሩ ኃማኖታዊና ባህላዊ ክብረ በዓላት አንዱ ነው። ቡሄ ሲከበር በባህላዊ ጨዋታው ላይ በሰፊው የሚሳተፉት ህፃናትና ወጣቶች ናቸው። ከህፃን እስከ አዋቂ ያሉ ወንዶች ብቻ የሚያበሩት ችቦ ከበዓሉ ቀድሞ የሚዘጋጅ ሲሆን በዕለቱም ከተለያዩ ባህላዊ ስርዓቶች የሚከወን ይሆናል። በተለይ በገጠሩ አካባቢ ያሉ ህፃናትና ወጣት ወንዶች ቀን ላይ ከየቤታቸው ዳቦና ጠላ በመያዝ ከመንደር ወጣ ያለ ቦታ ላይ ጊዜያዊ ጎጆ በመስራት ከመንደር ያመጡትን ዳቦ ይመገቡበታል። ማታ ላይ ችቦ በመለኮስ ጅራፍ በመያዝ፣ በማጮህ እንዲሁም ወደ አንድ አካባቢ በመሰባሰብ ጅራፍ በማጮህ፣ በተለያዩ የበዓል አልባሳትና ጌጣጌጦች ተውበው ይጫወታሉ።

ሌላው የቡሄ መለያው ለክርስትና ልጅ ድፍን ድፎ ዳቦ፣ ልብስና አዲስ ለተጋቡና አንድ ዓመት ላልበለጣቸው ሙሽሮች የቡሄ በሚል ሰፊ ድግስ ተገድሶ ዘመድ አዝማድና የቅርብ ወዳጅ ሰዎች ድፎ፣ አረቄ፣ ሽሮ፣ በርበሬና የተለያዩ የቤት ቁሳቁሶችን ይዞ መሄድ በቁሳቁስ እንዲደራጁ ማደረግ የተለመደ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜም እንደቤተሰብ የሀብት ደረጃ የቁም እንስሳትና የእርሻ መሬት ዘመድ አዝማድ በተሰበሰቡበት በስጦታ የሚበረከትበት ቀን ነው፡፡

### 3.4. የመርሐቤቴ ወረዳ ባህላዊ የወሊድ ስነ-ስርዓት

የመርሐቤቴ ወረዳ እንደማንኛውም ማህበረሰብ የራሱ የሆነ ባህልና ወግ ያለው አካባቢ ነው፡፡ ከባህልና ወጎቿ መካከል አንዱ የሆነውን ባህላዊ የወሊድ ስነ-ስርዓት ነው፡፡ አንዲት ሴት ልጅ ነፍሰ ጡር ስትሆን ቀደም ሲል በአካበቢ በባህላዊ ስርዓት አሁን ደግሞ በጤና ኤክስቴሽን ሰራተኞች ድጋፍ ይደረግላታል፡፡ ልጇን ከወለደች በኋላ ሊጠይቋት የመጡ ወዳጅ ዘመድ "እንኳን ማሪያም ማረችሽ" በማለት ሲጠይቋት እሷም በተራዋ "ማሪያም ታኑራችሁ" በማለት ምላሽ ትሰጣለች፡፡ ልዩ ልዩ ጨዋታዎችን ከተጨዋወቱ በኋላ ሊጠይቋት የመጡ ወዳጅ ዘመዶቸ ከቤት ወደ ውጭ ሲወጡ ለመሰናበቻ ደግሞ "ማሪያም በሽልም ታውጣሽ" በማለት መቀርው ይወጣሉ (ይሰናበታሉ)፡፡ ነፍሰ ጡር የሆነች ሴት ልጇን ከወለደች በኋላ ያለችበትን ክፍል (መኝታ ቤት) በነጠላ፣ በሸራ አልያም በሰንበሌጥ ሳር መከለያ ወይም መሸፈያ የሚሆን መጋረጃ ይዘጋጅላታል፡፡ እዚህ ላይ ነጠላ ለአካል ደህንነት መጠበቂያነት ከማገልገሉ በተጨማሪ የአራስ መኝታ ክፍል ለመጋረድ የሚያገለግል መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

### 3.5.የመርሐቤቴ ወረዳ የሰርግ ስነ-ስርዓት

በአንዳንድ ቀበሌዎች ሁለት ሴቶች ድድሆ ቅጠል ይዘው በመሄድ የምትታጨው ሴት ልጅ ቤተሰቦች ቤት በር (ደጅ) ላይ ይጥሉታል፡፡ የድድሆ ቅጠል መሆኑና ከበሩ ላይ የሚጥሉበት ምክንያት እመቤታችን ማርያም በስደቷ ወቅት ጎዝጉዛ ትቀመጥበትና ለጥላነትም ከሌሎቹ ዕጽዋቶች በመምረጥ ትጠቀምበት ስለነበር የማርያም ጉዝጓዝ ነው የበረከትና የሰላም ምሳሌ ነው በማለት ለሰላም ለዝምድና መምጣታቸውን ለማመልከት የድድሆ ቅጠል ይዘው በመሄድ ከበሩ ላይ ይጥሉታል፡፡ ከዚያም ገብተው ይቀመጣሉ፡፡

ከትንሽ ቆይታ በኋላ ተነስተው ይቆማሉ፡፡ ምን ፈልጋችሁ ነው ሲባሉ ልጃችሁን ለልጃችን ብለን ነው የመጣነው፣ ከእንጨት መርጦ ለታቦት ከሰው መርጦ ለሹመት እንደሚባለው አቻዎቻችን እንደሆናችሁ አውቀን መጥተናል ሲሉ ቁጭ በሉ ሲባሉ ቁጭ ይላሉ፡፡ ይሰተናገዳሉ፡፡ መጨረሻ ላይም ተመካክረን እንልክባችኋለን ይሏቸዋል፡፡ ከዚያ በኋላ ተመልሰው ይሄዳሉ፡፡ የሴቷ ቤተሰቦች ዝምድናን ጨምሮ ለጋብቻ ብቁ የሚድረጋቸውን ሁሉንም ነገር ካረጋገጡ እና አቻ መሆናቸውን ካወቁ በኋላ ለወንድ ቤተሰቦች

መስማማታቸውን መልዕክት ይልካሉ፡፡ ከዚያም ከወንድ ቤተሰብ ሁለት ሰዎች ሆነው በተቀጠሩበት ቀን ይሄዳሉ፡፡ ያለውን ነገር ሁሉ ተነጋግረው ከተማመኑ በኋላ የነገር ቁርጫ (የሰርጉን አጠቃላይ ሁኔታ ለመመካከር) ቀን ይይዛሉ፡፡ ከዚያ ምግብ ተመግበው /ተስተናግደው/ ይለያያሉ፡፡

ለነገር ቁርጫው ያገባ ታላቅ ወንድም፣ አባት፣ አጎት፣ ክርስትና አባት እና ታዋቂ ዘመድ ሆነው ይሄዳሉ፡፡ ከዚያም ከሴቷ ቤተሰቦች ጋር ስለጥሎሽ ተነጋግረው የሰርግ ቀን ይቆርጣሉ (ይወስናሉ)፡፡ከዚያ ድግሱ ይደገሳል፤ ሰርጉ ሦስት ቀን ሲቀረው የድድሆ ቅጠል ዳስ ይጣላል፤ የድድሆ የሆነበት ምክንያት ከላይ በተጠቀሰው መሰረት ነው፡፡ ሰርጉ ሊደርስ ስምንት ቀን ወይም ሦስት ቀን ሲቀረው አግቢዋ ጓደኞቿን እና የአካባቢውን ወጣቶች በእያንዳንዳቸው ቤት በመሔድ ልጅ አጫውት (እናትያ እያለች) ትጠራለች/ትለምናለች/፡፡ ጥሪ የተደረገላቸው አጫዋቾችም ከበሮ በመያዝ ክብ ሰርተው የተለያዩ አካባቢያዊ ዘፈንና ጭፈራዎችን እያካሄዱ እስከ ሰርጉ ቀን ሲያጫውቷት ይሰነብታሉ፡፡

ሰርጉ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የአካባቢው ማህበረሰብ ከጠላ መጥመቅ ጀምሮ እንጀራ በመጋገር፣ ወጥ በመስራት፣ ሽክና በማጠብ፣ ቂጣ በመጋገር፣ ኑግ በመውቀጥ እና ቆሎ በመቁላት ወዘተ ስራዎች ላይ ንቁ ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡ የልጅቷ ጓደኞች ፀጉሯን በመስራት፣ አንሶስላ (ግሽልጥ) በማሞቅ ልብሷን በማልበስ፣ ኩል በመኩላት ውበቷን ያሰማምራሉ፡፡

የሰርጉ ዕለት ወጣቶችን የጋጋሪ አዛውንቶች ደግሞ የመራቂ ተብለው ይጠራሉ ከዚያም ይስተናገዳሉ፡፡ መቆናቁን /የበሬ ስጋ/ በመስራት እና በቁና በመያዝ በጃቸው ልክ እንደ ቆሎ እየተዘገነ እና እየተጨበጠ ይሰጣል፡፡

ከዚህ በኋላ ሙሽሮች "ሆ" እያሉ እየዘፈኑና እየጨፈሩ ይመጣሉ፡፡ ወደ ሙሽሪቷ ቤት ሲቀርቡም የሙሽሪት ጓደኖች ወደ ዳሱ እንዳይገቡ ለመቆጣጠር ይዘጋጃሉ፤ ሲመጡ ወደ ዳሱ ውስጥ ሊገቡ ሲሉ የልጅቷ ጓደኞችም አናስገባም ሰርገኛ እያሉ በሩን ይይዙባቸዋል፡፡ ከዚያም ሰርገኞቹ ከበር ላይ ጨፍረው ይገባሉ፡፡ በተቀየሰላቸው ዳስ ውስጥ በመቆም የሆነ ነገር እንደፈለጉ በሚገልጽ አኳኋን ይጠብቃሉ፡፡ ሽማግሌዎች ሙሽሮችን ለምን ቆማችሁ? እያሉ ይጠይቋቸዋል፡ ክርክሩ ቀድሞ ያለቀ በመሆኑ ሙሽሮች ልጅ ታደርጉን ዘንድ በማለት ሲናገሩ፣ አግቢ ሙሽራውን ደግሞ ምንህ ናት? በማለት ሲጠይቁት መንግስት ይሙት ሚስቴ ናት! በማለት ይመልሳል፡፡እጃችሁ ከምን? ሲሏቸው ደግሞ "ከሽማ ጥቅል፣ ከወርቅ እንክብል" ይሉና ያመጡትን የሙሽራ ልብስ፣ ጌጣጌጥ ሁሉ ወጉን በጠበቀ መልኩ ያሳያሉ፡፡ ከዚያም መተዳደሪያውን ገልጾ ሲያበቃ ቁጭ በሉ ይባላሉ፡፡ ከዚያም የተለያዩ ዘፈኖችና ጭፈራዎችን ሲያካሂዱ ቆይተው በእናትና በአባቶች ተመርቀው ሙሽራዋን ወደ ሙሽራው

ቤት ይዘው ይሄዳሉ። ከዚያም ከወንዱ /ከሙሽራው/ ቤተሰቦች ሙሽሪትን በጀርባቸው አዝለው እስከ አጃቢዎችና ሚዜዎች ይገባሉ። እንዲሁም የተለያዩ ክዋኔዎች ይደረጋሉ። በዚህ ስርዓት ውስጥም ማህበራዊ ደረጃ ለማሳየትና ውበትን በማጉላት በኩል የጥናቱ ጉዳይ የሆኑት አልባሳትና ጌጣጌጥ ትልቁን ድርሻ ይይዛሉ።

### 3.6. የመርሐቤቴ ወረዳ የለቅሶ ስነ-ስርአት

የመርሐቤቴ ወረዳ ማህበረሰብ የራሱ የሆነ የለቅሶ ስርዓት አሉት። ከእነዚህም ውስጥ አንደኛው ከቅልና ከሸንበቆ የሟችን ምስል በመስራት ለማስለቀሻነት ካገለገለ በኋላ የተሰራውን የሰው ምስል በሟች ቀብር ላይ የማስቀመጥ ሂደት አንዱ ነው። ይህ ምስል የሚዘጋጀው በአካባቢው ለሚሞቱ ማንኛውም ሰዎች ሲሆን ተምሳሌቱም የሰው ልጅ ተሰባሪ እንደሆነ እና እድሜው አጭር እንደሆነ ከመርሐቤቴ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት (2013 ዓ.ም) የተገኘው የጥናት ሰነድ ያመለክታል። በተጨማሪም የለቅሶ ስርዓት ከቀብር ዕለት እስከ ሰባተኛው ቀን ድረስ በሟች ቤት ድንኳን ተጥሎ ከቀኑ በተጨማሪ ሌሊት ዶሮ ሲጮህ ከመኘታ እየተነሱ ያለቅሉ። እንዲሁም በለቅሶ ቀን ነጠላ መዘቅዘቅና ማሸረጥ፣ ሙሾ፣ ፉከራ ወዘተ ሂደቶች በቀብር ዕለት ይከወናሉ። እንዲሁም ነጭ ክር በአንገት ላይ ማሰር፣ ፀጉርን መላጨት፣ መሬት ላይ መተኛት፣ በደስታ ቤት አለመገኘት የሀዘን መገለጫዎች ናቸው። ይህ የለቅሶ ስርዓት አልባሳትን በመጠቀም ውበትን በማቅሰም (መዋቢያ አለመጠቀም) ወዘተ ከጥናቱ በቀጥታ የሚያገናኘው ነው።

### 3.7. ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ

የመርሐቤቴ ወረዳ ነዋሪ እንደማንኛውም ማህበረሰብ ህይወቱን ለመምራት የተለያዩ ስራዎችን ያከናውናል። የገጠሩ ማህበረሰብ በእርሻ የሚተዳደር ሲሆን የአስተራረስ ባህሉም በአብዛኛው በበሬ ላይ የተመሰረተ ሲሆን አልፎ አልፎ በአንዳንድ የገጠር ቀበሌዎች በበጋ ያረሱትን ማሳ (ያለሰለሱትን) በጋማ ከብቶች፣ በፍየሎች ወይም በላሞችን እንዲረባይ/እንዲረግጡት ያደርጋሉ። ይህም የእርሻ ወይም የዘር ዓይነት የሚከናንበት ምክንያት በበሬ ሲታረስ ለዘር የተዘጋጀው ማሳ ሰፊ ወይም ብዙ በመሆኑ የዘር ወቅት ሳያልፍ የሚደረግ ነው። ሌላው የመስኖ ስራዎችን በማከናወን አትክልትና ፍራፍሮዎችን እያመረቱ ህወታቸውን ይመራሉ። ከተማ በሆኑ አካባቢዎች የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ደግሞ በተለያዩ የንግድ ስራዎችና በመንግስት ስራ የሚተዳደሩ ናቸው። በመሆኑም የጥናቱ ጉዳይ የሆኑት አልባሳትና ጌጣጌጦችም በዚህ ኢኮኖሚያዊ ጉዳይ ላይ በተለይ በመገበያየት በኩል ተሳትፎ የሚደረግባቸው ዘርፍ ነው።

## በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የሰሜን ሸዋ ዞን ካርታ




ምንጭ፡- የመርሐቤቴ ወረዳ ኮሙዩኒኬሽን ጽ/ቤት ግንቦት 2015 ዓ.ም

## በአ.ብ.ክ.መ ሰሜን ሸዋ ዞን መርሐቤቴ ወረዳ ካርታ




ምንጭ፡-ምንጭ፡- የመርሐቤቴ ወረዳ ኮሙዩኒኬሽን ጽ/ቤት ግንቦት 2015 ዓ.ም

# ምዕራፍ አራት

## የመርሐቤቴ ማህበረሰብ አለባበስና አጊያጊያጥ

የመርሐቤቴ ወረዳ ማህበረሰብ አልባሳት በአካባቢው ሸማኔ ከተሰሩ ሸማዎችና የፋብሪካ ምርት ከሆኑ ብትን ጨርቆች ይዘጋጃሉ። እንዲሁም ጌጣጌጦቹ ከአካባቢው የዕደ ጥበብ ሙያተኞችና ከገበያ የሚገኙ ናቸው። አልባሳትና ጌጣጌጦች የለባሹን ደህንነት ከማስጠበቅና ውበት ከማጉላት በተጨማሪ ፆታን፣ ማንነትን፣ ዕድሜን፣ ጀግነነትን ኃይማኖትን፣ ማህበራዊ ግንኙነትን፣ ማህበራዊ ደረጃንና ሌሎች ጉዳዮችን መሠረት ተደርገው ይዘጋጃሉ። ይህም ሂደት Malinowski (1944) አንድ ማህበረሰብ ፍላጎቱን ለማሟሏት እርስ በርስ የሚተሳሰሩ ወይንም የሚደጋገፉ ተቋማትን የሚፈጥር መሆኑን እንደገለፁት ማህበረሰቡ ፍላጎቱን ለማሟላት ልብስ ሰሪ (ሸማኔ)፣ ልብስ ሰፊ፣ ልብስ አቅራቢ/ነጋዴዎች ጥልፍ ጠላፊ፣ ቆዳ ፋቂ፣ አንጥረኛ፣ ጫማ ሰሪ፣ ነቃሽ (ንቅሳት ሰሪ)፣ ወዘተ ተቋማት ፈጥሯል።

በአጠቃላይ ይህ ክፍል ተጠኚው ማህበረሰብ የሚገለገልባቸውን አልባሳትና ጌጣጌጥ ያላቸው ፋይዳ፣ የእርስ በርስ ግንኙነት ወይም መስተጋብር. የለውጥ ሂደታቸው ምን እንደሚመስል በSchlereth የቁሳዊ ባህል መተንተኛ ሞዴሎች አማካኝነት በምዕራፍ ሁለት ከቀረቡ ንድፈ ሃሳባዊ መነሻዎች ጋር በማመሳከር ትንታኔ የተሰጠበት ነው።

## 4.1 ሀገረሰባዊ አለባበስ

ሀገረሰባዊ ልብሶች በሴትና በወንድ ለየብቻ እንዲሁም በጋራ የሚለበሱ ናቸው። ከእነዚህም ውስጥ ቀሚስ፣ መቀነት፣ አንገት ልብስ፣ የአንገት ጥምጥም ሻርፕ (scarf)፣ ውስጥ ልብስ፣ ሻሽ፣ የፕላስቲክ ጫማዎች (ኮንጎ) በሴቶች ብቻ የሚለበሱ ሲሆኑ ቁምጣ፣ ሱሪ፣ ኮት (ጃኬት)፣ ካኒቴራ (ቲሸርት)፣ ባርኔጣ (ኮፍያ)፣ ኩታ፣ ፎጣ፣ ጥምጣም የሚባሉት ደግሞ በወንዶች የሚለበሱ ናቸው። እንዲሁም ጋቢ፣ ቡልኮ፣ ነጠላ፣ ጥምጣም፣ የጠፍር፣ ጎማ፣ ፕላስቲክ ጫማዎች በጋራ የሚጠቀሟቸው የልብስ ዓይነቶች ናቸው። እነዚህ አልባሳት በአካባቢው ከሚገኙ ጥሬ ዕቃዎችና የመሥሪያ ቁሶች እንዲሁም በገበያ ከሚገኙ ግብዓቶች የሚዘጋጁ/የተዘጋጁ ናቸው።

### 4.1.1. የሴቶች ሀገረሰባዊ ልብሶች

አልባሳቱ እንደሚለበሱበት አጋጣሚ የክትና የሰርክ ተብለው ይጠራሉ። የክት ሲባል ለበዓላት/ለልዩ ዝግጅት የሚለበሱትን ሲሆን የሰርክ ማለት ደግሞ በየቀኑ/ዘወትር የሚለበሱትን ነው። ብዙ ጊዜ የክት ልብሶች በነበራቸው የረጅም ጊዜ አገልግሎት ሲያበቃ

ወደ ሰርክ ልብስነት ይለወጣሉ። በእርግጥ የሰርክ ልብሶች ከመጀመሪያውኑ በአዲስ ሊዘጋጁ ይችላሉ። በጥቅሉ አልባሳቱ በስም፣ በዓይነት፣ በአሰራርና በመለበሻ ወቅት የተለያዩ ናቸው።

### 4.1.1.1. ጉያ ቀሚስ

የተጠኚው ማህበረሰብ አዋቂ ሴቶች/እናቶች በአዘቦትና በበዓላት ቀናት ከሚለብሷቸው አልባሳት መከከል ጉያ/ጉንፍ ቀሚስ አንዱ ነው። ይህ ሀገረሰባዊ ልብስ ከጥጥ ፈትል በአካቢው ሸማኔና ልብስ ሰፊ አማካኝት የሚዘጋጅ ሲሆን በአካባቢው አጠራር "ጉያ" ወይም "ጉንፍ" አንዳንድ ጊዜም "የእናቶች ቀሚስ" ተብሎ ይጠራል። ጉያ/ጉንፍ ቀሚስ ከአንገት እስከ እስከ እግር ጫፍ (በቁርጭምጭሚትና በባት መሀል) ያለውን የሰውነት ክፍል የሚሸፍን ልብስ ነው።

የቀሚሱ እጀታ (እጅ ማስገቢያው) እና ወገቡ ሰፋ ተደርጎ የሚዘጋጅ በመሆኑ ከሌሎች የቀሚስ ዓይነቶች በአሰራሩና በአገልግሎቱ እንዲለይ ያርገዋል። ይህም የባህላዊ ቁሱን ጥበብ ታሪካዊነት የሚያሳይ ነው። ጉያ/ጉንፍ ቀሚስ በአዋቂዎች ተመራጭ የሆነበትን ምክንያት፣ ለስራ ያለውን አመቺነት፣ ሰውነትን ከሙቀትና ቅዝቃዜ ለመከላከል ያለውን ፋይዳ አስመልክቶ ወ/ሮ ሽታ አባቡ ሲያስረዱ፦

> *ጉያ ቀሚስ የአዋቂዎች የደንብ ልብሳችን ነው። ቀሚሱ ቡና ስናፈላ፣ ጥጥ ስንፈትል በእጅጌው በክል ሰፊ ስለሆነ ልጆቻችንን ጡት ለማጥባት ያመቻናል። ደግሞም መቀነታችንን ብቻ በወገብ ታጥቀን ልጅ አዝለን እህል ለመፍጨት፣ እንጀራ ለመጋገር ይቀናል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ እጅጌው ሰፊ ስለሆነ ሲሞቀን ሰብሰብ ሲበርደን በትን (ለቅቅ) እያደረግን ክንዳችንን እናለብስበታለን።* (ቃለ መጠይቅ/ገረን ቀበሌ፣ ነሐሴ 12 ቀን 2013 ዓ.ም)

ከዚህ ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው ልብሱ ውበትን ከማጉላት ይልቅ ስራዎችን ለመስራት ቅደሚያ የሚሰጥ፣ እናትነትን የሚያመላክት መሆኑን ነው። እኔም በቀን 12/12/13 ዓ.ም በገረን ቀበሌ በመስክ ምልከታ ማረጋገጥ እንደቻልኩት የተጠኚው ማህበረሰብ አባል የሆነች ሴት ካላገባች፣ ካልወለደች ወይም ሳታገባምና ሳትወልድ ዕድሜዋ ከፍ ያለ ካልሆነ በቀር ጉያ/ጉንፍ ቀሚስን የማትለብስ መሆኑን ነው። ይህ የአለባበስ ስርዓት በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ስርዓተ መዋቅሩን ያመላክታል። በተጨማሪ ጉያ ቀሚስ የለበሰች ሴት የልጅነት ዘመኗን ጨርሳ ወደ እናትነት እና አዋቂነት ደረጃ የተሸጋገረች መሆኑን ተምሳሌታዊ ትርጉሙ ያስረዳል።

ከቀረበው ሃሳብ መረዳት የሚቻለው ሌላው ጉዳይ ጉያ/ጉንፍ ቀሚስ ውበትን ከማጉላት ይልቅ ለስራ ቅድሚያ የሚሰጥ ነው። ይህም ማለት ወጣቶች በዘመናቸው ማማር መዋብና ማጌጥ የሚፈልጉ ናቸው። ሆኖም ግን ቀሚሱ በአሰራር ዲዛይኑ ሰፊ በመሆኑ የለባሹን

ውበት ለማጉላት የሚያስችል አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር በወጣቶች ለመለበስ ተመራጭ ያላደረገው መሆኑን በቃለ መጠይቅና በመስክ ምልከታ ለማረጋገጥ ችያለሁ፡፡

ሌላኛው የጉያ/ጉንፍ ቀሚስ ፋይዳ ስንመለከት እናቶች በተመሳሳይ ጊዜ ውስጥ ለሚሰሯቸው ተደራራቢ ስራዎች አመቺ ልብስ መሆኑን ነው፡፡ ለምሳሌ አንዲት እናት ቡና እያፈላች በተመሳሳይ ጊዜ ውስጥ ወጥ ብትሰራ ሰፊ ተደርጎ በተዘጋጀው በቀሚሱ ጉያ (በእጅና ጎድን መሀል) በኩል ልጇን ጡት ለማጥባት የሚያገለግል ነው፡፡ በተጨማሪም የቀሚሱ ወገብ ሰፋ ተደርጎ መሰራቱ ወገባቸውን በነጠላ ብቻ በማሰር ልጆቻቸውን በጀርባቸውና በቀሚሱ መሀል በመያዝ/በ እንደ እህል መፍጨት፣ እንጀራ መጋገር፣ ልብስ ማጠብ ወዘተ ያሉ ስራዎችን ለማከናወን የሚያስችል ሀገረሰባዊ የእናቶች ልብስ ነው፡፡

የጉያ ቀሚስ ምንነትን ከትርጉም አንፃር ስንመለከት የኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ፣ ወመዝገበ *ቃላት (1948)* "ጉያ" የሚለውን ቃል *"ጭንና የጭን መካከል የህፃን መሸሻ፣ መደበቂያ*" ሲል ይተረጉመዋል፡፡ እንዲሁም የአቢሲኒያ ድረ ገፅ መዝገበ ቃላት (2024) *"በልብስና በአካል ውስጥ ያለ፣ የማይታይ፣ በጭን መሀል ያለ ሥውር አካል ሁሉ ጉያ ይባላል*" ሲል "*መጎነፍ*" የሚለውን ቃል ደግሞ *"ማጠብ፣ ማጀል፣ መቅረፅ፣ ማልበስ፣ መደጐስ"* በማለት ያብራራል፡፡

ከሁለቱ ትርጓሜዎች መረዳት እንደሚቻለው ጉያ (በእጅና በጎድን መካከል ባለው የሰውነት ክፍል) በኩል ህፃን ልጅ ለመያዝ፣ ለመደበቅ፣ ለመሸፈን፣ ለማሸሽ የሚያስችል ነው፡፡ እንዲሁም መጎነፍ የሚለው ቃል ጉንፍ ከሚለው ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙም ሰውነትን ማልበስ/መሸፈን የሚለውን ተግባር ያመላክታል፡፡

ከዚህ አንፃር ከላይ በቀረበው ትንተና ልብሱ ባለው ተግባርና የአሰራር ዓይነት ይህን ስያሜ ሊያስጠው እንደሚችል ይገመታል፡፡ በቀን 12/12/13 ዓ.ም በገረን ቀበሌ በነበረኝ የመስክ ምልከታ ጉያ ቀሚስ 3 ሜትር ርዝመት 80 ሳ.ሜ ስፋት ነጠላ እስከ 3000 (ሦስት ሺህ) ብር የሚገመት ወጪ ያለው መሆኑን ለማወቅ ችያለሁ፡፡ በማህበረሰብ ወግ መሠረት ሴት ልጅ ጥጥ ፈትላ ምትለብሰው ልብስ በሌሎቹ አካላት ከፍ ያለ ክብር የሚያሰጠው ነው፡፡ ከዚህ አንፃር እናቶች ለልጆቻቸው የዕውቀት ሽግግር የሚያደርጉ መሆኑን፡-

> *ጥጥ መፈልቀቅ፣ ማባዘት፣ መፍተልና መደወር ከእናቶቻችን የተማርነው ሙያ ነው፡፡ እንዳገራችን ሴቶች ሁሉንም ሙያ ማወቅ አለባቸው፡፡ ሙያ የሌላት ሴት ቤተሰብ፤፡ ጎረቤቱም ሌላውም ሰው ይንቋታል፣ ትዳሯም አይረጋ/ባሏ ይፈታታል፡፡ እኛም በልጆቻችን መሳቂያ እንዳሆን ጥጥ ፈትሎ ሸማ መልበስና ሌሎች ከእናቶቻችንና ከጎረቤቶቻችን የተማርናቸውን ሁሉንም ሙያወች ከልጅነታቸው ጀምሮ እናስተምራቸዋለን"*፡፡ (የቡድን 2 ተወያዮች/ በገረን ቀበሌ፡ ግንቦት 01 ቀን 2015 ዓ.ም)

ከዚህ ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው እናቶች ባህላዊ ስርዓቶችን፣ እውቀቶችን፣ እምነቶችን አስተሳሰቦችን፣ እሴቶችን ወዘተ ጠብቀው ለተተኪው ትውልድ ያላቸውን የተስተላልፎ ደረጃ ከፍተኛ መሆኑን ነው፡፡ ይህም ሃሳብ Parsons (1937) አንድ ማህበረሰብ ህልውናውን ለማስቀጠል አራት መሰረታዊ ግዳጆች ማለትም ማላመድ (Adaptation)፣ ግቦችን መለየት (Goal Attainment)፤ ቅንጅት (Integration)፤እና ማቆየት/መጠበቅ (Latency) ሲሉ ከገለፁት ሃሳብ ጋር ይመሳከራል፡፡

በጥቅሉ ጉያ/ጉንፍ ቀሚስ የለባሹን ማንነት የሚያሳወቅ፣ ውበት ከማጉላት ይልቅ በተመሳሳይ ጊዜ ውስጥ ተደራራቢ ስራዎችን ለማከናወን ታስቦ የሚሰራ፣ እንደ አየሩ ንብረት ሁኔታ ሰውነትን ከሙቀትና ከቅዝቃዜ መከላከል/መጠበቅ የሚያስችል፣ የማህበረሰቡን ስርዓተ መዋቅር የሚያመላክት፣ አንዲት ሴት ልጅ ካላገባች፣ ካልወለደች ወይም ሳታገባ ዕድሜዋ ከፍ ያለ ካልሆነ በቀር ቀሚሱን የማትለብስ መሆኑን፣እናትነትን ለማሳየት ተምሳሌታዊ ትርጉም ያለው፣ ስርዓቱን ጠብቆ ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ የቆየ፣ በአሰራሩ ጥበባዊ ታሪክነት ያለው በበዓላትና በአዘቦት ቀናት የሚለበስ ሀገረሰባዊ የእናቶች ልብስ መሆኑን የጥናቱ ግኝት ያመላክታል፡፡

**ፎቶ 1. የጉያ/ ጉንፍ ቀሚስ አለባበስ**





**ምንጭ፡- በ26/04/14 ዓ.ም ዓለም ከተማ በአጥኚው የተወሰደ**

## 4.1.1.2. እጀ ጠባብ ቀሚስ

እጀ ጠባብ ቀሚስ እንደ ጉያ ቀሚስ ከጥጥ ፈትል በሸማኔ የሚዘጋጅ የሴቶች ሀገረሰባዊ ልብስ ሲሆን እናቶች በተወሰነ ደረጃ ወጣቶች ደግሞ በስፋት በክብረ በዓላት፣ በልዩ ልዩ ዝግጅቶችና አዘቦት ቀናት የሚለበስ ነው፡፡ ቀሚሱ ከእጀታው በኩል ሰብሰብ/ጠበብ ተደርጎ ከሰውነት ቅርጽ ጋር ልከኛ/ተስማሚ ተደርጎ መዘጋጀቱና በልዩ ልዩ ጌጣጌጦች የሚዋብ መሆኑ የለባሹን ውበት የሚያጎላ የሴቶች ልብስ ነው፡፡ ይህ ቀሚስ በማህበረሰቡ ያሉ ወጣትና አዋቂዎች ተዘውትሮ የሚለበስ ቢሆንም በወጣቶች በስፋት የሚለብሱት እንደሆነ ነዋሪዎች ሲገልፁ፡-

> *እጀ ጠባብ ቀሚስ ከጉያ ቀሚስ ጠበብ ያለ ነው፡፡ እኛ አዋቂዎች ይህን ቀሚስ ብዙም አንለብሰውም፡፡ ወጣቶቹ ግን ሰውነታቸውን ስለሚስገምትላቸው ወይም ስለሚያሳምርላቸው በሰርክና፣ በክብሮም (ክብረ በዓል) ቀን ሁሉ ይለብሱታል፡፡ በአንገቱ፣ በእጅጌው፣ በወገቡና በቁመቱ በኩል ሳይሰፋና ሳይጠብ በልካቸው መሰራቱ ቀልጠፍ (ኮስተር) እንዲሉ ያደርጋቸዋል፡፡* (የቡድን ሁለት ተወያዮች/ ገረን ቀበሌ፡ ግንቦት 01 ቀን 2015 ዓ.ም)፡፡

ከቀረበው ቃለ መጠይቅና በቀን 01/06/15 ዓ.ም በገረን ቀበሌ በመስክ ምልከታ ባረጋገጥኩት መሰረት እጀ ጠባብ ቀሚስ በህፃናትና በዕድሜ የገፉ እናቶች የማይለበስ ልብስ መሆኑን ነው፡፡ ይህም ከፆታ በተጨማሪ ዕድሜን መሰረት ተደርጎ የሚለበስ ሀገረሰባዊ ልበስ መሆኑን መረዳት ያስችላል፡፡ እንዲሁም ከአሰራርና አገልግሎቱ አኳያ ስንመለከት በወጣቶችና በአዋቂዎች ያለው የቀሚሱ አሰራር የሚለያይ መሆኑን ነው፡፡ ይኸውም የወጣቶቹ ቀሚስ ውበትን በሚያጎላ መልኩ የተለያየ ቀለም ካላቸው የጥለት /ክርና ሻማ ጨርቆች ጌጥ የሚሰራ ሲሆን የአዋቂዎቹ ደግሞ ትንሽ ጌጥ ወይም ምንም ጌጥ የሌለው ተደርጎ ይዘጋጃል፡፡

የጌጣጌጡን ተምሳሌታዊ ትርጉም ስንመለከት በወጣቶች ቀሚስ ላይ የሚደረጉ ጌጣጌጦች የለባሾቹ ውበት እንደ አበባ ያማረ፣ የፈካና የደመቀ እንዲሁም ዕድሜያቸው ገና መሆኑን የሚያመላክት ሲሆን ጌጥ የሌለው የአዋቂዎቹ ቀሚስ ደግሞ የወጣትነት ዘመናቸውን ጨርሰው ከውጫዊ ውበት ይልቅ ለውስጣዊ ትኩረት ሰጥተው እየኖሩ መሆኑን በተለይም እናቶች ከዓለማዊ ሕይወት ይልቅ ለመንፈሳዊ ዓለም ያደሉ ወይም ትኩረት ስለመስጠታቸው የሚያሳይ ነው፡፡ ወ/ሮ ብዙጌጥ ግዛው *"የወጣቶቹና የአዋቂዎቹ ቀሚስ በጌጡ የተለያየ ነው፡፡ የወጣቶቹ ቀሚስ ከኋላው በኩል ከቀሚሱ ጫፍ፣ በአንገቱ፣ በደረቱና በእጀታው ላይ የሻማ ጨርቅና የጥለት ጥልፍና አዝራር ያደርጉበታል" ይላሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ዘይታ ቀበሌ/ ጥር ሚያዚያ 10 ቀን 2015 ዓ.ም)፡፡*

እዚህ ላይ በወጣቶቹ የሚለበሰው ቀሚስ በጥልፍ ያሸበረቀ መሆኑ ከትርጉም አኳያ የአለቃ ደስታ ተክለ ወልድ "ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት" ቀሚስን "በሐር የተጠለፈ፣ የተዘመዘመውን ጥልፍ ቀሚስ" ተብሎ ከሰጠው ብያኔ ጋር የሚስማማ ነው። ከታሪካዊነት አኳያ ስንመለከተው ደግሞ ይህ ቀሚስ ዘመናዊ የልብስ ማምረቻ መሳሪያ ከመግባቱ በፊት ጀምሮ በአካባቢው ከሚገኝ ጥሬ ዕቃና የመሥሪያ ቁስ እየተሰራ አሁን ድረስ አገልግሎት መስጠቱ መቻሉ የቁሱን ፋይዳዊነት (functionalist) እና ማህበረሰባዊ ታሪካዊነት (Social Historical) እንዲሁም በቁሱ ላይ ለውጥ አለመከሰቱን የሚያሳይ ነው።

በጥቅሉ እጅ ጠባብ ቀሚስ የለባሹን ደህንነት ለማስጠበቅ፣ ማንነትን ለማመላከት፣ ውበትን ለማጉላት የሚያገለግልና ዕድሜን መሰረት ተደርጎ የሚለበስ እንዲሁም በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ስርዓት መዋቅር የሚያሳይ ልብስ መሆኑን የጥናቱ ግኝት ያመላክታል። በተጨማሪም እጅ ጠባብ ቀሚስ አንድ ሜትር ከሰባ ቁመት ለሚኖራ ሴት ሦስት ሜትር ርዝመትና 80 ሳንቲ ሜትር ስፋት ካለው ነጠላ የሚሰራ ሲሆን እስከ 3000 (ሦስት ሺህ) ብር አጠቃላይ ዋጋ ያለው መሆኑን በወቅቱ በነበረኝ የመስክ ምልከታ ለማወቅ ችያለሁ።

**ፎቶ 2. የወጣቶችና አዋቂዎች እጀ ጠባብ ቀሚስ አለባበስ**

በእጀታውና በደረቱ ላይ ጌጥ ያለው የወጣቶች እጀ ጠባብ ቀሚስ



በእጀታው ላይ ጌጥ የሌለው የአዋቂዎች እጅ ጠባብ ቀሚስ



ምንጭ፡- በ12/12/12 ዓ.ም ገረን ቀበሌ እና በ10/05/15 ዓ.ም ግሬት በአጥኚው የተወሰደ

### 4.1.1.3. አርባሸንሸን ቀሚስ

ይህ የሴቶች ቀሚስ በክብረ በዓላትና በአዘቦት ቀናት የሚለብስ ሲሆን የፋብሪካ ምርት ከሆኑ ልዩ ልዩ ብትን (ዐርበ ወጥ) ጨርቆች በአካባቢው ልብስ ሰፊዎች የሚዘጋጅ ነው፡፡ ወ/ሮ ፀሐይ ሽናውለው *"አርባ ሽንሽን ቀሚስ ከወገብ እስከ እግር ጫፍ ድረስ ያለውን ልብስ እንዲሸበሽብ/እንዲሰበሰብ ተደርጎ ስለሚሰፋ ነው"* በማለት የልብሱን አሰራርና ስያሜ ያብራራሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ/ልብስ ሰፊ/ዘይታ ቀበሌ፡ ሚያዚያ 10 ቀን 2015 ዓ.ም)፡፡ ይህ ቀሚስ ጥንት ያልነበረ አሁን ላይ ግን ሁሉም የማህበረሰቡ ሴቶች በስፋት የሚለብሱት መሆኑን ወ/ሮ ጉርዶ ባህሩ *"አርባ ሽንሽን ቀሚስ ሁሉም ሴቶች ከገበያ እየተገዛ ይለብሱታል፡፡ የትላልቆቹ/አዋቂዎቹ ልብስ ጌጥ የለውም፡፡ ልጆቹና ወጣቶቹ ሽማቸው ላይ አቀብ ቁልቁል፣ አግድም እያደረጉ በጥለት፣ አዝራር ጌጥ ያበጁበታል"* ይላሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ/ዘይታ ቀበሌ፡ ሚያዚያ 10 ቀን 2015 ዓ.ም)፡፡ በተጨማሪም አቶ ዮናስ አንጓሌ *"በፋብሪካ የሚመረቱት ብትን ጨርቆች የተለያዩ ቀለም ያላቸው፣ ረጅም ዓመት የሚያገለግሉ፣ ለሰላሳና ጠንካራ ናቸው፡፡ የጥጥ ጨርቅ ደግሞ ሲለበሱ ከባድ፣ ዕድሜያቸውም አጭር ነው" በማለት በለባሹ ተመራጭ የሆኑበትን ምክንያት ያብራራሉ፡፡* (ቃለ መጠይቅ/ልብስ ሰፊ/ገረን ቀበሌ፡ ነሐሴ 12 ቀን 2013 ዓ.ም)፡፡

ከሦስቱ መረጃ ሰጪዎች መረዳት እንደሚቻለው ከስያሜ አንፃር ቀሚሱ ካለው የአሰራር ቅጥ (design) መሰረት የተሰጠው መሆኑን፣ ከታሪካዊነቱ አኳያ ደግሞ ዘመናዊ የልብስ ማምረቻ ፋብሪካ ምርቶች ከመጡ በኋላ መለበስ መጀመሩን፣ ከሚሰራበት ጨርቅ ጥራትና ጥንካሬ አኳያ ደግሞ ረጅም አገልግሎትና ምቾት የሚሰጥ መሆኑን እንዲሁም በሁሉም አጋጣሚዎችና የዕድሜ ደረጃ ባሉ ሰዎች በስፋት ተዘውትሮ የሚለበስ ሀገረሰባዊ የሴቶች ልብስ መሆኑን ነው፡፡ በአማካይ አንድ ሜትር ከ70 ሳንቲ ሜትር ቁመት ለሚኖራት ሴት አምስት ክንድ (ሁለት ሜትር ተኩል) ብትን ጨርቅና የማሰፊያ ዋጋውን ጨምሮ 3000 ብር የሚያስፈልግ መሆኑን በ10/08/15 ዓ.ም በዘይታ ቀበሌ በነበረኝ የመስክ ምልከታ ወቅት ማወቅ ችያለሁ፡፡

የቀሚሱ ነጫጭ አዝራሮቹ ተምሳሌታዊ (Symbolic) ትርጉሙን ስንመለከት እንደ ጨረቃ መድመቅን እንደ ከዋክብት መብዛትን እንዲሁም በልብሱ ላይ የሚኖረው የመስቀል ጌጥ ደግሞ ለባሹን ኃይማኖት ይገልፃል፡፡ አቶ ሰለሞን ምታው *"በአንድ ልብስ ላይ ብዙ አዝራር አድርጎ ማጌጥ ባገራችን አልነበረም፡፡ በግምት ከ20 ዓመት ወዲህ የመጣ ጌጥ ነው፡፡ አሁን ላይ ሁላችንም በብዛት የምንጠቀመው የባህላችን መገለጫ አድርገነዋል"* ይላሉ፡፡ (ቃለ

መጠይቅ/ዓለምከተማ፡ ሚያዚያ 15 ቀን 2015 ዓ.ም)፡፡

ከዚህ አንፃር በልብሱ ላይ የሚስተዋለው የአዝራር ጌጥ አጠቃቀም በሂደት እየተለመደ መጥቶ የባህሉ ባለቤት እንዲሆን ያደረገው መሆኑን Shove and Pantzar (2007) አንድን ነገር በተደጋጋሚ ከተከወነ ልምድ እየሆነና ተቀባይነቱ እየጨመረ እንደሚመጣና የመቀጠል ዕድሉ ሰፊ ነው ሲሉ ከገለፁት ጋር የሚስማማ ነው፡፡

**ፎቶ 3. በተለያዩ የዕድሜ ክልል የአርባ ሽንሽን ቀሚስ አለባበስ**




**ምንጭ፡- የመጀመሪያው ከወረዳው ባ/ቱ ጽ/ቤት በ26/04/14 ዓ.ም የተወሰደ፣ 2ኛው በ27/04/14 ዓ.ም ዓለም ከተማ 3ኛው በ10/05/15 ዓ.ም ግሬት ቀበሌ በአጥኚው የተወሰዱ**

## 4.1.1.4. መቀነት

መቀነት ከጥጥ ፈትል በሸማኔ ተሰርቶ በሴቶች ወገብ ላይ የሚታሰር ሀገረሰባዊ የልብስ ዓይነት ነው፡፡ ከትርጉም አንፃር ስንመለከት የአቢሲኒያ ድረ ገፅ መዝገበ ቃላት (2024) “መቀነት” ለሚለው ቃል “መጠምጠም መታጠቅ” በማለት የሚተረጉመው በመሆኑ መቀነት ስያሜውን ከዚህ ሊያገኝ እንደሚችል ይታመናል፡፡ በ14/01/14 ዓ.ም በጎረንዳ ቀበሌ በምልከታ ምልከታ ለማረጋገጥ እንደቻልኩት በተጠኚው ማህበረሰብ የአለባበስ ስርዓት መሰረት ያገቡ ሴቶች ወገባቸውን መቀነት የሚያስሩ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ቁሱ በማን ለምን እንደተሰራ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን መዋቅራዊነት (Structuralist) የሚያስገነዝብ ነው፡፡ መቀነት ያገቡ ሴቶችን ከመግለፁ በተጨማሪ የሴቶቹን ውበት ለማጉላት፣ ቀሚስን ሰብስቦ ለማሰር፣ ወገብ ለመደገፍ፣ ሣንቲሞችንና የብር ኖቶችን ለመያዣነት የሚያስችል መሆኑ የቁሱን ፋይዳዊነት (functionalist) የሚያሳይ ነው፡፡

በተጨማሪም "እናቴ ከመቀነቷ ፈልቅቃ ሰጠችኝ" የሚባለው የአበው አባባል መቀነት ሣንቲም ለማስቀመጥ የሚያገልግል ልብስ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ እንደ ወ/ሪት እሸቴነሽ ደርሶ ገለፃ *"እንደለባሹ የሰውነት መጠን የሚለያይ ቢሆንም የአዋቂዎች መቀነት በአማካይ 7 ክንድ (3 ሜትር ተኩል) ከ80 ሳ.ሜ ስፋትና ርዝመትና 700 ብር ዋጋ አለው፡፡ ይህም የሴቶቹን ወገብ 3 ዙር እንዲሆን ታስቦ የሚሰራ ነው"* (ቃለ መጠይቅ/ሸማኔ/ገረን ቀበሌ፡ ነሐሴ 12 ቀን 2013 ዓ.ም)፡፡

የመቀነትን ተምሳሌታዊ ትርጉሙ ስንመለከት ቀስተ ደመና ወይም የማሪያም መቀነት ሰማዩን በክብ ቅርፅ ዞሮ እንዳቀፈው ሁሉ መቀነትም የሴቶችን ወገብ አቅፎና ደግፎ የሚይዝ መሆኑን ለማመላከት እንዲሁም "ወገብን ጠበቅ" እንደሚሉት አበው ያገቡ ሴቶች ወገባቸውን መቀነት የሚያስሩበት ምክንያት በስነ ልቦናዊም ሆነ አካላዊ ጥንካሬን ይዘው ትዳራቸውን እንዲመሩ ለመምከርና ለማበርታት፣ ከትዳር አጋራቸው ጋር የቃል ኪዳን ትስስር የገቡ መሆኑን ሊያሳይ ይችላል፡፡

ሌላው መቀነት ወገብን ሦስት ጊዜ እንዲዞር ተደርጎ መሰራቱ በለባሹ እምነት መሰረት ታቦት ማደሪያውን 3 (ሦስት) ጊዜ ከሚዞረው ጋር የሚመሳሰል ተምሳሌታዊ ትርጉም አለው፡፡ በአካባቢው ሸማኔዎች እየተዘጋጀ ለተጠቃሚው/ለባሹ ማህበረሰብ አገልግሎት የሚሰጠው ይህ ቁሱ የተለያዩ ስሞች ያሉት መሆኑን ወ/ሪት እሸቴነሽ ደርሶ ሲገልፁ *"መቀነቱ በሚሰራበት የጥለት ዓይነትና ዲዛይ መሰረት ትፍትፍ፣ ዘንባባ፣ ራያ፣ ዶርዜ፣ አቋራጭ፣ ንቅስ፣ ቆቅማ ወዘተ የሚባሉ ስሞች አላቸው"* (ቃለ መጠይቅ/ሸማኔ/ገረን ቀበሌ፡ ነሐሴ 12 ቀን 2013 ዓ.ም)፡፡ ይህን ሀገረሰባዊ ልብስ ሴት ልጅ በሰርግ ጊዜ በጥሎሽ ከሚሰጣት ልብስ መሆኑና ያገቡ ሴቶችን ለማመላከት እንደሚረዳ አቶ አማረ ንጉስ ሲገልፁ *"መቀነት የሚታጠቁት ያገቡ ሴቶች ናቸው፡፡ ነገር ግን ያላገባች ሆና ዕድሜዋ ከፍ ያለች ሴት መቀነት መልበስ ብትፈልግ እንኳን የመቀነቱ የጥለት ጫፍ ሳይንዘረፈፍ ወይም እንዳይታይ ወደ ጉያዋ ትወሽቀዋለች (ታስገባዋለች)፡፡"* (ቃለ መጠይቅ/ጎራንዳ ቀበሌ፡ መስከረም 14 ቀን 2014 ዓ.ም)፡፡ ይህም ያላገቡ ሴቶች ካገቡ ሴቶች የሚለዩበት የራሱ የሆነ የመቀነት አስተሳሰር (አለባበስ ስርዓት) እንዳላቸው የሚያስገነዝብ ነው፡፡

በማህበረሰቡ ወግና ሥርዓት መሠረት ይህ የአለባበስ ስርዓት ያገቡ ሴቶች የሚለብሱት ልብስ እንደሆነ ከመረጃ ሰጪዎቹ ሃሳብ መረዳት ይቻላል፡፡ ነገር ግን በ14/01/14 ዓ.ም በጎራንዳ ቀበሌ የመስክ ምልከታ ባደረግሁበት ወቅት ይህን ሀገረሰባዊ ልብስ አንዳንድ ያላገቡ ሴቶች ሲለብሱት ተመልክቻለሁ፡፡ ይህም በማህበረሰቡ የአለባበስ ስርዓቱ ላይ ለውጥ መከሰቱን ያሳያል፡፡

ፎቶ 4. መቀነትና አንገት ልብስ ባላገቡና ባላገቡ ሴቶች




**ምንጭ፡- የመጀመሪያው ፎቶ በ14/01/14 ዓ.ም ጎራንዳ ቀበሌ እና ሁለቱ ፎቶዎች በ12/12/13 ዓ.ም ገረን ቀበሌ በአጥኚው የተወሰዱ**

## 4.1.1.5. አንገት ልብስ

አንገት ልብስ ከጥጥ ፈትል በአካባቢው ሸማኔ የሚሰራና ያገቡ ሴቶች በአዘቦት ቀናት የሚለብሱት የክብር ልብስ ነው፡፡ የአንገት ልብስ ምንነትን የአካባቢው ነዋሪዎች ሲገልፁ፡-

> *አንገት ልብስ ያገቡ ሴቶች ብቻ የሚለብሱት ነበር፡፡ አሁን ላይ ግን ያላገቡ ሴቶችም መልበስ ጀምረዋል፡፡ አንገት ልብስ የክብር ልብስ ነው፡፡ ደግሞም ቡና ስናፈላ ከትከሻችን ላይ ደረብ እናደርገዋለን፡፡ ወደ ጎረቤት ወይም ራቅ ወዳለ ቦታ ስንሄድም አንገት ልብሳችንን ለብሰን ነው፡፡ እንዲሁም ልጅና እቃን ለማዘል አካላችንን ለማልበስ ይጠቅማል፡፡* (የቡድን ሁለት ተወያዮች በገረን ቀበሌ፡ ግንቦት 01 ቀን 2015 ዓ.ም)

በተጨማሪም ወ/ሮ አስቴር አንዳርጋቸው *"አንገት ልብስ ያገቡ ሴቶች የሚለብሱት ልብስ ነው፡፡ ስታገባ አንዱ የጥሎሽ ዕቃ ሆኖ ይቀርባል"* ይላሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ/የመ/ወ/ባ/ቱ ጽ/ቤት ኃላፊ/ዓለምከተማ፡ ታህሳስ 27 ቀን 2014 ዓ.ም)፡፡ ከሁለቱ መረጃ ሰጪዎቼ ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው ይህ ሀገረሰባዊ ልብስ ያገቡ ሴቶችን ለማመላከት፣ ሰውነት ለመሸፈን፣ የአካል ደህነነትን ለመጠበቅ፣ በጀርባ የሚያዙ ነገሮችን ለማዘል፣ እንደ መቀነት ወገብን ለማሰር ወይም ለማሸረጥ የሚያገለግል መሆኑን ነው፡፡ ይህም ቁሱ ለማህበረሰቡ ለውን ፋይዳዊነት (functionalist) የሚያሳይ ነው፡፡

አንገት ልብስ እንደሚሰራበት የጥለት፣ የማግና የድር ዓይነት የተለያዩ የአንገት ልብስ ዓይነቶች መኖራቸውን ወ/ሪት እሸቴነሽ ደርሶ ሲገልፁ *"እንደ ማግ ዓይነትና የጥለት አሰራር አቋራጭ፣ ዘንባባ፣ ራያ፣ ዶርዜ፣ መጠብር፣ ወፍራም ወይም ስስ የአንገት ልብስ ዓይነቶች ይሰራሉ። አንድ አንገት ልብስ 2 ሜትር ተኩል ርዝመትና 80 ሳ.ሜ ስፋት ያለው ሲሆን እስከ 500 ብር ወጪ ይኖረዋል"።* (ቃለመጠይቅ/ሸማኔ/ገረን፡ ነሐሴ 12 ቀን 2013 ዓ.ም)።

በተጨማሪም ይህን ልብስ የተጠኚው ማህበረሰብ አንዳንድ አካባቢዎች ለሀብት መገለጫነት ይጠቀሙበታል። እንደ አቶ አባቢ ሙላቱ ገለፃ *"ብዙ ጥገት (የሚታለቡ ላሞች) ያሏቸው ባለጠጋ ሴቶች ነጩ አዲስ አንገት ልብስ ቅቤ ቀብተው ያጠቁሩታል። ሽታ እንዳይኖረው ደግሞ ሱዳን ሽቶ፣ አደስ፣ አርቲ፣ እንጁባን የሚባሉ ሽታ ያላቸውን ቅጠሎች ያረጉበታል።"* (ቃለ መጠይቅ/ጎራንዳ ቀበሌ፡ መስከረም 14 ቀን 2014 ዓ.ም)። እዚህ ላይ በተጠኚው ማህበረሰብ ቆላማ በሆኑ አካባቢዎች (ጎራንዳ፣ ማሪያም ሰርቃ፣ጎንዴ፣ ገብሮ) የሚኖሩ የማህበረሰቡ አባላት አንገት ልብስን ቅቤ ቀብተው መልበሳቸው ቁሱ ማህበራዊ ደረጃን የሚያሳይ ነው።

ይሁንና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ያላገቡ ሴቶች አንገት ልብስ ሲለብሱ መታየቱ ያገቡት ደግሞ እንደ ሻርፕ (scarf)፣ ፎጣ የመሳሰሉ የፋብሪካ ምርቶችን ማዘውተራቸው በቁሱና አለባበስ ስርዓቱ ላይ ለውጥ መከሰቱን ያስገነዝባል። ይህን ሃሳብ ወ/ሮ ሕይወት ታደሰ ገለፃ *"ያላገቡ ሴቶች አንገት ልብስን ያላገቡ ደግሞ እንደ ሻርፕ መልበስ ጀምረዋል ይህም ግሎባላይዜሽን በአለባበስ ስርዓቱ ላይ የፈጠረውን ተፅዕኖ ያሳያል።"* (ቃለ መጠይቅ/የመ/ወ/ባ/ቱጽቤት ባለሙያ/ዓለም ከተማ፡ ታህሳስ 27 ቀን 2014 ዓ.ም)። ይህም Rosenberg (1987) የባህል ለውጥን ከሚያፋጥኑ ነገሮች አንዱና ዋነኛው ቴክኖሎጂ ሲሉ ከገለፁት ሃሳብ ጋር የሚዛመድ ነው። የለውጡ ምክንያት ደግሞ የዘመነ ሉላዊነት ተፅዕኖና ማህበረሰቡ ለመለወጥ ያለው ፍላጎት ከፍተኛ መሆኑን በሸማኔ አሰርቶ ከመልበስ ይልቅ የፋብሪካ ምርት የሆኑትን ሻርፖችን ከገበያ ገዝተው ሲለብሱ በ5ቱም ቀበሌዎች ተመልክቻለሁ።

በጥቅሉ አንገት ልብስ ያገባች ሴቶችን ከማሳየቱ በተጨማሪ ከላይ በትንተናው እንደቀረበው አንገት ልብስ የአካል ደህንነትን ለመጠበቅና የተለያዩ ስራዎችን ለማከናወን የሚያስችል ነው። እንዲሁም ያገቡ ሴቶችን ማመላከቱ የማህበረሰቡ አባላት ከአንደኛው መዋቅር ወደሌላኛው መዋቅር ሲሸጋገሩ የሚያመላክት ነው። ይህ ሂደትም ቁሱ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን መዋቅርና ተግባር የሚያሳይ መሆኑን የጥናቱ ግኝት ያመለክታል።

### 4.1.1.6. ሻሽ

በሴቶች ራስ ላይ የሚታሰረው ይህ ሀገረሰባዊ ልብስ ከህፃን እስከ አዋቂ ያሉ ያገቡና ያላገቡ ሴቶች ይገለገሉበታል፡፡ ከአገልግሎቱ አንፃር ስንመለከት ህፃናትና ወጣቶቹ በዋናነት ውበትን ለማጉላት እናቶች ደግሞ ሰውነትን ከሙቀትና ከቅዝቃዜ ለመሸፈን ይገለገሉበታል፡፡ ወ/ሮ ገበያነሽ ሽትዬ ሲያስረዱ *"ሻሽን ያገቡና ያላገቡ ሴቶች ያስሩታል፡፡ ሹርባ የተሰራች ሴት የሹርባዋ ነዶ (የፀጉሩ ርዝመት) እንዲታይ አድርገው ያስሩታል፡፡ የተላጨ ወየም ሹርባ ያልተሰሩት ደግሞ ፀጉራቸው ሙሉ ለሙሉ እንዳይታይ አድርገው ያስሩታል፡፡"* (ቃለ መጠይቅ/ ጎራንዳ ቀበሌ፡ ጥር 10 ቀን 2014 ዓ.ም)፡፡ ከዚህ ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው ሻሽን ልጅ አዋቂ፣ ያገባ ያላገባ ሳይል ሁሉም የተጠኚው ማህበረሰብ ሴቶች የሚገለገሉበት መሆኑን ነው፡፡ በተጨማሪም ይህን ሀገረሰባዊ ልብስ አዋቂዎች ራስ የማዞር ህመምን ለመከላከል ሲሉ የሚያስሩት መሆኑን በሁሉም ቀበሌዎች የሚኖሩ እናቶችን በነበረኝ የመስክ ምልከታ ጊዜ ከጠይቅኳቸው እናቶች ምላሽ ተረድቻለሁ፡፡

ሌላው በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ የሻይ ዓይነቶች ዓለማዊና መንፈሳዊ ተብለው በሁለት የሚከፈሉ መሆኑን ወ/ሮ አበበች ከስክስ ሲገልፁ *"ተማሪዎቹ ካልሆኑ በቀር ሁሉም ሴት ከነጩ ሻሽ ውጭ ያለውን፣ የቆረቡ አዋቂዎች (ስጋ ወደሙን የተቀበሉ) ደግሞ ነጭ ሻሽ ያስራሉ፡፡"* (ቃለመጠይቅ/ኮራ ወንጪት ቀበሌ፡ መስከረም 21 ቀን 2014 ዓ.ም)፡፡ ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው ከጥጥ ፈትል የሚሰራውና በቀለም ነጭ የሆነው ሻሽ ለመንፈሳዊ ተግባር በፋብሪካ የሚመረቱና የተለያየ ቀለም ያላቸውን ደግሞ ለዓለማዊ አገልግሎት (መዋቢያ) ሲጠቀሙበት ይስተዋላል፡፡ የሻሽ ዓይነቱ የሚለያይ ሆኖ ረጅም የሚባለው 2 ሜትር ተኩል ርዝመት ያለው መሆኑን በቀን 27/04/14 ዓ.ም በዓለም ከተማ ገበያ ስፍራ ተጉዤ ለማረጋገጥ ችያለሁ፡፡

ተምሳሌታዊ ትርጉሙን ስንመለከት የጥቁር ሻሽ ትርጉም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ በነበረበት ጊዜ በራሱ ላይ የተደረገውን የእሾህ አክሊሉ ስቃይ ሀዘን ለመግለፅ ነው፡፡ ነጭ ሻሽ ደግሞ እንደ ማህበረሰብ እምነት አስተምህሮ በኦርዶቶክሳዊ ቅዱሳት ሥዕላት (፸፬) "ነጭ ቀለም ልብን ፈፅሞ ከሃጢያት ማጥራት" ሲል እንደገለፀው ልብን ንፁህ አድርጎ በመንፈሳዊ ህይወት ጸንቶ ለመቆየት ያለውን ሂደት የሚገልፅ ነው፡፡ እንዲሁም ወ/ሮ ተካበ አበበ *"ከብርድና ጣይ ይከላከላል፡፡ ራሳችንን ሲያመን እናስርበታለን፡፡ ፀጉራችንን እንሸፍንበታለን"* ሲሉ አገልግሎቱን ይገልፃሉ፡፡" (ቃለመጠይቅ/ኮራ ወንጪት ቀበሌ፡ መስከረም 21 ቀን 2014 ዓ.ም)፡፡ በጥቅሉ ሻሽ የለባሹን ሃይማኖት፣ ማንነት፣ ዕድሜን የሚያመላክት ሲሆን የአካል ደህንነትና ውበትን ለመጠበቅ፣ ገመናን ለመሸፈን የሚያገለግል

ሀገረሰባዊ ልብስ ነው፡፡ ይህ ልብስ  ዘመናዊ የልብስ ማምረቻ መሳሪያ ከመግባቱ በፊት ከጥጥ ፈትል የሚሰራ ጨርቅን ይጠቀሙበት እንደነበር ይገመታል፡፡

### ፎቶ 5. ሻሽ አስተሳሰር

የህፃናት ሻሽ አስተሳሳር



ያላገቡ ወጣቶች ሻሽ አስተሳሳር



የቆረቡ እናቶች ሻሽ አስተሳሳር



ሁለቱ ፎቶዎች በ14/01/14 ዓ.ም ጎራንዳ ቀበሌ

በ10/05/15 ዓ.ም ዘይታ ቀበሌ

ያገቡ ወጣቶች ሻሽ አስተሳሳር



በ10/05/15 ዓ.ም ግሬት ቀበሌ



በ26/04/14 ዓ.ም ዓለምከተማ

ምንጭ፡- በአጥኚው የተወሰዱ ፎቶዎች

### 4.1.1.7 የውስጥ ልብስ

የውስጥ ልብስ ከስሙ መረዳት እንደሚቻለው በሚታይ ልብስና በገላ መሃል ከህፃናት እስከ አዋቂ ያሉ ሴቶች የሚለብሱት የልብስ ዓይነት ሲሆን የፋብሪካ ምርት ከሆኑት ሳተን፣ ሻማ ወዘተ ከሚባሉ የጨርቅ ዓይነቶች የሚዘጋጅ ነው፡፡

ይህ የሴቶች ልብስ ከጥንት ያልነበረ፣ ነገር ግን በጊዜ ሂደት ውስጥ እየተተገበረ የመጣና በአሁኑ ጊዜም ሁሉም የማህበረሰቡ አባላት ሰርክ የሚለበስ ልብስ መሆኑን የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚከተለው ያብራራሉ፡-

> *ጨርቁን የምንገዛው ከገበያ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ስቅሉን እየገዛን አብዛኛውን ጊዜ ደግሞ በሙያተኛ (በልብስ ሰፊ) እናሰፋዋለን፡፡ ሸማው ወደ አገራችን ከመጣ 30 ዓመት ቢሞላው ነው፡፡ በፊት ለሃብታም የተዳረች ሙሽራ ብቻ ትለብስ ነበር፣ አሁን ግን በሁሉም የዕድሜ ደረጃ ያሉ ሴቶች ይለብሳሉ፡፡* (የቡድን አንድ ተወያዮች ጎራንዳ ቀበሌ፡ መስከረም 15 ቀን 2014 ዓ.ም)

Kaiser (1990) አልባሳት እንደአጠቃቀማቸው አራት ዓይነት ተግባር አላቸው ሲሉ ከጠቀሷቸው ውስጥ የለባሽን ምቾት መጠበቁ ልከኝነትን (modesty)፣ ውበትን ማጉላቱ ማጌጥን (adornment)፣ የአካል ደህንነት መጠበቁ መከላከልን (protective) ተግባር አላቸው፡፡ እንዲሁም የሀብት ደረጃን ለማሳየት የሚውል ልብስ ሲሆን አንድ ሜትር ከሰባ ሳ. ሜ. ቁመት ለሚኖራት ሴት ሁለት ሜትር ብትን ጨርቅ የሚያስፈልግ ሲሆን ከማሰፊያው 300 ብር ዋጋ ያለው መሆኑን በ15/01/14 ዓ.ም ጎራንዳ ቀበሌ በምልከታ አረጋግጫለሁ፡፡

**ፎቶ 6. በተለያዩ ዕድሜ ክልል ውስጥ ልብስ ሲለበስ**




**በ21/01/14 ዓ.ም ኮራ ቀበሌ** **በ25/04/14 ዓ.ም ዓለም ከተማ** **በ01/09/15 ዓ.ም ገረን ቀበሌ**

**ምንጭ፡- በአጥኚው የወሰዱ**

## 4.1.2. የወንዶች ሀገረሰባዊ ልብሶች

የተጠኚው ማህበረሰብ ወንዶች አልባሳት እንደሴቶቹ አልባሳት እንደሚለበሱበት አጋጣሚ የክትና የሰርክ ተብለው ይጠራሉ፡፡ አልባሳቱ ከጥጥ ፈትል፣ ከፋብሪካ ብትን ጨርቆች፣ ከጥለት/ ዘሃ ክር ወዘተ የሚሰሩ ሲሆን በስም፣ በዓይነት፣ በአሰራርና በመለበሻ ወቅት አንዳንዶቹም እንደለባሾቻቸው የዕድሜ ደረጃ የተለያዩ ናቸው፡፡

### 4.1.2.1 ቁምጣ

ቁምጣ በፋብሪካ ከተመረቱ ልዩ ልዩ ቀለም ካላቸው ብትን (ዐርበ ወጥ) ጨርቆች ከጉልበት በላይ ያለውን የሰውነት አካል ለመሸፈን አጠር ተደርጎ በአካባቢ ልብስ ሰፊዎች የሚዘጋጅ ሀገረሰባዊ ልብስ ነው፡፡ ይህ በብዛት በዕድሜ ከገፉ አባቶች በስተቀር በሁሉም የዕድሜ ክልል ባሉ ወንዶች ዘወትር የሚለበስ ነው፡፡ አቶ ገለታው ደሳለኝ እንደገለፁት *"በአዋቂዎችና በወጣቶች የሚለበስ በዓይነቱም በመጠኑም የሚለያይ ነው፡፡ የአዋቂ ወንዶች ሰፊና በላዩ ላይ ጌጥ የሌለው ነው፡፡ የህፃናትና የወጣቶቹ ደግሞ ጠባብ ሆኖ በላዩ ላይ አዝራር፣ የጥለት ክርና የሻማ ጨርቅ ጌጥ ያለው ነው" ይላሉ* (*ቃለ መጠይቅ*/ግሬት ቀበሌ፡ ጥር 03 ቀን 2015 ዓ.ም)፡፡ በተጨማሪም አቶ ያገኝ እንግዳሸት *"ቅርቃር/ጠባብ ቁምጣ ስራ ስንራመድ ስንቀመጥ ይመችናል፡፡ ሰውነት ያሳምራል፣ ደግሞም ወጣት ወንድ ልጅ ኮስተር (ቀልጠፍ) ያለ ልብስ ካለበሰ አያምርበትም"* በማለት ጠባብ ቁምጣ በወጣቶች ለመለበስ የሚመረጥበትን ምክንያት ያብራራሉ፡፡ (*ቃለ መጠይቅ*/ገረን ቀበሌ፡ ነሐሴ 12 ቀን 2013 ዓ.ም)፡፡

ከሁለቱ መረጃ ሰጪዎቹ መረዳት እንደሚቻለው በአዋቂ ወንዶችና ወጣቶች የሚለብሱት ቁምጣ በዓይነት፣ በአሰራር፣ በአገልግሎት የተለያዩ ናቸው፡፡ ይህም የአዋቂዎች ቁምጣ ሰፋ ተደርጎ የሚሰራ ሲሆን የወጣቶቹ ደግሞ በአሰራር ጠባብ፣ በዓይነት ደግሞ የተለያዩ ቀለም ባላቸው ሻማ ጨርቆች ጌጥ የሚዘጋጁ፣ በአገልግሎታቸው ደግሞ አካልን ከመጠበቅ ይልቅ ውበት በማጉላት ላይ የሚያተኩሩ ናቸው፡፡ በተጨማሪም አቶ አስቻለው ማሞ ሲገልፁ *"የህፃናት ቁምጣ እንደ ካኒቴራ ሆድና ደረትን የሚሸፍን ጨርቅ፣ በቀበቶ ፈንታ መያዣ (ማንገቻ) ያለው ጨርቅ ከቁምጣው ጋር አብሮ የሚሰፋ ነው"* ይላሉ፡፡ (*ቃለ መጠይቅ*/ ወንጪት ቀበሌ፡ መስከረም 21 ቀን 2015 ዓ.ም)፡፡ ሀገረሰባዊ ልብሱ የሰውነት ደህንነትን መጠበቅ፣ ውበትን ማጉላት፣ ገንዘብን መያዝ ወዘተ ተግባራት እንዳሉት ነዋሪዎቹ ሲገልፁ፡-

> *ቁምጣ ቆላማ ለሆነ አገር ሰውነት እንዳይሞቅ ያደርጋል፡፡ ስራ ለመስራት፣ ለመታጠብና ወንዝ ለመሻገር፣ ወጣቶቹ ባትና ታፋቸውን በሳሙና እየተሞነደሉ (እየቆነጁ) ለመታየትም፣ ሣንቲም በኪስ ለመያዝ ያገለግላል፡፡* (የቡድን 3 ተወያዮች/ ኮራ ወንጪት ቀበሌ፡ መስከረም 21 ቀን 2014 ዓ.ም)

አቶ ገለታው ደሳለኝ በበኩላቸው *“አዋቂዎቹ የሚለብሱት ቁምጣ ጌጥ የለውም። የወጣቶቹ ቁምጣዎች ግን በሻማ ጨርቅና የጥለት ክር መስቀል ጌጥ አለው። ቁምጣው በተሰፋበት ጨርቅ ደግሞ የጩቤ፣ የሽጉጥ ጌጥ ያሰሩበታል። የህፃናቱ ቁምጣዎች በሻማ ጨርቅ አቀብ ቁልቁል፣ አግድም ጌጥ ያበዙበታል”* ይላሉ። (ቃለ መጠይቅ/ ግሬት ቀበሌ፡ ጥር 03 ቀን 2015 ዓ.ም)።

በአልባሳቱ ላይ የሚደረጉ ጌጣጌጦችን ተምሳሌታዊ ትርጉም ስንመለከት ከውበት በተጨማሪ እምነቱን፣ ፍላጎቱን፣ ፍልስፍናውን፣ እሴቱን ወዘተ የሚገልፁ ናቸው። ለምሳሌ የመስቀል ቅርፅ ጌጥ እምነቱን ለመግለፅ፣ እንደ አበባና አዝራር ያሉት ደግሞ ወጣትነቱን ለመግለፅ የሚያመላክቱ ሲሆኑ የሽጉጥ ቅርፅ ያለበት ጌጥ ደግሞ ጀግንነቱን ተኳሽነቱን የሚገልፁ ናቸው። ነገር ግን በአዋቂዎች የሚለበሱ ቁምጣዎች ጌጥ የሌላቸው መሆኑ ከውበት ይልቅ የሰውነት አካል ደህንነትን ለመጠበቅ ትኩረት ያደረጉ መሆኑን ያስረዳል።

**ፎቶ 7. በተለያየ ዕድሜ ቁምጣ ሲለበስ**




**ምንጭ፡- በ21/01/14 ዓ.ም ኮራ ቀበሌ፣ በ10/05/15 ዓ.ም ግሬት ቀበሌ፣ በ12/12/13 ዓ.ም ገረን ቀበሌ በአጥኚው የተወሰደ**

Durkheim (1893) ማህበራዊ መዋቅሮች በጊዜ ሂደት በሰዎች መስተጋብር የሚፈጠሩ እንዲሁም ግለሰቦች፣ ቡድኖች እና ተቋማት እርስ በርስ የሚደጋገፉ መሆኑን እንደ ቋንቋዎች፣ እሴቶች እና ምልክቶች አሏቸው። ይህም ማህበረሰቡ የተረጋጋ (socially stable) እንዲሆን በጋራ የሚያገለግሉ መሆናቸው ይናገራሉ። ከዚህ አኳያ ይህ ሀገረሰባዊ

የወንዶች ልብስ የማህበረሰቡ ማንነት ይዞ ከትውልድ ትውልድ መተላለፉ ማህበረሰቡ እንዲረጋጋ አደርጎታል፡፡ በጥቅሉ ይህ ሀገረሰባዊ የወንዶች ልብስ ዕድሜን፣ ፆታን፣ ማንነትን መሰረት ተደርጎ የሚለበስ መሆኑ በቀላሉ የማህበረሰቡን መዋቅርና ተግባር እንዲሁም እምነት፣ እውቀትና ፍልስፍና የሚያመላክት መሆኑን የጥናቱ ግኝት ያመላከታል፡፡ ለአዋቂ ወንዶች በአማካይ ሁለት ሜትር ተኩል ብትን ጨርቅና 1000 ብር ወጪ መኖሩን በ03/05/15 ዓ.ም በግሬት ቀበሌ በመስክ ምልከታ አረጋግጫለሁ፡፡

## 4.1.2.2. ሱሪ

**ቦላሌ ወይም ሰፊ ሱሪ፡-** በዕድሜ የገፉ አባቶች በበዓላትና በአዘቦት ቀናት የሚለብሱት የልብስ ዓይነት ነው፡፡ ልብሱ ከወገብ እስከ እግር ድረስ ያለውን የሰውነት ክፍል የሚሸፍን ሆኖ በሰውነት ልክ (ሳይሰፋና ሳይጠብ) የፋብሪካ ምርት ከሆኑ ብትን ጨርቆች በአካባቢው ልብስ ሰፊዎች የሚዘጋጅ ነው፡፡ በአማካይ አንድ ሜ. ከሰባ ሳ. ሜ. ቁመት ለሚኖረው ወንድ ሙሉ ልብስ 3 ሜትር ከሩብ ብትን ጨርቅ ማሰፊያውን ጨምሮ 1500 ብር ወጪ እንደሚያስፈልግ በ27/04/14 ዓ.ም በዓለም ከተማ ከነበረኝ ምልከታ ተረድቻለሁ፡፡

**ፎቶ 8. ሱሪ**




**ምንጭ፡- የመጀመሪያው ፎቶ በአጥኚው በ12/12/13 ዓ.ም ገረን ቀበሌ 2ኛው ከወረዳው ባ/ቱ/ጽቤት 2016 ዓ.ም የተወሰደ**

**ተነፋነፍ ሱሪ፡-** ይህ የሱሪ ዓይነት በፋብሪካ ከተመረቱ ብትን ጨርቆች በአካባቢው ልብስ ሰፊዎች የሚዘጋጅ ሲሆን የሰውነት ደህንነትን ለመጠበቅ፣ ዕድሜን፣ ማህበራዊ ደረጃን የሚያመላክት ነው። አቶ እናትዬ ብሬ ገለፃ *"ተነፋነፍ ሱሪን በብዛት ሽማግሌዎች ለበዓላት ቀን የሚለብሱት ልብስ ነው"* (*ቃለ መጠይቅ/ጎራንዳ ቀበሌ፡ መስከረም* 14 *ቀን* 2014 *ዓ.ም*)። ይህ ከጉልበት በላይ በጣም ሰፊ በመሆኑ በነፋስ ስለሚሞላና ድምፅ ስለሚሰጥ ተነፋነፍ የሚለውን ስም ሊያሰጠው ይችላል።

## 4.1.2.3. ኮት (jacket)

ኮት (jacket) ተብሎ የሚጠራው የልብስ ዓይነት ከህፃን እስከ አዛውንት ያሉ የተጠኚው ማህበረሰብ ወንዶች ከቁምጣና ሱሪ ጋር አላባሽ አድርገው የሚለብሷቸው ናቸው። እነዚህ የልብስ ዓይቶች ደግሞ በዕድሜና በአሰራራቸው የተለያዩ ሲሆኑ ከጥጥ ፈትል በአካባቢው ሽማኔ የሚዘጋጁት የአደሌ (የጥጥ) ጃኬቶች በአዋቂ ወንዶች ብቻ ይለበሳሉ። አቶ አጥላባቸው ጋሎ እንደገለፁት *"አደሌ ኮት ግራና ቀኝ የሚከፈት ሳይሆን እንደሹራብ ከጨንቅላት ወደ ትከሻ በማውረድ የሚለበስና ባገራችን ሽማኔዎች የሚሰራ የክብር ልብስ ነው።"* (*ቃለ መጠይቅ/ግሬት ቀበሌ፡ ጥር* 03 *ቀን* 2014 *ዓ.ም*)።

ይህም እንደዛሬው የኮት መቆለፊያ (አዝራሮች) በሌሉበት ዘመን በዚህ መልክ መሰራቱ የቁሱን ጥበባዊ ታሪክነት ያሳያል። እንዲሁም ቀደም ሲል በስፋት ይለበስ የነበረና ባህላዊነት (Cultural) የሚያንፀባርቅ ነው። ነገር ግን በአሁኑ ወቅት ይህ ልብስ ከአገልግሎት እየራቀ የመጣ መሆኑን መረጃዎቼን ለመሰብሰብ ደጋግሜ በሄድኩባቸው በጎንራዳ፣ ዘይታ እና ኮራ ወንጭት ቀበሌዎች ሲለበሱ አለመመልከቴ አንዱ ማረጋገጫ ነው።

ሌላው የኮት (jacket) ዓይነት የቁምጣ ወይም ሱሪ አላባሽ የሚባለው ነው። ይህ ኮት የፋብሪካ ምርት ከሆኑ ልዩ ልዩ ብትን ጨርቆች በአካባቢው ልብስ ሰፊ አማካኝነት የሚዘጋጅ መሆኑን አቶ ዮናስ አንጓሌ *"ቁምጣ ወይም ሱሪ አላባሽ ኮት ቁምጣና ሱሪው በተዘጋጀበት የጨርቅ ዓይነት ግራና ቀንኝ ተካፋች ተደርጎ የሚዘጋጅ ነው። የአዋቂዎች ኮት ጌጥ ስለማይፈልጉ ሌጣውን (ያለጌጥ) አድርገን፣ የህፃናትና ወጣቶቹ ደግሞ በጌጥ በሻማ ጨርቅ ጌጥ ይሰፋል"* ሲሉ ያብራራሉ። (*ቃለ መጠይቅ/ልብስ ሰፊ/ገረን ቀበሌ፡ ነሐሴ* 12 *ቀን* 2013 *ዓ.ም*)። ከዚህ ሃሳብ መረዳ እንደሚቻለው አዋቂ ወንዶች ውበትን ለማጉላት የማይፈልጉ መሆኑንና ወጣቶቹ ደግሞ ውበትን ማጉላት ቅድሚያ የሚሰጡ መሆኑን ነው። ሌላው በማህበረሰቡ ወንዶች የሚለበሱት የኮት ዓይነቶች በገበያ የቀረቡና ቀድመው የተዘጋጁ (ready-made) የምርት ዓይነት ናቸው። እነዚህ የኮት ዓይነቶች በብዛት የሚለበሱት በወጣቶችና አዋቂዎች መሆኑን ምልከታ ባደርግኩባቸው ቀበሌዎች አረጋግጫለሁ።

በጥቅሉ የኮት (jacket) የሚባለው የወንዶች ሀገረሰባዊ ልብስ በሸማኔ በልብሰ ሰፊ፣ እና በነጋዴዎች በኩል የሚዘጋጅና አንዱ ላንዱ የሚደጋገፍ መሆኑ Malinowski (1944) አንድ ማህበረሰብ ፍላጎቱን ለማሟሏት እርስ በርስ የሚተሳሰሩ ወይንም የሚደጋገፉ ተቋማትን እንደሚፈጥር ከገለፁት ጋር የሚመሳከር ነው፡፡ በተጨማሪም ይህ ልብስ የለባሹን ውበት የሚያጎላ፣ የአካል ደህነነትን የሚያስጠበቅ፣ ማህበራዊ ደረጃ የሚያሳይ መሆኑን ያገነዝባል፡፡

**ፎቶ 9. ኮትና ሱሪ (ሙሉ ልብስ)**

ቦላሌ ሱሪ ከነአላባሹ ኮት | አደሌ/የጥጥ ኮት | ጂንስ ኮት







**ምንጭ፡- በ12/12/13 ዓ.ም ገረን ቀበሌ፣ በ10/05/15 ዓ.ም ግሬት ቀበሌ፣ በ21/01/14 ዓ.ም ኮራ ቀበሌ በአጥኚው የተወሰዱ ፎቶዎች**

## 4.1.2.4. ሹራብ እና ካኒቴራ

የተጠኚው ማህበረሰብ ወንዶች ከሚለብሷቸው አልባሳት መካከል ሹራብና ካኒቴራ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ሹራብና ካኒቴራ በኮትና በገላ መሀል የሚለበሱ የውስጥ ልብሶች ናቸው፡፡ ሹራብ የተለያዩ ቀለም ካላቸው የጥለት ክር በአካባቢው የዕደ ጥበብ ሙያተኛ የሚሰራ ሲሆን ካኔቴራ ደግሞ በፋብሪካ የሚመረት የወንድ ልብሶች ናቸው፡፡ ሹራብ በበዓላት፣ በልዩ ዝግጅት ወቅት በወጣቶች የሚለበስ ሲሆን ካኒቴራ ደግሞ በበዓላትና በአዘቦት ቀናት በሁሉም ዕድሜ ክልል ያሉ ወንዶች የሚለበስ ነው፡፡ በእርግጥ እነዚህ አልባሳት አሁን ላይ ቤሌሎች የፋብሪካ ምርቶች እየተተኩ መምጣታቸውን በመረጃ በሁሉም ቀበሌዎች በነበረኝ የመስክ ምልከታ አረጋግጫለሁ፡፡ በተጨማሪም እነዚህን አልባሳት ነዋሪዎቹ ሲገልፁ "ድሮ *በአባቶቻችን ጊዜ ተቆላፊ ያልሆነ ከአቡጀዴ የሚሰራ ኮት (jacket)፣ በእኛ ጊዜ ደግሞ*

*ከጥለት የሚሰራ ሹራብ፣ ከዚያ ትንሽ ቆየት ብሎ አግድም መስመር ያለው ካኒቴራ መጣ፣ እንደገና አሁን ደግሞ ተቆጥሮ የማያልቅ ዘመን አመጣሽ ካኒቴራ መጣ። ይኸው ልጅ አዋቂ ሳይል አገሬው በሙሉ ከገበያ እየገዛ ይለብሳሉ"* በማለት ያስረዳሉ። (የቡድን አንድ ተወያዮች/ ጎራንዳ፡ 14/01/14 ዓ.ም)።

ከመረጃ ሰጪዎቹ ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው የሚለብሱ ካኒቴራዎች የሚለዋወጡ ናቸው። በእርግጥ እነዚህ አልባሳት በየጊዜው የሚለዋወጡ ቢሆንም የአካባቢው ልብስ ሰፊዎች፣ የዕደ ጥበብ ሙያተኞች (handcrafts)፣ ነጋዴዎች በጋራ ሆነው የማህበረሰቡን የመልበስ ፍላጎት ሲያሟሉ መቆየታቸውን መገንዘብ ያስችላል። ለምሳሌ ከአቡጀዴ የሚዘጋጁ ልብሶች ከአገልግሎት ሲርቁ ከጥለት ዘሃ ክር በጥበብ ሰሪዎች የተዘጋጁ ሹራቦች ቀጥሎ የፋብሪካ ምርት የሆኑና ሰያፍ ጨርቅ (ድርብ ስፌት) ያለባቸው ካኒቴራዎች እንዲሁም በየዘመኑ ተመርተው ለገበያ የሚቀርቡ ቲሸርቶች የለባሹን ፍላጎት እንዲሟሉ አድርገዋል።

እዚህ ላይ ቀዳሚ የነበረውና ከጥለት የተሰራው ሹራብ ከአገልግሎት እየራቀ ሲሄድ የፋብሪካ ምርት የሆነው ካኒቴራ በአዲስ መተካቱን ያመላክታል። ይህን ሃሳብ Wallace and Wolf (1999፣18) እዳሉት የስርዓተ ማህበሩ ክፍሎች እርስ በርስ የሚደጋገፉ መሆናቸው ጠቅሰው ስርዓቱ ሲረበሽ ወይም ሲታወክ ክፍሎች እንደገና በመደራጀት ወደ ሚዛናዊነት እንደሚመለሱ ከገለፁትን ሀሳብ ጋር ይጠራራል። በጥቅሉ ይህን ልብስ የሚያዘጋጁ የእደ ጥበብ ሙያተኞች በቁጥር አነስተኛ መሆናቸውና የፋብሪካ ምርቶች ገበያ ላይ በስፋት መገኘታቸው Haferkamp (1992፣103) እንዳሉት ዘመናዊው ማህበረሰብ አስተማማኝ እና የተሻለ ህይወት ለመኖር የመጡ ለውጦች ናቸው። ምክንያቱም አልባሳቱ ውበትን ከማጉላት በተጨማሪ ረጅም አገልግሎት የሚሰጡ ለአለባበስ ምቹና ቀላል እንዲሁም በቀላሉ ከገበያ የሚገኙ በመሆናቸው ማህበረሰቡ እንዲመጡ አድርጓቸዋል።

**ፎቶ 10. የጥለት ሹራብ**



**ፎቶ 11. ባለሰረዘ ካኒቴራ**



**ምንጭ፡- ከወረዳው ኮሙዩኒኬሽን ማህበራዊ ሚዲያ በ15/092015 ዓ.ም የተወሰዱ ፎቶዎች**

### 4.1.2.5. ባርኔጣ እና ኮፍያ

**ባርኔጣ፡-** የሚባለው የራስ ልብስ ከተለያዩ ቀለማት የጥለት ክሮች በዕደ ጥበብ ሙያተኞች የሚሰራ ሆኖ በላዩ ላይ የመስቀል ጥልፍና አዝራር ይደረግበታል፡፡ እንደ አቶ ጉርምስ አየለ *“ባርኔጣ ወጣት ወንዶች በበዓላትና በሰርግ ጊዜ የሚያደርጉት የቁንጥ (የጌጥ) ልብስ ነው፡፡”* (ቃለ መጠይቅ/ጎራንዳ ቀበሌ፡ መስከረም 14 ቀን 2014 ዓ.ም)፡፡ በተጨማሪም ባርኔጣ ማንነትን ለመለየት የሚያስችል መሆኑን ወ/ሮ ሕይወት ታደሰ ሲገልፁ *“ሙሽራው በሰርጉ ቀን በራሱ ላይ ነጭ ስስ ሻሽ ጠምጥሞ በላዩ ላይ ባርኔጣ ያደርግበታል፡፡ ይህም ሙሽራውን ከማስዋቡ በተጨማሪ ከሚዜዎቹ ተለይቶ እንዲታይ ያደርጉበታል”፡፡* (ቃለ መጠይቅ/ዓለም ከተማ፡ ታህሳስ 27 ቀን 2014 ዓ.ም)፡፡ የባርኔጣውን ሰማያዊ ቀለም ተምሳሌታዊ ትርጉም ስንመለከት አንድን ወንድ ልጅ ወደ ተረጋጋ የትዳር ሕይወት እየገባ መሆኑን ያመለክታል፡፡

**ኮፍያ፡-** በዋናነት ራስን ከፀሃይ፣ ከዝናብና ከብርድ ለመከላከል ወጣቶችና አዋቂዎች የሚያደርጉት ልብስ ነው፡፡ ኮፍያ (Cap) በፋብሪካ ተመርቶ የሚመጣ ሲሆን አሰራሩም ከፊት ለፊት የፀሃይ መከለያ አለው፡፡ ኮፍያን በብዛት ዘወትር አዋቂ ወንዶች ይገለገሉበታል፡፡ በተጨማሪም ኮፍያው ረጅም አገልግሎት እንዲሰጥ በሚል በላዩ ላይ የሻማ ጨርቅ ተደርቦ ይሰፋበታል፡፡ አልባሳቱ ውበትን ማጉላት፣ ደህንነትን ማስጠበቅ፣ ዕድሜን፣ ማህበራዊ ደረጃና ማንነትን የሚገልፁ ናቸው፡፡ አሰራሮቹም የማህበረሰቡን እውቀት፣ ጥበብ፣ ፍልስፍ፣ እምነትናን የሚገልፁ ናቸው፡፡ እዚህ ላይ የሁለቱን ቁሶች ቅርፅ ስንመለከት ባርኔጣ በዋናነት ውበትን ለማጉላት ታስቦ የተሰራ ሲሆን ኮፍያ ደግሞ የአካል ደህንነትን መጠበቅ ብቻ ሳይሆን በጭንቅላት ለሚከናወኑ የሸክም ስራዎች ለማከናወን ታስቦ እንደተዘጋጀ ያሳያል፡፡

**ፎቶ 12. ባርኔጣ** **ፎቶ 13 ኮፍያ**







**ምንጭ፡- በ10/08/15 ዓ.ም ዓለም ከተማ፣ በ21/01/14 ዓ.ም ኮራ ቀበሌ፣ በ10/05/15 ዓ.ም ገረን ቀበሌ በአጥኚው የተወሰዱ ፎቶዎች**

### 4.1.2.6. ፎጣ

የማህበረሰቡ ወንዶች አዘውትረው ከሚለብሷቸው ሀገረሰባዊ አልባሳት መካከል አንዱ ሲሆን ከባለቀለም ጥለት ዘሃ በሸማኔ የሚሰራ ነው፡፡ ፎጣ ከወገብ በላይ ያለውን የሰውነት ክፍል ከብርድና ከፀሃይ የአካል ደህንነትን መጠበቅ፣ ዕቃ ለመያዝ፣ ውበትን ለማጉላት ወዘተ ያገለግላል፡፡ አቶ ሰለሞን ምታው *“ፎጣ ሰውነትን ከሙቀተና ከቅዝቀዜ ለመጠበቅ፣ ዕቃዎችን ለመያዝና ለመሸከም፣ ለጤና፣ ለውበት እንዲሁም ከንፈር ወዳጅን ለማሽኮርመም ወይም ለማማለል የሚያገለግል ሀገረሰባዊ ልብስ ነው”* በማለት ይዘረዝራሉ (ቃለመጠይቅ/ዓለም ከተማ፡ ሚያዚያ 10 ቀን 2015 ዓ.ም)፡፡ እዚህ ላይ ይህ ሀገረሰባዊ ልብስ የሰውነት ደህንነትን መጠበቅ ቀዳሚ ተግባሩ ሲሆን ውበትን ማጉላት፣ ወንዶች ለአቅመ አዳም መድረሳቸውን ለማመላከት እና ፍቅረኛሞች ፍቅራቸውን ለመግለፅ የሚያስችል ተግባር መኖሩ Merton (1968) ማህበራዊ መዋቅር በርካታ ተግባራት እንዳላቸውና አንዳንዶቹ በግልፅ የሚታወቁ (manifest) አንዳንዶቹ ደግሞ በግልፅ የማይታወቁ ወይም ስውር (latent) ተግባራት እንደሆኑ ከገለፁው ጋር የሚናበብ ነው፡፡ ሌላው ይህን ልብስ የሚለበሱት በብዛት ወጣቶች መሆኑ የስርዓተ ማህበሩን መዋቅርና ተግባር የሚያሳይ ነው፡፡ ይሁንና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሀገረሰባዊ ልብሱን ወጣቶች በሌላ የፎጣ ዓይነት እየተኩ መሆኑ በሀገረሰባዊ ልብሱ ላይ ለውጥ መከሰቱን የሚሳይ ነው፡፡

**ፎቶ 14. ፎጣ**

በሸማኔ የተሰራ ነባሩ የጥለት ፎጣ



በፋብሪካ የተመረተ አዲሱ ፎጣ



ምንጭ፡- በ27/04/14 ዓ.ም ዓለም ከተማ እና፣ በ21/01/14 ዓ.ም ኮራ ቀበሌ በአጥኚው የተወሰዱ ፎቶዎች

## 4.1.2.7. ኩታ

ኩታ እንደዛሬው ፎጣ በስፋት መለበስ ሳይጀመር ያገቡ ወንዶች በትከሻቸው ላይ የሚደርቡት የክብር ልብስ ነው፡፡ ኩታ በአካባው ሸማኔ ከጥጥ ፈትል የሚዘጋጅ ነጭ ልብስ ሲሆን እንደ ወ/ሪት እሸቴነሽ ደርሶ ገለፃ “የኩታ ርዝመት 2 ሜትር ተኩል ከ80 ሳ.ሜ ሲሆን ከነጠላ የሚያንስና 400 ብር ዋጋ ያለው ነው፡፡” (ቃለ መጠይቅ/ገረን ቀበሌ፡ ነሐሴ 12 ቀን 2013 ዓ.ም)፡፡ አገልግሎቱን በተመለከተ ደግሞ አቶ አማረ ንጉስ *“ኩታ አጠፍ ተደርጎ በትከሻ ላይ የሚለበስ የክብር ልብስ ነው፡፡ ኩታ የሚለበሱ ሰዎች ደግሞ ለጋብቻ የደረሱና ያገቡ ወንዶች በበዓላት፣ በማህበራዊ ዝግጅቶች ላይ የሚለበሱት ነው፡፡”* (ቃለ መጠይቅ/ጎራንዳ ቀበሌ፡ መስከረም 14 ቀን 2014 ዓ.ም)፡፡

ይህ ሀገረሰባዊ ልብስ ያገቡ ወይም ያላገቡ ወንዶች ብቻ መልበሳቸው የማህበረሰቡን መዋቅርና ተግባር ያሳያል፡፡ በእርግጥ ይህ ሀገረሰባዊ ልብስ በአሁኑ ወቅት የፋብሪካ ምርት በሆነ ፎጣዎች እየተቀየረ መጥቷል፡፡ ነባሩን ልብስ እየቀየሩ የመጡት የፎጣዎችን ስንመለከት በመጠን ከፍ ያሉ፣ በቀለም ደግሞ የተለያዩ መሆናቸውን በ21/01/14 ዓ.ም በኮራ ወንጪትና በ03/05/15 ዓ.ም በግሬት ቀበሌዎች በምልከታ አረጋግጫለሁ፡፡ የኩታ ነጭ ቀለም ተምሳሌታዊ ትርጉምን ቄስ ማደፍሮ አበበ በለው ሲገልፁ “ፊቱም እንደፀሐይ አበራ ልብሱም እንደ ብርሃን ነጭ ሆነ የሚለውን የጌታን አብነት ለማመልከት የሚለውን መፅሐፍ ቅዱሳዊ መነሻ በማድረግ ነው ይላሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ/ጎራንዳ ቀበሌ፡ መስከረም 14 ቀን 2014 ዓ.ም)፡፡

**ፎቶ 15. የኩታ አለባበስ**




**ምንጭ፡- በ21/01/14 ዓ.ም ኮራ ቀበሌ እና በ10/05/15 ዓ.ም ግሬት ቀበሌ በአጥኚው የተወሰዱ ፎቶዎች**

### 4.1.2.8. ጋቢ እና ነጠላ

ነጠላና ጋቢ ከጥጥ ፈትል በሽማኔ የሚሰሩ ሰውነትን ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል ለማልበስ የሚያገለግሉ ሀገረሰባዊ አልባሳት ናቸው፡፡ ብዙ ጊዜ ነጠላና ጋቢ ከአገልግሎት ልዩነት በቀር በአሰራርና በዓይነታቸው ተቀራራቢነትና ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ እንደ ወ/ሪት እሸቴነሽ ደርሶ ገለፃ *"ነጠላ ርዝመቱ 3 ሜትር ከ80 ሳ.ሜ ስፋት ያለው ሲሆን ዋጋው 500 ብር ነው፡፡ ጋቢ ርዝመቱ 3 ሜትር ተኩል ከ80 ሳ.ሜ ስፋትና 800 ብር ዋጋ አለው፡፡"* (ቃለ መጠይቅ/ገረን ቀበሌ፡ ነሐሴ 12 ቀን 2013 ዓ.ም)፡፡ ነጠላ በሁለቱም ፆታና የዕድሜ ደረጃ የሚለበስ ሲሆን ጋቢ ደግሞ ብዙ ጊዜ በአዋቂ ወንዶች አልፎ አልፎ ደግሞ በአዋቂ ሴቶች ይለበሳሉ፡፡ ነጠላና ጋቢ ለባሹን አካል ደህንነት ከማስጠበቃቸው በተጨማሪ ለተለያዩ ማህበራዊ አገልግሎት የሚውሉ መሆኑን አቶ ጌታቸው ዘውዴ ሲገልፁ፡-

> *ነጠላና ጋቢ ባገሬው የሚለበሱ የክብር ልብሳችን ናቸው፡፡ በሰርግ ወቅት ለብሰን እንደምቅበታለን፣ ቤተክርስቲያን እንቆርብበታለን፣ ሴቶቹ ደግሞ ልጅ ያዝሉበታል፣ የክብሮ (በዓላት) ቀን፣ ወንዱም ሴቱም ወጣትና አዋቂው ነጠላ ይለብሳሉ፡፡ ገበያ ሲሄዱ ይለብሱታል፣ ለሰርግ ጊዜም የጥሎሽ ዕቃ ነው፡፡ ለጌጥም ለብርድም የሚሆን ልብሳችን ነው፡፡ ጋቢን ደግሞ አዋቂ ወንዶች ለሽምግልና፣ ለዕድር፣ ለሀዘን፣ ለቁርባን፣ ለክብሮ፣ ቤተክርስቲያን ስናስቀድስ ሁሉ እንለብሰዋለን፡፡ (ቃለ መጠይቅ/ግሬት ቀበሌ፡ ጥር 03 ቀን 2015 ዓ.ም)፡፡*

ከዚህ ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው ሀገረሰባዊ አልባቱ በሁለቱም ፆታ፣ በአዘቦትና በበዓላት ቀናት፣ ለዓለማዊ፣ መንፈሳዊ የሚለበሱ፣ ማንነትን፣ ማህበራዊ ደረጃንና የዕድሜ ደረጃን የሚያመላክቱ መሆኑን ነው፡፡

**ፎቶ 16. የአዋቂዎች ወንዶች ጋቢ አለባበስ** **ፎቶ 17. የአዋቂዎች ሴቶች ነጠላ አለባበስ**





**ምንጭ፡- በ18/01/14 ዓ.ም ግሬት ቀበሌ በአጥኚው የተወሰዱ ፎቶዎች**

በሌላ መልኩ እነዚህ አልባሳት ማህበረሰቡ ሀዘኑን ለመግለፅ ከሚገለገልባቸው አልባሳት መካከል ይጠቀሳሉ፡፡ ይህን ሃሳብ አቶ ክብረቴ አስፋው ሲናገሩ፡-

> *ነጠላና ጋቢ በለቅሶ የቅርብ ቤተሰብ ከሆነ ነጠላውን በማሸረጥ (በማገልደም) ራቅ ያለ ዝምድና ከሆነ ደግሞ የጥለት ጫፍ ወደላይ በማድረግ ወይም ነጠላውን በመዘቅዘቅ ወንዱም ሴቱም በለቅሶ ጊዜ የምንለብሰው ልብሳችን ነው፡፡* (ቃለ መጠይቅ/ግሬት ቀበሌ፡ ጥር 10 ቀን 2014 ዓ.ም)

እንደ መረጃ ሰጪዎቼና በ12/12/13 ዓ.ም በገረን፣ በ21/01/14 ዓ.ም በኮራ ወንጪት፣ በ03/05/15 ዓ.ም በግሬት ቀበሌዎች በቅሶ ጊዜ በምልከታ እንዳስተዋልሁት የማህበረሰቡ አባላት ሀዘናቸውን የሚገልፁበት የራሳቸው የአለባበስ ስርዓት አላቸው፡፡ ይኸውም እናቶች በሞት የተለያቸው ቤተሰብ ወይም የቅርብ ዘመድ ከሆነ ነጠላ/ጋቢውን በማጠፍ በወገባቸው ላይ ያሸርጡታል፣ ዝመድናቸው ራቅ ያለ ከሆነ ደግሞ የነጠላ/ጋቢውን ጥለት በጭንቅላት በኩል በማድረግ ወይም ነጠላውን ዘቅዝቀው ሀዘናቸውን ይገልፃሉ፡፡ እንዲሁም አባቶች ደግሞ የቅርብ ዘመድ/ቤተሰብ በሞት ሲለያቸው ነጠላውን በትከሻና በወገብ ላይ ያስሩታል፡፡

ዝምድናው የራቅ ከሆነ የነጠላ/ጋቢውን ጥለት ወደ ላይ በማድረግ ሀዘናቸውን ይገልፁበታል፡፡ እንደ አቶ አማረ ንጉስ ገለፃ *"እናቶች ከወገባቸው ያሸረጡት ወይም የታጠቁት ነጠላ/ጋቢ ሀዘኑ ሰባት ቀን እስከሚሞላ ድረስ እንዳሰሩት ይቆያሉ"*፡፡ (ቃለ መጠይቅ/ጎራንዳ ቀበሌ፡ መስከረም 14 ቀን 2014 ዓ.ም)፡፡ Spencer (1898) የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ማህበራዊ ስርዓቱን ለማስጠበቅ በጋራ ሆነው የተለያዩ ተግባራትን ያከናውናሉ እንዳሉት እነዚህ አልባሳት የማህበረሰቡን የለቅሶ ስርዓት በማስጠበቅ በኩል ከፍተኛ ሚና ያላቸው ሲሆን የጥለት ጫፉ ወደታች ተደርጎ ሲለበስ ደስታን ወደ ላይ ተዘቅዝቆ ሲለበስ ደግሞ ሀዘንን የመግለፅ ተምሳሌታዊ ትርጉም አለው፡፡

**ፎቶ 18. በለቅሶ የጊዜ የአዋቂ ሴቶች ነጠላና ጋቢ አለባበስ**







ምንጭ፡- በ12/121/13 ዓ.ም ገረን ቀበሌ በአጥኚው የተወሰዱ ፎቶዎች

ፎቶ. 19. በለቅሶ የጊዜ የአዋቂ ወንዶች ነጠላና ጋቢ አለባበስ




ምንጭ፡- በ18/01/14 ዓ.ም ግሬት ቀበሌ በአጥኚው የተወሰዱ ፎቶዎች

## 4.1.2.9. ቡልኮ

ቡልኮ አንዳንድ ጊዜም ነጠላ ጋቢ በመባል የሚታወቅ ሲሆን በሀገር ሽማግሌዎች፣ የእምነት አባቶችና አዋቂ ወንዶች የሚለበስ የክብር ልብስ ሲሆን በሽመና ከሚሰሩ አልባሳት ትልቅ ነው፡፡ ወ/ሪት እሸቴነሽ ደርሶ *"ቡልኮ ርዝመቱ 3 ሜትር ተኩል ከ80 ሳ.ሜ ስፋት አለው፡፡ የሚሸጠውም በ1500 ብር ነው፡፡"* (ቃለ መጠይቅ/ሽማ/ገረን ቀበሌ፡ ነሐሴ 12 ቀን 2013 ዓ.ም)፡፡ እንዲሁም ወ/ሮ አስቴር አንዳርጋቸው *"ቡልኮ ለሙሽሪት ቤተሰቦች የሚሰጥ የጥሎሽ ልብስና በአዋቂ ወንዶችና የሀገር ሽማግሌዎች የሚለብሱት በዋጋም ውድ የሆነ የክብር ልብስ ነው፡፡"* (ቃለመጠይቅ/የባ/ቴ/ጽ/ቤት ኃላፊ/ ዓለምከተማ፡ ታህሳስ 27 ቀን 2014 ዓ.ም)፡፡

ከዚህ ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው ይህ ሀገረሰባዊ ልብስ በሰርግ ወቅት የወንዱ ቤተሰብ ለሴቷ ቤተሰብ ማቅረብ ካለበት የስጦታ (ጥሎሽ) ዕቃዎች ውስጥ አንዱና ዋናው ሆኖ እንዲቀርብ የሚታዘዝ መሆኑን ነው፡፡ ይህ ተግባር የግለሰቡን ፍላጎትና የኢኮኖሚ ደረጃ ከግምት ሳያስገባ በማህበረሰቡ ደንብ መሰረት ተፈፃሚ እንዲሆን የሚወሰደው እርምጃ ፈረንሳዊው Durkheim (1964) ማህበራዊ እውነታዎች በግለሰቡ ላይ ውጫዊ ጫናን ማሳደር የሚችሉ ናቸው ካሉት ሃሳብ ጋር የሚመሳከር ነው፡፡ በተጨማሪም ይህ ሀገረሰባዊ ልብስ በገቢ አቅማቸው ከፍ ያሉ፣ ልጅን ለትዳር ያበቁ (ያጋቡ)፣ ሰውን በማስታረቅ፣ በማሸማገል፣ በመምከር፣ በማስተማር፣ ከፍተኛ ተደማጭ ወይም ተሰሚ የሆኑ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የእምነት አባቶች ወዘተ በዋናነት ይለብሱታል፡፡

ይህም Chavarria (2002) ሀገረሰባዊ አልባሳት የአንድን ግለሰብ ዕድሜ፣ ፆታ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የትውልድ ቦታ፣ ስፍራ፣ ሃይማኖት፣ የማህበራዊ ደረጃ፣ ሙያ ወዘተ ጉዳዮችን እንደሚያመለክት ከሚገልፁት ሃሳብ ጋር ይጠራራል፡፡

በጥቅሉ ይህ ልብስ ማህበራዊ ደረጃን፣ ማንነትን፣ ፆታን፣ ዕድሜ በመግለፅ እንዲሁም የአካል ደህንነት በመጠበቅ በኩል ያለው ፋይዳ Kaisser (1990፣15) አልባሳት ማህበራዊ ደረጃንና ማንነትን በማሳየት በኩል ከፍተኛ ተግባራት አላቸው ካሉት ሃሳብ ጋር ይዛመዳል፡፡

## 4.1.2.10. የመነኩሴ ልብስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ትውፊትና ልማድ መሰረት መነኮሳት ቢጫ ቀሚስ ያደርጋሉ፡፡ የተጠኚው ማህበረሰብ አባላትም ወደ ምንኩስና ዓለም ገብተው ሲኖሩ የሚለብሱት በቤተክርስቲያኗ ህግ መሰረት ሃይማኖታዊ አልባሳትን ይለብሳሉ፡፡ ቄስ ማደፍሮ አበበ እንደገለፁት *"ምንኩስና የዓለምን ክብር ትቶ፣ በንፅህናና በፆም በፀሎት፣ ለእግዚአብሔር ማደር ነው፡፡ መነኮሳቱ ደግሞ በሚለብሱት ቀሚስና ቆብ የሚታወቁ ናቸው"* ሲሉ ያስረዳሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ/ጎራንዳ ቀበሌ፡ መስከረም 14 ቀን 2014 ዓ.ም)፡፡ በዚህም መነሻነት ተምሳሌታዊ ትርጉሙን ስንመለከት መነኮሳት የሚለብሱትን የቢጫ ቀለም ጧፍ እየቀለጠ ለሌሎች ብርሃን እንደሚሆነው ሁሉ መንፈሳዊ ሕይወትም በፆምና በፀሎት ለሌሎች ብርሃን መሆንን እንዲሁም ቆቡ የጌታን አክሊ ሾህን ያመለክታል፡፡

## 4.1.2.11 ጥምጣም

ጥምጣም በተጠኚው ማህበረሰብ ካሉ ኃይማኖታዊ የአለባበስ ስርዓት አንዱ ሲሆን በእምነቱ ከተፈቀደላቸው የእምነት አባቶች ብቻ የሚለብሱት የልብስ ዓይነት ነው፡፡ እንደ እምነቱ አስተምህሮ አንድ ወንድ ልጅ ከልጅነቱ ጀምሮ የሚጠበቅበትን ትምህርት ካጠናቀቀ በኋላ ካህን ተብሎ ሲሰየም ልብሰ ተክህኖ (የካህናት ልብስ) ይለብሳል፡፡ ይህ ልብስ በራስ ላይ የሚደረግበትን ምክንያት ቄስ ማንደፍሮ አበበ "በመጽሀፍ ቅዱስ ኦሪት ዘሌያውያን (8:9) ጠቅሰው *"እግዚአብሄርም ሙሴን እንዳዘዘው በራሱ ላይ መጠምጠሚያዉን አደረገ የሚለውን ቃል ለማመልከት ነው" ይላሉ፡፡"* (ቃለ መጠይቅ/ ጎራዳ ቀበሌ፡ መስከረም 14 ቀን 2014 ዓ.ም)፡፡ በጥቅሉ ከዚህ ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው ልዩ ለሆነ አምልኮ ወይም መንፈሳዊ አገልግሎት መታዘዝን ያመለክታል፡፡ ይህ ልብስ በአሰራርና በአጠማጠም እንዲሁም በአገልግሎቱ የተለየ መሆኑ Homberger (2015) አልባሳት ሃይማኖታዊ ማንነትን ለማመላከት ያገለግላል ሲል ከገለፁት ሃሳብ ጋር የሚዛመድ ነው፡፡

## 4.1.3. *ሀገረሰባዊ መጫሚያ (ጫማ)*

በሁሉም የዕድሜ ክልልና በሁለቱም ፆታ ያሉ የተጠኚው ማህበረሰብ አባላት ከተለያዩ ቁሶች የተሰሩ ጫማዎችን ይለብሳሉ ወይም ያደርጋሉ፡፡ በማህበረሰቡ የሚደረጉ ጫማዎቹ የለባሹን ደህንነት ለመጠበቅ፣ ውበትን ለማጉላትና ማህበራዊ ደረጃንና ፆታን የሚገልፁ ናቸው፡፡

Spencer (1898) የማህበረሰቡን (አባላቱን) ሥነ ሕይወታዊና ማህበራዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ባህላዊ ወዘተ ተቋማትን የሚያቋቁምና ተቋማቱ እርስ በርስ መዋቅራዊ ትስስር ያላቸው መሆኑን ያስረዳል፡፡ ከዚህ አንፃር ባህላዊ የጠፍር ጫማ ሰሪዎች ወይም ቆዳ ፋቂዎች፣ ጎማ ጫማ ሰሪዎች እና የፋብሪካ ምርት የሆኑትን ጫማዎቸን የሚያቀርቡ የንግድ ተቋማትን ደግሞ ማህበረሰቡ ፍላጎቱን ለማሟላት የፈጠራቸው ተቋማት ናቸው፡፡ በዚህ መነሻነት የማህበረሰቡ አባላት በሁለቱም ፆታዎች የሚለብሷቸውን ጫማዎች ዓይነትና ፋይዳ ምን እንደሚመስል በምልከታና በቃለ መጠይቅ ያገኘኋቸውን መረጃዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

**ጠፍር ጫማ፡- ይህ** ጫማ በአካባቢው ቆዳ ፋቂዎች ከእንስሳት ቆዳ የሚዘጋጅ በአዋቂ ወንዶችና ሴቶች በክብረ በዓላት ቀናት ይደረጋል፡፡ ጠፍር ጫማ የሰውን አካል ደህንነት በመጠበቅ፣ ውበትን ለማጉላትና ማህበራዊ ደረጃን የሚያሳይ ነው፡፡ ገለታው ደሳለኝ ሲያብራሩ *"ጠፍር ጫማ ድሮ እናቶችና አባቶች በክብረ በዓላት ወቅት ብቻ የሚያደርጉት ከነጭ በሬ ወይም ቆዳ የሚሰራ የክብር ጫማ ነበር፡፡ አሁን ላይ ግን በዘመን አመጫሽ ጫማ እየተኩት ነው፡፡"* (ቃለ መጠይቅ/ግሬት ቀበሌ፡ ጥር 10 ቀን 2014 ዓ.ም)፡፡

**ጎማ ጫማ፡-** ይህ የጫማ ዓይነት ከመኪና ጎማ በአካበቢው ጫማ ሰሪዎች የሚሰራ ሲሆን በሁሉም ዕድሜ ያሉ ወንዶች በበዓላትና በአዘቦት ቀናት የሚለብሱት ነው፡፡ ጎማ ጫማ በወንዶች ብቻ የሚለበስ መሆኑ ፆታ አመልካች መሆኑን በሁሉም ቀበሌዎች በወንዶች ብቻ ሲለበሱ ተመልክቻለሁ፡፡ እንደ አቶ ንጉስ ብርቅነህ ገለፃ *"የጎማ ጫማ ረጅም ጊዜ የሚያገለግል፣ በዋጋ ርካሽ፣ በየቀኑ የሚለበስ፣ በፀሃይ፣ በዝናብ፣ በጭቃ የሚደረግ ነው፡፡"* (ቃለ መጠይቅ/ጫማ ሰሪ/ዘይታ ቀበሌ፡ ሚያዚያ 10 ቀን 2015)፡፡ እዚህ ላይ የጫማው አገልግሎት ለአካባቢው መልክዓ ምድር ተስማሚ መሆኑን ያመለክታል፡፡

**ከገበያ የሚገዙ ጫማዎች ፡-** የፕላስቲክ ምርት የሆኑት እንደ ኮንጎ፣ ሸበጥ፣ ሸራ፣ ቆዳ ያሉ ጫማዎች በፋብሪካ ተመርተው ለገበያ ከቀረቡ የሚገዙ ናቸው፡፡ ጫማዎቹ ያላቸው ውበትና ልስላሴ በወጣቶቹ እንዲዘወተሩ አድርጓቸዋል፡፡ ወ/ሮ ተካበ አበበ *"አዋቂዎቹ የሚያደርጉት የጠፍር ጨማ ሲሆን ህጻናትና ወጣቶቹ ሴቶች ኮንጎ ጫማ ወጣት ወንዶቹ ደግሞ ሸበጥ ጫማ ገዝተው ያደርጋሉ፡፡"* (ቃለ መጠይቅ/ኮራ ቀበሌ፡ መስከረም 21 ቀን 2014 ዓ.ም)፡፡

የማህበረሰቡ መለያ የነበሩት የጠፍር የጎማ ጫማዎች የፋብሪካ ምርት በሆኑ ዘመናዊ (ጥልፍልፍ፣ ቶርሽን፣ ሸራ፣ ቆዳ፣ ስኒከር) እየተለወጡ መሆኑ Calhoun (1994) ለውጥ በጊዜ ሂደት ሁሉንም ነገሮች እንደሚለውጥና በማህበራዊ አወቃቀር ቅርፅ ላይ ቀላል ወይም ውስብስብ ለውጦችን እንደሚመጣ ከገለፁት ጋር የሚዛመድ ነው፡፡

ፎቶ 20. ሀገረሰባዊ ጫማዎች

በ14/01/14 ዓ.ም የወንዶች ጎማ ጫማ የሴቶች የፕላስቲክ/ ኮንጎ ጫማ አለባበስ ጎራንዳ ቀበሌ





በ12/12/13 ዓ.ም የወንዶች ሸበጥ ጫማና የሴቶች ጥልፍልፍ ጫማ ገረን

የጠፍር ጫማ በ10/081/5ዓ.ም ዓ/ከ







ምንጭ፡- ሁሉም ፎቶዎች በአጥኚው የተወሰዱ ናቸው

## 4.2. ሀገረሰባዊ ጌጣጌጦች በወንዶችና በሴቶች

ጌጣጌጦች ሰውትን ለማሳመር ወይም ለማስዋብ በተለያዩ የሰውነት ክፍሎች ላይ የሚደረጉ፣ የሚንጠለጠሉ፣ የሚለበሱ፣ የሚያዙ ናቸው፡፡ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ለሺ ዓመታት ውበትን ለማጉላት (ለመዋቢያነት ሲያመርቷቸው) እና ሲጠቀምባቸው ቆይተዋል፡፡ የመዋቢያ ቁሶቹ እንደየሀገሩ ባህል፣ እምነት፣ ፍልስፍና፣ እሴት፣ እንዲሁም የቁስ ዓይነት፣ ቅርፅ (ዲዛይን)፣ ቀለም (መልክ) እና ማህበረሰቡ በሚሰጣቸው ውክልናም የተለያዩ ናቸው፡፡ ተጠኚው ማህበረሰብም በሁሉም የዕድሜ ክልልና በሁለቱም ፆታ የሚዘወተሩ ሀገረሰባዊ ጌጣጌጦች ያሉት ሲሆን ጌጣጌጦቹ ፆታን፣ የዕድሜ ደረጃን፣ የለባሹን ማንነት፣ ማህበራዊ ደረጃ እና ኃይማኖታዊ ተግባር ወዘተ ጉዳዮችን የሚገልፁ ናቸው፡፡ በዚህ መነሻነት የማህበረሰቡ ሴቶችና ወንዶች አብዛኛው ጌጣጌጦችን በጋራ የሚጠቀሟቸው በመሆኑ እንደሚደረጉበት/እንደሚለበሱበት የሰውነት ክፍል ዓይነታቸውን፣ ፋይዳቸውንና ተምሳሌታዊ ትርጉማቸው ምን እንደሚመስል እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 4.2.1 የራስ ጌጦች

**ዛጎልና አዝራር፡-** ይህን የመዋቢያ ቁስ ያገቡ ሴቶች በሹርባቸው ላይ የሚያስሩት የመዋቢያ ጌጥ ነው፡፡ በተጨማሪም በተቈጠረጠረ የህፃናት ፀጉር (ጉድሮ) ላይ ዛጉልና አዝራሮቹን በክር በማያያዝ ውበትን ለማጉላትና የፀጉርን ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስችል መሆኑን ወ/ሮ ጥሩነሽ ተጫነ *"የውበት ዕቃዎቹን ወይም ጣጌጦችን የምንገዛው ከገበያ ነው፡፡ ነጭ ዛጎልና አዝራር ደግሞ ፀጉሩ በሰው ዐይን እንዳይገባ (እንዳይመናመን) ይከላከላል፡፡* (ቃለ መጠይቅ/ግሬት ቀበሌ፡ ጥር 10 ቀን 2014 ዓ.ም)፡፡ እዚህ ላይ ነጭ ቀለም በባህሪው ቶሎ የሚታይ በመሆኑ እንደ ተጠኚው ማህበረሰብ እምነት ነጭ ቀለም ዐይን ከመግባት (ከመታመም) የሚከላከል ነው፡፡

**ፎቶ 21. ዛጎልና አዝራር**



**ምንጭ፡- በ14/01/14 ዓ.ም ጎራንዳ ቀበሌ በአጥኚው የተወሰደ**

**ሚዶ (ፀጉር ማበጠሪያ)፡** በብዛት ወጣት ወንዶች በጉፈሬያቸውና በደረት ኪሳቸው ላይ ሰክተው የሚይዙት ሲሆን ሴት ልጅ በምታገባበት ጊዜም በአገልግሏ ውስጥ ተደርጎ በጥሎሽ መልክ የሚሰጥ ቁስ ነው፡፡ ሚዶ ፀጉርን ለማበጠር ከማገልገሉም በላይ ለመዋቢያነት የሚሰጠው ቦታ ከፍ ያለ ነው፡፡ ሚዶ ከእንጨት፣ ከብረት፣ ከሸቦና ከፕላስቲክ የሚሰራ የመዋቢያ ቁስ መሆኑን 27/04/14 ዓ.ም በዓለምከተማ ገበያ ቦታ በመሄድ አረጋግጫለሁ፡ ሚዶዎች በአካቢው የእጅ ሙተኞች ሊሰሩ ወይም ከገበያ ሊገዙ ይችላሉ፡፡

**ፎቶ 22. ሚዶ የራስ ጌጦች**



**ምንጭ፡- በ10/081/5 ዓ.ም ዓለም ከተማ በአጥኚው የተወሰደ**

## 4.2.2. የአንገት ጌጦች

በምልከታው ወቅት እንዳስተዋልሁት በተጠኚው ማህበረሰብ ዘንድ በሁለቱም ፆታና በሁሉም የዕድሜ ደረጃ አንገት ላይ የሚደረጉ በርካታ ጌጣጌጦች አሉ፡ እነሱም፡- የአንገት መስቀል፣ ብር መስቀል፣ ትልቅና ትንሽ ድንብል፣ እንቆ፣ አርጌሽልሙት፣ ማተብ (ኀፍታ)፣ ድምርጥ (ዶቃ)፣ ብር ቅጥል፣ አሸንክታብ (ቁርበተ አሊም) ወዘተ የሚባሉ የአንገት ጌጦች ናቸው፡፡

**የአንገት መስቀል/ብር መስቀል፡-** ይህ የጌጥ ዓይነት ከወርቅ፣ ከብር፣ ከመዳብ፣ ከነሃስ ወይም ከሌላ ማዕድን በአንጥረኛ የሚሰሩና በሁለቱም ፆታና በሁሉም የዕድሜ ክልል የማህበረሰቡ አባላት የሚገለገሉባቸው ናቸው፡፡ በመስቀል ቅርፅ የተሰሩ እነዚህ ባህላዊ የመዋቢያ ጌጣጌጦቹ በዋናነት ውበትን ለማጉላት የሚጠቀሙባቸው ሲሆን እንደተጠኚው ማህበረሰብ እምነት አስተምህሮ ጌታ እየሱስ ክርስቶስ በቀራኒዮ የተሰቀለበትን የከፈለውን መስዋዕትን ከልብ የሚያምኑ ስለመሆኑ የመግለፅ ተምሳሌታዊ ትርጉም አለው፡፡ እንደ ቁስ ማደፍሮ አበበ *"መስቀልን ከልባችን የምናምንበት በመሆኑ ነው በልባችን ትይዩ ከደረታችን ላይ የምናጠለጠለው"* በማለት ይገልፃሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ/ጎራንዳ ቀበሌ፡ መስረም 14 ቀን 2014 ዓ.ም)፡፡

**ድንብል፡-** ቀደም ሲል ከብር፣ ከነሃስና ከመዳብ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ከሌላም ቁስ ጋር ተቀላቅሎ የሚሰራና ያገቡ ሴቶች አንገታቸው ላይ በጥቁር ክር የሚያንጠለጥሉት ሀገረሰባዊ የጌጣጌጥ መሆኑን አቶ ጌታነህ አርጋው *"ድንብል ያገቡ ሴቶች የሚዋቡበት ሲሆን አልፎ አልፎ ያላገቡ ሴቶችና ወንዶች ማህተብ (ከነፍታ) ጋር ያደርጉታል። ድንብል በአንገት ላይ ሲንጠለጠል በጥቁር ክር ታስሮ ነው።"* (*ቃለ መጠይቅ*/ ጎራንዳ ቀበሌ፡ መስከረም 14 ቀን 2014 ዓ.ም)። ሌላኛው መረጃ አቀባይ አቶ ግርማ ተሰማ እንዳሉት *"ድንብል ትንሽና ትልቅ ያለው ሲሆን ትልቁን ወደ ደረት ዝቅ እንዲል ማሰሪያ ክሩን ረዘም ይደረጋል። የትንሹን ድንብል ማሰሪያ ክር ደግሞ አጠር ተደርጎ ነው"* በማለት የአስተሳሰር ስርዓቱን ይገልፃሉ። (*ቃለ መጠይቅ*/ጎራንዳ ቀበሌ፡ መስከረም 14 ቀን 2014 ዓ.ም)።

እዚህ ላይ በ14/01/14 ዓ.ም በጎራንዳ ቀበሌ በምልከታ ማየት እንደቻልኩት ህፃናትና ያላገቡ ሴቶች ትንሹን ድንብል የሚያደርጉ ሲሆን ያገቡና አዋቂዎች ደግሞ ትልቁና ትንሹን በአንድ ላይ ያደርጋሉ። ይህም ሂደት የሰውን ልጅ የእድገት ሽሽግር እንዲሁም ጌጣጌጡ የሚታሰሩበት ጥቁር ክር ደግሞ የክርስትና እምነት ተከታይነትን ያመለክታል።

**ፎቶ 23. ድንብል**



ምንጭ፡- ከወረዳዊ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት 2015 ዓ.ም ማህበራዊ ሚዲያ የተወሰደ

**ዶቃ (ድምርጥ)፡-** በተለያዩ ቀለማት ከጠንካራ ፕላስቲክ የሚሰራ ሲሆን ውስጠ ክፍት የሆነና ድቡልቡል ቅርፅ (cylinder) ያለው የአንገት ጌጥ ነው። ይህን የአንገት ጌጥ ተጠቃሚ ማህበረሰብ ዶቃ/ድምርጥ ሲሉ ይጠሩታል። እንደ አቶ አበጀ ገስጥ ገለፃ *"ይህ የአንገት ጌጥ ሁሉም ሰው በብዛት ወጣቶች ከብር ቅጥል፣ ከድንብል፣ ከአንገት መስቀል፣ ከእንቆና ከአርጌሽ ልሙት ጋር የሚታሰር ነው"* (*ቃለ መጠይቅ*/ዘይታ ቀበሌ፡ ሚያዚያ 10 ቀን 2015 ዓ.ም)።

አቢሲኒያ ድረ ገጽ መዝገበ ቃላት (2024) መደመር የሚለውን ቃል "መሰብሰብ፣ ማከብ፣ ማከማቸት፣ መጠምጠም" የሚል ትርጉም ሰጥቶታል፡፡ ከዚህ አንፃር ማህበረሰቡ ድምርጥ ያለበት ምክንያት ዶቃዎቹ (ድምርጦቹ) በአንድ ላይ ተሰብስበው ወይም ተከማችተው በአንገት ላይ ስለሚታሰሩ ሊሆን ይችላል፡፡ በአንድ ክር ላይ የሚታሰሩ የዶቃ/የድምርጥ ብዛት ከ5 እስከ 9 የሚደርስ መሆኑን በምልከታ ለማረጋጥ ችያለሁ፡፡

**ፎቶ 24. ዶቃ**



**ምንጭ፡- በ21/01/14 ዓ.ም ኮራ ቀበሌ በአጥኚው የተወሰደ**

**ብር ቅጥል፡-** ይህ የአንገት ጌጥ በአንደኛው ፊት የሰው ምስል በሌላኛው ደግሞ የአንበሳ ምስል ያለበትን ወይም በተለምዶ ጠገራ ብር፣ ስሙኒ እና ሽልንግ የሚባሉትን የመገበያያ ሣንቲሞችን እርስ በርስ በማያያዝ (በመቀጠል) በአንጥረኛ የሚሰራ ነው፡፡ እነዚህ ከብርና ከነሃስ የሚሰሩ የአንገት ጌጦች የክር ማስገቢያ ቀዳዳ እንዲኖራቸው ተደርጎ የሚሰሩ ሲሆን የለባሹን ውበት ለማጉላት ለብቻ ወይንም ከሌሎች የአንገት ጌጦች ጋር ይደረጋሉ፡፡ ይህ የአሰራር ሂደታቸውም ብር ቅጥል የሚል መጠሪያ ያገኙ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ አቶ ኃይለማሪያም አበራ *"ብር ቅጥል ጌጥን የሚያደርጉት ያገቡ ሴቶች ነበሩ፡፡ አሁን ላይ ያላገቡ ሴቶችና ህፃናትም ያደርጉታል"* በማለት በቁስ አጠቃቀም ላይ ያለውን ለውጥ ያስረዳሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ/ ግሬት ቀበሌ፡ ጥር 10 ቀን 2014 ዓ.ም)፡፡ ከዚህ ሃሳብ ለመረዳት እንደሚቻለው ብር ቅጥል የአንገት ጌጥ ያገቡ ሴቶች የሚዋቡበት ጌጣጌጥ መሆኑና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ያላገቡ ሴቶችም እየተጠቀሙበት መሆኑ በቁሱ አጠቃቀም ላይ ለውጥ መኖሩን ያመላክታል፡፡ በተጨማሪም ይህ የአንገት ጌጥ በዋጋ ከፍ ያለ መሆኑ ማህበራዊ ደረጃን የሚጠቁም ነው፡፡

**ፎቶ 25. ብርቅጥል**





**ምንጭ፡- በ14/01/14 ዓ.ም ጎራንዳ ቀበሌ በአጥኚው የተወሰደ**


**አርጌሽ ልሙት፡-** የሚባለው ጌጣጌጥ እንደ እንቆ መስቀል ከመዳብ፣ ከነሃስ አንዳንድ ጊዜም ከብር በአንጥረኛ የሚሰራ የአንገት ጌጥ ነው፡፡ አቶ ፍቃዱ ግዛው *"አርጌሽ ልሙት የአንገት መስቀልን ያገቡና ያላገቡ ወጣት ወንዶችና ሴቶች በአንገታቸው ላይ የሚያደርጉት የጌጥ ዓይነት ነው፡፡ አርጌሽ ልሙት የተባለውም የሚያገባትን ወይም ያገባትን ሴት ለዘላለሙ የኔ ብቻ አድርጌሽ ልኑር እንደማለት ነው"* ሲሉ ይናገራሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ/ጎራንዳ ቀበሌ፡ መስከረም 14 ቀን 2014 ዓ.ም)፡፡ ይህን የአንገት ጌጥ መነሻው ወንዶች ለሚያገቧቸው ሴቶች ውበታቸውን አጉልቶ ለማሳየት ቢሆንም ያላገቡ ሴቶችም ለመዋቢያነት የሚገለግሉባቸው መሆኑን ነው፡፡

**ፎቶ 26. አርጌሽ ልሙት**

አርጌሽ ልሙት ጌጥ በወንዶች ሲደረግ



አርጌሽ ልሙት ጌጥ በሴቶች ሲደረግ



**ምንጭ፡- በ25/04/14 ዓ.ም ዓለም ከተማ በአጥኚው የተወሰደ**

**ማህተብ (ጎፍታ)፡-** ይህ የአንገት ጌጥ ከጥለት ክር (ዘሃ) በተጠቃሚው ማህበረሰብ የሚሰራ ሲሆን ከጫፉ ላይ ጭራ መሰል ዘርፍ (ጎፍታ) በተለያየ ቀለማት እንዲኖረው ተደርጎ ይዘጋጃል፡፡ የመዋቢያ ጌጡ ብቻው ወይም ከተለያዩ የአንገት ጌጦች ጋር አብሮ ይደረጋል፡፡ አቶ በላይሁን ደሳለኝ *“ጎፍታ (ማህተብ) ያገቡ ወጣት ወንዶችና ሴቶች ያደርጉታል”* ይላሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ/ኮራ ወንጪት ቀበሌ፡ መስከረም 21 ቀን 2014 ዓ.ም)፡፡ እዚህ ላይ ማህተብ (አተበ፣ አመለከተ፣ ባከ) ከሚል የግዕዝ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጓሜውም መታወቂያ ወይም ምልክት እንደማለት ነው፡፡ በአንገታቸው ላይ ማህተብ (ጎፍታ) ያገቡ ሰዎችን ያመለክታል፡፡

**ፎቶ 27 የሴቶች ማህተብ (ጎፍታ)**



**ፎቶ 28 የወንዶች ማህተብ (ጎፍታ)**



**ምንጭ፡- በ25/01/14 ዓ.ም ዓለም ከተማ በአጥኚው የተወሰደ**

**እንቆ፡-** በመስቀል ቅርፅ ከመዳብ ወይም ከነሃስ በመጠን ትንሽ ተደርጎ በአንጥረኛ የሚሰራ የአንገት ጌጥ ሲሆን በሁለቱም ፆታ ያሉ ህፃናትና ወጣቶች ለመዋቢያነት ይጠቀሙበታል፡፡ አቶ አውራሪስ ማብረጃ *“እንቆ የተባለበት ምክንያት አንገት ላይ በጥቁር ክር ሰብሰብ ወይም አነቅ አድርጎ ስለሚታሰር ነው፡፡”* (ቃለ መጠይቅ/ኮራ፡ መስከረም 21 ቀን 2014 ዓ.ም)፡፡

**አሸንክታብ ወይም ቁርበተ ሀሊም፡-** ክታብ ቃሉ አረብኛ ሲሆን ትርጉሙም መፅሐፍ እንደ ማለት ነው፡፡ የአቢሲኒያ ድረ ገፅ መዝገበ ቃላት (2024) ለሕመም መድሃኒት እንዲሆን በክርስትና ስም አስማት እየተፃፈ በባሕር ዐረብ (ቆዳ) ተሰፍቶ በሐር ክር እየተሰካ አንገት ላይ የሚንጠለጠል ነው ሲል ያብራራል፡፡ ይህን ከቆዳ የሚሰራ የአንገት ጌጥ ክታብ፣ አሸንክታብ/ቁርበተ ሀሊም ተብሎ ይጠራል፡፡ ወ/ሮ ሽታ አባቡ *“በብዛት በአዋቂ ሴቶች አልፎ አልፎ በሁለቱም ፆታዎች ህፃናት አንገት ላይ ለመዳኒትና ለጌጥ ተብሎ ይደረጋል”* ይላሉ፡፡ (ቃለመጠይቅ/ገረን ቀበሌ፡ ነሐሴ 12 ቀን 2013 ዓ.ም)፡፡ የመዋቢያ ቁሰ ቅርፁ ስንመለከት ሞላ፣ ጠፍጣፋ፣ ክብ፣ ሦስት መዓዘን ሆኖ እንደሚሰራ በምልከታ ለማወቅ ችያለሁ፡፡ የቁሱ ቅርፅ እንደሚሰራበት ቁስ፣ የፈውስ ዓይነት፣ እንደሚዘጋጅበት ጊዜ ወዘተ የሚለያይ ነው፡፡

ፎቶ 29.አሸንክታብ በህፃትና ወጣቶች





ምንጭ፡- 2ቱ ፎቶዎች በ12/12/13 ዓ.ም ገረን ቀበሌ 3ኛው ኮራ ቀበሌ በ21/01/14 ዓ.ም ኮራ ቀበሌ በአጥኚው የተወሰዱ

**የሙሽራ አገልግል፡-** ይህ የስፌት ቁስ ስንደዶ፣ አክርማ፣ ሰበዝና አለላ ከሚባሉ የሳር ዓይቶች የሚሰራና በእንስሳት ቆዳ የሚለበጥ ነው፡፡ ከሙዳይ ጀምሮ በየደረጃው የተለያዩ መጠን ያላቸው የአገልግል ዓይነቶች ያሉ ሲሆን በአማካይ 2 (ሁለት) ኪሎ ግራም መመዝን የሚችለውን አገልግል ያገቡ ወጣት ሴቶች በአንገት በማንጠልጠል እንደመዋቢያ ይገለገሉበታል፡፡ ወ/ሮ ምሳው ፀጋው *"ለሴቷ ስታገባ በጥሎሽ የተሰጣትን የአለላ አገልግልን በአንገቷ ላይ ታንጠለጥለዋለች፡፡ በአገልግሉ ውስጥ ደግሞ ሚዶ፣ ኩል፣ ሽቶ፣ መስታወት ያሉ ማጌጫዎችን ትይዝበታላች፡፡"* ሲሉ ቁሱ ያለውን ፋይዳ ያብራራሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ/ግሬት ቀበሌ፡ ጥር 10 ቀን 2014 ዓ.ም)፡፡

ፎቶ 30. ሙሽራ አገልግል



ምንጭ፡- በ12/12/13 ዓ.ም ገረን ቀበሌ በአጥኚው የተወሰደ

**ሀብል፡-** ከወርቅ፣ ከብር፣ ከነሃስ ወይም ከሌላ ማዕድን በአንጥረኞች የሚሰራ ሲሆን በሴቶች አንገት ላይ የሚንጠለጠል ወይም የሚደረግ ጌጥ ነው፡፡ እንደ አቶ አውራሪስ ማብረጃ *ይህን የአንገት ጌጥ የከተማ ሰው ባል እንጂ የእኛ አልነበረም፡፡ አሁን ላይ ግን በውድ ዋጋ እየተገዛ ለሚያገቡ ሴቶች ጥሎሽ ይጣላል፡፡ ያገቡ ሴቶችም ማህተብ (ነፍታ) ትተው ዘመን አመጣሹን (ሀብል) ጌጥ በአንገታቸው ላይ ያስራሉ፡፡"* (ቃለ መጠይቅ/ኮራ ወንጪት ቀበሌ፡ መስከረም 21 ቀን 2014 ዓ.ም)፡፡ እዚህ ላይ ይህ አዲስ ቁሳዊ ባህል በተግባር አዲስ በዋጋው ደግሞ ውድ የሆነ ልምምድ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡

**የአንገት ክር (ማህተብ)፡-** ይህ በአንገት ላይ የሚታሰር ክር (ማዕተብ) የወረዳው ማህበረሰብ ደስታውን እና ሀዘኑን ለመግለፅ ይጠቀምበታል፡፡ በዚህም መሰረት የተጠኚው ማህበረሰብ አባላት 99.9 ከመቶ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታዮች መሆናቸውን ከወረዳው ባ/ቱ ጽ/ቤት የተኘነው መረጃ ይጠቁማል፡፡ የማህበረሰቡ አባላት የተጠመቁ ክርስቲያኖች መሆናቸውን ለማሳወቅ ከሕፃን እስከ አዛውንት ያሉት በሙሉ በአንገታቸው ላይ ጥቁር ክር ያስራሉ፡፡ ይህ በአንገት ላይ የሚታሰር ጥቁር ክር ከሃይማኖታዊ መለያው በተጨማሪ ደስታን ለመግለፅና ውበትን ለማጉላት የተለያዩ ጌጣጌጦችን በአንገቱ ላይ ለማሰር ያገለግላል፡

በሌላ መልኩ የተጠኚው ማህበረሰብ አባላት ሰው በሞት ሲለይ ሀዘንን ለመግለፅ በአንገታቸው ላይ ከጥጥ ፈትል የሚዘጋጅ ነጭ ክር ያስራሉ፡፡ አቶ ኃይለማሪያም አበራ ገለፃ *"በአንገት ላይ የሚታሰረው ነጭ ክር እንደ ሀዘኑ ክብደትና ከሟች ጋር እንደለው ቅርበት የሚወሰን ሆኖ በአማካይ ከ6 ወር እስከ አንድ ዓመት ድረስ አንገት ላይ ይቆያል፡፡"* (ቃለ መጠይቅ/ግሬት ቀበሌ፡ ጥር 10 ቀን 2014 ዓ.ም)

**ፎቶ 31. የአንገት ነጭ ክር (ማህተብ)**



**ምንጭ፡- በ21/01/14 ዓ.ም ጎራንዳ ቀበሌ በአጥኚው የተወሰደ**

### 4.2.3. የጆሮ ጌጦች

ሰውነትን ለማሻሻል ከሚደረግባቸው ሰው ሰራሽ ዘዴዎች ውስጥ አንዱ በጆሮ ላይ የሚንጠለጠሉ ወይም የሚለጠፉ የጆሮ ጌጦች ናቸው፡፡ እነዚህ የጆሮ ጌጦች ከልዩ ልዩ ቁስ የሚሰሩ ሲሆኑ ውበትን ከማጉላት በተጨማሪ ዕድሜ፣ ፆታ፣ ማንነትና ማህበራዊ ደረጃን ለመግለፅ የሚያገለግሉ ናቸው፡፡

**ሎቲ፡-** ይህ የጆሮ ጌጥ በሴቶች የጆሮ ልም (ስስ) አካል ላይ የሚንጠለጠል ሲሆን ከብር፣ ከነሃስ፣ ከመዳብ፣ ከኒኬል ወይም ከሌላ ማዕድን በአንጥረኛ የሚሰራ ወይም ከገበያ የሚገዛ ነው፡፡ ወ/ሮ ምሳው ፀጋው *"ሎቲ ዘርፍ ያለው የአዋቂ ሴቶች የጆሮ ጌጣችን ነው፡፡ ወጣቹ አያደርጉትም በዋጋ ውድ አይደለም፣ የምንገዛውም ከገበያ ነው"* ሲሉ ያብራራሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ/ግሬት ቀበሌ፡ ጥር 10 ቀን 2014)፡፡ በሎቲው ላይ ያሉት ተንጠልጣይ ጌጦቹ እንደ ተጠኚው ማህበረሰብ እምነት የቤተክርስቲያን ጉልላት ዘርፍን የሚያመላክት ነው፡፡

**የጆሮ ጉትቻ፡-** ከወርቅ፣ ከብር፣ ከነሃስ ወይም ከሌላ ማዕድን በአንጥረኛ የሚሰራ ወይም ከገበያ የሚገዛ ሲሆን በሴቶች የጆሮ ልም (ስስ) አካል ላይ የሚንጠለጠል ወይም የሚለጠፍ ጌጥ ነው፡፡ ጆሮ ጌጥ በብዛት ያገቡ ሴቶች ውበትን ለማጉላት የሚጠቀሙበት ሲሆን በሰርግ ጊዜ አንዱ የጥሎሽ ሆኖ ይቀርባል፡፡ አቶ ሰንበት ቸረኝ *"ዋጋው ውድ የሆነ ጆሮ ጌጥ የሚጥል ሀብታም ሰው ነው፡፡"* ይላሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ/ግሬት ቀበሌ፡ ጥር 10 ቀን 2014 ዓ.ም)፡፡ ይህም ማህበራዊ ደረጃን ለማሳየት የሚያገለግል ነው፡፡ በጥቅሉ ቁሶቹ የለባሹን ውበት ከማጉላታቸው በተጨማሪ የሚሰሩባቸው የቅርፅ ዓይነቶች የማህበረሰቡን እምነት፣ ፍልስፍና፣ አመለካከት፣ እሴት ወዘተ መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ የጆሮ ጉትቻን መቼ ማድረግ እንደተጀመረ ማወቅ ባይቻልም ተጠኚው ማህበረሰብ እንደሚከተለው እምነት ምሳሌ 25፡12 *"የምትሰማን ጆሮ የሚዘልፍ ጠቢብ ሰው እንደ ወርቅ ጉትቻ እንደሚያንፀባርቅም ዕንቁ እንዲሁ ነው"* ከሚለው መጽሐፈ ቅዱሳዊ ትርጓሜን መነሻነት የተጀመረ ሊሆን ይችላል፡፡

በጥቅሉ እነዚህ ሰውነትን ለማሻሻል ሚደረጉ ጌጣጌጦች Evans (1970) በሰውነት ላይ የሚጨመሩ ጌጣጌጦች ዋና ተግባራቸው ውበትን ለማጉላት ነው ሲሉ እንደገለፁት የተጠኚው ማህበረሰብ የሚጠቀሟቸው ጌጣጌጦች ውበትን ለማጉላት፣ማህበራዊ ደረጃን ለማሳየት፣ ማንነትን ለመግለፅ፣ ፆታን ለማመላከት ይጠቀሙባቸዋል፡፡፡

**ፎቶ 32. የጆሮ ጌጥ**

**ጉትቻ የጆሮ ጌጥ**



**ሎቱ የጆሮ ጌጥ**



**ምንጭ፡- በ12/12/13 ዓ.ም ገረን ቀበሌ እና በ10/05/15 ዓ.ም ግሬት ቀበሌ በአጥኚው የተወሰደ**

## 4.2.4.የወገብ ጌጥ

ውበትን ለመጨመር ማሻሻያ ከሚደረግባቸው የሰውነት አካል ውስጥ አንዱ በወገብ ላይ የሚታሰሩ ወይም የሚደረጉ ናቸው።

**ዝናር፡-** ከጠፍር/ከሸራ የሚሰራ የጥይት መያዣ ሲሆን በወንዶች ወገብ ላይ ልክ እንደቀበቶ የሚታጠቁት ነው። የአቢሲኒያ ድረ ገጽ መዝገበ ቃላት (2024) "ከጠፍር ወፍለቅ የሚለፋ የጥይት መደርደሪያ ሆኖ የወገብ መታጠቂያ ዝናር ሰቅ (ቀበቶ)" ነው በማለት ይተረጉመዋል። እዚህ ላይ አባቶቻችን የጥበብ ባለቤቶች በመሆናቸው ዝናርን በሠላም ጊዜ ለመዋቢያነት ወይም ለማጌጥ በጦርነት ጊዜ የጥይት አረራቸውን ደርድረውና የሕይወት መስዋዕት ከፍለው ሀገራቸውን ከጠላት የተከላከሉበት ቁስ ነው። አቶ ክብረቴ አስፋው *"ዝናር ከአባቶቻችን የወረስነው የራስ መጠበቂያ ዕቃ ሲሆን ጥይትን በወገብ ላይ ለመያዝና ለማጌጥ እንጠቀምበታለን፣ ዝናር የሚታጠቁ አዋቂ ወንዶችና ገንዘብ ያላቸው ናቸው።"* (ቃለ መጠይቅ/ግሬት ቀበሌ፡ ጥር 10 ቀን 2014 ዓ.ም)። እዚህ ላይ ዝናር ራስን ከጠላት ለመከላከልና ውበትን ማጉላት የሚያገለግልና በሀብትና በስልጣን ደረጃቸው ከፍ ያሉ እንዲሁም በአካባቢው ጀግና የሚባሉ ሰዎች የሚገለገሉበት ቁስ መሆኑን በ12/12/13 ዓ.ም በመስክ ምልከታ ወቅት ለመገንዘብ ችያለሁ።

ፎቶ 33. የወገብ ጌጥ




ምንጭ፡- በ25/01/14 ዓ.ም ዓለም ከተማ እና በ12/12/13 ዓ.ም ገረን ቀበሌ በአጥኚው የተወሰደ

**ጨቤ፡-** ይህ ባህላዊ ቁስ ከቢላ ትንሽ ከፍ ተደርጎ በአንጥረኛ ከብረት የሚሰራ ሲሆን በበዓላትና በአዘቦት ቀናት አዋቂና ወጣት ወንዶች በወገብ ላይ የሚያስሩት ቁስ ነው፡፡ ጨቤ በአንደኛው ጫፍ በኩል ሹል የሆነ፣ በሌላኛው ጫፉ በኩል ደግሞ ከከብት ቀንድ የሚሰራ መያዣ እጀታ አለው፡፡ ቁሱ በሁለቱም ጎኖቹ (ጠርዞቹ) በኩል ስል ስለትና በወገብ ላይ መታሰር እንዲችል ከእንስሳት ቆዳ የተሰራ መያዣ ማህደር (ሰገባ) ያለው ነው፡፡ ጨቤ ውበትን ለማጉላት፣ የአካል ደህንነትን ለመጠበቅ፣ ዕድሜ፣ ፆታ፣ ማንነትና ማህበራዊ ደረጃን ለመግለፅ ይጠቀሙበታል፡፡ አቶ አማረ ንጉስ *"ጨቤ ያገቡም ያላገቡም ወንዶች ከወገባቸው በስተቀኝ በኩል የሚታጠቁት የውበትና የጀግንነት መሳሪያ ሲሆን አደን ለማደን፣ እንስሳት ለማረድ ወይም ለመባረክ፣ ከጠላትና ከአውሬ ራስን ለመጠበቅ ያገለግላል፡፡"* (ቃለ መጠይቅ/ጎራንዳ ቀበሌ፡ መስከረም 14 ቀን 2014)፡፡ ከዚህ አንፃር ይህ ቁስ የወንዶችን ውበት ለማጉላት እንስሳትን ለማረድ ወይም ለመባረክ ጨምር የሚገለግል ነው፡፡

## 4.2.5. የእጅ ጌጦች

የተጠኚው ማህበረሰብ ህፃናት፣ ወጣቶችና እናቶች በክንድ፣ በጣት፣ በእጅ የሚያዙ ሀገረሰባዊ የመዋቢያ ጌጣጌጦች ማለትም ብራምባር፣ ቀለበት፣ ጨሌ፣ የእጅ ጎፍታ (ዛጎል ጌጥ)፣ ዱላ፣ ጭራ እና ጃን ጥላ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ጌጣጌጥ የሚባሉት የተጠኚው ማህበረሰብ አባላት የሚደርጓቸውን ያጠቃልላል፡፡

**የእጅ አምባር/ብራምባር፦** ከነሃስ፣ ከኒኬል ከመዳብ እና ከብር በአንጥረኛ የሚሰራና ያገቡ ሴቶች የሚያደርጉት የእጅ ጌጥ ነው፡፡ አምባር/ብራምባር በሦስት ዓይነት መጠን ይሰራል፡፡ ይህም ቀጭን አምባር አማካይ የክብደት መጠኑ 15 ግራም፣ እንዲሁም መካከለኛ ብራምባር አማካይ የክብደት መጠኑ 25 ግራም፣ በመጨረሻም ሰፊ አምባር አማካይ የክብደት መጠኑ 35 ግራም ተደርጎ ይሰራል፡፡ *ሰፋ ተደርጎ የሚሰራው የሀብት ደረጃን የሚመላከት ነው፡፡ አምባር ውበትን ከማጉላቱም በላይ ያገቡ ሴቶችን ለመለየት መረጃ የሚሰጥ ከመሆኑ በተጨማሪ እናቶች ቁርጥማትና የትኩሳት ህመም ሲሰማቸው አምባሩን በእጃቸው ላይ ያደርጉታል፡፡"* ሲሉ መረጃ ሰጪዎቹ ያብራራሉ፡፡ (የቡድን ሁለት ተቀያዮች/ ገረን ቀበሌ፡ ግንቦት 01 ቀን 2015 ዓ.ም)፡፡

የአምባር ተምሳሌታዊ ትርጉሙን ስንመለከት ጌታ እየሱስ ክርስቶስ በቀራኒዮ መስቀል ላይ በከፈለው የህይወት መስዋዕትነት ጊዜ በቀኝና በግራ እጁ ላይ የተቸነከሩትን ሳዶርና አላዶር ቅንዋተ መስቀል ሚስማሮችን፣ የአገባች ሴት እጅ መያዝን፣ በፍቅር መማረክን፣ አብሮ ለመዝለቅ ቃል መግባትን የሚያመላክት ነው፡፡ በተጨማሪም በመጽሃፍ ቅዶስ ኦሪት ዘፍጥረት ላይ የይስሐቅ ሚስት የነበረችው ርብቃ "የሎሌውን ግመሎቹ ውሃ እንዳጠጣችና ሎሌው የወርቅ ቀለበትና አምባር እንደሰጣት (ዘፍጥረት 24:22) ይገልፃል፡፡ ስለሆነም ውድና ውብ የሆኑ የጌጥ ዕቃዎች ከስነ ፍጥረት ጀምሮ መጠቀም የተጀመረ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

**ፎቶ 34. የወጣቶች ብራምባር ፎቶ 35. የእናቶች ብራምባር**





**ምንጭ፦ በ14/01/14 ዓ.ም ጎራንዳ ቀበሌ እና በ10/05/15 ዓ.ም ግሬት በአጥኚው የተወሰደ**

**ቀለበት፦** ይህ የእጅ ጣት ከነሐስ፣ ከመዳብ፣ ከብር፣ ማዕድናት በአንጥረኛ የሚሰራ ነው፡፡ ቀለበት በሁለቱም ፆታ ያሉ ወጣቶች ውበትን፣ ማህበራዊ ደረጃን፣ ያገቡ መሆኑን ለመግለጽ፣ አዋቂ ሴቶች ደግሞ ከህመም ለመዳን በሚል እምነት ያደርጉታል፡፡ አቶ አማረ

ንጉስ *"ያገቡ ሰዎችና ሀብታም ሰዎች የብርና የወርቅ ቀለበት ያደርጋሉ። አዋቂዎቹ ደግሞ በእጅ ላይ ብረት ማሰር በሰይጣን ከመለከፍ ያድናል በሚል እምነት ብር ቀለበትን በጣታቸው ላይ ያስራሉ"* ይላሉ። (ቃለመጠይቅ/ጎራንዳ ቀበሌ፡ መስከረም 14 ቀን 2014 ዓ.ም)።

**ጨሌ ጌጥ፡-** በተለያዩ ቀለማት በፋብሪካ የሚሰራ ሆኖ ክር ማሳለፊያ ያለው ውስጠ ክፍት የሆነ ትንሽ ጌጥ ነው። የሚሰራውም ከፕላስቲክ መሰል ቁስ ሲሆን ይህን ሃሳብ አቶ በላይሁን ደሳለኝ ሲገልፁ *"ጨሌ በእጅና በአንገት ላይ ያገቡ ሴቶች የሚያደርጉት ጌጥ ነው። አሁን ላይ ያላገቡ ሴቶችም ያደርጉታል"* ይላሉ። የቁሱን ለውጥና ተግባር ይገልፃሉ።(ቃለ መጠይቅ/ኮራ ወንጪት ቀበሌ፡ መስከረም 21 ቀን 2014 ዓ.ም)።

**ጥላ ወይም ጃንጥላ፡-** ከፀሐይና ከዝናብ ለመከላከል፣ ውበትን ለማጉላትና ማህበራዊ ደረጃን ለማሳየት፣ ያገቡና ያላገቡ ሴቶችን ለመለየት ያገለግላል። ወ/ሮ አስቴር አንዳርጋቸው *"ጃንጥላ ሴቶች ሲያገቡ አንዱ የጥሎሽ ዕቃ ሲሆን ጃንጥላ የያዘች ሴት ያገባች መሆኑ ይታወቃል። ለመዋቢያነት ትገለገልበታለች"* ይላሉ። (ቃለ መጠይቅ የባ/ቱ/ጽ/ቤት ኃላፊ/ዓለም ከተማ፡ ታህሳስ 27 ቀን 2014 ዓ.ም)። እዚህ ላይ ያገቡ ሴቶች ጃንጥላ የሚይዙበትን ተምሳሌታዊ ትርጉሙን ስንመለከት የጃንጥላ ቅርፅ ከቤት ጎጆ ጋር የሚያመሳስለው በመሆኑ በአንድ ጣሪያ ስር ቤተሰብ መስርቶ መኖርን ያመለክታል።

**የእጅ ጎፍታ፡-** ይህ ጌጥ ከዛጎልና ከእንስሳት ቆዳ የሚሰራ ሲሆን በሁለቱም ፆታ ህፃናት እጅ ላይ የሚታሰር ነው። በማህበረሰብ ልምድ መሰረት ቁሱ ለበሽታ መከላከያ ለውበት የሚያገለግል ነው። *"እጅ ጎፍታ የህፃናቱን ውበት ከመጠበቁ በላይ* "የእጅ ጎፍታ ለጌጥና *ህፃናቱ ዐይን እንዳይገቡ (እንዳይታመሙ)፣ እጃቸውን ሲያወዛውዙ በሚሰማው ድምፅና በሚያዩት የእጅ ጌጥ እንዲጫወቱ የሚያደርግ ነው"* ይላሉ።(ቡድን ሁለት ተወያዮች/ በገረን ቀበሌ፡ ግንቦት 01 ቀን 2015)።

**ፎቶ 36. የእጅ ጎፍታ**



**ምንጭ፡- በ25/04/14 ዓ.ም ዓለም ከተማ አጥኚው የተወሰደ**

**ዱላ፡-** በሁሉም የዕድሜ ክልል ያሉ ወንዶችና በዕድሜ የገፉ ሴቶች በበዓላትና በአዘቦት ቀናት የሚገለገሉበት ነው፡፡ ይህ ቁስ ለመዋቢያነት፣ ለምርኩዝ (ለመደገፍ)፣ ከሰውና ከእንስሳት ጥቃት ራስን ለመጠበቅ ወይም ለመከላከል ሁሉም ወንዶችና አዋቂ ሴቶች ይገለገሉበታል፡፡ የዱላ አሰራርና ዓይነቶችን መረጃ ሰጪዎቼ  እንደሚከተለው ገልፀውታል፡፡

> *ዱላ በረሃ ከሚገኙ የተመረጡ ተክትሎ ይዘጋጃል፡፡ ዘመናዊ ነን ያሉ ሰዎች ካልሆኑ በቀር በሁሉም ወንዶች የሚያዝ ነው፡፡ አዋቂ ሰዎች የምንይዘው ዱላ ከዘራ፣ ዘንግ፣ መቋሚያ ይባላሉ፡፡ ወጣቶቹ የሚይዙት ደግሞ ስዕል፣ ከዘራ፣ አጭር፣ ረጅም፣ ዝግር (ሽመል) ይባላል፡፡ የአዋቂዎች ዱላ ብዙም ጌጥ አይደርግበትም፡፡ የወጣቶቹ ዱላ ግን ለጥንካሬና ለውበት በበሬ ጅራት (ጎመድ)፣ በጥምዝ ብረት (ጅንፎ) እና በአዝራር ያጌጠ ነው፡፡ ዱላው እንዲጠነክርና ውበት እንዲኖረው ለረጅም ወራት ጭስ ላይ ተሰቅሎ በቅቤ እንዲታሽ ይደረጋል፡፡ የዱላ አዘገጃጀት ባለሟልነት የሚያሳይ ነው፡፡* (የቡድን አንድ ተወያዮች/ ጎራንዳ ቀበሌ፡ መስከረም 14 ቀን 2014)

ከዚህ ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው “ከሰው መርጦ ለሹመት ከእንጨት መርጦ ለታቦት” እንደሚሉት አባቶች ቁሱ ሲዘጋጅ የራሱ ጥበብ ያለው መሆኑንና ተግባሩም ውበትን ለማጉላት፣ ራስን ከአደጋ ለመጠበቅ የሚያስችል ነው፡፡ በተጨማሪም የሚዘጋጁ የዱላ ዓይነቶች የሰዎቹን እውቀት፣ ጥበብና ፍላጎትን መሰረት ያደርጋል፡፡

**የእጅ ጭራ፡-** መረጃዎችን ለመሰብሰብ በተንቀሳቀስኩባቸው ቀበሌዎች በምልከታ እንዳስተዋልሁት ተጠቃሚው ማህበረሰብ ከቃጫና ከማዳበሪያ የሚያዘጋጁት ሲሆን አልፎ ከፈረስ ጭራ የተዘጋጀውን ደግሞ ከገበያ ይገዛሉ፡፡ ጭራ በዕድሜ የገፉ አባቶች የሚያዘወትሩት ሲሆን ትናንሽ በራሪ ንፍሳትን ለመከላከል ይጠቀሙበታል፡፡

**ፎቶ 37. ዱላ**

የወጣቶች ዱላ



የአዋቂዎች ዱላ



ምንጭ፡- በ25/01/14 ዓ.ም ዓለም ከተማ እና በ12/12/13 ዓ.ም ገረን ቀበሌ በአጥኚው የተወሰደ

በጥቅሉ ከላይ በምዕራፉ በእያንዳንዱ አልባሳትና ጌጣጌጦች የቀረቡ ትንታኔዎችን ከቁሶቹ ፋይዳ አንፃር ጠቅለል አድርገን ስንመለከት፡-

**ማህበራዊ ደረጃን ከማሳየት አኳያ፡-** የተጠኚው ማህበረሰብ አልባሳትና ጌጣጌጦች በለባሹ ማህበረሰብ መካካል ማህበራዊ ደረጃዎችን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ከአልባሳት "ጉያ ቀሚስ" በእናቶች ብቻ የሚለበስ መሆኑ፣ "ውስጥ ልብስ" ለደህንነት መጠበቂያ ብቻ ሳይሆን ሀብትን ለማሳየት የሚያገለግል መሆኑ፣ "ቡልኮ" ከፍተኛ የገቢ ደረጃ ያላቸው ወይም የእምነትና የሀገር ሽማግሌዎች የሚለብሱት መሆኑ፣ ከጌጣጌጦቹ ደግሞ የአንገት ሃብል፣ ድንብል፣ ብር መስቀል ወዘተ መዋቢያዎች ማህበራዊ ደረጃዎችን የሚያሳዩ ናቸው፡፡

**ኃይማኖትን ከመግለፅ አኳያ፡-** የተጠኚው ማህበረሰብ አልባሳትና ጌጣጌጦች ማለትም እንደ ልብሰ ተክህኖ (የካህናት ልብስ)፣ ልብሰ ምንኩስና (የመነኩሴ ልብስ)፣ ቆብ፣ ነጭ ሻሽ፣ ወጣቶች ልበሱ ላይ የሚያርጉት የመስቀል ቅርፅ ያለው ጥልፍ እንዲሁም በሁሉም ዕድሜና ፆታ ያሉ ሰዎች በአንገታቸው ላይ የሚያደርጉት መስቀል፣ የአንገት ክር (ማህተብ) ወዘተ ኃይማኖትን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

በተጨማሪም በሴቶችም ሆነ ወንዶች በልብሳቸው ላይ የሚያሰሩት የመስቀል ምልክት፣ በህፃናት እጅና ፀጉር ላይ የሚደረጉ ዛጎልና ጎፍታ፣ እንዲሁም ሴቶች በእጃቸው ላይ የሚያደርጉት ብራምባር፣ በአንገታቸው ላይ የሚያደርጉት አሸንክታብ ለመዋቢያነት ከማገልገሉ ባሻገር እርኩስ መንፈስን ለመከላከል የሚያስችል እንደሆነ በለባሾቹ ይታመናል፡፡

**ፆታን ከማመልከት አኳያ፡-** የማህበረሰቡ አልባሳትና ጌጣጌጦች ፆታን መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ ለአብነት ያህል እንደ ቀሚስ፣ አንገት ልበስ፣ መቀነት፣ ሻሽ፣ ሴቶችን፣ እንደ ቁምጣ፣ ጃኬት፣ ፎጣ፣ ካኒቴራ፣ ኮፍያ፣ ወዘተ ያሉ ደግሞ ወንዶችን እንዲሁም ከጌጣጌጦች ብርመስቀል፣ ጨሌ፣ ብራምባር፣ ጆሮ ጉትቻ፣ ኮንጎ ጫማ ደግሞ ሴቶችን እንደ ዱላ፣ ዝናር፣ ጩቤ ያሉት ደግሞ ወንዶችን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

**ከተግባቦት** (Communication) **አኳያ፡-** አልባሳትና ጌጣጌጦቹ የተለያዩ መልዕክቶችን የሚያስተላልፉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ቡልኮ ማህበራዊ ደረጃን ለመግለፅ፣ ቁምጣ፣ ሱሪ፣ ቀሚስ ፆታን ለማመላከት፣ መቀነት፣ አንገት ልብስ፣ ኩታ፣ ጋቢ ያሉት ደግሞ ማንነትን ለመጠቆም፣ ጉያ ቀሚስ፣ ነጠላ፣ ጋቢ ዕድሜ ለመግለፅ እንዲሁም ጥምጥም፣ ነጭ ሻሽ፣ የመነኩሴ ልብስ ደግሞ ሃይማኖትን የሚገልፁ/መልዕክት የሚያስተላልፉ ናቸው፡፡

**ማንነትን ከመግለፅ አኳያ፡-** አልባሳት ከሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎት ውስጥ አንዱ ሲሆን የሰዎች ማንነት በማሳወቅ በኩል ከፍተኛ ሚና የሚጫወት ነው፡፡ የማህበረሰብ አልባሳት እና ጌጣጌጦች የግለሰቦችን ወይም ቡድን ማንነት በመግለፅ ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ለምሳሌ የሚከተሉት እምነት ለማሳየት የመስቀልን ምስል በሚገለገሉባቸው አልባሳት ላይ በጥልፍ መልክ ጌጣጌጦቹን የመስቀል ቅርፅ ያሰራሉ፡፡

**ማህበራዊ ሁኔታዎችን ከማመላከት አኳያ፡-** የመርሐቤቴ ወረዳ ማህበረሰብ አልባሳትና ጌጣጌጦች ማህበራዊ ሁኔታዎችን የሚያመላክቱ ናቸው፡፡ ለምሳሌ መቀነት መታጠቅ፣ አንገት ልብስ መልበስ፣ ብራምባር ማድረግ ያጋቡ ሴቶች መሆናቸውን የሚገልፅ ነው፡፡ እንዲሁም የነጠላ/ጋቢ ጥለትን ወደ ጭንቅላት አድርጎ (ዘቅዝቆ) መልበስ፣ ፀጉር ሙሉ ለሙሉ መላጨት፣ በአንገት ላይ ነጭ ክር ማሰር፣ ወዘተ ጉዳዮች ሀዘንን ያመለክታሉ፡፡

**ዕድሜን መግለፅ አኳያ፡-** ሀገረሰባዊ አልባሳትና ጌጣጌጦች የለባሹን የዕድሜ ደረጃ ለመግለፅ የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ቡልኮና ተነፋነፍ ሱሪ በአባቶች፣ ጉያ ቀሚስ በእናቶች፣ ጠባብ ቀሚስ በወጣቶች የሚለበስ ሲሆን ፎጣ ደግሞ አልፎ አልፎ በህፃናት አብዛኛውን ጊዜ በወጣቶች ወንዶች የሚለበሱ ናቸው፡፡ ከጌጣጌጦች ደግሞ አርጌሽ ልሙት፣ ድምርጥ፣ ጎፍታ በወጣቶች የሚደረጉ ሲሆን እንደ ዛጎልና አዝራር ያሉ ጌጦች በህፃናትና ወጣት ሴቶች የሚያደረጉ ቁሶች ናቸው፡፡

**የመከላከል ተግባርን በተመለከተ፡-** የሰው ልጅ አካል በተለያዩ ውጫዊ ጉዳዮች የሚጠቃ በመሆኑ የአልባሳት አንደኛው ተግባር የሰውነት አካል ደህንነትን መጠበቅ/መከላከል ነው፡፡ ይህም ሰውነትን ከሙቀት፣ ከብርድ፣ ከዝናብ፣ ከእሾህ፣ ከጋሬጣ፣ ከእንቅፋት፣ ከእንስሳት ጥቃት ወዘተ ጉዳዮች መከላከል ማለት ነው፡፡ የተጠኚው ማህበረሰብ አልባሳት ሰውነትን ከውጫዊ አካላት የመከላከል ተግባር ያላቸው ናቸው፡፡

**ውበትን ከመግለፅ አኳያ፡-** የተጠኚው ማህበረሰብ አልባሳትና ጌጣጌጦች ልከኛ ወይም ጨዋነት የሚባል የአለባበስ ስርዓት ያላቸው ሲሆን በተግባራቸውም መሸፈን ያለበትን የሰውነት አካል የሚሸፍኑና አካልን ከውጫዊ ጥቃት የሚከላከሉ እንዲሁም በቀለም፣ በጌጣጌጥና በአሰራር ዲዛይናቸው ውበትን የሚያጎሉ ናቸው፡፡

## 4.2 የፀጉር አሰራር

በተጠኚው ማህበረሰብ ውስጥ ጉድሮ፣ ቁንጮ፣ ጋሜ፣ ጎፈሬ፣ ቅምቅሞ፣ ቁንዲድ፣ ሹርባና ልጩ የሚባሉ የፀጉር አሰራር ዓይነቶች አሉት፡፡ እነዚህ የፀጉር አሰራር ዓይነቶች ፆታን፣ ዕድሜን፣ ማንነትን መሠረት ያደረጉ ወይም የሚገልፁ ናቸው፡፡

**ልጩ፡-** ፀጉርን ሙሉ ለሙሉ መላጨት ወይም ማስወድ ማለት ነው፡፡ ይህን የፀጉር አሰራር በብዛት የሚጠቀሙት በሁለቱም ፆታ ያሉ አዋቂዎች ናቸው፡፡ ይህ የፀጉር አሰራር ደስታና ሀዘን ለመግለፅ ያገለግላል፡፡ ወ/ሮ በዛብሽ ዘነበ *"እንደ ወጣቶቹ ፀጉር አሳድገን ሹርባ ስለማንሰራ በየጊዜው እንላጨዋለን፡፡ ደግሞም ቤተሰብ ወይም የቅርብ ወዳጅ ሲሞት እንላጫለን"* ይላሉ፡፡ (ቃለ መጠየቅ/ግሬት ቀበሌ፡ ግንቦት 01 ቀን 2015 ዓ.ም)፡፡

**ጉድሮ፡-** በሁለቱም ፆታ በአማካይ ከ2 እስከ 4 ዓመት ዕድሜ ያላቸውን ህፃናት ለማስዋብ የሚተገበር የፀጉር አሰራር ዓይነት ነው፡፡ ይህ የፀጉር አቆራረጥ በግንባር በኩል ያለውን የፊት ለፊት ፀጉር እና ከመሀል ወደ ኋላ ያለውን ፀጉር በክብ ቅርፅ እንዲያድግ ተደርጎ ሌላው ሙሉ ለሙሉ በየጊዜው የሚላጭ ነው፡፡ ከዚያም እንዲያድግ የተደረገውን ፀጉር በማድቦልቦል (ድሬድ) እንዲሆን በማድረግ ዛጎልና አዝራሮች በላዩ ላይ በክር ይታሰሩበታል፡፡ እንደ አበጀ ገስጥ ገለፃ *"ጉድሮ በወንድና ሴት ህፃናት ላይ የሚሰራ ነው፡፡ ለጌጥ የሚደረጉት ዛጎል፣ አዝራርና ዶቃ ጌጦች ደግሞ ህፃናቱ ከሰው ዐይን እንዳይገቡ ለመከላከል ነው"* (ቃለ መጠይቅ/ዘይታ ቀበሌ፡ ሚያዚያ 10 ቀን 2015 ዓ.ም)፡፡

**ጋሜ፡-** ይህን የፀጉር አሰራር ዓይነት የሚተገብሩት አማካይ ዕድሜያቸው ከ 08 እስከ 15 ዓመት የሆኑት ወንዶች ናቸው፡፡ አቶ አውራስ ማብረጃ *"ጋሜ ማለት ከፊት ለፊት እስከ መሀል አናት ድረስ ያለው የፀጉር ክፍል በመካከለኛ የቁመት መጠን ያድጋል፡፡ ሌላው ሙሉ ለሙሉ እንዲላጭ ወይም ፀጉሩ እንዲቆረጥ የሚደረግ የፀጉር ቁርጥ ዓይነት ነው"* ሲሉ ይገልፃሉ፡፡ (ቃለ መጠየቅ/ኩራ ወንጪት ቀበሌ፡ መስከረም 21 ቀን 2014 ዓ.ም)፡፡

**ቁንጮ፡-** ዕድሜያቸው ከ8 (ስምንት) ዓመት ያልበለጡ ወንዶች የፀጉር አሰራር ዓይነት ነው፡፡ አቶ ሰለሞን ምታው *"ቁንጮ ከፊትለፊት በግንባር በኩል ያለውን ፀጉርን በማሳደግ (በማስቀረት) እና ሌላውን ሙሉ ለሙሉ በመላጨት የሚሰራ የቁርጥ ዓይነት ነው፡፡"* (ቃለ መጠየቅ/ዓለም ከተማ፡ ሚያዚያ 15 ቀን 2015 ዓ.ም)፡፡

**የወንዶች ፍሪዝ፡-** ይህ የፀጉር አቆራረጥ ድሮ ያልነበረና በአሁኑ ጊዜ በብዛት ወጣቶች የሚያዘወትሩት የፀጉር አሰራር መሆኑን አቶ ተኮላ ባዩ *"ከላይ ያለውን ፀጉር ትተው ሌላው ሙሉውን ይላጩታል፣ ያልተላጨው ፀጉር ያቁጠረጥሩታል፣ ያጋምዱታል"* በማለት ያስረዳሉ፡፡ (ቃለ መጠየቅ/ገረን ቀበሌ፡ ነሐሴ 12 ቀን 2013 ዓ.ም) ፡፡


**ጎፈሬ-** ፀጉርን ሙሉ ለሙሉ በማሳደግና በሚዶ ወደጎንና ወደላይ በማበጠር/በማቆም ውበትን ለማጉላት የሚከወን የፀጉር አሰራር ዓይነት ነው፡፡ አቶ ግርማ ተሰማ *"ወጣቶች ሲጎረምሱና ሚስት ማግባት ሲፈልጉ አንዳንዴም ጀግንነታቸውን ለማሳየት ጎፈሬ ያጎፍራሉ፡፡ ጎፈሬው ጥሩ ሽታ እንዲኖረው አርቲ፣ እንጆባን አልፎ አደስና ቅቤ ያደርጉበታል*" ይላሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ/ጎራንዳ ቀበሌ፡ መስከረም 14 ቀን 2014 ዓ.ም)፡፡ በምልከታ ለማረጋገጥ አንደቻልኩት ይህን የፀጉር አሰራር የሚተገብሩት ያላገቡ ወጣት ወንዶች ሲሆኑ ሚዶና ኮፍያ በጎፈሬያቸው ላይ በማድረግ ውበትን ለማጉላት ይጠቀማሉ፡፡

**ቅምቅሞ፡-** ይህ የፀጉር አሰራር ፀጉርን ሙሉ ለሙሉ በመላጨት ሹርባ መሰራት እስከሚችል ድረስ ያለው ጎፈሬ መሳይ ፀጉር ነው፡፡ ይህን የፀጉር አሰራር አማካይ ዕድሜቸው ከ9 እስከ 14 የሚሆኑ ሴቶች ላይ በብዛት ይከናወናል፡፡ በዋናነት በቤተሰብ ፍላጎት የሚተገበረው ይህ የፀጉር አሰራር ተምሳሌታዊ ትርጉም እንደ አቶ ክብረቴ አስፋው ገለፃ *"ሴት ልጅ ፀጉሯን ቅምቅሞ ካደረገች እንደ ሀገራችን ባህል ለመታጨት ደርሳለች"* እንደማለት ነው ሲሉ ያብራራሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ/ግሬት ቀበሌ፡ ጥር 10 ቀን 2014 ዓ.ም)፡፡


**ቁንዲድ፡-** ይህን የፀጉር አሰራር በታጨና ባላገቡ ሴቶች የሚተገበር ነው፡፡ ቁንዲድ ሲባል የቅምቅሞ (ጎፈሬነት) ዘመኑ አብቅቶ ሹሩባ ለመሰራት የደረሰ ፀጉር ዓይነት መሆኑን ወ/ሮ ጉርዶ ባህሩ *"ባገራችን ወግ ሴት ልጅ ከቅምቅሞ ወደ ቁንዲድነት ከተሸጋገረች ለመታጨት የደረሰች መሆኑን ማሳበቂያ (መግለጫ) ነው" ይላሉ፡፡* (ቃለ መጠይቅ/ዘይታ ቀበሌ፡ ሚያዚያ 10 ቀን 2015 ዓ.ም)፡፡ እዚህ ላይ በአማካይ ከ13 እስከ 16 ዓመት ያሉ ሴቶች የሚጠቀሙት የፀጉር አሰራር መሆኑን በምልከታ አረጋግጫለሁ፡፡

**ሹሩባ፡-** ይህ የአሰራር ዓይነት ፀጉርን በመግመድ፣ በመጎንጎን ወይም በማጠላለፍ መልክ የማስያዝ ተግባር ነው፡፡ ይህ ሀገረሰባዊ የመዋቢያ ብዙ ጊዜ የሚተገብሩት ያገቡ ሴቶች ሲሆኑ ከቅርብ ጊዜ ወዲሁ ያላገቡ ሴቶችም ሲጠቀሙት ይስተዋለል፡፡ ሹርባ በሁሉም ቀናት የሚገለገሉበት ሲሆን የሚጠቀሟቸው የአሰራሮች ዓይነቶች አሳስራ፣ ድፊቶሽ፣ ልምጭ ከዱላ፣ ጉንጉን አግድሞሽ ዛሌዋ ወዘተ የሚባሉ ናቸው፡፡

**ፎቶ 38. የፀጉር አሰራር ዓይነቶች**




ምንጭ:- የመጀመሪያው በ12/12/13 ዓ.ም ገረን እና 2ኛውና 3ኛው በ14/01/14 ዓ.ም ጎራንዳ ቀበሌ በአጥኚው የተወሰዱ




ምንጭ:- የመጀመሪያው በ25/01/14 ዓ.ም ዓም ከተማ፣ 2ኛው በ14/01/14 ዓ.ም ጎራንዳ ቀበሌ፣ በ21/01/14 ዓ.ም ግሬት ቀበሌ በአጥኚው የተወሰዱ ፎቶዎች

በተጠኚው ማህበረሰብ በሁሉም የእድሜ ደረጃና ፆታዎች የሚተገበሩት የፀጉር አሰራሮች የማይታዩ/ስውር ተግባራት አላቸው፡፡ ለምሳሌ ለጋብቻ የደረሱ ሴቶችና ወንዶች የሚሰሩት የጸጉር ዓይነት ውበትን ከማስጠበቁ በተጨማሪ ለአቅመ አዳምና ሄዋን የደረሱ መሆኑን ያመላክታል፡፡ ይህም Merton (1968) በስርዓተ ማህበሩ ውስጥ ያሉ ተግባራት አንዳንዶቹ በግልፅ የሚታወቁ (manifest) ሌሎቹ ደግሞ ደግሞ በግልፅ የማይታወቁ ወይም ስውር (latent) ተግባራት ያላቸው ሲሉ ከገለፁት ሃሳብ ጋር የሚመሳከር ነው፡፡

## 4.4 የአልባሳቱና ጌጣጌጦች የለውጥ ሂደትና ማህበረሰባዊ አተያይ

የዚህ ጥናት አንዱ አነሳሽ ምክንያት የማህበረሰቡ የማንነት መገለጫ የሆኑት አልባሳትና ጌጣጌጦች ለውጥ እየተስተዋለባቸው መሆኑን በማየት ነው። ከዚህ አንፃር ይህ ክፍል በቁሶቹ ላይ እየተስተዋለ ያሉ የለውጥ ሂደት ምክንያቶችን ይመረምራል። በተለይ ለውጥ የተስተዋለው ዘመነ ሉላዊነት (globalization) በፈጠረው ተፅዕኖ? ወይስ ማህበረሰባዊ የለውጥ ፍላጎት መኖር ይሆን? የጉዳዩ ባለቤት የሆኑት ማህበረሰቡ፣ የመንግስትና የእምነት ተቋማት በለውጡ ዙሪያ ምን አተያይ አላቸው? ለውጡ ሚዛናዊ እንዲሆን ምን ምን ስራዎች ተከናወነዋል? ምን የመጡ ለውጦች አሉ? ለውጥ ካልመጣ ምን መደረግ አለበት? ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል። በቁሶቹ ላይ የሚስተዋለው የለውጥ ሂደትን ምን እንደሚመስል የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚከተለው ይገልፃሉ።

> *እኛ የምንለብሰው የአዋቂዎቹ ልብስ ብዙም አይለወጥም፤ የልጆቹና የወጣቶቹ ግን ይለዋወጣል። ድሮ ባመት ወይም በሁለት ዓመት አንድ ጊዜ የምንለብሰው የአሁን ዘመን ወጣቶች ከበዓል በዓል አያሸግሩትም። ለፋሲጋ ለአንቁጣጣሽና ለጥምቀት ወይም ለጥምቀት አይደግሙትም/አይለብሱትም። ድሮ ነው እንጂ አሁን ላይ ገንዘብ ካለ ምን የማይገዛ ነገር አለ? ዕድሜ ለገበያ ሁሉ ነገር ሞልቷል። በፊት ግን ብሩም ልብሱም ገበያውም ሽግር ነበር። (የቡድን አንድ ተወያዮች ጎራንጻ ቀበሌ፡ መስከረም 14 ቀን 2014 ዓ.ም)*

ከዚህ ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው ገበያው በሚፈጥረው ተፅዕኖ መሰረት ወጣቶች የሚልሱት ልብስ በየጊዜው ተለዋዋጭ መሆኑን ነው። ይህ የገበያ ስርዓት ደግሞ በቴክኖሎጂ የታገዘ በመሆኑ ወጣቶቹ ለሚለብሱት ልብስ ትኩረት እንዲሰጡ ማድረጉን መገመት ይቻላል። Rosenberg (1987) ቴክኖሎጂ የባህል ለውጥን ከሚያፋጥኑ ነገሮች አንዱና ዋነኛው መሆኑን ይጠቅሳሉ። ለዚህ የለውጥ ሂደት የዘመነ ሉላዊነት ያመጣው ተፅዕኖ መሆኑን ያስገነዝባል።

እንደ ለውጥና ቀጣይነት ንድፈ ሃሳብ አተያይ የአንድ ማህበረሰብ ባህል በውስጣዊና ውጫዊ በሆኑ ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ ምክንያቶች መለወጣቸው የማይቀር መሆኑን Chalfart (1988) "ለውጥ የተፈጥሮ ሕግ ነው" በማለት የለውጥ አይቀሬነትን ይገልፃሉ።

ከዚህ አንፃር በማህበረሰቡ ቁሶች ላይ እየተደረገወን ያለውን ለውጥ ነዋሪዎቹ ሲገልፁ፡-

> *ያገራችንን ቁምጣ ሁሉም ሰው እየተወ ጂንስ፣ ከፋይ፣ ካኪ ዘመን (አመጣሽ ጨርቆችን) የሚለብስበት ምክንያት ብዙ ጥቅም ስለተገኘበት ነው። ሱሪ ሰውነትን ስለሚከልል በእባብና ጊንጥ ከመነቀር፣ ማር ስንቆርጥ በንብ ከመነደፍ፣ በመንደር በውሻ ከመነከስ፣ በጫካ ውስጥ ስንሄድ ደግሞ በእሾህና በጋሬጣ (ከእንጨት) ከመወጋት፣ እንዲሁም ማሽላ በሚወቃበት ጊዜ የማሽላው ብናኝ (ቅንቅን) ሰውነታችንን እንዳያሳክከን ያደርጋል። በአጠቃላይ ሱሪ ከቁምጣ የተሻለ ጥቅም ስላለው ያገሬው ሰው ይለብሰዋል በማለት ያስረዳሉ።* (የቡድን ሦስት ተወያዮች/ ኮራ ቀበሌ፡ መስከረም 21 ቀን 2014 ዓ.ም)

ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው ይህም ለውጥ በውጣዊም ሆነ በውጫዊ ግፊቶች የሚመጣ በመሆኑ በማህበረሰቡ የአለባበስ ስርዓት ላይ የተስተዋለው ለውጥ የዘመነ ሉላዊነት (globalization) ያስከትለው ተፅዕኖ ብቻ ሳይሆን የተሻለ የአኗኗር ስርዓትን ለመከተል ማህበረሰባዊ ፍላጎት ያለ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ እዚህ ላይ የተፈጥሮ ህግ የሆነውን ለውጥ ማስቀረት ስለማይቻል ትውልድን የሚታደግበትን ማህበረሰባዊ አስተሳሰብ ወይም አመለካከት ላይ መስራት እንደሚገባ Chalfart (1988) ይመክራል፡፡ ከዚህ አንፃር እንደ ወ/ሮ ህይወት ታደሰ ገለፃ *"በአልባሳትና ጌጣጌጦች ላይ የሚስተዋለው ለውጥ ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ ነው፡፡ ይህን ጉዳይ መከላከል እንዲቻል ከተለያዩ አካላት ጋር በመሆን ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ ይሰራል፡፡ ነገር ግን ቁሱ ከሚሰጠው አገልግሎት አኳያ እየመዘኑ ትምህርቱን የሚቀበሉበትና የማይቀበሉበት አጋጣሚዎች አሉ"* ሲሉ ይገልፃሉ፡፡ (ቃለመጠይቅ/ የባ/ቱ/ጽ/ቤት/ ባለሙያ/ዓለም ከተማ፡ ታህሳስ 27 ቀን 2014 ዓ.ም)፡፡

እዚህ ላይ የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት በኩል ከሚመለከታቸው አጋር አካላት ጋር በመሆን የማህበረሰቡ ማንነት መገለጫ የሆኑት ቁሶች እንዳይጠፉ ለቁሱ ባለቤት ግንዛቤ እየሰጠ መሆኑን ነው፡፡ ይሁንና ተጠቃሚው ማህበረሰብ የቁሶቹን አገልግሎት ከዕለት ተዕለት ህይወቱ ተጠቃሚነት ጋር እያቀራኘ ለመቀበልና ላለመቀበል የሚደረገው ሂደት ለቁሳዊ ለውጡ ተግባራዊነት ማህበረሰባዊ ፍላጎት መኖሩን ያሳያል፡፡ ሌላው Haferkamp (1992) ለውጥ በግለሰቦች፣ በታዋቂ ሰዎች፣ በቡድኖች፣ በማህበራዊ ሁኔታዎች፣ በቁሶች አማካኝነት ሊጀመር እንደሚችል በጠቀሱት መሰረት ለቁሶቹ መለወጥ በዋናነት የሚስተዋለው በማህበረሰቡ አባላት በተለይም በወጣቶች ላይ መሆኑን በነበረኝ የመስክ ምልከታ ወቅት አረጋግጫለሁ፡፡

በተጨማሪም በተጠኚው ማህበረሰብ አባላት መሪነት በተለይም በወጣቶቹ በኩል እየተስተዋለ ያለውን የለውጥ ሂደት ወ/ሮ አስቴር አንዳርጋቸው እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡፡

> *የአልባሳትና ጌጣጌጦቹ ለውጥ የሚስተዋለው በዋናነት በወጣቶቹ ላይ ነው፡፡ ለዚህም ምክንያቱ በትምህርት ወይም በስራ ምክንያት ወደሌላ አካባቢ የሚሄዱ በመሆኑ ቀደም ሲል ሲጠቀሙባቸው ከነበሩት ቁሶች ለተወሰነ ጊዜ ይርቃሉ፡፡ተመልሰው ሲመጡም የኖሩበትን ቁስ ሳይሆን አሁን እየተጠቀሙበት ያለውን ቁሶች ይጠቀማሉ፡፡ ሌሎች የቤተሰብ አባሎቻቸውም እነሱን እያዩ የእነሱን ዓይነት ልብስ መልበስ ላይ ትኩረት ያደርጋሉ፡፡ በዚያ ላይ ገበያው ብዙ አማራጭ ይዞ ስለሚመጣ የፈለጉትን እንዲለብሱ አድርጓቸዋል፡፡ በተጨማሪም አንዳንድ አካላት ቁምጣ መልበስ ካለመሰልጠን ጋር ያገናኙታል፡፡ ሲሉ የለውጦቹን ምክንያት ይዘረዝራሉ፡፡* (ቃለ መጠይቅ፡/የባ/ቱ/ጽ/ቤት/ኃላፊ/ዓለም ከተማ፡ ታህሳስ 27 ቀን 2014 ዓ.ም)፡፡

ከዚህ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው ለአልባሳትና ጌጣጌጦቹ ለውጥ ዋና ምክንያቱ የማህበረሰባዊ ለውጥ ፍላጎት መኖርና ዓለም በአንድ መንደር ስር መተዳደሯ የፈጠረው ተፅዕኖ መሆኑን ያስረዳል። እዚህ ላይ የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤትና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ከእምነት ተቋማት ጋር በመቀናጀት በህፃናትና በማህበረሰቡ ላይ የግንዛቤ ስራው ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ ያመላክታል። በተለይ ለለውጥ ምክንያት የሆኑ የማህበረሰቡ አባላት የሆኑ ወጣቶች በራስ ማንነት ላይ እንዲያተኩሩ ለማድረግ የእምነት ተቋማት ከፍተኛ ድርሻ አላቸው።

እንደ ቄስ ማንደፍሮ አበበ ገለፃ *"ወጣቶቹ ዘመን አመጣሹን ጂንስ በላሌ ይለብሳሉ። አሁን ላይ ቁምጣና ኮት መልበስ እየተው ነው። የአገራችን ልብስ ሰፊዎች አንደጂንስ እያደረጉ ካሽሚር ጨርቁን ቢሰፋላቸው ይለብሱት ነበር። ጂንስ ዋጋውም ውድ ነው።* (ቃለ መጠይቅ/ጎራንዳ ቀበሌ፡ መስከረም 14 ቀን 2014 ዓ.ም)። በጥቅሉ ለለውጡ አንዱ ምክንያት የአካበቢው ልብስ ሰፊዎች የወጣቶችን ፍላጎት የሚያሟላ ሱሪ ማዘጋጀት ባለመቻላቸው የሌላ ሀገር ምርት የሆኑ ሱሪዎችን ለመጠቀም የተገደዱ መሆኑን ያስገነዝባል። ይህም Haferkamp (1992) ዘመናዊው ማህበረሰብ ኑሮውን አስተማማኝ እና የተሻለ ለማድረግ ይጥራል እንዳሉት ማህበረሰቡ ምቹ ኑሮ ለመኖር ሲል ይጠቀምባቸው የነበሩ ቁሶቹን በአዳዲስ እየለወጣቸውና የራሱ እያደረጋቸው መሆኑን ያሳያል።

በዚህም መሰረት በተጠኚው ማህበረሰብ ያሉ ወጣቶች ከ2013 ዓ.ም በፊት ጥቂት ወጣቶች ለበዓላትና በልዩ ልዩ ፕሮግራም ቀናት ብቻ ይለብሷቸው የነበሩት እንደ ጂንስ፣ ከፋይ፣ ካኪ ሱሪዎች፣ የአንገት ፎጣዎች እንዲሁም የፕላስቲክ፣ የቆዳ፣ የሸራ ወዘተ ያሉ አልባሳት እስከ በ2015 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ በሦስት ዓመታት ውስጥ በተደጋጋሚ ባደረግኳቸው ምልከታዎች አብዛኛው አልባሳት እየተቀየረ መሆኑን ነው። ይህም ቁሶቹ ሙሉ ለሙሉ በሌላ ቁስ የመተካት ወይም ቁስ ቅየራ (material convension) እና አዲስ የአለባበስ ባህልን መለማመድን ደግሞ የአለባበስ ስርዓት ለውጥ (Dress code change) ብለን ልጠራው እንችላለን። በመስክ ምልከታና በቃለ መጠይቅ ባረጋገጥኩት መረጃ መሰረት በከፍተኛ ደረጃ ለውጥ የተስተዋለባቸውን በሁለቱም ፆታ ያሉ ህፃናትና ወጣቶች የሚገለገሉባቸውን አልባሳትና ጌጣጌጦችን ላይ ነው። ለዚህ ምክንያቱ ውጫዊና ውስጣዊ የለውጥ ግፊቶች (push factors) በመኖራቸው እንደሆነ ከላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት ያስችላል።

### 4.4.1. የአልባሳትና ጌጣጌጦች ለውጥ ንፅፅር

በአልባሳትና ጌጣጌጦቹ ላይ የተስተዋለውን ለውጥ በንፅፅር ማየት እንዲያስችል በአዘቦት ቀናት ባደረግኩት የመስክ ምልከታ ወቅት ለውጥ የተከሰተባቸውን ቁሶችና ተጠቃሚዎችን መምረጥ አስፈልጓል፡፡ በዚህም መሰረት በሁለቱም ፆታ ያሉ የአዋቂ አልባሳትና ጌጣጌጥ ላይ ለውጥ እምብዛም አልተስተዋለም፡፡ ስለሆነም ከፍተኛ የለውጥ እንቅስቃሴ ከሚስተዋልባቸው ከህፃናትና ወጣቶች አልባሳት ቁምጣ፣ ኮት፣ ፎጣ፣ ጎማ ጫማ ሲሆኑ ከጌጣጌጥ ደግሞ የአንገት ጌጦች እንዲሁም በአማካይ ከ4 እስከ 8 ዓመት ያሉት ወንዶች የሚጠቀሙትን ቁንጮ እና ከ08 እስ 15 ዓመት ያሉት ወጣቶች የሚጠቀሙትን ጋሜ የፀጉር አሰራሮች ተመርጠዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ከህፃናትና ወጣት ሴቶች አልባሳት ቀሚስ፣ ውስጥ ልብስ፣ ሻሽ፣ ጫማዎችን እንዲሁም ከጌጣጌጦች የአንገት ጌጦችን፣ ከፀጉር አሰራር ደግሞ ቅምቅሞና ቁንዲድ የተባሉት ለንፅፅር ተመርጠዋል፡፡ ቅምቅሞ ከ9 እስከ 14 ዓመት፣ ቁንዲድ ከ13 እስከ 16 ዓመት ያሉ ሴቶች ይጠቀሙታል፡፡

ለንፅፅር እንዲያመች ለባሹ በሌላ ቁስ ተክቶ እየተጠቀማቸው ያሉትንና ሙሉ ለሙሉ ከአገልግሎት ያራቃቸውን “ √ ” የትክክለኛ ምልክት (tickmark) የሚወክል ነው፡፡ ለውጥ ያልታየባቸው ወይም አሁንም የቀጠሉ ቁሶችንና መዋቢዎችን ለማመላከት “ x ” ትክክለኛ ባልሆነ ምልክት (wrong mark) እንዲሁም ለመግለፅ ሲሆን ለባሹ ባለበት ዕድሜ የማይጠበቅበት ወይም የማይመለከት መሆኑን ለማሳየት “ * ” በኮከብ ምልክት (asterisk) የሚወክል ነው፡

### 4.4.2. የህፃናት ወንዶችና ሴቶች አለባበስና አጊያጊያጥ ንፅፅር

**ፎቶ 39. የህፃናት አለባበስና አጊያጊያጥ**

ህፃናት ወንዶች 14/01/14 ዓ.ም ጎራንዳ ቀበሌ



ህፃናት ሴቶች 15/09/15 ዓ.ም ጎራንዳ ቀበሌ



ምንጭ፡- በአጥኚው የተወሰዱ ፎቶዎች

| ተ/ቁ | የህፃናት ወንዶች አልባሳትና ጌጣጌጥ ፎቶ | | | | | የህፃናት ወንዶች አልባሳትና ጌጣጌጥ ፎቶ | | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2014 ዓ.ም ጎራንዳ ማሪያም ሰርቃ ቀበሌ | | | | | 2015 ዓ.ም ጎራንዳ ማሪያም ሰርቃ ቀበሌ | | | | |
| | አልባሳት ጌጣጌጥና የፀጉር አሰራር | ህፃን 1 | ህፃን 2 | ህፃን 3 | ህፃን 4 | አልባሳት ጌጣጌጥና የፀጉር አሰራር | ህፃን 1 | ህፃን 2 | ህፃን 3 | ለጥናቱ ንፅፅር እንዲያመች "√" ተለውጧል "x" አልተለወጠም " * " የማይመለከት ማለ››ትን ይወክላል |
| | | | | | | | | | | |
| 1 | ቁምጣ | √ | x | √ | √ | ቀሚስ | x | x | x | |
| 2 | ኮት | √ | x | √ | √ | ውስጥ ልብስ | √ | √ | x | |
| 3 | ቲሸርት | √ | √ | √ | √ | የአንገት ጌጥ | x | x | x | |
| 4 | ፎጣ | √ | √ | √ | √ | ሻሽ | √ | √ | √ | |
| 5 | ጫማ | x | x | x | x | ጫማ | x | x | x | |
| 6 | ቁንጮ | * | x | x | x | ቁንጮ | * | x | x | |
| 7 | ጋሜ | √ | * | * | * | ቅምቅሞ | x | * | * | |
| | | | | | | | | | | |

**ሠንጠረዥ 1. የህፃናት ወንድና ሴት የአዘቦት ቀናት አለባበስና አጊያጊያጥ ንፅፅር**

በሠንጠረዥ አንድ ላይ በንፅፅር ከቀረበው መረዳት እንደሚቻለው በህፃናት ወንዶች ላይ ያለው አለባበስ ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ የተቀየረ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ለዚህም ማሳያ የሚሆነው በፎቶው ላይ የሚታዩት አራት ህፃናት ወንዶች በ2014 ዓ.ም በጎራንዳ ማሪያም ሰርቃ ቀበሌ የሚኖሩ ህፃናት ሲሆኑ ከአራቱ ህፃናት የሦስቱ ሙሉ ሉሙሉ እንዲሁም የአንዱ ህፃን በከፊል ልብሶች የተለወጡ ናቸው፡፡

ህፃናት ወንዶች ካኒቴራ (T-shirt) መልበስ መጀመራቸው በአለባበስ ስርዓት ላይ እየተስተዋለ ያለውን ፈጣን ለውጥ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ነገር ግን በጌጣጌጥና በፀጉር አሰራር ላይ ለውጥ አልተከሰተም፡፡ በዚያው ቀበሌ በ2015 ዓ.ም በተደረገው ምልከታ በፎቶው ላይ እንደሚታየው ከሦስቱ ሴት ህፃናት ሁለቱ አዋቂዎች የሚለብሱትን የውስጥ ልብስ ለብሰዋል፡፡ ይህም በአለባበስ ላይ ለውጥ ተከስቷል፡፡ ነገር ግን በሌሎች አልባሳትና ጌጣጌጦች እንዲሁም የፀጉር አሰራሮች ላይ ለውጥ አልተስተዋለም፡፡

ፎቶ 40. የወጣት ወንዶች አለባበስና አጊያጊያጥ

18/01/14 ዓ.ም ግሬት ቀበሌ

22/09/15 ዓ.ም ግሬት ቀበሌ





ምንጭ በአጥኚው የተወሰዱ ፎቶዎች

| የወጣት ወንዶች ፎቶ 1 | | | | | የወጣት ወንዶች ፎቶ 2 | | | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ/ቁ | 2014 ዓ.ም ግሬት ቀበሌ | | | | 2015 ዓ.ም ግሬት ቀበሌ | | | | | |
| | አልባሳት፣ ጣጌጥና የፀጉር አሰራር | ወጣት 1 | ወጣት 2 | ወጣት 3 | ወጣት 1 | ወጣት 2 | ወጣት 3 | ወጣት 4 | ወጣት 5 | ለጥናቱ ንፅፅር እንዲያመች “√” ተለውጧል “x” አልተለወጠም “ * ” የማይመለከት ማለትን ይወክላል |
| 1 | ቁምጣ | x | √ | X | √ | x | X | √ | x | |
| 2 | ኮት | x | x | √ | √ | √ | √ | √ | x | |
| 3 | ቲሸርት | √ | √ | √ | √ | √ | √ | √ | √ | |
| 4 | ፎጣ | √ | √ | √ | √ | x | √ | √ | x | |
| 5 | ጫማ | x | √ | X | √ | x | X | √ | x | |
| 6 | ዱላ | x | x | √ | √ | x | √ | √ | √ | |
| 7 | ቁንጮ | * | * | * | * | * | * | * | * | |
| 8 | ጋሜ | * | * | * | * | * | * | * | * | |
| 9 | ፍሪዝ | √ | √ | √ | √ | √ | √ | √ | √ | |

ሠንጠረዥ 2. የወጣት ወንዶች የአዘቦት ቀናት አለባበስና አጊያጊያጥ ንፅፅር

በሠንጠረዥ ሁለት ላይ እንደተመላከተው በወጣት ወንዶች የሚለብሱት አለባበስ እየተቀየረ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በፎቶው ላይ የሚታዩት ወጣት ወንዶች በ2014 ዓ.ም እና በ2015 ዓ.ም በግሬት ቀበሌ የሚኖሩ ሲሆኑ በመጀመሪያው ፎቶ ያሉ ወጣቶች

እያንዳንዳቸው ከፊል የአለባበስ ለውጥ አድርገዋል፡፡ በሁለተኛው ፎቶ ላይ የሚታዩ ወጣቶች ደግሞ በከፊልና ሙሉ ለሙሉ የአለባበስ ለውጥ ማድረጋቸውን ያሳያል፡፡

ከጌጣጌጥ አንፃር ስንመለከት ደግሞ በሁለቱም ፎቶዎች ላይ ያሉ ወጣቶች ድንብልና ድምርጥ ካደረጉት ሁለቱ ወጣቶች በስተቀር ሁሉም ወጣቶች ያደረጉት የአንገት መስቀልን ብቻ ነው፡፡ ይህም ቀደም የሚጠቀሟቸው የአንገት ጌጣጌጦች ተብለው በተጠቀሱት መሰረት ሲታይ ወጣቶቹ ሀገረሰባዊ ጌጣጌጦች ሙሉ ለሙሉ የለወጡ መሆኑን ያመላክታል፡፡ እንዲሁም በዱላና ፎጣ ቁሶች ላይ የለውጥ ክስተት ያረፈባቸው መሆኑን መረዳት ያስችላል፡፡ ሌላው ማየት የሚቻለው የፀጉር አሰራር ሂደት ሲሆን ወጣቶቹ የራሳቸው ያልሆነውን ፍሪዝ የፀጉር ደጋግመው ስለተጠቀሙት የራሳቸው አካል አድርገውታል፡፡ ይህም የመዋቢያ ስርዓት ለውጥ መደረጉን ያሳያል፡፡

**ፎቶ 41. የወጣት ሴቶች አለባበስና አጊያጊያጥ**

14/01/14 ዓ.ም ጎራንዳ



01/09/15 ዓ.ም ገረን



21/01/14 ዓ.ም ኮራ



ምንጭ፡- በአጥኚው የተወሰዱ ፎቶዎች

| የወጣት ሴቶች ፎቶ 1 | | | | | የወጣት ሴቶች ፎቶ 2 | | የወጣት ሴቶች ፎቶ 3 | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ/ቁ | 2014 ዓ.ም ጎራንዳ ቀበሌ | | | | 2015 ዓ.ም ገረን ቀበሌ | | 2014 ዓ.ም ኮራ ቀበሌ | | |
| | አልባሳ ትጌጣጌ ጥና ፀጉር አሰራር | ወጣት 1 | ወጣት 2 | ወጣት 3 | ወጣት 1 | ወጣት 2 | ወጣት 1 | ወጣት 2 | ለጥናቱ ንፅፅር እንዲመች "√" ተለውጧል "x" አልተለወጠም " * " የማይመለከት ማለትን ይወክላል |
| 1 | ቀሚስ | x | X | x | X | x | X | X | |
| 2 | መቀነት | √ | X | x | X | √ | X | X | |
| 3 | አንገት ልብስ | √ | √ | x | X | x | X | X | |
| 4 | ሻሽ | x | * | √ | X | x | √ | X | |
| 5 | ጫማ | x | X | x | √ | x | X | X | |
| 6 | የራስ ጌጥ | * | √ | * | * | * | * | * | |
| 7 | የአንገት | x | X | x | X | x | X | X | |
| 8 | የእጅ | x | X | x | X | x | X | X | |
| 9 | ቅምቅሞ ፀጉር | * | √ | * | * | * | * | * | |
| 10 | ቁንዲድ | * | √ | * | * | * | * | * | |
| 11 | ሹርባ | * | √ | * | * | * | * | * | |

### ሠንጠረዥ 3. የወጣት ወንዶች የአዘቦት ቀናት አለባበስና አጊያጊያጥ ንፅፅር

በሠንጠረዥ ሦስት ላይ ከቀረበው መረዳት እንደሚቻለው በወጣት ሴቶች ላይ ብዙም ለውጥ አልተስተዋለም፡፡ በፎቶው ላይ የሚታዩት ወጣት ሴቶች በ2014 ዓ.ም እና በ2015 ዓ.ም የጎራንዳ፣ ገረን፣ ኮራ ቀበሌዎች ነዋሪ ናቸው፡፡ በፎቶው ሁለት ወጣት አንድ ላይ ከምትታየው (ብራምባር) ካደረገቺው በስተቀር ሁሉም ያላገቡ ናቸው፡፡ ስለዚህ መቀነት ያሰሩ፣ አንገት ልብስ የለበሱ፣ ሹርባ የተሰሩ ወጣቶች የአለባበስ ስርዓት ለውጥ አድርገዋል፡፡ ምክንያቱም ከላይ የተጠቀሱትን አልባሳት መልበስ የሚጠበቅባቸው ያገቡ ሴቶች በመሆናቸው ነው፡፡ በተጨማሪም በፎቶ ቁጥር ሁለት ወጣት አንድ ያደረገችው ጫማ የቁስ ለውጥ መደረጉን ያመለክታል፡፡

በጥቅሉ የለውጡን ንፅፅር በየምድባቸው ስንመለከት በሠንጠረዥ አንድ ላይ እያንዳንዳቸው ወንዶች ህፃናት የተጠቀሟቸው አልባሳትና ጌጣጌጦች አጠቃላይ ድምር 28 ሲሆን 15 የተለወጡ፣ 9 ያልተለወጡ፣ 4 የማይጠበቅባቸው ቁሶች ናቸው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ሴቶች ህፃናት የተጠቀሟቸው አልባሳትና ጌጣጌጦች 21 ሲሆኑ 5 የተለወጡ፣ 3 ያልተለወጡ፣ 3 የማይመለከታቸው ናቸው፡፡

እንዲሁም በሠንጠረዥ ሁለት ላይ የወጣት ወንዶችን አልባሳትና ጌጣጌጦች ስንመለከት ብዛት 72 ሲሆኑ 38 የተለወጡ፣ 18 ያልተለወጡ፣ 16 የማይመለከታቸው ናቸው። በመጨረሻም በሠንጠረዥ ሦስት ላይ ወጣት ሴቶች የተጠቀሟቸው አልባሳትና ጌጣጌጦች ብዛት 77 ሲሆኑ 11 ሲለወጡ 36 ያልተለወጡ፣ 25 የማይመለከታቸው/የማይጠበቅባቸው ናቸው። በጥቅሉ ይህ አሃዛዊ መረጃ የሚያመለክተን ለውጡ በስፋት የሚዳስሳቸው የህፃናትና ወጣቶች አልባሳትና ጌጣጌጦችን እንደሆነ ያስገነዝባል።

የለውጡ ምክንያት ከላይ በትንተና ምዕራፉ እንደተመላከተው ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች በመኖራቸው ነው። ውስጣዊ ሲባል ህብረተሰቡ የተሻለ ኑሮ ለመኖር ከሚያደርገው እንቅስቃሴ የመጣ የለውጥ ፍላጎት ሲሆን ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ወጫዊ የሚባለው ነው። ይህም ቴክኖሎጂ የፈጠረው ተፅዕኖ መሆኑን በሦስቱ የመረጃ መሰበሰቢያ ዘዴዎች ያገኘሁት መረጃ ያረጋግጣል። እዚህ ላይ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ Yenealem (2016) Adeyemiን (2008) ጠቅሰው የለውጡ ክስተት በቁሳዊ ባህሎች ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ከፍተኛ ይሆናል ሲሉ ገልፀዋል። ከዚህ አንፃር በቴክኖሎጂ ምክንያት የሚመጡ ለውጦችን ከቴክኖሎጂ ማራቅ/ማሸሽ ስለማይቻል ቀዳሚውና ዋናው ነገር ማህበረሰቡን ከቴክኖሎጂ ጋር እያዛመዱ ባህሉ እንዲጠበቅና እንዲያለማ ማስተማር ባህሉን ሊያስጠብቅ ይችላል።

# ምዕራፍ አምስት

## 5.1 ማጠቃለያና የይሁንታ ሀሳቦች

ይህ ጥናት በመርሐቤቴ ወረዳ ማህበረሰብ አልባሳትና ጌጣጌጦች ላይ የተደረገ ሲሆን ከዓይነታዊ የምርምር ዘዴ አንዱ በሆነው ገላጭ የምርምር ስልትን የተከተለ ነው፡፡ በመግቢያው ላይ እንደተገለፀው፣ ጥናቱ አንድ ዓብይ ዓላማና ሌሎች ንዑስ ዓላማዎች ያሉት ሲሆን ዓብይ ዓላማውም ለጥናት በተመረጠው አካባቢ የሚከወኑ የሴቶችና ወንዶች አለባበስና አጊያጊያጥ ፋይዳ መመርመር ነው፡፡ እንዲሁም የቁሶቹን አካላዊ ገፅታ ማሳየት፣ ትዕምርታዊ ትርጉም መግለፅ፣ የቁሶቹን የለውጥ ሂደት መመርመር እና ቁሶቹን ለመጪው ትውልድ እንዲሸጋገሩ ሰንዶ ማቆየት የጥናቱ ንዑሳን ዓላማዎች ናቸው፡፡

ጥናቱ ታላሚ ናሙና (Purposive sampling) አመራረጥ ዘዴን መሰረት በማድረግ በመርሐቤቴ ወረዳ ከሚገኙ 23 ቀበሌዎች ውስጥ ጎራንዳ ማሪያም ሰርቃ፣ ግሬት ዋሪኝ፣ ገረን፣ ዘይታ ማጋስ፣ ኮራ ወንጪት የተባሉ አምስት ቀበሌዎችን በመምረጥ እንደ ቆዳ ስፋታቸውና የህዝብ ብዛታቸው ከእያንዳንዳቸው ቀበሌዎች ከ 5 እስከ 9 ብዛት ያላቸው 23 ወንዶችና 13 ሴቶች በድምሩ 36 ሰዎችን በመመረጥ በመረጃ አቀባይነት እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡

ይህን ጥናት ከግብ ለማድረስ ቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮችን እንዲሁም ቃለ መጠይቅ፣ ምልከታና ተተኳሪ የቡድን ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ ስልቶችን በመጠቀም መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ በዘዴዎቹ አማካኝነት በምዕራፍ ሁለት ከቀረቡት ንድፈ ሃሳቦች አኳያ ተተንትነው ከሚከተለው የማጠቃለያ ነጥቦች ላይ ተደርሷል፡፡

በጥናቱ ትንተና የተሰጠባቸው 7 የሴቶች፣ 9 የወንዶች፣ 6 የጋራ በድምሩ 22 አልባሳት ናቸው፡፡ እንዲሁም 12 የሴቶች፣ 5 የወንዶች፣ 7 በጋራ በድምሩ 24 ጌጣጌጦች ላይ ትንተና ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም 3 የሴቶች፣ 4 የወንዶች፣ 2 የጋራ በድምሩ 9 የፀጉር አሰራር ዓይነቶች ላይ ትንተና ተሰጥቶበታል፡፡

ትንተና የተሰጠባቸው የሴቶች አልባሳት ጉያ ቀሚስ፣ እጀ ጠባብ ቀሚስ፣ አርባሽንሽን ቀሚስ፣ ውስጥ ልብስ፣ መቀነት፣ አንገት ልብስ፣ ሻሽ በሚባሉ አልባሳት ላይ ሲሆን በወንዶች ደግሞ ቁምጣ፣ ሱሪ፣ ኮት፣ ሹራብ/ካኒቴራ፣ ባርኔጣ/ኮፍያ፣ ፎጣ፣ ኩታ፣ ጥምጣም፣ ጎማ ጫማ ወዘተ በተባሉ አልባሳት ላይ ነው፡፡ በተጨማሪም ሴትና ወንድ በጋራ ከሚገለገሉባቸው ውስጥ ልብሰ ምንኩስና/የመነኩሴ ልብስ፣ ነጠላ፣ ጋቢ፣ ቡልኮ፣ ከጠፍር፣

ከፕላስተክ፣ የተሰሩ ጫማዎችን ያካተተ ነው፡፡ አብዛኛዎቹ አልባሳትና ጌጣጌጦች በሁሉም የዕድሜ ክልል ይለበሳሉ፡፡

ከሀገረሰባዊ ጌጣጌጦች የራስ ጌጦች (ሚዶ፣ ዛጎልና አዝራር)፣ የአንገት ጌጦች (የአንገት መስቀል/ብር መስቀል፣ ድንብል፣ ዶቃ/ድምርጥ፣ ብር ቅጥል፣ እንቆ፣ አርጌሽ ልሙት፣ ማህተብ/ጎፍታ፣አሸንክታብ/ቁርበተ ሀሊም፣ የሙሽራ አገልግል፣ ሀብል፣ የአንገት ክር/ማህተብ)፣ የጆሮ ጌጦች (ሎቲ፣የጆሮ ጉትቻ)፣ የወገብ ጌጥ (ጨቤ፣ዝናር)፣ የእጅ ጌጥ (ብራምባር፣ ቀለበት፣ ጨሌ፣ ጃንጥላ፣ የእጅ ጎፍታ፣ ዱላ፣ ጭራ) የሚባሉ ናቸው፡፡ እንዲሁም ልጩ፣ ጉድሮ፣ ቁንጮ፣ ጋሜ፣ ጎፈሬ፣ ፍሪዝ/ቁጥጥር፣ ቅምቅሞ፣ ቁንዲድ፣ ሹሩባ የሚባሉ የሴትና የወንድ አሰራር ዓይቶች በጥናቱ ተዳሰዋል፡፡ በዚህም መነሻነት ቀጥሎ የቀረቡት ሃሳቦች በምዕራፍ አራት በቀረበው ትንተና መሰረት የተመላከቱ የጥናቱ ግኝቶች ናቸው፡፡ ይኸውም፡-

ከቁሶቹ አዘገጃጀት አኳያ አልባሳቱ በሦስት ተቋማት/አካላት ማለትም በሸማኔዎች፣ በልብስ ሰፊዎች፣ ነጋዴዎች አማካኝነት የሚቀርቡ ወይም የሚዘጋጁ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ከጥጥ ፈትል በሸማኔ ከሚዘጋጁ አልባሳት መካካል ጉያ ቀሚስ፣ እጀ ጠባብ ቀሚስ፣ መቀነት፣ አንገት ልብስ፣ አደሌ ኮት፣ ኩታ፣ ጥምጣም ነጠላ፣ ጋቢ፣ ቡልኮ የሚባሉት ሲሆኑ የፋብሪካ ምርት ከሆኑት ብትን (ዐርበ ወጥ) ጨርቆች በልብስ ሰፊዎች የሚዘጋጁት ደግሞ አርባሽንሽን ቀሚስ፣ ውስጥ ልብስ፣ ቁምጣ፣ ሱሪ፣ ኮት የሚባሉት ናቸው፡፡ እንዲሁም በነጋዴ ለገበያ የሚቀርቡ የተዘጋጁ ልብሶች (Ready-made) ደግሞ ውስጥ ልብስ፣ ሻሽ፣ ሱሪ፣ ኮት፣ ሹራብ/ካኒቴራ፣ ባርኔጣ/ኮፍያ፣ ፎጣ እና በሁለቱም ፆታ ያሉ የጎማ፣ ፕላስቲክ፣ ቆዳ ጫማዎች ናቸው፡፡

በተመሳሳይ መንገድ ጌጣጌጦቹም በሦስት አካላት ማለትም በቀጥቃጮች/አንጥረኛ፣ በነጋዴዎች እና ተጠኚው ማህበረሰብ በራሱ እውቀት የሚዘጋጁ/የሚቀርቡ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ብራምባር፣ ጨቤ፣ የአንገት መስቀል/ብር መስቀል፣ ብር ቅጥል፣ በአካባቢው ከሚገኙ ቀጥቃጮች/አንጥረኛ የሚዘጋጁ ሲሆን ዛጎል፣ አዝራር፣ ድንብል፣ ዶቃ/ድምርጥ፣ እንቆ፣ አርጌሽ ልሙት፣ ሀብል፣ ሎቲ፣ የጆሮ ጉትቻ፣ ጨሌ፣ ጃንጥላ፣ ወዘተ በነጋዴዎች ለገበያ የሚያቀርቡ ናቸው፡፡ እንዲሁም ሚዶ፣ ጎፍታ/ማህተብ፣ አሸንክታብ/ቁርበተ ሀሊም፣ የሙሽራ አገልግል፣ የእጅ ጎፍታ፣ ዱላ፣ ጭራ የሚባሉት ማህበረሰቡ በራሱ እውቀት የሚዘጋጃቸው ናቸው፡፡ እነዚህ አልባሳትና ጌጣጌጦቹ በሚሰሩበት ቁስ፣ ወቅት፣ ቀለም፣ አሰራር ቅርጽ (design)፣ በመጠን፣ በዋጋ፣ የተለያዩ ሲሆኑ የለባሹ ፆታ፣ ዕድሜ፣ ማንነት ወዘተ መሰረት ተደርገው የሚዘጋጁ ናቸው፡፡

እንደ መዋቅራዊ ተግበራዊነት ንድፈ ሃሳብ አተያይ አልባሳትና ጌጣጌጦችን የሚያዘጋጇቸው እነዚህ ተቋማት/አካላት ማለትም ሸማኔ፣ ልብስ ሰፊ፣ ልብስ አቅራቢ/ነጋዴዎች፣ ጥልፍ ጠላፊ፣ ቆዳ ፋቂ፣ አንጥረኛ፣ ጫማ ሰሪ፣ ያሉት ማህበረሰቡ ፍላጎቱን ለሚሟላት የፈጠራቸው ተቋማት ናቸው፡፡ እነዚህ ተቋማት ደግሞ ማህበረሰቡ ፍላጎቱን ለማሟላት የፈጠራቸው ሲሆኑ እርስ በርስ የሚደጋገፉና የሚተሳሰሩ ናቸው፡፡ ይህም ስርዓተ ማህበሩ/መዋቅሩ እንዲረጋጋና ማንነቱን ይዞ እንዲቀጥል አድርገዋል፡፡

ከአገልገሎት አኳያ ደግሞ የተጠኚው ማህበረሰቡ አልባሳትና ጌጣጌጦች የለባሹን ደህንነት የሚያስጠብቁ፣ ውበትን የሚያጎሉ፣ ፆታን፣ ማንነትን፣ ዕድሜን፣ ጀግንነትን፣ ኃይማኖትን፣ ማህበራዊ ግንኙነትን፣ ማህበራዊ ደረጃንና ሌሎች ጉዳዮችን ለመግለፅ ያገለግላሉ፡፡ ለምሳሌ ዕድሜን መሰረት ተደርገው የሚለበሱ አልባሳት ስንመለከት የአዋቂዎች የአካል ደህንነትን ለማስጠበቅ ትኩረት የሚሰጡ ሲሆን የወጣቶች ደግሞ ውበትን ማጉላት ላይ ያተኩራሉ፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ጌጣጌጦቹን ስንመለከት አዋቂዎቹ የህመም ፈውስ ለማግኘት፣ ወጣቶቹ ለውበት ማጉሊያት ይጠቀማሉ፡፡ ለምሳሌ ብራምባርን ወጣቶች አንዲት ያገባች ሴት ልጅን ለማስዋቢያነትና ያገባች መሆኑን ለማመላከት ሲጠቀሙበት አዋቂ ሴቶች ደግሞ ጠበብ ያለውን የብራምባር ዓይነት ለህመም ፈውስነት ይገለገሉበታል፡፡

ሌላው የማህበረሰቡ ቁሶች ጥበባዊ፣ ታሪካዊ፣ አካባቢያዊ፣ መዋቅራዊ፣ ማህበረሰባዊ ወዘተ መለያ ያላቸው ናቸው፡፡ ለምሳሌ ጉያ ቀሚስ ከትውልድ ትውልድ እየተላለፈ የቆየ መሆኑ የቁሶብ ታሪካዊነቱ የሚያሳይ ሲሆን ከአሰራር ጥበባዊነቱ አኳያ ደግሞ የለባሹን ተግባርና ባህሪ መሰረት ተደርጎ የሚዘጋጅ ነው፡፡ ይኸውም እናቶች ልጆቻቸውን ጡት እንዲያጠቡ ሰፋ ተደርጎ መዘጋጀቱ የእናትነትን ባህሪና የሚያሳይ ነው፡፡ በተጨማሪም አንዲት ሴት ልጅ ካላገባች፣ ካልወለደች ወይም ሳታገባ ዕድሜዋ ከፍ ያለ ካልሆነ በቀር ቀሚሱ በወጣቶች የማይለበስ መሆኑን የጥናቱ ግንኝት ያመለከታል፡፡ እንዲሁም ይህም ልብስ በእናቶች ብቻ የሚበስ መሆኑ የማህበረሰቡን መዋቅር የሚያሳይ ነው፡፡

ከተምሳሌታዊ ትርጉም አኳያ ቁሶቹ የማህበረሰቡን አመለካከት፣ ፍልስፍና፣ እውቀት፣ እምነት፣ ማንነት፣ ማህበራዊ ደረጃ፣ ውበትን፣ ፆታ ወዘተ የተለያዩ መልዕክቶችን ያስተላልፋሉ፡፡ ለምሳሌ በወንዶች ጎፈሬ፣ በሴቶች ቅምቅሞ እና ቁንዲድ የሚባሉ የፀጉር አሰራሮች ውበትን ለመግለፅ ካለው ፋይዳ በተጨማሪ ለአቅመ ሄዋንና አዳም የደረሱ መሆኑን ለማመላከት ያገለግላሉ፡፡

በተጨማሪም አንድ ቁስ በተለያየ የአለባበስ ዓይነት ሲለበስ የራሱ የሆነ ትርጉም የሚሰጥ ነው፡፡ ለምሳሌ ነጠላ በሠርግ፣ በክርስትና፣ በበዓላት ቀን ሲለበሱ የሰዎችን ደስታ ይገልፃሉ፡፡ በተቃራኒው ሀዘን በሚኖር ጊዜ ጥቁር በመልበስ ሳይሆን የነጠላ ጫፉን (ጥለት ያለበትን) ወደ ላይ አድርጎ በመልበስ ሀዘንን ለመግልፅ ያገለግላል፡፡ ይህም ማለት የነጠላው ጫፍ ወደታች ተደርጎ ከተለበሰ ደስታን ወደላይ ተደርጎ ከተለበሰ ደግሞ ሀዘንን የመግለጽ ተምሳሌታዊ ትርጉም አለው፡፡

እንደ ለውጥና ቀጣይነት ንድፈ ሃሳብ አተያይ ደግሞ ለውጥ የማይቀር የተፈጥሮ ህግ በመሆኑ በውስጣዊና በውጫዊ ግፊት ምክንያት ለውጥ ይከሰታል፡፡ ውስጣዊ ግፊት ሲባል የሰው ልጅ የተሻለ ኑሮ ለመኖር ሲል የሚደርጋቸውን እንቅስቃሴዎች ሲሆን ውጫዊ ሲባል ደግሞ በዘመነ ሉላዊነት (globalization) የሚፈጥረውን ተፅዕኖን ለማመላከት ነው፡፡

በዚህም መሠረት በቁሶቹ ላይ ያለውን የለውጥ ሂደት መመልከት እንደሚቻለው በሦስት ዓመታት ልዩነት የሚከተሉትን የለውጥ ዓይነቶች መኖራቸውን የጥናቱ ግኝት ያመላክታል፡፡ እነሱም ምንም ለውጥ ሳያስተናገዱ ፀንተው የኖሩ ቁሶች፣ በከፊል የተለወጡ እና ሙሉ ለሙሉ የቁስ ቅየራ ወይም የተተው የተደረገባቸው ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- ምንም ለውጥ ሳያስተናገዱ ፀንተው የኖሩ ከሚባሉት ውስጥ እንደ መነኩሴ ልብስ፣ ጥምጥም፣ ጋቢ፣ ነጠላ፣ ቡልኮ፣ ቦላሌ ሱሪ፣ ቁምጣ፣ ጉያ ቀሚስ፣ መቀነት ያሉ አልበሳትና የአንገት መስቀል፣ ብራምባር፣ አርጌሽ ልሙት፣ ድንብል፣ ጨቤ፣ ዝናር፣ የአንገት ማህተብ (ጎፍታ)፣ ሚዶ፣ ወዘተ የሚባሉ ጌጣጌጦች ለውጥ ያልታየባቸው ፀንተው የቆዩ ቁሶች ናቸው፡፡

በሁለተኛ ደረጃ በከፊል የተለወጡ አልባሳትና ጌጣጌጦች የሚባሉት የወጣት ወንዶች ቁምጣ፣ ኮፍያ፣ የወጣች ሴቶች አርባሸንሽን ቀሚስና ሻሽ ጌጣጌጦች ደግሞ የአንገት መስቀል፣ ጆሮ ጌጥ (ጉትቻ) ሲሆኑ ከሚሰሩበት ቁስ፣ ዲዛይንና ዋጋ አኳያ በከፊል ለውጥ ያሳዩ ናቸው፡፡

የመጨረሻውና ሦስተኛ ደረጃ ሙሉ ለሙሉ የተተው የሚባሉት ቁሶቹ የተሰሩበትን መቀየር ወይም ሙሉ ለሙሉ መተውን ይመለከታል፡፡ ለምሳሌ የቁስ ቅየራ የተደረገባቸው ከጥጥ የሚሰራው አንገት ልብስ የፋብሪካ ምርት በሆነው ሻርፕ መሳይ ፎጣ፣ የወንዶች ጎማ ጫማና የሴቶች ኮንጎ ጫማ በጥልፍልፍና ሸራ፣ የወንዶች ቁምጣ በጂንስና ከፋይ ሱሪ ወዘተ ተተክተዋል፡፡ ይህም የቁስ ቅየራ መደረጉን ያመላክታል፡፡ ሙሉ ለሙሉ የተተው የሚባሉት ደግሞ ጠፍር ጫማ፣ የሙሽራ አገልግል፣ ወለባ የፀጉር ጌጥ፣ ቡቅርና ሳዱላ የሚባሉ ፀጉር አሰራሮች ሙሉ ለሙሉ ከአገልገሎት የራቁ መሆናቸውን ነው፡፡

## 5.2. የይሁንታ ሃሳብ

የመርሐቤቴ ወረዳ ማህበረሰብ አልባሳትና ጌጣጌጦች ተፈጥሯዊ ማንነታቸውን ይዘው እንዲቆዩና ለመጪው ትውልድ መተላለፍ እንዲችሉ የሚከተሉት ምክረ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

1. ጥናቱ እንደሚያመለክተው ለውጡ በዋናነት የሚስተዋለው በወጣቶቹ ላይ ነው፡፡ ይህም ስለባህል ያላቸውን ግንዛቤ እምብዛም በመሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም በየቀበሌው ለሚገኙ ወጣቶች ባህላቸውን እንዲጠብቁ ተከታታይና ወጥነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ ቢሰራ መልካም ነው፤
2. በተመሳሳይ መልኩ ህፃናት ባህላቸውን አውቀው እንዲያድጉ፣ በመጤ ባህሎች እንዳይጠለፉና በኋላም የባህላቸው አምባሳደር መሆን እንዲችሉ ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጀምሮ ተገቢውን ግንዛቤ እንዲያገኙ የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤትና ትምህርት ጽ/ቤት ጋር በቅንጅት ቢሰሩ፤
3. በሽመና፣ በጥልፍ፣ በአንጥረኝነት/ቀጥቃጭነት እንዲሁም በቆዳ ስራ ላይ ለተሰማሩ ሙያተኞችን ማደራጀት፣ የመስሪያ ቦታና ቁሳቁስ ማቅረብ፣ የገበያ ትስስር መፍጠር እንዲሁም ባህልን መሰረት አድርገው እንዲሰሩ ስልጠናዎች መስጠት ቢቻል፤
4. ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራው ላይ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የእምነት አባቶች፣ የወጣት አደረጃጀት፣ የኪነ ጥበብ ሙያተኞች ወዘተ ስለወረዳው አልባሳትና ጌጣጌጦች እንዲያውቁት የማድረግ ስራ መስራት ቢሰራ፤
5. በሀገረሰባዊ አልባሳትና ጌጣጌጦቹ የለውጥ ሂደት ላይ ጥናት በማካሄድ ለባህሉ ባለቤት ተደጋጋሚ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ማከናወን ቢቻል፤
6. የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሁሉንም የማህበረሰቡን አልባሳትና ጌጣጌጦች መዝግቦ ቢይዝ፤
7. ማህበረሰቡ ለባህሉ ያለው ጥበቃ ከፍ እንዲል የወረዳውን ቁሳዊ ሀብቶች በዓይነት ተሰብስበው በወረዳው ወይም በከተማ አስተዳደሩ አንድ ሙዚየም ቢቋቋምና ለህዝብ እይታ ክፍት ቢደረግ
8. የማህበራዊ ሚዲያን በስፋት በመጠቀም የወረዳውን ቱባ ባህል የማስተዋወቅ ስራ ቢሰራ፤

# የአማርኛ ዋቢ ጽሑፎች


መሬ መፅሔት፡፡ (1996 ዓ.ም)፡፡ ዓለም ከተማ አስተዳደር፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ፡፡ (1993 ዓ.ም) አዲሱ መደበኛ ትርጉም፡፡ አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ መፅሐፍ ቅዱስ ማህበር::

ሰሎሞን ተሾመ፣ (2007 ዓ.ም)፡፡ *ፎክሎር ምንነቱና የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ* (2ኛ ዕትም) አዲስ አበባ፡፡ (የታተመበት ቦታና አሳታሚው ድርጅት ስም የለውም)፡፡

ሰይድ ይማም፡፡ (2002 ዓ.ም)፡፡ "በከሚሴ ከተማ ዙሪያ በሚገኙ ገጠር አካባቢዎች የወጣት "ወንዶችና ሴቶች አለባበስና አጊያጊያጥ ጥናት"፣ ያልታተመ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ለአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርቲ፡፡

ቅዱስ ቁርኣን፡፡ (1997 ዓ.ም) 2ተኛ እትም፡፡ አዲስ አበባ፣ ነጃሺ አሳታሚ ድርጅት፡፡

የኢትዮጵያ ታሪክ፡ ኑብያ አክሱም ዛጉዬ በተክለ ጻድቅ መኩሪያ የተደረሰ እንዲሁም በትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት በ1951 ዓ.ም የታተመ መጽሐፍ::

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፡፡ (1951 ዓ.ም) 1ኛ ዕትም፡፡ አዲስ አበባ፣ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡፡

_________፡፡ (1953 ዓ.ም) 1ኛ ዕትም፡፡ አዲስ አበባ፣ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡፡

አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡፡ (1948 ዓ.ም)፡፡ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፣አዲስ አበባ፣አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

አመልማል ተሻለ፤ (2004 ዓ.ም)፡፡ "በባንጃ ወረዳና አካባቢዋ የአዊ ብሄረሰብ አለባበስና ጌጣጌጦች ገላጭ ጥናት"፣ ያልታተመ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ ለአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

አያል አድማሱ፡፡ (1992 ዓ.ም)፡፡ "የጎጃም አካባቢ አልባሳት ስያሜ" ያልታተመ የአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

አዜብ ወርቅነህ፡፡ (2006 ዓ.ም)፡፡ "የካፍቾ ብሔረሰብ የሴቶችና የወንዶች አለባበስና አጊያጊያጥ"፣ ያልታተመ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ ለአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

አፀደ ያረጋል፡፡ (2003 ዓ.ም)፡፡ "የኮንሶ ሃገረሰባዊ አልባሳት እና ጌጣጌጦች ገላጭ- ተንታኝ ጥናት" ያልታተመ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ ለአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ውብሸት አሰፋ፡፡ (1978 ዓ.ም)፡፡ "የወይዛዝርት አልባሳትና ጌጣጌጥ ስሞች በአማራው ባህል" ያልታተመ የአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡ (1992 ዓ.ም)፡፡ *የስነጽሁፍ መሠረታዊያን*፡ አዲስ አበባ ፣ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

የኔዓለም አረዶ፡፡ (2000 ዓ/ም)፡፡ "የአርሲ ሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጥ ጥናት" ያልታተመ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ ለአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣

ያሬድ ተፈራ፡፡ (2002 ዓ.ም)፡፡ "በሰቆጣና በአበርገሌ ገጠራማ ወረዳዎች የሴቶችና የወንዶች የአለባበስና አጊያጊያጥ ማህበራዊ እሴቶች" ያልታተመ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ ለአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርቲ፡፡

ደስታ ተክለ ወልድ፡፡ (1962)፡፡ *ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት*፡፡ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ድርሳነ ዑራኤል፡፡ (2011 ዓ.ም) በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አዲስ አበባ፣ በትንሳዔ ዘጉባዔ ማተሚያ ቤት፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ (1991 ዓ.ም)፡፡*የስነ ቃል መምሪያ*፡፡ አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፡፡

# የእንግሊዝኛ ዋቢ ጽሑፎች


Adams W.Y. and Adams E.W. (1991). *Archaeological Typology and Practical Reality*. Cambridge: Cambridge University Press..

Aishwariya, S., Dr. (2018). *A Review On The History, Theories And Early*

Al-Sheikh, A. R. (2014). *The Changes of Heroism in the Palestinian Cultural Discourse*. Journal of Palestinian Studies, 25, 104.

Aronin, L., & Singleton, D. (2012). *Multilingualism* (Vol. 30). John Benjamins Publishing.

*Comte, Auguste (1998). Auguste Comte and positivism : the essential writings. Lenzer, Gertrude. New Brunswick, NJ: Transaction Publishers.*

Barton, A. H. (1969). *Communities in disaster; A sociological analysis of collective stress situations* (1st ed.). Garden City, NY: Doubleday.

Encyclopedia Britannica. https://www.britannica.com/biography/Henri-de-Saint-Simon

Bradley, L. A., & Homberger, T. (2015). *Recent work on the history and culture of religion and dress*. *Canadian Journal of History*, *50*(2), 317-325.

Brett, D. (2005). *Rethinking decoration: pleasure and ideology in the visual arts*. Cambridge University Press.

Ben-Amos, Dan. (1978). *The Modern Local Historian in Africa. In Folklore in the Modern World*, edited by Richard M. Dorson, 327–43. The Hague: Mouton.

Campbell, C. (1987). *The Romantic Ethic and the Spirit of Modern Consumerism*. New York: Basil Blackwell

Chalfant, H. P., & LaBeff, E. (1988). *Understanding people and social life: introduction to sociology.* St. Paul, West Pub. Co.

Charama T .(2002). *Fashion as communication,* London Routledge.

Charon JM. (1998). *Symbolic Interactionism: An Introduction, An Interpretation, An Intergration.* 6th ed. USA: Prentice Hall.

Clark, G. (1986). *Symbols of excellence* . London: Cambridge University Press.

Cleary, Ann MC. (2004). "*Method and Theory of Material Culture Studies.*

Damhorst, ML. (1990). *In search of a common thread: classification of information communicated through dress.* Clothing and Textiles Research Journal, 8(2), 1–12

Danesi, Marcel. (2004). *Message, Signs And Meanings*; A Basic Textbook in Semiotics and Communication theory. 3rd ed. Toronto. Canadian Scholar's Press Inc.

Dawit Assefa, et. Al. (2005). *Harmful Traditional Practices: For the Ethiopian Health Center Team.*: Awassa, College Awassa.

Deetz, J. (1977). *Material culture and archaeology-what's the difference*. *Historical archaeology and the importance of material things*, 9-12.

Dorson, R. M. (Ed.). (1972). *Folklore and folklife: An introduction*. University of Chicago Press.

Dundes, A. (1980). *Interpreting folklore*. Indiana University Press.

Durkheim, E. (1893). *The Division of Labour in Society*. New York: The Free Press.

Eicher, J. B., & Roach, M. E. H. (1992). *Definition and classification of dress: Implications for analysis of gender roles.* Berg Publishers, Inc..

Ferguson, L. (1977). *Historical Archaeology and the Importance of Material Things* (Vol. 2). Society for Historical Archaeology.

Fleming, E. McClung. (1974). *Artifact Study: A Proposed Model*. Online at:URL: http:// www,Jstor.org/stable/ 118052

Glassie, H. H. (1968). *Pattern in the material folk culture of the Eastern United States*. Philadelphia, PA: University of Pennsylvania Press.

_________. (1999). *Material Culture. Blomington and Indianapolis.* Indiana University Press.

Goldstein, Kenneth S. A .(1964). *Guide for Field Work in Folklore*. Hatboro Pennsylvania: the American Folklor in Society.

Gracia, M. (2008).*Communicating through clothing: The meaning of clothing among Hispanic women of different levels of acculturation*. College of communication; Florida University

Gray, D. E. (2004). *Doing Research in the Real World*. London: SAGE Publications.

Haferkamp, H. and Smelser, N. (eds), (1992). *Social Change and Modernity, Berkeley*, CA: University of California Press

Herbert Spencer .(1998). *The Principles of Sociology*, Vol. 3. New York: D. Appleton and Company.

https://www.abyssinica.com/search

Kaiser, S. (1990). *The Social Psychology of Clothing: Symbolic Appearance in Context*. 2nd ed., Macmillan, New York.

Kaiser, M. K., Proffitt, D. R., & McCloskey, M. (1985). *The development of beliefs about falling objects. Perception & Psychophysics*, *38*(6), 533-539.

Klemm, P. M. (2002). *Shaping the future, wearing the past: dress and the decorated female body among the Afran Qallo Oromo in eastern Hararghe, Ethiopia*. Emory University.

Kothari, C.R. (2004).*Research Methodology: Methods and Techniques*. 2nd Edition, New Age International Publishers, New Delhi.

Leach, Maria. (1996). *Standard Dictionary of Folklore; Mythology and Legend*. New York; Funk and Wagnall's Company.

Lincoln, Y., & Guba, E. (1985). *Naturalistic Inquiry* Vol. 75 Sage. *Beverly Hills, CA*.

Lurie, Alison. (1981). *The language of clothes.* New York: Random House Inc

Malinowski B (1944). *A Scientific Theory of Culture and Other Essays*. Chapel Hill: The University of North Carolina Press.

Marshall, C., & Rossman, G. B. (1999). *Designing qualitative research* (3ed.). Thousand Oaks, CA: Sage Publications

Marshall, H. (1981). *Folk architecture in Little Dixie: A regional culture in Missouri*. Columbia, MO: University of Missouri Press.

Merton, Robert K. (1968). *Social Theory and Social Structure,* Enlarged edition. New York: Free Press,

Miller, D. (1987). *Material culture and mass consumption*. Oxford, UK: Basil Blackwell Ltd.

_________. (1994). *Artefacts and the meaning of things*. In Ingold, T. (ed.) Companion encyclopedia of anthropology: 396-419. Routledge. London.

_________. (Ed.). (1998). *Material cultures: Why some things matter*. University of Chicago Press.

Oestigaard, T. (2004). *Approaching material culture*. Journal of Nordic Archaeological Science,14, 79-87.

Ozougwu, A.M. (2004). *Clothing and personal attractiveness of adolescents related to conformity to clothing mode, peer acceptance and leadership potential*. Home Economics Research Journa l8,3(203).

Pheto-Moeti, M. B. (2005). *An Assessment of Seshoeshoe Dress as a Cultural Identity for Basotho Women of Lesotho*. MSc diss., University of the Free State. http://hdl.handle.net/11660/1555.

Pheto-Moeti, B., Riekert, D. M., & Pelser, A. J. (2018). *The popularity of Seshoeshoe dress for Basotho women. Journal of Consumer Sciences*.

Pitt-Rivers, A. H. L. F. (1906). *The evolution of culture: And other essays* (Vol. 12748). Clarendon Press.

Prown, J. D. (1982). *Mind in matter: An introduction to material culture theory and method*. *Winterthur portfolio*, *17* (1), 1-19.

Radcliffe-Brown, A.R. (1958). *Method in Social Anthropology*, Selected Essays by Radcliffe-Brown. (edited) M.N. Srinivas, Chicago: University of Chicago Press.

Renfrew, C. (1998). *Mind and matter: cognitive archaeology and external symbolic storage*. *Cognition and material culture: the archaeology of symbolic storage,* 1-6.

Roderick Floud, ROSENBERG (N.). (1977). *Perspectives on Technology*, *The Economic Journal*, Volume 87, Pages 375–376.

Sebesta, Judith L. (1941). *weavers of Fate; Symbolism in the costume of roman Women*. http://beach.ksu.edu/curricula/photo-curriculum/pdfs/material-culture.pdf.

Schensul, S. L., Schensul, J. J., & LeCompte, M. D. (1999). *Essential ethnographic methods: Observations, interviews, and questionnaires* (Vol. 2). Rowman Altamira.

Schlereth, T. J. (1980). *Artifacts and the American Past*. American Association for State and Local History, 1400 Eighth Avenue, South, Nashville, TN 37203.

_________. (Ed.). (1985). *Material culture: A research guide*. Lawrence, KS: University Press of Kansas.

Shove, E., Watson, M., & Pantzar, M. (2012). *The dynamics of social practice: Everyday life and how it changes.*

Schwandt, T.A. (2007). *The Sage Dictionary of Qualitative Inquiry* (3rd ed.). Thousand Oaks: Sage

Schoemaker, G. H. (1990). *Folklore and Religion: Approaches to Folklore Fieldwork*. *The Emergence of Folklore in Everyday Life. Bloomington: Trickster Press, Indiana University*, 59-72.York.

Selby, H. A., & Garretson, L. R. (1981). *Cultural anthropology*. *(No Title).*

Sims, Martha C. and Stephens, Martine. (2005). *Living Folklore: An Introduction to the Study of People and Their Traditions*. UTAH: UTAH State University.

Parsons, T. (1951). *The Social System*. Free Press, New York.

Tardif, J., & Farchy, J. (2006). *Les enjeux de la mondialisation culturelle* (No. hal-00272738).

Thoms, William John 1946 (1846). *Folk-Lore, in Duncan Emrich, Folk-Lore*: William John Thoms", California Folklore Quarterly 5(4), pp. 355–374, at pp. 361–362.

Tortora & Eubank. (1989). *Survey of Historic Costume.* Fairchild Publications Capital Cities Inc. Company, 3, 1-6

Twigg, S. (2007). *Customary cloths: practices and conceptions* . London: Cambridge Univeristy Press.

UNESCO. (2011). *Kit of the Convention for the Safeguarding of the Intangible Cultural Heritage*. https://ich.unesco.org/en/kit.

Wilson, William A. (1986.). *Documenting Folklore. In Folk Groups and Folklore Genres*: *An Introduction.* In Elliot Oring, (ed). Logan፡ Utah State University Press.

Woodward, Ian.(2007). *Understanding Material Culture*. Los Angles: SAGE Publication.

Yenealem Aredo (2016). *Description and Documentation of Traditional Dress : the Case of Arsi Oromo*. (Unpublished doctoral dissertation]. Addis Ababa University.

Yoder, Don (1972). *Folk Costume. In Folklore and Folklife: An Introduction*. Dorson, Richard M. (1972). (ed.). Chicago and London: The University of Chicago press

# አባሪ 1.

## አባሪ 1. ለተለያዩ መረጃ አቀባዮች የቀረቡ ጥያቄዎች

### ሀ. ግላዊ መረጃዎችን ለማግኘት የተሰናዱ ጥያቄዎች

1. ሙሉ ስምዎት ማን ይባላል?
2. ዕድሜዎስንት ነው?
3. የትውልድ ስፍራዎት የት ነው?
4. አሁን የሚኖሩበትስ ቀበሌ ማን ይባላል? በቀበሌው ስንት ዓመት ኖረዋል?
5. የሚከተሉት ኃይማኖት ምንድነው?
6. የቤተሰብ ሁኔታ (ያገባ ወይስ ያላገባ) ያገቡ ከሆነ ስንት ልጆች አልዎት?
7. የቀለም ትምህርት ተምረዋል? (መደበኛ፣ መሠረተ ትም/ት፣ ኃይማኖት ወይም ሌላ)
8. መተዳደሪያዎ ምንድነው?
9. በሚኖሩበት ቀበሌ ወይም ጎጥ ምን ዓይነት ማህበራዊ ኃላፊነት (ሥልጣን) አለዎት?
10. አካባቢው መርሐቤቴ የተባለበት ምክንያት ምንድነው? ስያሜውን እንዴት አገኘ?

### ለ. በቃለ መጠይቅ አካባቢና ባህላዊ መረጃዎችን ለማግኘት የቀረቡ ጥያቄዎች

1. በሚኖሩበት አካባቢ ምን ዓይነት የባህላዊ አልባሳትና ጌጣጌጦች አሉ?
2. የአልባሳትና ጌጣጌጦቹ ስያሜዎች ምን ይባላል?
3. ቁሶቹ ያላቸው አገልግሎት ወይም ጠቀሜታ ምንድነው? እንዲሁም ምን ትርጓሜ ወይም ተምሳሌት አላቸው?
4. አልባሳቱና ጌጣጌጦቹ በማን? ከምን? እንዴት ይሰራሉ/ይዘጋጃሉ?
5. ህፃናት ሴቶች እና ወንዶች ምን ዓይነት ልብሶችን ይለብሳሉ? ምን ዓይነት ጌጣጌጦችን ያደርጋሉ ለምን?
6. ልጆች ሴቶች እና ወንዶች ምን ዓይነት ልብሶችን ይለብሳሉ? ምን ዓይነት ጌጣጌጦችን ያደርጋሉ ለምን?
7. ወጣት ሴቶች እና ወንዶች ምን ዓይነት ልብሶችን ይለብሳሉ? ምን ዓይነት ጌጣጌጦችን ያደርጋሉ ለምን?
8. ጎልማሳ ሴቶች እና ወንዶች ምን ዓይነት ልብሶችን ይለብሳሉ? ምን ዓይነት ጌጣጌጦችን ያደርጋሉ ለምን?
9. በዕድሜ የገፉ ሴቶች እና ወንዶች ምን ዓይነት ልብሶችን ይለብሳሉ? ምን ዓይነት ጌጣጌጦችን ያደርጋሉ ለምን?

10.ያላገቡ ወጣት ሴቶች እና ወንዶች ምን ዓይነት ልብሶችን ይለብሳሉ? ምን ዓይነት ጌጣጌጦችንስ ያደርጋሉ ለምን?

11.ያገቡ ሴቶች እና ወንዶች ምን ዓይነት ልብሶችን ይለብሳሉ? ምን ዓይነት ጌጣጌጦችንስ ያደርጋሉ ለምን?

12.አልባሳትና ጌጣጌጦቹ በምን አጋጣሚ /ወቅት/ የሚለበሱና የሚደረጉ ናቸው? ለምን?

13. በበዓላት ቀናት የአለባበስና የአጊያጊያጥ ዓይነቶች አሉ? ከበዓል በዓል ይለያያሉ?

14.በሰርግ ወቅት ምን ዓይነት የአለባበስና የአጊያጊያጥ ዓይነቶች አሉ?

15.በሀዘን ወቅት ምን ዓይነት የአለባበስ ዓይነቶች?

16.ምን ዓይነት የአዘቦት አልባሳትና ጌጣጌጦች አሉ? በምን መልኩ ይለብሳሉ? ይደረጋሉ?

17.በነጠላ፣ በቀሚስ፣ በኩታ፣ በጋቢ፣ በመቀነት፣ በአንገት ልብስ የሚደረጉ የቀለም ዓይነቶች ምን ምን ናቸው? ቀለም ባይኖረውስ ከልብስ ልብስስ ይለያያሉ? ለምን?

18.ንቅሳት (ውቅራት) በየትኛው የሰውነት ክፍል ላይ ይደረጋል? ጥቅሙ ምንድነው?

19.ንቅሳት (ውቅራት) በዕድሜ ደረጃስ ይለያየሉ? ወይስ አንድ ናቸው?ሚለያዩ ከሆነ ምክንያቱ ምንድነው?

20.ከልጅነት እስከ አዋቂ የወንዶች ፀጉር አያያዝ ምን ይመስላል? በማስረዘም በማሳጠር በመላጨት ምን ዓይነት ትርጉም አላቸው?

21.በተለያየ የዕድሜ ክልል ያሉ ሴቶች ምን ዓይነት የፀጉር አሰራር (አያያዝ) ዓይነቶች አሉ? ካሉ ምንን ያመለክታል?

22.የልብስ ቁልፍ (አዝራር) የት የት ቦታ ላይ ይደረጋል? ለምን? እንዲህ መደረጉስ መቼ ተጀመረ?

23.ባህላዊ ልብሶችን እና ጌጣጌጦችን በማየት የሰዎችን ዕድሜ የኑሮ ደረጃ፣ ሃይማኖት እና ፆታ መገመት ያስችላል? ወይስ አያስችልም? ካስቻለ እንዴት?

24.በእርስዎ ጊዜ ልብሶች እና ማጌጫዎች የተለወጡበት ሁኔታ አለ? ካለ ምክንያቱ ምንድነው? እንዳይለወጡ ማድረግ አይቻልም ነበር?

25.በዘመናዊ መልኩ እየተሰሩ ስለሚገኙት አልባሳትና ጌጣጌጦች ምን አስተያየት አለዎት?

26.የመርሐቤቴ ባህላዊ አልባሳትና ጌጣጌጦች ባህላዊነታቸውን ጠበቀው እንዲቆዩ ምን መደረግ አለበት ይላሉ?

## ሐ. በሙያውን የተሰማሩና ያለውን የግብይት ሁኔታ ለመገንዘብ የተዘጋጁ ጥያቄዎች

1. በምን ሙያ በማህበረሰቡ ዘንድ ይታወቃሉ?
2. የአልባሳትና ጌጣጌጥ አሰራር ሙያን ከየት ከማን መቼ እንዴት አገኙት/ተማሩት/?
3. የመስሪያ ቁሶች ምን ምን ናቸው? እንዴትስ ይሰራሉ?
4. ልብሶች እና ጌጣጌጦችን ሲሰሩ በትዕዛዝ ወይስ በራስ ፍላጎት ሰርቶ ገበያ ለማቅረብ?
5. ቁሶችን ሰርተው ሲሸጡ የገበያው ሁኔታ ምን ይመስላል? በይበልጥ የሚፈለጉበት ወቅት መቼ መቼ ነው?
6. ልብሶችንና ጌጣጌጦችን በብዛት የሚገዙት የትኞቹ የህብረሰተሰብ ክፍሎች ናቸው?
7. ልብሶችንም ሆነ ጌጦችን የሚገዙት ምን ዓይነት የህብረተሰብ ክፍሎች ናቸው
8. ቀደም ሲል በነበረውና በአሁኑ ወቅት የገበያ ሁኔታው ምን ይመስላል?
9. ይህ ስራ ከሌሎች የስራ ዘርፎች በህይወትዎ ላይ ምን ዓይነት ለውጥ አምጥቷል?
10. ይህን ስራ በመስራትዎ በማህበረሰቡ ዘንድ የሚያሰጥዎት ክብር ምን ይመስላል?
11. እርስዎስ ቀደም ባለው ጊዜ ከማ/ሰቡ ጋር የነበረዎት ግንኙነት የት ድረስ ነበር አሁንስ?

### ለተተኳሪ ቡድን ውይይቶች

1. በአካባቢው ምን ዓይነት የተለመዱት የአለባበስ እና አጊያጊያጦች አሉ? ምንስ ተብለው ይጠራሉ? ስያሜያቸው ከምን ጋር የተያያዘ ነው?
2. በአካባቢው ያሉ የአለባበስ እና አጊያጊያጦች ዓይነቶች በሚደረጉበት አጋጣሚ በፆታ፣ በቀለም በሚሰሩበት ቁስ እና በአሰራራቸው ወዘተ ይለያያሉ? በምንስ ይለያያሉ?
3. ልብሶችን እና ጌጣጌጦችን በማን ይሰራሉ? የአሰራር ሂደታቸው ምን ይመስላል? ማህበረሰቡ ለእነዚህ ሰዎች ያለው አመለካከት ምን ይመስላል?
4. በአልባሳቱና ጌጣጌጡ የተስተዋሉ ለውጦች አሉ? ካሉ ምክንያቶቹ ምንድን ናቸው ይላሉ?
5. ባህላዊ አልባሳትና ጌጣጌጦች ባህላዊነታቸውን ተጠብቆ ለማቆየት ምን መደረግ አለበት ይላሉ?

# አባሪዎች 2.

## 1. በሁሉም የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተሳተፉ መረጃ ሰጪዎች አጠቃላይ መረጃ

| ተ.ቁ | የመረጃ አቀባዩ ሙሉ ስም | ዕድሜ | ፆታ | የመኖሪያ ስፍራ/ቀበሌ | ስራ ( መተዳደሪያ) |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ወ/ሮ አስቴር አንዳርጋቸው | 35 | ሴት | ዓለም ከተማ | የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ኃላፊ |
| 2 | ወ/ሮ ሕይወት ታደሰ | 27 | ሴት | ዓለም ከተማ | በባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት የባህል ልማት ባለሙያ |
| 3 | ወ/ሮ ሽታ አባቡ | 50 | ሴት | ገረን | አርሶ አደር |
| 4 | ወ/ሪት እቴነሽ ደርሶ | 18 | ሴት | ገረን | ሸማኔ |
| 5 | ወ/ሮ ጉርዶ ባህሩ | 65 | ሴት | ዘይታ | አርሶ አደር |
| 6 | ወ/ሮ ገበያነሽ ሽትዬ | 30 | ሴት | ጎራንዳ | አርሶ አደር |
| 7 | ወ/ሮ አበበች ከስክስ | 50 | ሴት | ኮራ | አርሶ አደር |
| 8 | ወ/ሮ በዛብሽ ዘነበ | 50 | ሴት | ግሬት | አርሶ አደር |
| 9 | ወ/ሮ ብዙጌጥ ግዛው | 30 | ሴት | ኮራ | አርሶ አደር |
| 10 | ወ/ሮ ምሳው ፀጋው | 37 | ሴት | ግሬት | አርሶ አደር |
| 11 | ወ/ሮ ተካበ አበበ | 23 | ሴት | ኮራ | አርሶ አደር |
| 12 | ወ/ሮ ጥሩነሽ ተጫነ | 38 | ሴት | ግሬት | አርሶ አደር |
| 13 | ወ/ሮ ፀሐይ ሽናውለው | 25 | ሴት | ዘይታ | ነጋዴ/ልብስ ሰፊ |
| 14 | አቶ ተኮላ ባዩ | 35 | ወንድ | ገረን | አርሶ አደር |
| 15 | አቶ ያግኝ አንግዳሽት | 18 | ወንድ | ገረን | አርሶ አደር |
| 16 | አቶ ዮናስ አንጓሌ | 27 | ወንድ | ገረን | ነጋዴ/ልብስ ሰፊ |
| 17 | አቶ አበጀ ገስጥ | 27 | ወንድ | ዘይታ | ነጋዴና አርሶ አደር |
| 18 | አቶ አባቢ ሙላቱ | 81 | ወንድ | ጎራንዳ | አርሶ አደር |
| 19 | አቶ አማረ ንጉስ | 38 | ወንድ | ጎራንዳ | አርሶ አደርና የቀበሌ ሊቀመንበር |
| 20 | አቶ አናትዬ ብሬ | 57 | ወንድ | ጎራንዳ | አርሶ አደር |
| 21 | አቶ ፍቃዱ ግዛው | 65 | ወንድ | ጎራንዳ | አርሶ አደር |
| 22 | አቶ ጉታነህ አርጋው | 70 | ወንድ | ጎራንዳ | አርሶ አደር |
| 23 | አቶ ግርማ ተሰማ | 60 | ወንድ | ጎራንዳ | አርሶ አደር |
| 24 | አቶ ጉርምስ አየለ | 40 | ወንድ | ጎራንዳ | አርሶ አደር |
| 25 | ቄስ ማንደፍሮ አበበ | 63 | ወንድ | ጎራንዳ | አርሶ አደር |
| 26 | አቶ አስቻለው ማሞ | 60 | ወንድ | ዘይታ | አርሶ አደር |
| 27 | አቶ ጋሎ አጥላባቸው | 45 | ወንድ | ግሬት | አርሶ አደርና ም/ሊቀመንበር |
| 28 | አቶ ገለታው ደሳለኝ | 48 | ወንድ | ግሬት | አርሶ አደር |
| 29 | አቶ ጌታቸው ዘውዴ | 52 | ወንድ | ግሬት | አርሶ አደርና ሚሊሻ |
| 30 | አቶ ኃይለማሪያም አበራ | 57 | ወንድ | ግሬት | አርሶ አደርና ሚሊሻ |
| 31 | አቶ ክብረቴ አስፋው | 50 | ወንድ | ግሬት | አርሶ አደር |
| 32 | አቶ ሰንበት ቸረኝ | 40 | ወንድ | ግሬት | አርሶ አደርና ሚሊሻ |
| 33 | አቶ በላይሁን ደሳለኝ | 65 | ወንድ | ኮራ | አርሶ አደር |
| 34 | አቶ አውራሪስ ማብረጃ | 63 | ወንድ | ኮራ | አርሶ አደር |
| 35 | አቶ ሰለሞን ምታው | 48 | ወንድ | ዓለም ከተማ | ግንበኛና ድምፃዊ |
| 36 | አቶ ንጉስ ብርቅነህ | 25 | ወንድ | ዘይታ | ነጋዴ/ጫማ ሰሪ |

## 2. በተተኳሪ ብድን ውይይት የተሳተፉ ሰዎች አጠቃላይ መረጃ


| ተ/ቁ | የመረጃ አቀባዩ ሙሉ ስም | ዕድሜ | ፆታ | የመኖሪያ ስፍራ | መተዳደሪያ | መረጃ የተሰ. ቀን (ዓ.ም) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ወ/ሮ ሽታ አባቡ | 50 | ሴ | ገረን | አርሶ አደር | 01/09/2015 |
| 2 | ወ/ሮ ብዙጌጥ በላቸው | 35 | ሴ | ገረን | አርሶ አደር | 01/09/2015 |
| 3 | ወ/ሮ በለጥሻቸው ደረጀ | 27 | ሴ | ገረን | ልብስ ሰፊ | 01/09/2015 |
| 4 | ወ/ሪት እቴነሽ ደርሶ | 18 | ሴ | ገረን | ሽማኔ | 01/09/2015 |
| 5 | ወ/ሮ እታለም አየለ | 22 | ሴ | ገረን | ነጋዴ | 01/09/2015 |
| 6 | አቶ አባቢ ሙላቱ | 81 | ወ | ጎራንዳ | አርሶ አደር | 14/01/2014 |
| 7 | አቶ ጌታነህ አርጋው | 70 | ወ | ጎራንዳ | አርሶ አደር | 14/01/2014 |
| 8 | አቶ አማረ ንጉስ | 38 | ወ | ጎራንዳ | አርሶ አደር እና የቀበሌ ሊቀመንበር | 14/01/2014 |
| 9 | ቄስ ማንደፍሮ አበበ | 63 | ወ | ጎራንዳ | አርሶ አደርና ካህን | 14/01/2014 |
| 10 | ቄስ አበበ በለው | 68 | ወ | ጎራዳ | አርሶ አደርና ካህን | 14/01/2014 |
| 11 | አቶ በላይሁን ደሳለኝ | 65 | ወ | ኮራ | አርሶ አደር | 21/01/2014 |
| 12 | አቶ አውራሪስ ማብረጃ | 63 | ወ | ኮራ | አርሶ አደር | 21/01/2014 |
| 13 | አቶ ሽንቁጥ ዘለቀ | 60 | ወ | ኮራ | አርሶ አደር | 21/01/2014 |
| 14 | አቶ ምሳው ግርማ | 27 | ወ | ኮራ | አርሶ አደር | 21/01/2014 |
| 15 | አቶ ከፈለኝ ግዛው | 29 | ወ | ኮራ | አርሶ አደር | 21/01/2014 |

# አባሪ 3


## የፎቶ አባሪዎች



በቃለ መጠይቅ፣ በምልከታ፣ በተሳትፎና በተተኳሪ የቡድን ውይይት መረጃ ስሰበሰብ



ለገበያ የቀረቡ የጠፍር፣ የፕላስቲክ፣ የጎማ ጫማዎች እና አልባሳት



በራስ፣ በአንገት፣ በእጅ፣ በወገብ ላይ የሚደረጉ/የሚያዙ ጌጣጌጦች



ያገቡ ሴቶች አለባበስና አጊያጊያጥ



ያላገቡ ወጣቶች አለባበስና አጊያጊያጥ



በሀገረሰባዊ አለባበስ ላይ የሚታይ ፈጣን ለውጥ



ሃይማኖታዊ የአከባበር ስርዓት



ባህላዊ የወጣቶች ጨዋታ



ትውልድ የተረከበው የአባቶች ተነፋነፍ ሱሪና ዝናር አለባበስ

በመርሐቤቴ ወረዳ የሴቶችና የወንዶች አለባበስና አጊያጊያጥ በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የሂዩማኒቲ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሙዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር፣ ለአርት ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ያቀረብሁት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ስራ (original work) ነው፡፡ በተጨማሪም በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኳቸው መረጃዎች ምንጭ በትክክል የጠቀስኩ መሆኑንና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ህጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ፍስሃ ጌታቸው

ፊርማ _______________

ቀን _______________

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

መስከረም 2017 ዓ.ም